# @BOOKALEM

# የመጻሕፍት አለም

@BOOKALEM

# ፓፒዮ

5ተኛ ዕትም



ትርጉም በ ጌታቸው ገብሬ

@BOOKALEM

# ፓ ፒ ዮ

# PAPILLON

ድርሰት

ሄንሪ ሽሪየ

ትርጉም

በ

ጌታቸው ገብሬ

የሽፋን ሥዕል፤ ሉቃስ አማረ

የኮምፒውተር ጽሑፍ፤ ራሔል ከበደ እና ልዋም ተ/ሃይማኖት

በመጀመሪያ በ1985 ዓ.ም በኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ታተመ

በድጋሚ በ2006 ዓ.ም በእማይ ማተሚያ ቤት ታተመ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

©All Rights Reserved

@BOOKALEM

## መታሰቢያነቱ

የድርሰትን ጉዞ «ሀ» ብለህ ስትጀምር
ምኞትህ ተሳክቶ ማየት ስለነበር
ብዙ ዕቅድ አውጥተህ
ሌት ከቀን አስበህ
«ፓፒዮን» ተርጉመህ
ለህትመት አብቅተህ
አየሁ ተሳካልኝ ሞላልኝ ምኞቴ
«ባንኮን» መተርጎም ነው ቀጣይ ፍላጎቴ
አልክና ለህዝቡ አጉል ተስፋ ሰጥተህ
ቃልህን ሳትፈፅም ሞት አደናቀፈህ
ይህ የራስህ ትርጉም ላንተው ማስታወሻ
ይሁንልህ በቃ እስከመጨረሻ

*ወ/ሮ ዙሪያሽ ጃራ ለሜ*

*ባለቤቱ*

@BOOKALEM

# ምስጋና

ይህ አጓጊና መሳጪ የትርጉም መጽሐፍ በድጋሚ ታትሞ ለአንባቢዎች ይደርስ ዘንድ የተለያዩ አስተዋጽኦ ያደረጉትን በሙሉ የተርጓሚው ባለቤትና ልጆቻቸው ማመስገን ይፈልጋሉ፡፡

በመጀመሪያ ፓፒዮ እንዲተረከና የሚዲያ ሽፋን እንዲያገኝ በማድረግ ትንሳኤውን ላበሰረው እና የተርጓሚው ስራ እንደገና እንዲታወስ ከፍተኛውን ሚና ለተጫወተው ለፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት እና ለመላው ሰራተኞቹ በተለይ ደግሞ በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት የኦፕሬሽን ዘርፍ ምክትል ስራ አስፈፃሚ ለሆኑት ለአቶ ብሩክ ከበደ ፣ ለጋዜጠኞች ዘካርያስ ብርሃኑ፣ ዮናስ አዘዘ እና ሰዩም ፈቀደ ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን፡፡

በመቀጠልም ለአርቲስት ሽመልስ አበራ (ጆሮ) እና ባዩሽ አለማየሁ መፅሐፉን እንደሚገባ በመተረካቸው፣ ለጃፋር መጽሐፍት ቤት ባለቤት ለአቶ ጃፋር ሺፋ ድጋሚ መጽሐፉን አሳትሞ ለገበያ እንዲቀርብ በማድረጉ፣ በመጨረሻም ከመላው አገሪቱ ስልክ በመደወል አድናቆታቸውን ለገለጹልን እና ለድጋሚ ህትመት ላበረታቱን በሙሉ ከልብ የሆነ ምስጋና እናቅርባለን፡፡

ወ/ሮ ዙሪያሽ ጃራ እና
ልጆቻቸው




@BOOKALEM

## ከመጀመሪያው የመጽሐፉ አሳታሚ

በሐምሌ ወር 1967 ከፍተኛ የመሬት መንቀጥቀጥ በደረሰበት ዓመት፥ አንድ የስድሳ ዓመት አዛውንት በካራካስ ጋዜጦች ላይ በአልበርቲን ሳራዚን የተጻፈውን ባያነብ ኖሮ፥ ምናልባትም ይህ መጽሐፍ ፈጽሞ ሊጻፍ ባልተቻለ ነበር።

ብሩህ ገጽ ያላትና ሳቅ የማይለያት ይህች መንፈሰ ጠንካራ ጥቁር አልማዝ አሁን ሞታለች። በአንድ ዓመት ገደማ ብቻ ጽፋ በመላው ዓለም ዝናን ካተረፈችባቸው ሦስት መጻሕፍት መካከል ሁለቱ የሚተርኩት ስለ ራሷ ከወህኒ ቤት ማምለጥና ስለ ወህኒ ቤት ኑሮዋ ነበር።

አዛውንቱ ሰውዬ ፥ ሄንሪ ሻሪየ ሲሆን ፥ እዚያ ለመድረስ ረጅም መንገድ ተጉዟል - ከካየን የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት። እቅጩን ለመናገር ያህል በ1933 ወደዚያ ሥፍራ ተግዞ ነበር። ሕገወጥ መሆኑን መካድ ባይቻልም የእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ግን ያልገደለውን ነፍሰ ገዳይ ተብሎ ነበር።

ሄንሪ ሻሪየ፣ በአራዳው ዓለም መጠሪያ ስሙ ፓፒዮ ፥ የተወለደው በ1906 ከአንድ የመምህራን ቤተሰብ አርዴሽ በምትባል ቦታ ነበር። ትውልዱ ፈረንሣዊ ሲሆን ፥ በኋላ ግን የቬኔዙዌላ ዜጋ ሆኗል። የቬኔዙዌላ ሕዝብ የሚያደንቀው በጨዋነቱ እንጂ ባለፈው የወንጀለኛነት ሪከርዱ አይደለም። ከአሰቃቂው የቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ለማምለጥ በትግሉ ያሳለፋቸው ዐሥራ ሦስት ዓመታትም ያለፈውን ታሪኩን ከማጨለም ይልቅ የወደፊት ዕድሉን ብሩህ አድርገውለታል።

በሐምሌ ወር በ1967 ሻሪየ ካራካስ ወደሚገኘው የፈረንሣይኛ መጻሕፍት መሸጫ መደብር ሔዶ ፥ "ለስትራጋል" የተባለ አንድ መጽሐፍ ገዛ። እስከዚያ ጊዜ ድረስ ስለራሱ አስደናቂ ታሪኮች አንዲት መስመር እንኳ ለመጻፍ ፍጹም አላሰበም። ታታሪና ኑሮን የሚወድ ሰው ነበር። ሰው አፍቃሪና ንቁ ፥ የሚማርክ ጎርናና ድምፅ የታደለ የደቡባዊ ፈረንሣይ ሰው ነበር። ታሪኮቹን የሚያቀርበው ልክ እንደ አንድ ዕውቅ ተራኪ ስለሆነ ያለአንዳች መሰልቸት ለብዙ ሰዓት ማዳመጥ ይቻላል። እንግዲህ ተአምሩን እነሆ - ምን ጽሑፋዊ ክሂሎትን ሳያክልበት (በጻፈልኝ ደብዳቤ ውስጥ "አስገራሚ ታሪኮቹ



@BOOKALEM

እንሁልህ ፤ ባለሞያ ይጸፍልኝ ብሎኛል፡፡) የማዳም አልበርቲ ሳራዚንን አርአያ በመከተል፡፡

ታዩታላችሁ፥ ትሰሙታላችሁ፥ ኑሮውን ትኖራላችሁ፥ ድንገት የአንድ ገጽ የመጨረሻ መስመር ላይ ስትደርሱ ፥ ወደ መጽዳጃ መሔዱን ሲነግራችሁ (በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ፥ ያ ቦታ ብዙ ድርጊት የሚከናወንበት ነበርና) እንባችሁን መግታት አትችሉም፡፡ ምክንያቱም ወደዚያ የሚሄደው ሽሪየ ሳይሆን እናንተው እንደሆናችሁ ስለምታስቡ፥ ከመቅጽበት ገጹን ትገለብጣላችሁ፡፡

"ስትራጋል"ን አንብቦ ከጨረሰ ከሦስት ቀን በኋላ ቁጭ ብሎ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን ምዕራፎች በአንድ ጊዜ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ ጻፈ፡፡ ለእንደዚህ ዓይነቱ እንግዳ የሆነ አስደናቂ ታሪኩ አንዳንድ ምክሮች ለማግኘት ሲል ረዘም ላለ ጊዜ አቋርጦ ቆየ፡- ምናልባትም ታሪኩን ካማከራቸው ሌሎች ሰዎች ይልቅ ፥ ይበልጥ ያስደነቀው ራሱን ስለሆነ ፥ የቀሩትን ደግሞ በ1968 መግቢያ ላይ ሊያጠናቅቅ ተነሳ፡፡ ዐሥራ ሦስቱንም ማስታወሻዎች በሙሉ በሁለት ወር ውስጥ ጨረሰ፡፡

ልክ እንደ ማዳም አልበርቲን ፥ የእርሱም ረቂቅ ጽሑፎች በመስከረም ወር በፖስታ ቤት በኩል ደረሱኝ፡፡ ከሦስት ሳምንት በኋላ ሽሪየም ፓሪስ መጣ፡፡ የአልበርቲንን ጽሑፎች ከዮሐንስ ገነ ፓውሼ ጋር አሳትሜላቸው ስለነበር ፥ በዚህ ምክንያት ሽሪየም እምነቱን በእኔ ላይ ጣለው፡፡

መጽሐፉን ያጠናቀረው ከፍተኛ ትዝታ ባፈለቀበት ወቅት ሲሆን፥ የተተየበውም ስሜቱ በማረካቸውና ፈቃደኞች በሆኑ ፥ ግን እምብዛም የፈረንሣዊኛ ቋንቋ ችሎታ በሌላቸው ግለሰቦች ነበር፡፡ እንዲያም ሆኖ ምንም ዐይነት ለውጥ አላደረግሁበትም፡፡ አልፎ አልፎ ነጥቦችና ሰረዞችን አስተካክያለሁ፣ በጣም ግልጽ ያልሆኑና ትርጉማቸውም የሚያደናግር አንዳንድ ጊዜም የተዘበራረቁና ታሪኩን የሚያምታቱ ሐሳቦችን ካራካስ ውስጥ የተለመደ ግን ከዚያ ውጭ እንግዳ የሆኑ ቀበሌኛ አነጋገሮችንና ጥቂት የስፖኝ ቃላትን አሻሽያለሁ፡፡

ለታሪኩ ዕውነተኛነት መተማመኛ ልሰጥበት እችላለሁ፡፡ ከሠላሳ ዓመታት በኋላ በመጠኑም ቢሆን፣ ዝርዝር ሐሳቦች መደብዘዛቸው ስለማይታበል በማስታወስ መስተካከላቸው ግልጽ ነው፡፡ ከሥረ መሠረቱ ሐቅ ለመሆኑና የቅኝ ግዛቱን አስቃቂ



@BOOKALEM

ወህኒ ቤት ኑሮ ወይም ሰቆቃ ሽሪየ ፍጹም እንዳላጋነነው ለማረጋገጥ "ካየን" የተባለውን የፕሮፌሰር ዴቪን መጽሐፍ ማንበብ ብቻ ይበቃል:: (የጁልያር ስብሰብ መዛግብት፥ 1965)

በቅኝ ግዛት ወህኒ ቤቶች የቅጣት አስተዳደር ውስጥ የነበሩትን የእሥረኞች ፥ የዘበኞችና የወህኒ ቤት አዛገሮች ትክክለኛ ስሞች በሙሉ እኛ በመሰለን መንገድ ቀይረናቸዋል:: የመጽሐፉ ዓላማ ግለሰቦችን ለመኰነን ሳይሆን በአንድ የተለየ ሕብረተሰብ ውስጥ የተለዩ ክፍሎችም እንዳሉ ለመግለጽ ያህል ነው:: ከቀናት አቆጣጠር አኳያም ተመሳሳይ እርምጃ ወስደናል:: አንዳንዶቹ አስተማማኝ ሲሆኑ ፥ ሌሎች ደግሞ በግምት ናቸው:: ከዚህ ውጪ ሌላ እርምት አልተካሔደም::

የሽሪየ ፍላጎት ታሪክ ለመጻፍ ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ በራሱ ተማምኖ፥ ምንም ነገር ሳይበግረው ሕይወቱን እንዴት እንዳሳለፈ ለመናገር ነው:: የዚህም ውጤት፥ ራሱን ከወንጀለኞች በተገቢው መንገድ ለመጠበቅ ፍላጎት ባለው አንድ ሕብረተሰብና፥ ስብዕናን የሚያጎድፍ የጭቆና ሥርዓት በምትከተል አንዲት የሰለጠነች ሀገር መካከል የነበረው ቅራኔ አልዋጥልህ ብሎት የታገለ የአንድ ልዩ ግለሰብ መዘከር ለመሆን በቃ::

ዮሐንስ ፒየር ካስቴልኖው

---

ይህን መግቢያ የጻፍኩት በግንቦት ወር 1969 ነበር:: መጽሐፉ የታተመው በዚያው ዓመት በሰኔ ወር ፈረንሣይ ውስጥ ነበር:: በሚያዚያ ወር 1970 አንድ ሚሊየን ቅጅ እዚያው ተሸጠ:: አንድ ጸሐፊ ይህን ያህል መጻሕፍት ሊሸጥ የቻለውና ሚስተር ሻሪየንም በማሞገስ እውነተኛ ድርጊታቸውን ተማምኖበት ለማሳተም የተነሳሳው ምናልባት ምን ነገር ይዞ ይሆን የሚል ጥያቄ በአንዳንድ አካባቢ በዚያው ሰሞን እስኪሥቶ ነበር:: እንደነዚህ የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ሲባል፣ የላፎ አሳታሚ ድርጅትና ባለታሪኩ በተገኙበት መጋቢት ወር 1970 አንድ ጋዜጣዊ ጉባኤ ተደረገ:: አንዳንድ ወቅቶችና ጥቃቅን እውነታዎች ከጊዜ መርዘም የተነሳ ተዘንግተው ቢሳሳቱም፣ ይህ መጽሐፍ ትክክልና በእርግጥም የራሳቸው ከንዋኔ መሆኑን ሚስተር ሽሪየ በድጋሚ ራሳቸው አረጋግጠዋል:: ከዚያም ቦሶይ ራሳችር እንዳሉት፣ "እዜያ ገሃነም እሳት ውስጥ" የገቡት ታሪክ ለመጻፍ ብዕር አንግበው እንዳልሆነ ተችተውበታል::



@BOOKALEM

# መግቢያ ከተርጓሚው

ዝናው በዓለም የተደነቀውን "ፓፒዮ" የተሰኘ መጽሐፍ ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ ተርጉሜ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎቹ ሳበረከት ደስታ ይሰማኛል።

መጽሐፉ በቅጽል ስሙ «ፓፒዮ» (ቢራቢሮ) እየተባለ የሚጠራው ሄንሪ ሻሪየ ባልፈጸመው ወንጀል የእድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ተፈርዶበት የፈረንሣይ ቅኝ ግዛት ወደነበረችው ፈረንሣይ ጊያና (በደቡብ አሜሪካ ሰሜናዊ ክፍል የምትገኝና አሁን ሲሪናም በሚል ሥያሜ የምትጠራ) አሰቃቂ ወህኒ ቤት ከተላከ በኋላ በተደጋጋሚ እያመለጠና እየተያዘ የተቀበለውን ፍዳና ያየውን የቁም ስቃይ፥ በወህኒ ቤቱም ሆነ በተለያዩ ሥፍራዎች ያጋጠሙትን የግለሰቦችና ማህበረሰቦች አኗኗር በሥፋት የሚገልጽ እውነተኛ ታሪክ ነው።

በውጪ ቋንቋ የተጻፈውን መጽሐፍ ምንም ሳይቀንስ ጋኑም ሳይጨምር ቃል በቃል ወደ አማረኛ መተርጎም ከባድ ተግባር ነው። የአንድን ሕብረተሰብ የሥነ ጽሑፍ ቋንቋና ዘይቤ ሳይዛቡ በትክክል ለሌላው ሕብረተሰብ ለማንጸባረቅ ምን ያህል አታካች ሥራ እንደሚሆን አንባቢ ሊገነዘበው ይችላል።

ጽሑፉን ወደ አማርኛ ስመልሰው ተስማሚ ፍቺ ያላገኘሁላቸውን አንዳንድ ቃላት በግዕዝና በዘልማድ በሚነገረው ቋንቋ የተካሁ ስሆን፥ አንዳንድ የእንግሊዝኛ ፥ ጣሊያንኛ ፥ ፈረንሣይኛና የስፓኝ ቃላትን እንዳሉ በመገልበጥ በመጨረሻው ገጽ ላይ መግለጫ ሰጥቸባቸዋለሁ።

ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች እንግዳ ይሆናሉ ብዬ የገመትኳቸውን ገርፒ፣ ሙቲው፣ ሴንት ዦሴፍ፣ ዲያብል፣ ወዘተ ... የመሳሰሉ የፈረንጅኛ አጠራሮችን ዮሐንስ፣ ማቴዎስ፣ ቅዱስ ዮሴፍ፣ ዲያቢሎስ ወዘተ ... በማለት ለውጫቸዋለሁ።

ዘመኑ የተገለጸው በአውሮፓውያን አቆጣጠር ነው። ሰዓቱን ግን ለአንባቢያን በቀላሉ ለመከታተል እንዲያመች ከኢትዮጵያውያን ሰዓት አቆጣጠር ቀመር ጋር አስተካከየዋለሁ።



@BOOKALEM

የሸሪየ ድርጊትና ትረካዎች በማያሻማ መንገድ ዕውነት ለመሆናቸውና አንባቢም ከጥርጣሬ ባሻገር እንዲሆን፥ መጽሐፉ ለመጀመሪያ ጊዜ በፈረንሣይኛ ሲታተም ያስተዋወቁት ጸሐፊ ዮሐንስ ፒየር ካስቴልኖው ያሰፈሩትን መግቢያና የላፎን አሳታሚ ድርጅት በአዘጋጀው ጋዜጣዊ ጉባኤ ላይ ራሳቸው ባለ ታሪኩ ተገኝተው የሰጡትን መተማመኛ ቃል በቃል ተርጉሜ ከዚህ በሚቀጥለው ገጽ አቅርቤያለሁ::

ሄንሪ ሸሪየ ከአሰቃቂው ወህኒ ቤት ነጻ ከወጡ በኋላ ያጋጠማቸውን የኑሮ ውጣ ውረድ ለማሳተም ያላቸውን ፍላጎት በ'ፓፒዮ' የመጨረሻ ገጽ ላይ በገቡት ቃል መሠረት "ባንኮ" የተባለ ሁለተኛ መጽሐፍ አዘጋጅተው የላፎን አሳታሚ ድርጅት በአዘጋጀው ጋዜጣዊ ጉባኤ ላይ ራሳቸው ባለ ታሪኩ አስመርቀዋል:: ጊዜና ሁኔታ ከፈቀደ እኔም አንድ ቀን "ባንኮ»ን ተርጉሜ ለወገኖቼ ለማቅረብ ተስፋ አደርጋለሁ::

ጌታቸው ገብሬ

(ደሴ)

@BOOKALEM

# አንደኛ ማስታወሻ

## ወደ ገሃነመ እሳት መውረድ

**ችሎት**(ቡክዓለም ያቀረበው መጽሐፍ-BOOKALEM)

ሕሊና የሚያስት ቅጣት ነበረ - ካረፈብኝ ከርን ክብደት የተነሣ ለሚቀጥሉት ዐሥራ አራት ዓመታት ከተዘረርኩበት መነሣቱ አልሆነልኝም። ያንን ያህል መዓት ላወረዱብኝም ሰዎች ቢሆን፣ አድራጎታቸው ሳይከብዳቸው አልቀረም።

ወቅቱ ኢ.ኤ.አ. ጥቅምት 26 ቀን 1931 ነበር። ለአንድ ዓመት በጥበቃ ጣቢያው ቆይቼባት ከነበረችው ክፍል ከጥዋቱ ሁለት ሰዓት ላይ አወጡኝ። ጺሜን ተላጭቼና በጥንቃቄ ለብሼ ነበር። ልብሱ በጥሩ ሰፊ የተዘጋጀ በመሆኑ አምሮብኛል። ነጭ ሸሚዜ፣ ዘንጠፍ ብሎ የወረደውና ድብዘዝ ያለው ሰማያዊው ከራቫቴ ማራኪነቴን ጨምረውልኛል።

ሐያ አምስት ዓመቴ ነበር፣ ግን የሐያ ዓመት ልጅ ነው የምመስለው። ፖሊሶቹ በጨዋ አቀራረቤ ይሉኝታ ተሰምቷቸው ስለነበር፣ በአክብሮት ይዘውኛል። የእጄን ካቴና እንኳ ሳይቀር አውልቀውልኝ ነበር። ስድስታችንም ከሙሉ፣ ማለት አምስቱ ፖሊሶችና እኔ ፓሪስ ከሚገኘው የሲየ ፍርድ ቤት ሕንፃ በአንድ ማረፊያ ክፍል ውስጥ በሁለት አግዳሚ ወንበሮች ላይ ተቀመጥን። በእኛ ትይዩ የሚገኙት መዝጊያዎች ወደ ችሎቱ ክፍል የሚያሳልፉ ነበሩ። ከውጭ በኩል አየሩ ጭፍግግ ብሏል።

በነፍስ ግድያ ወንጀል ፍርዴን ለመቀበል በመቃረብ ላይ ነበርኩ። ጠበቃዬ ሬይሞንድ ሂውበርት ሰላምታ ሊያቀርብልኝ ወደ እኔ መጣ፡ «ተጨባጭ ማስረጃ የላቸውም፤ እኛ በነጻ እንደምንለቀቅ እተማመናለሁ» አለ። በዚያች «እኛ» ባላት ቃል ፈገግ አልኩ። እርሱ ሳይሆን፣ እኔው ነበርኩ ለራሴው ጥብቅና የቆምኩት። አንድ ሰው ወህኒ ቤት ስለገባ ጠበቃውም አብሮ ይገባል ማለት አይደለም።

አንድ ዘበኛ መጥቶ ወደ ውስጥ እንድንገባ ቀሰቀሰን። ሁለቱ መዝጊያዎች ወለል ብለው ተከፈቱና በዳርና ዳር አራት ፖሊሶችና አንድ የሃምሳ አለቃ እንደተገተሩ ወደ ሰፊው አዳራሽ ገባሁ። የሚጠብቀኝን ውርጅብኝ እንደሚጠቁመኝ ሁሉ የማየው በሙሉ፣ ምንጣፎቹ፣ በትላልቆቹ መስኮቶች ላይ የተሰቀሉት መጋረጃዎች፣ በእኔ ላይ ፍርድ ሲሰጡ ተጣድፈው የተቀመጡት ዳኞች የለበሷቸው ካባዎች እንኳን ሳይቀሩ ቀይ ሆኑብኝ።

«ችሎት ተሠይሟል!»

ሰብሳቢው ዳኛ፣ ከዚያም አምስቱ ዳኞች ቆባቸውን እንዳደረጉ በስተቀኝ በኩል



@BOOKALEM

ካለ አንድ መዝጊያ በቅደም ተከተል ገቡ። ሰብሳቢው ዳኛ ከመካከለኛው ወንበር ፊት ለፊት ሲቆም የግራና የቀኝ ዳኞች ደግሞ በጎንና ጎን ቦታቸውን ያዙ።

ከፍሉን ረጭ ያለ ጸጥታ ሞላው። ከእኔ ጀምሮ ሁሉም ሰው ቀጥ ብሎ ቆመ። ከዚያም ዳኞቹ ተቀመጡ። እኛም እነሱን አይተን ተቀመጥን።

ሰብሳቢው ዳኛ ፈዛዛ ዐይኖችና ፍም የመሰለ ጉንጭ ያለው ወፍራም ሰው ነበር። ስሙ ቤቪን ይባላል። ቅንጣት ስሜት ሳይኖረው አትኩሮ ይመለከተኛል። ዘግየት ብሎም አድልዎ የሌለበት ብያኔውን በጥንቃቄ ይመራል። ከብዙ ጊዜ የዳኝነት ልምዱ የተነሣ በምስክሮችም ሆነ በፖሊሶች ላይ ያለው እምነት ጽኑ መሆኑን ሁኔታው በይፋ ይናገራል። ፍርዱን ብቻ ያነብንብ እንጂ በተከሳሽ ላይ ለሚሠነዘረው ጡጫ ኃላፊነትን አይወስድም።

ዓቃቤ ሕጉ ፐራደል ይባል ነበር። እንገት በማስቀንጠስም ሆነ ለሀገር ውስጥና ለቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ሰዎችን በማቅረብ «በቁጥር አንድ» መጋቢነቱ የጭካኔ ዝናን አትርፏል።

ፐራደል ያለአንዳች ሰብዓዊ ርኅራኄ ወንጀለኛን ለመበቀል ሕዝቡን ወክሎ የቆመ አፈሲያላዊ ነበር። ሕግና ፍትሕን ይወክላል፣ በማጣመምና ማንኛውንም ነገር ወደ ራሱ ፍላጎት በመጠምዘዝ የልቡን ያደርሳል። የጀቢራ ዐይኖቹ ትኩር ብለው ቁልቁል ይመለከቱኛል። ቁልቁለት የሆነበትም ምክንያት ከእኔ በላይ በመቀመጡና ቁመቱም ረጅም በመሆኑ ነበር። ስድስት ጫማ በመርዘሙም ይጀነናል። ቀይ ካባውን እንደለበሰ ሲሆን፣ ኬፑን ግን ከፊት ለፊቱ አስቀምጦ መንሽ በመሰሉት ትላልቅ እጆቹ አካሉን ደባበሰ። ባለትዳር መሆኑን ለማመልከት የወርቅ ቀለበት አድርጓል። በትንሿ ጣቱ ላይ ደግሞ በሚገባ የተወለወለ የፈረስ ኮቴ ምልክት ያለበት ሌላ ቀለበት ነበረው።

ይበልጥ ሲጫነኝ በማሰብ ወደፊት ትንሽ ሰገግ በማለቱ እንዲህ የሚለኝ ይመስለኛል። «ስማ ቀልደኛው ጓደኛዬ፣ ከእኔ ማምለጥ እችላለሁ ብለህ ብታስብ በጣም ተሳስተሃል። አታውቃቸውም እንጅ እጆቼ ሲበጫጭቁህ የተዘጋጁ የአውሬ ጥፍሮች ሆነዋል። ጠበቆች የሚፈሩኝ እጆቼ የገቡልኝን ተከሳሾች እንዲያመልጡ ዕድል ስለማልሰጣቸው ነው።

«ወንጀለኛም ሆንክ ወይንም ንፁሕ ሰው ለእኔ ጉዳዩ አይደለም። ተግባሬ ማንኛውንም ለአንተ ማንበርከኪያ የጋጠመኝን ዘዴ ሁሉ መጠቀም ነው። ቅጥ ያጣ የምንትማርትር ኑሮህን፣ በፖሊሶች ብርታት የተሰበሰበብህን መረጃ፣ ፖሊሶቹ ራሳቸው የመሰከሩብህና በመርማሪዎቹ ተቀናብሮ የቀረበብህን የግፍ አድራጎትህን አጣምሬ ፈጽሞ ተቀባይነትን በማሳጣት ተቾዎች ከሕብረተሰቡ ውጭ ወርውረው እንዲጥሉህ ማድረግ አለብኝ።»



@BOOKALEM

በእውን እየተናገረኝ ነው ወይንስ በሕልሜ? ያም ሆነ ይህ በዚህ «ሰው በላ» ፍጡር በተመሰጠ ተማርኬ ነበር።

«ልትከራከር አትሞክር። ለማምለጥ አትሞክር። በምንም መንገድ ወደ ቅጣት ጎዳናህ አሽቆልቁዬ ልልክህ ነው። በተቺዎቹም በኩል እምነት እንደማይኖርህ አምናለሁ። ከዚያ አኳያ ግብዝ እንዳትሆን። እነርሱ ስለሕይወት ምንም ነገር አያውቁም።

«ተመልከታቸው ከፊት ለፊትህ ናቸው። እነዚያን ከሩቅ መንደር ወደ ፓሪስ የመጡ ዐሥራ ሁለት ደደቦች በግልጽ ለማየት ችለሃል? አንዳንዶቹ ጡረተኞች፣ ሌሎቹ አነስተኛ ነጋዴዎች የሆኑ ንዑስ ከበርቴዎች ናቸው። ስለእነርሱ መናገር ዋጋ የለውም። በሞንትማርትር ስላሳለፍከው ኑሮም ሆነ ዕድሜህ ገና ሐያ አምስት ዓመት መሆኑን ተረድተው ያዝኑልኛል ብለህ መጠበቅ አትችልም። ለእነርሱ ፒጋሌና ፕላስ ብላንሽ የመሳሰሉት የምሽት ክበቦች ራሳቸው ገሃነም እሳት ሲሆኑ፣ ማንም ግማሽ ሌሊት በዚያ የሚያሳልፍ ሰው ሁሉ የሕብረተሰብ ጠላት ነው። በመሆኑም በዚህ ዓይነቱ ነጥብ ላይ በተቺነት ማገልገሉን ከመውደድም ከመጠን በላይ ይኮሩበታል። በተጨማሪም እነርሱም ቢሆኑ የሚፈጽሙት አንዳንድ መናኛ ተንኮል በዚህን ጊዜ ወለል ብሎ እንደሚታያቸው አረጋግጥልሃለሁ።

«ወጣትና መልከ መልካሙ ሲ የሞንትማርትሬው ዶን ጅዎን ነህ ብዬ ስገልጽልህ ምንም ነገር እንዳልደበቅሁ በእርግጥ ትገነዘባለህ? በቀጥታ ያንተ ጠላቶች እንዲሆኑ አደርጋቸዋለሁ። ተሸቀርቅረሃል። ይህን ያህል ማሸብረቅ አይገባህም ነበር። አለማወቅህ እንጂ! ትልቁ ስሕተትህ እዚያ ላይ ነው። በልብሶችህ እንደሚቀኑ አታይም? የእነርሱን የሚገዙት ከአውርዱልኝ መደብር ነው። በሕልማቸው እንኳ ወደ ልብስ ስፌት ቤት ሄደው አያውቁም።»

አሁን አራት ሰዓት ስለሆነ ጉዳያችንን ለመጀመር ተዘጋጅተን ነበር። ከፊት ለፊቴ ስድስት ዳኞች ሲኖሩ ከእነርሱ ውስጥ አንደኛው ያለውን የጭካኔ ሃይልና ብልሀነት በሙሉ በመጠቀም እነዚህን ዐሥራ ሁለት ነጋዴዎች ወንጀለኛ መሆኔንና ለዚህም ተገቢው ቅጣቴ ወህኒ ቤት መውረድ ወይም ሞት መሆኑን ለማሳመን ታጥቆ የተነሳብኝ ዓቃቤ ሕግ ነበር።

የተከሰሰኩት ሞንትማርትር ውስጥ በሚዘዋወር አንድ አቃጣሪና እርግብ ሻጭ ሰው ግድያ ነበር። ማስረጃ አልነበረም፣ ግን ፖሊሶቹ በየጊዜው አንድ ወንጀለኛ ባቀረቡ ቁጥር የደረጃ እድገት ስለሚያገኙ እኔ ወንጀለኛ እንድሆን ይገፋፉ ነበር። ማስረጃ ከማጣታቸው የተነሳ ከጥርጣሬ ጥላ ሥር የሚጥል አንድ «ሚስጥራዊ» መረጃ አለን ይላሉ። በዋና ፖሊስ መምሪያ ፓሊየን በሚል ስም የሚጠራ እንደ ተንቀሳቃሽ ቴፕሪኮርደር የሚቆጠር ቀንደኛ ምስክር መልምለው ነበር። ለፍርድ ቤቱም ይበልጥ



@BOOKALEM

ተጨባጭ ማስረጃ ነው የሚባለው እርሱው ነው፡፡ ከአሁን ቀደም እንደማላውቀው ብረዳም ሰብሳቢው ዳኛ እድልዎ የሌለበት በሚመስል ድምፅ እንደዚህ አለኝ፡፡

«ይህ ምስክር ይዋሻል ትላለህ፡፡ መልካም፣ ግን ለምን ይዋሻል?»

«ክቡር ሆይ፣ ከታሰርኩበት ጊዜ ጀምሮ ለሊቱን እንቅልፍ ሳይወስደኝ የቆየሁት ሮላንድ ፐቲን በመግደሌ ምክንያት ተጸጽቼ አልነበረም፡፡ አልገደልኩትም፡፡ ይህ ምስክር በተቻለ መጠን ለምን እኔን ለመጉዳት ቆርጦ እንደተነሳና እንደዚሁም ፍርድ ቤት ጠበቃዬ አዲስ የመከላከያ ነጥብ ባነሳ ቁጥር ለምን እንደሚያኮላሽበት ምክንያቱን ለመረዳት በመሞከር በሀሳብ በመናወዜ ነበር፡፡

ክቡር ሆይ ምስክሩ ራሱ የሚያስጠይቀው አንድ ወንጀል በመፈጸም ላይ እንዳለ በፖሊስ መያዙንና በእኔ ላይ እንዲመሰክርም ድርድር ማድረጋቸውን አውቃለሁ፡፡ 'በፓፒዮ ላይ የምታቀርበውን የምስክርነት ቃል ከሌላ አቅጣጫም እንመለከተዋለን' ሲሉ ደልለውታል ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሻለሁ፡፡»

, በዚያን ጊዜ የቱን ያህል ወደ እውነቱ መቃረቤን አላወቅሁትም ነበረ፡፡ ፖሊየን ራሱን ባለንጹሕ ሪኮርድና የተከበረ ሰው አድርጎ በችሎቱ ላይ ለማስገንዘብ ሞከሯል፡፡ ሆኖም ከጥቂት ዓመታት በኋላ አደገኛ ዕፅ ሲያቀብል በወንጀለኛነቱ ተይዞ ለመታሰር በቃ፡፡

ጠበቃዬ ሂውበርት ሊገላገልልኝ ሞከረ፡፡ ግን ከዓቃቤ ሕጉ ጋር መቋቋም አልሆነለትም፡፡ አንደኛው ምስክሬ ቡፍሬይ እንኳ በብስጭት ገንፍሎ የትንሽ ጊዜ ችግር ተፈጥሮበት ነበር፡፡ ብልጣ ብልጡ ፕራደልም ረቺ ለመሆን በቃ፡፡ ሌላው ቀርቶ ተችዎቹን ያለመጠን በማሞካሸት በዚህ አስገራሚ ጠባዩ እንደአቻና ተባባሪዎቹ አድርገው ራሳቸውን እንዲቆጥሩ ገፋፋቸው፡፡

በዚያ ሌሊት አምስት ሰዓት ላይ ፍርድ ተሰማ፡፡ ያለማንገራገርም እጄን ሰጠሁ፡፡ ንጹሕ የነበርኩት ወንጀለኛ ሆኜ ተገኘሁ፡፡

የፈረንሣይ ኅብረተሰብ ፕራደል በተባለ ዓቃቤ ሕጉ አማካይነት አንድን የሐያ አምስት ዓመት ወጣት በዕድሜ ይፍታህ እሥራት ለማስወገድ ተሣካለት፡፡ ይድነቃችሁ፣ ቅጣቱ የሚሻሻል አልነበረም! ይህ እንደ ጣፋጭ ምግብ በሣህን ሙሉ ተቆልሎ የቀረበልኝ ውሳኔ የተነገረኝ በለዛቢሱ የመሐል ዳኛ ቤቪን አንደበት ነበር፡፡

«እስረኛው እንዲቆም ይጠየቃል»፡፡

ተነሣሁ፡፡ ሁሉም ሰው ትንፋሹን ዋጥ አድርጎ ስለያዘ ክፍሉ ጸጥ ብሏል፡፡ ልቤም የምቱን ፍጥነት ትንሽ ጨመረ፡፡ ተቺዎቹ ወደ እኔ ይመለከታሉ፡፡ አለበለዚያም ራሶቻቸውን ይቀረቅራሉ፡፡ ያፈሩ ይመስላል፡፡

ከአንዱ በስተቀር ለሁሉም ጥያቄዎች ተችዎች፣ ‹በአዎንታ› መልሰዋል፡፡



@BOOKALEM

እርሱም በቂም በቀል ያልተፈጸመ ወንጀል መሆኑን ነው:: ስለሆነም «የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ተፈርዶብሃል:: የምትናገረው ጉዳይ አለህ?»

አልተነቃነቅኩም:: የእስረኛ መቆሚያ ሣጥኑን አግዳሚ ብቻ ትንሽ ጠበቅ አድርጌ ያዝኩ:: «ክቡር ሆይ፣ አዎ፣ በአንድ ፖሊስ ለተቀነባበረ ሻጥር ተዳረግኩ እንጂ፣ በሐቅ ንፁሕ ነኝ ማለት እፈልጋለሁ::»

በስተኋላ ካለው ወንበር በተለይ ተጋብዘው ከተቀመጡት ወይዛዝርት የሆነ ማጉረምረም ተነሣ:: ድምፄን ከፍ ሳላደርግ እንዲህ አልኳቸው:: «እርኩስ ስሜታችሁን ለማርካት ወደዚህ የመጣችሁ፣ በሉል የተሸቀረቀራችሁ እናንተ ሴቶች፣ ዝም በሉ:: ድራማው አብቅቷል:: በሕጋችሁና በፖሊሶቻችሁ አንድ የነፍስ ግድያ ወንጀል ተጣርቷል፣ ስለዚህ ልትደሰቱ ይገባል::»

«እባክህ ይህን እስረኛ ወዲያ ብታገልልን» አለ ሰብሳቢው ዳኛ:: ወደ ውጭ ከመወሰዴ በፊት አንድ ጎላ ያለ ድምፅ ሰማሁ፣ «አትጨነቅ የእኔ ፍቅር፣ እዚያው ድረስ እከተልሃለሁ::» እውነተኛዋን መልካሟ የእኔዋ ኒኔቴ ፍቅሯን እያስተጋባችልኝ ነበር:: በችሎቱ አዳራሽ የነበሩትም የአራዳ ጓደኞቼ አጨበጨቡልኝ:: ስለዚህ ግድያ እውነቱን ያውቁ ስለነበርና እኔም ባለማልቀሴ ኩራት እንደ ተሰማቸው ለመግለጽ ነበር::

ከችሎቱ በፊት ወደነበርንበት አነስተኛ ክፍል ተመልሰን ሔድን:: እዚያም ፖሊሱ እጄ ውስጥ ካቴና አስገባና ቆለፈው:: ከእነርሱም ውስጥ ከአንደኛው የግራ እጅ አንጓ ጋር የእኔን ቀኝ እጅ አንጓ አቆራኙ:: ማንም ሰው አይናገርም:: አንድ ሲጃራ ጠየቅኩ:: ዘበኛው አወጣና አቀጣጥሎ ሰጠኝ:: በየጊዜው ወደ አፌ በወሰድኩና ባወረድኩ ቁጥር ፖሊሱም የእኔን እንቅስቃሴ ለመከተል ክንዱን ማንሣት ወይም ማውረድ ነበረበት:: የሲጃራውን ሦስት አራተኛ ጨረስኩ:: አሁንም አንድ ቃል እንኳ አልተሰነዘረም:: ግልጡ ሠረገላ እኛን እየጠበቀ ነበር:: ሁላችንም መቀመጫው ላይ ቦታችንን ያዝን:: «ጥበቃ ጣቢያ» አለ ሃምሳ አለቃው::

## ጥበቃ ጣቢያ

የንግሥት ማሪ አንቷኔት የመጨረሻው ቪላ ስንደርስ፣ ፖሊሱ አንድ የመተማመኛ ደብዳቤ የጥበቃውን ኃላፊ አስፈረመና አስረከበኝ:: ከፖሊሶቹ ጋር አንድም ቃል ሳንነጋገር ከመለያየታችን በፊት በካቴና የታሰረውን እጄን ሃምሳ አለቃው ጨበጠኝ::

«ምን ፈረዱብህ?» ሲል የጥበቃ አዛዡ ጠየቀኝ::

«ዕድሜ ልክ!»

«ማመን አልችልም» አለና እንደገና ፖሊሱን ትኩር ብሎ ሲመለከተው፣



@BOOKALEM

እንዳልኩት መሆኑን አረጋገጠለት። ከዚያም ብዙ ነገሮችን ያየውና ስለእኔም ከስ በሚገባ የተረዳው ይህ ሃምሳ ዓመት ዕድሜ ያለው የወህኒ ዘበኛ እነዚህን የማጽናኛ ቃላቶች ጣለልኝ።

«እነዚያ ውሾች! ዕብዶች መሆን አለባቸው!»

የእጄን ካቴና በዝግታ አወለቀና በተለይ ሞት ለተፈረደባቸው፣ ለዕብዶች፣ በጣም አደገኞችና የዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት ለተፈረደባቸው ማሠሪያ እንዲሆን ወደተቀየሰው ድርብርብ ክፍል ይዞኝ ሔደ።

«በርታ ፓፒዮ» አለኝ በሩን በመዝጋት ላይ እንዳለ። «ጓዞችህንና ከአሁን በፊት በሌላው ክፍል ስታገኝ የነበረው ዓይነት ተመሳሳይ ምግብ ይላከልሃል። እንገትክን አትድፋ» አለ።

«አመሰግናለሁ ጌታዬ። እመነኝ እንገቴን አልደፋም፣ እነርሱም ዕድሜ ልካቸውን እንደሚታፈኑ ተስፋ አደርጋለሁ።»

ከትንሽ ደቂቃ በኋላ በመዝጊያዬ ላይ አንድ የሚቧጥጥ ድምፅ ሰማሁ።

«ምንድነው?»

«ምንም አይደለም። እኔ ነኝ አንድ ምልክት እየሰቀልኩ ነው» የሚል አንድ ድምፅ መለሰ።

«ለምን? ምን ይላል?»

«ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተፈረደበት፣ በዐይነ ቁራኛ ይጠበቅ» የሚል።

በእውነት እብዶች ናቸው ብዬ አሰብኩ። ያ የወረደብኝ የፍርድ በትር ራሴን እንድገድል ሊገፋፋኝ ይችላል ብለው በእርግጥ ያስባሉ እንዴ? እንገቴን አልደፋሁም፣ በዚያ ሁኔታም እጠብቀዋለሁ። ሁሉንም ልታገላቸው ነው፣ ከነገ ጀምሮ ተግባሬን እቀጥላለሁ።

በማግሥቱ ቡናዬን በመጠጣት ላይ እንዳለሁ፣ ይግባኝ መጠየቅ ይኖርብኝ ይሆን ስል ራሴን ጠየቅሁት። በሌላ ፍርድ ቤት የተሻለ ዕድል አገኝ ይሆን? ይህን ለማድረግ ምን ያህል ጊዜ ይወስድብኛል? ምናልባት አንድ ዓመት . . . ዐሥራ ስምንት ወራት፣ ግን ለምን? በዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ፋንታ ሐያ ዓመት ለማግኘት?

ማንኛውንም ዋጋ ከፍዬ ለማምለጥ እስከወሰንኩ ድረስ የዓመቶቹ ቁጥር ፋይዳ የለውም። አንድ ሌላ እስረኛ ለሰብሳቢው ዳኛ አመልክቶ የነበረውን አቤቱታ አስታውሳለሁ።

«ክቡር ሆይ፣ ለመሆኑ በፈረንሣይ ውስጥ የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ማከተሚያው እስከ መቼ ይሆን?»

በክፍሌ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እመላለሳለሁ። ብቻዋን ከዓለም ጋር



@BOOKALEM

ለወንድሟ ልትከራከር ለሞከረችው እህቴና ለሚስቴ የማጽናኛ ሰልክ ደውያለሁ፡፡

ያከተመ ነገር ነበር፣ መኃረጃው ተዘግቷል፡፡ ከእኔ ይበልጥ የሚሰቃዩት ቤተሰቦቼ ናቸው፡፡ ከከፍለ ሀገር.ርቆ የሚኖረው ምስኪኑ አባቴም ይህን ከባድ መሰተል ለመሸከም ይሳነዋል፡፡

ይህን ማሰላሰል እንደጀመርኩ ከሐሳቤ ብንን አልኩ፡፡ በእርግጥ አንተ ንጹሕ ነበርክ፡፡ ግን ማን ያምንሃል ስል ራሴን ጠየቅሁት፡፡ ንጹሕነትህን በየቦታው እየዞርክ መወትወት አቁም፡፡ መሣቂያ ብቻ ነው የሚያደርጉህ፡፡ ያውም ሌላ ሰው በፈጸመው፡፡ በአንድ አቃጣሪ ግድያ ምክንያት ዕድሜ ልክ መታሰር ከባድ ግፍ ነው፡፡ አፍህን መዝጋት ይሻላል፡፡

ያም ሆነ ይህ፣ በቅድሚያ መደረግ የሚገባው ጉዳይ ማምለጥ ከማፈልግ አንድ ሌላ እስረኛ ጋር ግንኙነት መፍጠር ነበር፡፡

ከማርሴይ የመጣ ዴጋ የተባለ አንድ ሰው አስታወስኩ፡፡ ምናልባት ጺጉር ማስተካከያ ቤት አገኘው ይሆናል፡፡ በየቀኑ ጺሙን ለመላጨት ይሔዳል፡፡ እኔም እንደዚሁ እዚያው ለመሔድ ጠየቅኩ፡፡ እዚያ በምደርሰበት ወቅት ፊቱን ወደ ግድግዳው አዙሮ ቁሞ ነበር፡፡ ረዘም ላለ ጊዜ ተራውን እየጠበቀ ለመቆየት እንዲያመቸው አንድ ሌላ ሰው ቀድሞት እንዲሔድ ዕድል ሲሰጠው ተመለከትኩት፡፡ እኔም አንድ ሌላ ሰው ፈቀቅ እንዲልልኝ በኃይል ገፈተርኩና ልክ ከእርሱ ቀጥዬ አንድ ቦታ ያዝኩ፡፡ ድምፄን ዋጥ በማድረግ በለሆሳስ፣

«ታዲያስ ዴጋ ሁኔታዎች እንዴት ናቸው?» ስል አናገርኩት፡፡

«ደህና ነኝ ፓፒ፡፡ ዐሥራ አምስት ዓመት ተፈረደብኝ፡፡ የአንተስ እንዴት ነው? ያለጥርጥር እንደ.ቀለዱብህ ሰማሁ፡፡»

«አዎ፣ ዕድሜ ልክ ተፈረደብኝ፡፡»

«ይግባኝ ልትጠይቅ ነው?»

«አልጠይቅም፣ ጥሩ ምግብ እየበላሁ አቋሜን አጠነክራለሁ፡፡ ጠንካራ መሆን ይኖርብሃል ዴጋ፡፡ አንድ ቀን ጠንካራ ጡንቻዎች ያስፈልጉን ይሆናል፡፡ ትንሽ ገንዘብ አለህ?»

«አዎ፣ በፓውንድ ስተርሊንግ ዐሥር ሺ ፍራንክ አለኝ፡፡ አንተስ?»

«አንዲት ቤሳ የለችኝም»

«ትንሽ ምክር ልስጥህ? ጥቂት ገንዘብ ቶሎ ብለህ ፈላልግ፡፡ ጠበቃህ ሂውበርት ነበር አንዴ? እርሱ ጭራሽ አይረዳህም፣ ከንቱ ነው፡፡ ይልቅስ አንድ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ ሚስትህን አሲዘህ ወደ ዳንቴ ላካት፡፡ ለዶሚኒክ ሪቼ እንድትሰጠው ንገራትና እርግጠኛ ነኝ ታገኛለህ፡፡»



@BOOKALEM

«ሽሽሽ፣ ዘበኛው ወደ እኛ እየተመለከተ ነው።»

«ታዲያስ፣ ትንሽ ጨዋታ ይዛችኋል?»

«ምን የሚያስደስት ነገር አለ?» ብሎ ዴጋ መለሰለትና በማከታተል፣

«እርሱ ሕመም ይሰማኛል ይላል» አለው።

«ምን አገኘው? የፍርድ ቤት ቁንጣን ነው?» ብሎ ቂሎ በሳቅ ፈነዳ።

እንግዲህ ይኸው ነው። አንዴ ከቅጣት ወጥመድ ገብቻለሁ። የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት በተፈረደበት አንድ የሐያ አምስት ዓመት ወጣት ላይ እየቀለደ እንደ ዕብድ ይንከትከት እንጂ።

የገንዘብ መደበቂያ ቱቦየን አገኘሁ። በመካከሏ ተከፋች የሆነች በጣም የምታንጸባርቅ አንዲት የአሉሚኒየም ቱቦ ነበረች። የአምስት ሺ ስድስት መቶ ፍራንክ አዲስ ኖቶች ታጭቀውባታል። እንዳገኘኋት ሳምኳት። አዎ ርዝመቷ ሁለት ኢንች ተኩል የሆነና አውራ ጣት የምታክለውን ያችን አንዲት ትንሽ ቱቦ ወደ ፊንጢጣዬ ከመግፋቴ በፊት እንደገና ሳምኳት። ፊንጢጣዬ እንዲሰፋልኝ ያለማቋረጥ ትንፋሼን ለረጅም ጊዜ ወደ ውስጥ ሳብኩ። ካዝናዬ መሆኑ ነበር። ልብስህን ሁሉ አውልቅ፣ እግሮችህን ለየብቻ አንፈራጥ፣ እንጢስ በል፣ ወይም ወደፊትና ወደ ኋላ አጎንብስ፣ እነሱን ደስ ባላቸው መንገድ ሁሉ ሊበረብሩኝ ይችላሉ። የገንዘብ መደበቂያዋ ቱቦ ወደ ወተት አንጀቴ አሻቅባ ወጥታለች። የአካላቴ አንዷ ክፍል ሆናለች። ሕይወቴንና ነጻነቴን፣ የመበቀያዬንም ጎዳና መከፈቻ በውስጤ ተሸክሚያለሁ። በሐሳቤ ውስጥ የሚመላለሰው ይህ ነበር፣ ብቀላ። በእርግጥም ሐቁ ይኸው ብቻ ነበር።

ከውጭ ጨለማው ከብዷል። በክፍሌ ውስጥ ብቻዬን ነኝ። ከጣራው ላይ አንድ ኃይለኛ መብራት ስለሚበራ መዝጊያው መካከል በምትገኝ አንዲት ቀዳዳ ዘበኛው ሊያየኝ ይችላል። ኃይለኛው ብርሃን ዐይኔን ወጋኝ። በቆሰለው ዐይኔ ላይ አንድ መሐረብ አጣጥፌ አስቀመጥኩበት። ትራስ በሌለው የብረት አልጋዬ ፍራሽ ላይ ተጋደምኩና ያንን አሰቃቂ ፍርድ እየደጋገምኩ ማብሰልሰል ጀመርኩ። ይህን ረጅም ታሪክ ሳይታጠፍ እንድትረዱትና እኔንም ከትግሌ ጋር ምን እንዳቆራኘኝ፣ በረጅሙ መተንተን ይኖርብኛል። ከእነዚያ በሕይወት ተቀብሬባቸው ከነበሩት ቀኖች በኋላ ምን እንደተደረገና በአዕምሮዬ መነጽር ያየሁትን ማንኛውንም ነገር በሙሉ ልነግራችሁም ይገባኛል።

ከአመለጥኩ በኋላ ምን ማድረግ ይኖርብኛል? አሁን የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ ስላለችኝ፣ ለጊዜው ምንም የሚያሳስበኝ ነገር ይኖራል ብየ ፍጹም አላስብም።

እንግዲህ በተቻለ ፍጥነት ወደ ፓሪስ እመለሳለሁ። ከዚያም በመጀመሪያ የምገድለው ሰው ያን አዋሻኪ ፖሊየንን ይሆናል። ከዚያ በኋላ ሁለቱን ጀሮ ጠቢዎች።



@BOOKALEM

ግን ሁለቱ ጆሮ ጠቢዎች በቂ አይሆኑም፣ ጆሮ ጠቢዎቹን በሙሉ መግደል አለብኝ። ወይም በብዛት የሚቻለውን ያህል። አንድ በርሜል ውስጥ የቻለውን ያህል ፈንጂ አሞላበታለሁ። ያ በትክክል ምን ያህል እንደሚይዝ አላውቅም። ሐያ፣ ሠላሳ፣ ዐርባ ፓውንድ? ለብዙ ሰዎች መግደያ የሚያስፈልገኝ ምን እንደሚሆን ለማሰላሰል ሞከርኩ። የማፈንጃው ከምሱር በከፍተኛ ጥንቃቄ ተጠምዶበት በፈንጂ የተወጠረውና ሲመለከቱት ግን አልባሌ ነገር የሚመስለው በርሜል ቁል ብሎ ሲታየኝ ለመከለያ በመሐረም ሸፍኛቸው የነበሩትን ዐይኖቼን ከውስጥ በ ጭፍን አደረግኩ። ቀይ በ36 የኪደ ኦርፌቫር ጎዳና ላይ ከሚ ዋናው ፖሊስ መምሪያ ሁለተኛ ፎቅ ስምሪት ክፍል ውስጥ፣ ልክ ከጠዋቱ አራት ሰዓት መፈንዳት አለበት። በዚያ ሰዓት የዕለቱን የሥራ ትዕዛዝ ለመቀበልና ሪፖርት ለመስማት ቢያንስ አንድ መቶ ሃምሳ ፖሊሶች በክፍሉ ውስጥ ይኖራሉ። ይህን ለመውጣት ስንት ደረጃዎች አሉ፣ በትክክል ማወቅ ይኖርብኛል።

ለመፈንዳት በሴኮንድ የሚቆጠር ጊዜ ሲቀረው በርሜሉን ከመንገዱ ወደ አድራሻው ለመውሰድ ምን ያህል ጊዜ እንደሚፈጅብኝ በትክክል መገመት አለብኝ። ለመሆኑ በርሜሉን የሚሸከመው ማነው? መልካም፣ ቀይ . . . በመግቢያው ፊት ለፊት ድንገት በአንድ ታክሲ እደርስና ሁለቱን ዘበኞች በባለሥልጣን ትዕዛዝ ድምፅ እንደዚህ ብዬ እነግራቸዋለሁ። «ይህን በርሜል ወደ ስምሪት ክፍል ውሰዱ። እኔም እዚያው እመጣለሁ። የላከሁት ዋናው ኢንስፔክተር ዱቧ መሆኔንና በትንሽ ደቂቃ ውስጥ እዚያው እንደምመጣ ለኮሚሽነር ዱፖ ንገሩት።»

ግን ይታዘዙኝ ይሆን? በሠራዊቱ ውስጥ ካሉት ከነዚያ ሁሉ ደደቦች መካከል የእኔ ዕድል ሁለት ነጭ ለባሾችን ብቻ መግደል ቢሆንስ? ከዚያም እኔም ቢጨርሱኝ። ሌላ የተሻለ ነገር ማሰብ አለብኝ። ስለሆነም ደጋግሜ አሰብኩ። ማንኛውንም ነገር መቶ በመቶ እርግጠኛ ሆኜ ለመቀበል ፈጽሞ አልሆነልኝም።

ውሃ ለመጠጣት ተነሣሁ። ብዙ ማሰቤ ራስ ምታት አሳድሮብኝ ነበር። ዐይኔን ሳልሸፍን እንደገና ተጋደምኩ። ጊዜው ተንተተገኝ። ያ መብራት ደግሞ፣ ያ መናጢ መብራት ነበር! መሐረቤን አራስኩና እንደገና አስቀመጥኩበት። ቅዝቃዜው በሚገባ ተሰማኝ። ከብደቱም ጨርቁ ዐይኔ ላይ ምርግ ብሎ እንዲቆይ አደረገው። ከዚያ ወዲያ ዘወትር እንደዚሁ አደርጋለሁ።

የወደፊት በቀላዬን አንድ ላይ እያቀነባበርኩ የማጠፋቸው ሰዓቶች እጅግ የላቁ ከመሆናቸው የተነሣ አቅዶቼ አሁኑ ልክ በተግባር ላይ የዋሉ ይመስሉኝ ጀመር። ዘወትር ሌሊትና ቀኑንም በከፊል ማምለጤ በገሃድ እንደተሳካልኝ ሁሉ ፓሪስ ውስጥ እዞራለሁ። አመልጣለሁ፣ ፓሪስም እመለሳለሁ። ከዚያም እንደሚታወቀው በቅድሚያ በያኔዬን



@BOOKALEM

ለፖሊየን፣ ቀጥሎም ለጆሮ ጠቢዎቹ አቀርባለሁ:: ግን ተቺዎቹስ? እነዚያ ውላጆች የሰላም ኑሮን እየገፉ ናቸው? እነዚያ ግብዞች ሥራቸውን በከፍተኛ ጥራት እንዳከናወኑ ሁሉ ደስ ብሏቸውና ፈንድቀው በኩራት እንደ ተወጠሩ በጎረቤቶቻቸው ፊት ታላቅ መስለው ለመታየትና ጸጉራቸውን ሳያበጥሩ ከሚጠብቋቸው ሚስቶቻቸው ጋር ሾርባ ለመጋት ወደቤታቸው ሔደው መሆን አለባቸው::

ተቺዎቹን ምን ማድረግ ይኖርብኛል? ምንም:: መልሱ ይኸው ነበር:: በእርግጥም ታላፊነት የጎደላቸው አሳዛኝ ፕርቅሞች ነበሩ:: ዝም ብዬ እተዋቸዋለሁ::

እነዚህን ሐሳቦች በመጻፍ ላይ እንዳለሁ ከረጅም ዓመታት በፊት የነበሩ ሐሳቦች አሁን ከፉኛ በሚያስፈራ ሁኔታ እየተጋረጡ፣ ረጭ ባለ ጸጥታና በሙሉ ብቸኝነት አንዲት ከፍል ውስጥ ተዘግቶብኝ የሐሳብ ኑሮን መግፋቴ ስሜቴን ይከነክነዋል:: በእርግጥ ሁለት ሕይወቶችን ኖሬያለሁ:: ወደቤቴ፣ ወደ አባቴ ወደ እናቴ ወደቤተሰቦቼ፣ ወደ ሕፃንነቴና በየደረጃው ካንዱ ወደሌላው የሕይወት ዘመኔ በሐሳቤ እየበረርኩ የፈለግሁበት ቦታ ሁሉ ዞሬያለሁ::በሌላ በኩል ሲጋው አእምሮዬ በፈለሰፋቸው በስፓኝ ውስጥ ባሉ ቤተ መንግሥቶች ውስጥ በመኖር ላይ እንደምገኝ አድርጌ ራሴን ለማሳመንም በቅቼ ነበር::

ሠላሳ ስድስት ዓመታት አልፈዋል፣ በዚያ የሕይወት ዘመኔ ያሳለፍኳቸውን ሁሉ አስታውሼ ለመጻፍ አእምሮዬ እምብዛም አይጨነቅም::

አላደርገውም! ተቺዎቹን አልጎዳቸውም:: ግን የዓቃቤ ሕጉስ ጉዳይ? እርሱንማ . . .! እሱንስ አልምረውም! ከዚህም በላይ ለአሌክሳንደር ዱማስ ምስጋና ይግባውና በጣም ተስማሚውን ቅጣት በሚገባ አግኝቼለታለሁ:: «የሞንቴ ኪሪስቶ መኳንንት» በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ያንን ምስኪን ከንቱ ሰው በአንድ ከምድር ሥር በተሠራ ከፍል ውስጥ ቆልፈውበት እንደገደሉት ዐይነት፣ ልክ እኔም እንደዚያው አደርጋለሁ::

በተቻለው መጠን የመጨረሻ አሰቃቂ ውድቀት እንዲገጥመኝ ማገኛውንም ነገር ሁሉ የፈጸመብኝ፣ በቀይ ካባ ውስጥ የተሸፈነው ያስ ጆቢራ አሞራ? አዎ በተለይ በእርሱ ላይ የማተኩረው፣ ከፖሊሶቹና ከፖሊየን በኋላ ይሆናል:: ከሥሩ ከመቀመቅ የጠለቀ ምድር ቤት ወፍራም ግድግዳና ከባድ መዝጊያ ያለው አንድ ቪላ እከራያለሁ:: መዝጊያው ወፍራም ካልሆነም ራሴው በኪሻና በጥጥ እለብደዋለሁ:: አንድ ጊዜ ቪላውን ካገኘሁ በኋላ ጌታው ፕራደልን እፈልግና አፍኜ እወስደዋለሁ:: ወዲያውኑ እንደደረስን በግድግዳው ካሉት ቀለበቶች ጋር በሰንሰለት እጠፍረዋለሁ:: ከዚያም የእኔ ተራ ይጀምራል::

ከእርሱ ፊት ለፊት ነኝ:: ከተከደኑት የዐይኖቹ ቆቦች ሥር በልዩ ሁኔታ ግልጽ



@BOOKALEM

ሆኖ አየዋለሁ፡፡ እርሱ በፍርድ ቤቱ እንደ ተመለከተኝ ዐይነት እኔም እመለከተዋለሁ፡፡ የትንፋሹ ሙቀት በፊቴ ላይ ይሰማኛል፡፡

በእርሱ ላይ ያነጣጠርኩት ኃይለኛ የብርሃን ጨረር የጆቢራ ዐይኖቹን ስላደናበራቸው በጭንቀት ተደናግጠዋል፡፡ ግዑዝ በሆነው ፊቱ ላይ ወፍራም የላብ ጠብታዎች ቁልቁል ይወርዳሉ፡፡ አዎ፣ የእርሱንም መልስ እያዳመጥኩ የእኔንም ጥያቄዎች አሰማለሁ፡፡ ጊዜውን በጋራ ስሜት እገፋዋለሁ፡፡

«አንተ መናጢ ደደብ፣ ለመሆኑ ታስታውሰኛለህ? እኔ ፓፒዮ ነኝ! ወደ ዕድሜ ልክ ፅኑ እሥራት እንድገባ አንተ በደስታ የተስማማህብኝ ያ ፓፒዮ! በሮማውያን የሕግ አንቀጾች ላይ ያጠፋሃቸው እነዚያ ሁሉ ሌሊቶች፣ ግሪክና ላቲን ለማጥናት የወጣትነት ዘመንህን በመሠዋት ዕውቀትን ለማትረፍ ያሳለፍካቸው እነዚያ ሁሉ አድካሚ ዓመታት፣ አሁን ዋጋ አላቸው ብለህ ታስባለህ? የት ለመድረስ ነበር ያለምከው አንተ ከንቱ? የተሻለ የሕብረተሰብ ሕግ ለመፍጠር ነበር? ሰላም ለሽብር ፋጣሪዎች በዓለም ውስጥ ከፍተኛ ጠቃሚ ነገር መሆኗን ለማሳመን ነበር? አንድ ቤዛ የሆነ አዲስ ሃይማኖት ለመስበክ ነበር? ወይም ሌሎች ሰዎች በቀላሉ የትሻሉ የሚሆኑበትን አለበለዚያም ቢያንስ ከፉ መሆናቸውን እንዲያቆሙ ለመንገር ነበር? –

«ከዚህ ውስጥ ምንም ነገር አልፈጸምክም፡፡ የሚገፋፋህ አንድ ምኞት ብቻ ነው፡፡ መንጣላጠል፣ መንጠላጠል፣ በወራዳው ሙያህ መሰላል ላይ መንጠልጠል፡፡ ለአንተ ክብርህ ሰውን ለቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ዳረጎት አቅራቢነትና ይበልጥ ደግሞ ለሞትና ለስቃይ ከፍተኛ ችሮታ ለጋሽ መሆን ነበር፡፡

«ዲብለር፣ (በ1932 ዋና ገዳይ የነበረ) ቅንጣት ታህል ምስጋና ሊያቀርብልህ ቢፈልግ በየዓመቱ መጨረሻ ላይ አንድ ሣጥን ምርጥ ሻምፓኝ ይልክልሃል፡፡ በአንድ ዓመት ውስጥ አምስት ወይም ስድስት ተጨማሪ ጭንቅላቶች ለመቁረጥ መቻሉ ለአንተ ምስጋና አይደለም? አንተ ዓሣማ! ያም ሆነ ይህ አሁን በ[illegible] ግድግዳ ላይ በሰንሰለት ጠፍሬሃለሁ፡፡

«የፍርዱን ውጤት ስትሰማ የነበረህን ፈገግታና የፍንደቃ አስተያየት በሚገባ አስታውሳለሁ! አሁን ታድያ ወዳጄ፣ ያንን ሁሉ ልለውጠው ነው፡፡ ይሁንና እኔ ያሳጋጠመኝ አንድ ዕድል አለህ፡፡ እኔ ማልቀስ አልቻልኩም፣ አንተ ግን [illegible] ችላለህ፡፡ ስለዚህ ቀጥል፡፡ የፈለግከውን ያህል አልቅስ፣ አልቅስ፣ የፈለግከውን ያህል ጩህ፡፡ ምን ባደርግህ ይሻለኛል? በረኃብ እንድትሞት ልተውህ? አይሆንም፣ በቂ አይሆንም፡፡ በቅድሚያ ዐይኖችህን አወልቃቸዋለሁ፡፡ ይህም አይሆንም፡፡ ያ በኋላ የሚመጣ ነው። በመጀመሪያ ያንን እንደ ጨቤ የተሣለ እንዲያውም ከጩቤ የበለጠ እንደ ምላጭ የሰላውን ያን መዓተኛ ምላስህን እቆርጠዋለሁ፡፡ ያንን ምላስ ለዝነኛው ሙያህ



@BOOKALEM

ሽርሙጠህበታል!»

ጭንቅላቴ እስኪዞር ድረስ እየደጋገምኩ እራመዳለሁ፣ ግን ድንገት መብራቱ ጠፍቶ በመንጋት ላይ ያለው የቀን ውጋጋን በከፍሌ መስኮት ፍርግርግ ብረቶች ውስጥ እስኪገባ ድረስ . . . ከርሱ ጋር ፊት ለፊት እንደ ሆንኩ ቆየሁ::

እንዴት ሊሆን ቻለ? በአንድ ጊዜ ነጋ ማለት ነበር? እነዚያ ሰዓቶች ምንኛ ቆንጆዎች ነበሩ! የረጅም ረጅም ሌሊት እንዴት ፈጥኖ ሔደ!

በአልጋዬ ላይ እንደ ተቀመጥኩ አዳምጣለሁ:: ምንም ነገር የለም:: ፍጹም ፀጥታ:: አልፎ አልፎ በመዝጊያ በኩል አንድ ትንሽ ድምፅ «ቲክ» ትላለች:: ዘበኛው ድምፅ የሌለው ነጠላ ጫማ አድርጎ አንዲት የተዘጋች ትንሽ ቀዳዳ እየገለጠ ዐይኑን በማጮለቅ እኔ ሳላየው እየተመለከተኝ ነበረ::

በፈረንሣይ ሪፑብሊክ የተወጠነው መሣሪያ አሁን ሁለተኛውን ደረጃ ይዞ ነበር:: በሚያስደንቅ ሁኔታ ተግባራዊ ሆኗል:: የመጀመሪያው ደረጃ የተበሳጨን ሰው አውድም ነበር:: ግን ያ በቂ አልሆነም:: ሰውየው በጣም ፈጥኖ መሞት አይኖርበትም፣ ወይም ራሱን በራሱ በመግደል ማምለጥ የለበትም:: ይፈልጉታል:: እስረኞች ባይኖሩ የቅጣት አስተዳደር ምን ሊያደርግ ኖሯል? የሌሎቹን ቢሮክራቶች ህልውና ለማረጋገጥ እስረኛ መጠበቅና ወደ ቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤቶች መሔድ ሊኖርበት ነው::

«ቲክ» የምትለውን እንደገና ስለሰማሁ ፈገግ አልኩ:: ተዝናኑ፣ ጊዜያችሁን እያባከናችሁ ነው፣ ብየ በዝግታ ነገርኳቸው:: እኔ አላመልጣችሁም - ያውም ራሱን በራሱ ይገድላል ብላችሁ እናንተ በምትሠጉበት መንገድ:: አንድ ነገር ብቻ እጠይቃችኋለሁ:: በተቻለ መጠን ጤነኛ እንደሆንኩ ቆይቼ ባስቸኳይ ወደ ፈረንሣይ ጊያና እንድሔድ::

ስማ የእኔ የጥንቱ የወህኒ ዘበኛ፣ ባልደረቦችህ ሕፃናት መዘምራን እንዳልሆኑ ዐውቃለሁ፣ ታዲያ በየጊዜው ያችን «ቲክ» የምትል ድምፅ የሚያሰማው ማነው:: ከእነርሱ ጋር ስትነጻጸር አንተ ጥሩ አባት ነህ:: ይህንንም ከረጅም ጊዜ በፊት ዐውቃለሁ:: ምክንያቱም ሣልሳዊ ናፖሊዮን አሰቃቂ ወህኒ ቤቶችን ፈቀረቁር:: እነዚህን ወንበዴዎች ማነው የሚጠብቃቸው? ተብሎ ተጠይቆ ነበረ:: የሰጠውም መልስ «የባሱ ወንበዴዎች» በማለት ነበር:: ከጊዜ በኋላ የአሰቃቂ ወህኒ ቤቶቹ መሥራች አባት ውሸቱን እንዳልነበረ ሐቁን ለማረጋገጥ ችያለሁ::

ከላከ፣ ከላከ፣ አለችና በመዝጊያዬ መካከል ያለች ስምንት ኢንች ካሬ የሆነች አንዲት ቀዳዳ ተከፈተች:: ቡናና ሁለት ፓውንድ የሚመዝን አንድ ቁራሽ ዳቦ አቀበሉኝ:: እስረኛ እንደመሆኔ ሆቴል ውስጥ ገብቼ ለመመገብ ያለኝ እድል አከትሟል:: ሆኖም ገንዘብ እስካለኝ ድረስ ሲጋራ ለመግዛትና ከአነስተኛ ሆቴል ምግብ ለማስመጣት



@BOOKALEM

እችላለሁ፡፡ የቀረኝ ትንሽ ቀን ስለሆነ ምንም የሚያሳስበኝ ነገር አልነበረም፡፡ የጥበቃ ጣቢያው፣ እስረኞች ከሰው ተለይተው በግዞት ለጥቂት ቀናት የሚቆዩበት ክፍል ነበር፡፡ ሁለት ሲጋራ አንዱን በስድስት ፍራንክ ከስድሳ ሂሳብ ገዛሁ፣ አንዱን ላኪስትራይክ በደስታ አጨስ ጀመር፡፡ ለመልስ የሚሰጡ ሳንቲሞች በፍትህ ስም መወሰዳቸው ስለማይቀር ሽርፍራፊ ምንዛሬዎቹን አጠፋቸው ነበር፡፡

በዳቦ ውስጥ አንዲት ትንሽ ማስታወሻ ተሸጉጣ አገኘሁ፡፡ የተላከችው ከዴጋ ሲሆን ወደ ተባይ ማራገፊያ ክፍል እንድሄድ ትጠቁማለች፡፡

«በከብሪት ሣጥን ሦስት ቅማሎች ልኬልሃለሁ፡፡ ፍልውሃ መታጠቢያ ክፍል መጥተህ እንድንገናኝ፡፡ «የከብሪት እንጨቶቹን አውጥቼ ሳጥኗን ስፈትሽ ሦስት ወደል ቅማሎች አገኘሁ፡፡ ምን ማድረግ እንደሚኖርብኝ ገባኝ፡፡

ተባይ ጨረሰኝ ብዬ እነዚህን ቅማሎች ለዘበኛ ማሳየት አለብኝ፡፡ ጓዜን ጠቅልዬ ከነፍራሼ ነገ ጠዋት ወደ ፍልውሃ እንድሄድና እኔ ብቻ ስቀር ተባዮቹን በሙሉ እንዳራግፍ ዘበኛው ይፈቅድልኛል፡፡ ዘዴያችን ሰመረና በማግስቱ ጠዋት ዴጋ ጋር መታጠቢያው ክፍል ተገናኘን፡፡ ወታደሮች የሉም ብቻችንን ነበርን፡፡

«አመሰግናለሁ ዴጋ፣ ምስጋና ይድረስህና በገንዘብ መደበቂያ ቱቦ ያለውን ገንዘብ አገኘሁ፡፡»

«ችግር ፈጠረብህ እንዴ?»

«ምንም አላስቸገረኝም፡፡»

«መጸዳጃ ቤት በምትሔድበት ወቅት ወደ ፊንጢጣህ ውስጥ መልሰህ ከመከተትህ በፊት ቱቦውን በሚገባ እንድታጥባት፡፡»

«እሺ፣ ቱቦዋ ተስተካክላ ስለተዘጋጀች ኖቶቹ ገና አዲስ እንደሆኑ ናቸው፡፡ አልተበላሹም፡፡ ከያዝኳት ሰባት ቀን መሆኑ ነበር፡፡»

«ሁኔታው በመሳካቱ ተደስቻለሁ፡፡»

«ወደፊት ምን ለማድረግ ዕቅድ አለህ ዴጋ?»

«ዕብድ በመምሰል ላጭበረብር ነው፡፡ ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መሄድ አልፈልግም፡፡ እዚሁ ፈረንሳይ ውስጥ ስምንት እና አሥር እሥራት መታሰር እመርጣለሁ፡፡ ግንኙነት አለኝ፣ አምስት ዓመት ለማስቀነስ እችላለሁ፡፡»

«ዕድሜህ ምን ያህል ነው?»

«ዐርባ ሁለት፡፡»

«አብደሃል እንዴ! ታዲያ ዐሥር ወይም አሥራ አምስት ዓመት ወህኒ ቤት ውስጥ ቆይተህ ከወጣህ ሽማግሌ መሆንህ ነው እኮ! ጽኑ እሥራት ያስፈራሃል እንዴ?»

«አዎ፣ የዚያን የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ኑሮ እፈራለሁ ብል



@BOOKALEM

አላፍርበትም። ታውቃለህ የጊያና ደሴት በጣም አስቃቂ ነው። በየዓመቱ ከእሥረኞቹ ከመቶ ስማንያውን ያጣሉ። ኮንቮይ በየጊዜው እየተካቸው ነው። አንዱ ሲሄድ ሌላው ይመጣል። እያንዳንዱ ኮንቮይ ከአንድ ሺህ ስምንት መቶ እስከ ሁለት ሺህ ሰዎች ያጓጉዛል።

«ቁምጥና ከሳተህ፣ ቢጫ ወባ ወይም የደም ተቅማጥ ወዲያውኑ ይቀስፍሃል፣ ሳንባ ነቀርሳና የወባ ወረርሽኝም የዚያኑ ያህል ነው። ከነዚህ ሁሉ በሽታዎች ካመለጥክ ሌላው የሚጠብቅህ እድል በቆርቆሮ ቱቦ ለደበቅከው ገንዘብ ሲል ከሚገድልህ እጅ መውደቅ ወይም በእንዱ ረብሻ መሞት ይሆናል። እመነኝ ፓፒዮ፣ ይህን የምነግርህ አንተን ተስፋ ለማስቆረጥ እንዳይመስልህ። ግን የምናገረውን በትክክል ምን እንደሆነ አውቃለሁ። በአጭር ጊዜ ውስጥ ማለት፣ በአምስት እና በሰባት ዓመት እንኳ ወደ ፈረንሳይ የተመለሱ እሥረኞችን አውቃለሁ። የሰው ዝቃጭ ናቸው። ከዓመቱ ዘጠኙን ወር የሚያሳልፉት ሆስፒታል በመመላለስ ነው። ለማምለጥም ቢሆን አንተ እንደምትገምተው እንደዚህ ቀላል እንዳይመስልህ።»

«አምንሃለሁ ዴጋ፣ ግን በራሴ ስለምተማመን በዚያ በማይረባ ቦታ ብዙ ጊዜ ለመቆየት አልፈልግም። ጥሩ ጀልባ ቀዛፊ ነኝ። ባህሩንም አውቀዋለሁ። ስለዚህ ለማምለጥ ጊዜ አይፈጅብኝም። አሥር ዓመት ሙሉ ራስህን በግዞት ለማቆየት የሚቻል ይመስልሃል? አምስት ዓመት እንኳ ቢቀንሱልህ፣ ለዚያውም ማድረጋቸው ገና አስተማማኝ አይደለም። ፈጽሞ እብደት ሳይገጥምህ ብቸኝነትን ሙሉ በሙሉ መቋቋም ይቻላል? እስኪ እኔን አሁን ተመልከት አንድ ክፍል ውስጥ ብቻዬን ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ! የምታነበው ነገር የለህ፣ ወደ ውጪ መውጣት አይፈቀድ፣ የምታነጋግረው የለህ። ስልሳ ደቂቃ ሳይሆን እንደ ስድስት መቶ ደቂቃዎች ይረዝምብሃል። ታሪኩ ይህ ብቻ ሳይሆን ሌላ ብዙ ነገር አለ።»

«ሊሆን ይችላል፣ ግን አንተ ወጣት ነህ። እኔ ዐርባ ሁለት ዓመት ሆኖኛል።»

«ስማ ዴጋ፣ የሚያስፈራህ ነገር አለ እንዴ? እስረኞቹ ናቸው?»

«ፓፒ እንግዲያውስ እውነቱን ከፈለግህ አዎ። እነርሱው ናቸው። ሚሊዮኔር እንደ ነበርኩ ማንም ያውቃል። በዚህ ምክንያት ቢያንስ ሃምሳ ወይም መቶ ሺ ፍራንክ ይይዛል ብለው ቢገድሉኝ ምን የሚያግዳቸው ነገር አለ?»

«አዳምጥ፣ በአንድ ነገር መስማማት ትፈልጋለህ? ወደ ዕብዶች ሐኪም ቤት ላለመግባት ቃል ግባልኝና እኔም ዘወትር ከጎንህ ሳልነጠል ልጠብቅህ ቃል እገባልሃለሁ። እርስ በርሳችን በሚገባ እንተባበራለን። ጠንካራና ፈጣን ነኝ። በጩቤ ትግልም ችሎታ አለኝ፣ ቀደም ሲልም የውጊያውን ስልት ተምሬአለሁ። ስለዚህ አታስብ። እርግጥ ሌሎች እስረኞች ሊያከብሩን አይፈልጉም፣ ቢሆንም አይደፍሩንም። ለማምለጥ ሌላ እስረኛ



@BOOKALEM

መጨመር አያስፈልገንም፡፡ ገንዘብ ከሆነ አንተም ሆንክ እኔ ይዘናል፡፡ ጀልባ መቅዘፍና ኮምፓስ እንዴት እንደሚስተካከል ዐውቃለሁ፡፡ ታዲያ ከዚህ ወዲያ ምን ትፈልጋለህ?»

ትኩር ብሎ ፊት ለፊት ተመለከተኝና . . . ሁለታችንም በስሜት ተቃቅፈን በሐሳብ መስማማታችንን አጸደቅን፡፡

ከትንሽ ጊዜ በኋላ የፍልውሃ መታጠቢያ ክፍሉ መዝጊያ ተከፈተ፡፡ ሁለታችንም ተለያየንና መንገዳችንን ቀጠልን፡፡ ከፍላችን ብዙም የተራራቀ ስላልነበረ፣ በየጊዜው ወደ ጸጉር ማስተካከያ፣ ወደ ሐኪም ቤት፣ በሰንበት ቀን ደግሞ ግቢው ውስጥ ወደምትገኘው ጸሎት ቤት ስንሔድ እንገናኛለን፡፡

ዴጋ የተያዘው መንግሥት ያሳተማቸውን የገንዘብ ሰነዶች በማጭበርበር ሲጠቀም ነበር፡፡ አንድ የሐሰት ሰነድ ደላኝ፣ ልክ እንደ ኦርጅናሉ ኖት እያስመሰለ ቀይሯቸው ነበር፡፡ በማያስነቃ ዘዴ ባለ አምስት መቶውን ኖት ቁጥሩን ፍቆ፣ ወደ ዐሥር ሺ ኖት ይለውጠዋል፡፡ ሥራው በጣም ግሩም ነበር፡፡ ወረቀቱ ተመሳሳይ ስለነበረ ባንኮችም ያለመጠራጠር ይቀበሉታል፡፡ በዚህ ሁኔታ ለብዙ ዓመታት ሲያጭበረብር ቆይቷል፡፡ የገንዘብ ሚኒስቴሩም ፍንጩን ለማግኘት ግራ ተጋብቶ ነበር፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን ብሪውሌ የተባለ ሰው እጅ፣ ከፍንጅ ይያዛል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ፣ ዴጋ ጉዳዩን ዳዋ ልበስ ብሎ ማርሴይ ውስጥ የሚገኘውን ሬስቶራንቱን ያለሥጋት ያስተናብር ነበር፡፡ በከተማው ከሚገኙት ዕውቅ የደቡብ ፈረንሣይ ጎሣዎችና ከየአህጉሩ ከሚመጡ ተዘዋዋሪ ወመኔዎች ጋ በየዕለቱ እየተገናኘ ሲዝናና ያመሻል፡፡

በ1929 ሚሊዮኔርነቱን አረጋገጠ፡፡ አንድ ቀን ማታ ሺክ ያለ ልብስ የለበሰች አንዲት ውብ ኮረዳ ወደ ሬስቶራንቱ ጎራ ብላ፣ አቶ ሉዊ ዴጋ ወዴት እንደሚገኝ ትጠይቃለች፡፡

«እኔ ነኝ እመቤቴ፣ ምን ልርዳሽ? ወደሚቀጥለው ክፍል ገብተሽ ትጠብቂኝ?» ይላታል፡፡

«የብሪውሌ ሚስት ነበርኩ፡፡ የተጭበረበረ የገንዘብ ኖት ሲጠቀም ተይዞ፣ ፓሪስ ውስጥ በእስር ላይ ይገኛል፡፡ በሳንቴ የእስረኛ ጎብኝዎች ማረፊያ ክፍል ውስጥ ተነጋግረን የእርስዎን ሬስቶራንት አድራሻ ሰጥቶኝ ነበር፡፡ ለጠበቃ ማቆሚያ የሚሆን ሐያ ሺ ፍራንክ እንዲሰጡኝ ንገሪ ብሎኝ ነው የመጣሁት» ትላለች፡፡

ዴጋ ፈረንሣይ ውስጥ አሉ ከሚባሉት አራዳዎች ቀንደኛው ሆኖ ሳለ በወንጀሉ ውስጥ እርሱም እንዳለበት ሴትየዋ ማወቋ አደገኛ መሆኑን እየተረዳ፣ ይህን የማይገባ መልስ መስጠት የለበትም ነበር፡፡ ይሁንና፣

«እመቤቴ፣ ስለአንቺ ባል ምንም የማውቀው ነገር የለም፡፡ ገንዘብ የምትፈልጊ ከሆነ ጎዳና ወጥተሽ ተዘዋወሪ፡፡ በጣም ቆንጆ ስለሆንሽ ከምትፈልጊው በላይ ታገኛለሽ»



@BOOKALEM

ይላታል።

ምስኪኗ ሴት ይህን ቃል መቋቋም ስለተሣናት እንባዋን ረጭታ ሮጣ ወጣች። ከዚያም በፍጥነት ወደ ፓሪስ ተመልሳ ለባሏ ነገረችው። ብሪውሌም ከመጠን በላይ በገነ። በማግሥቱ ለመርማሪው ዳኛ ምስጢሩን በሙሉ ዘክዝኮ ተናገረ። የሐሰት ኖቱንም የሰጠው ዴጋ እንደነበረ በማጋለጥ ሕጋዊ ክስ መሠረተበት።

በፈረንሣይ ዕውቅ የሆኑ የፖሊስ ነጭ ለባሾች ዴጋን መከታተል ጀመሩ። በአንድ ሣምንት ውስጥ ዴጋ፣ ኖት ደላገፉ፣ አታሚውና ዐሥራ አንድ ግብረ አበሮች ጭምር ተይዘው በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው ታሰሩ። ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቀርቦ ለዐሥራ አራት ቀናት ያህል ችሎቱ ሲያጣራ ሰነበተ። ለእያንዳንዱ እስረኛ መንግሥት ከፍተኛ ጠበቃ አቁሞላቸው ነበር። ብሪውሌም ሽንጡን ገትሮ ተከራከረ። የመጨረሻውም ውጤት፣ በፈረንሣይ የታወቀው ምላጭ አራዳ፣ በማይረባ ሐያ ሺ ፍራንክና በተነፈሰው ጸያፍ አነጋገር የተነሣ ለዐሥራ አምስት ዓመት ጽኑ እስራት ተዳረገ። እንደዚህ ከመሰለው ሰው ጋር ነበር የሞትና የሽረት ውል የተፈራረምኩት።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . ጊዜ እራመድና ከዚያም እዞራለሁ። አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . አሁንም እዞራለሁ። ለብዙ ሰዓቶች በመዝጊያውና በመስኮቱ መካከል በክፍሉ ውስጥ ወዲያና ወዲህ ስራመድ አቆያለሁ። ሲጃራ ስላጨስኩ ሞራሌ ከፍ ብሎ ለማንኛውም ነገር ተዘጋጅቻለሁ። ለጊዜው ስለ ብቀላ ምንም ነገር እንዳላስብ ራሴን በራሴ ቃል አስገባሁት። ዓቃቤ ሕጉንም በሰንሰለት ከፊት ለፊቴ አስሬ እንደተውኩት ፍርዱን ይጠብቅ። ይሁን እንጂ፣ እንዴት አድርጌ እንደምገድለው ገና አልወሰንኩም።

በከፍሌ መዝጊያ በኩል ድንገት የሚያስደነግጥ አንድ የጣዕረሞት ጩኸት ሰርስሮ ገባ። ምን ይሆን ድምፁ? ያንድ የሚደበደብ ሰው እሪታ ይመስላል። ግን ይህ ቦታ ፖሊስ ጣቢያ አልነበረም። ምን እንደሆነ የማውቅበት መንገድ አጣሁ። በውድቅት ሌሊት የሚሰማው እሪታ መንፈሴን ረበሸው። ይህንን መርግ የሆነ መዝጊያ አልፎ እዚህ ክፍል ድረስ የሚሰማ ድምፅ ምን ዓይነት ኃይል ቢኖረው ነው! ያለጥርጥር አንድ ሰው አብዷል ማለት ነው። መቸም እዚህ ቦታ የማይደረግ ነገር የለም። ጮክ ብየ ራሴን ጠየቅኩት። «የፈለገው ነገር ቢሆን አንተ ምን ቸገረህ? ስለራስህ ብቻ፣ ስለራስህ ስለአዲሱ አጋርህ ስለ ዴጋ ብቻ አስብ።»

ጎንበስ ብየ ቀና አልኩና ወደ ኋላ ለጠጥ በማለት ደረቴን ደህና አድርጌ በአንድ ወፍራም ቡጢ አቀመስኩት። በእርግጥ የሚሰማ ምት ቢሆንም፣ ማንኛውም አቋሜ አስተማማኝ ነበር። የእጆቼ ጡንቻዎች ፈርጠም ብለው በጥሩ ቅርፅ ላይ ይገኛሉ።

የእግሮቼስ ሁኔታ? እንኳን ደስ አላችሁ ልላቸው ይገባል። በቀን ውስጥ ዐሥራ



@BOOKALEM

ስድስት ሰዓት እየተራመድኩባቸው ፍጹም የመዛል ስሜት አይታይባቸውም። በጭንቅላት ላይ ውሃ ማንጠባጠብን ቻይናውያን ፈለሰፉ። ፈረንሣውያን ዝምታን ፈለሰፉ። ከማንኛውም የከፋ ቅስም ሰባሪ መጨቆኛ አገኙ። መጽሐፍ የለም፣ ጋዜጣ የለም፣ እርሳስ የለም፣ መስኮቱ ትንሽ ብርሃን የሚያስገቡ ቀዳዳዎች ይኑሩት እንጂ ከወፍራም ቋሚ ምሰሶዎች ጋር ሙሉ በሙሉ በጣውላ የተሸፈነ ነው።

የሚያሸብረው ጩኸት ፍጹም ሰላም ነሳኝ። ልክ በወጥመድ ውስጥ እንዳለ አውሬ የክፍሉን ዙሪያ አማተርኩ። በዕውን በሕይወቴ እንደተቀበርኩና ብቻየን የተጣልኩ መሆኔ ተሰማኝ። በእርግጥም ብቻየን ነበርኩ። ከለቅሶ በስተቀር ምንም ነገር ወደ እኔ የሚደርስ የለም።

መዝጊያው ተከፈተ። አንድ አረጋዊ ቄስ ነበሩ። ሌላው ቢቀር ብቻህን አልሆንከም። በቀጥታ ከፊት ለፊትህ አንድ ቄስ ቆመውልሃል።

«እንደምን አመሸህ ልጄ ፈጠን ብዬ ባለመምጣቴ ይቅርታ አድርግልኝ። ግን በበዓሉ ምክንያት ነበር። እንደምን አለህ?» ያለምንም ተጨማሪ ሥነ ሥርዓት ሩህሩህ አረጋዊ ወደ ክፍሌ ገቡና በታጣፊ አልጋዬ ላይ ተቀመጡ። «ምን አድርገህ ነው?» ሲሉ ጠየቁኝ።

ንጹሕነቴን መደጋገሙ ፋይዳ ቢስ መሆኑን ስለ ተመለከትኩ፣ «ፖሊሶች አንድ ሰው ገድለሃል ይሉኛል፤ እንደዚያ ከሆነም ያሉት መሆን አለበት» በማለት ፈጠን ብየ መለስኩላቸው።

«ምን ዓይነት ሰው ኖሯል?»

«አንድ አቃጣሪ።»

«ታዲያ ለአንድ ወራዳ ሰው ግድያ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ፈረዱብህ? አልገባኝም። በቂም በቀል ኖሯል?»

«አይደለም»

«ማመን አልችልም፣ የእኔ ምስኪን ልጅ። ምን ላደርግልህ እችላለሁ? ከእኔ ጋር መጸለይ ትፈልጋለህ?»

«ይቅርታ አድርጉልኝ አባቴ፣ ፈጽሞ የምከተለው የሃይማኖት መመሪያ ስለሌለኝ እንዴት እንደሚጸለይ አላውቅም።»

«የእኔ ልጅ፣ ልዩነት የለውም። ራሴው እጸልይልሃለሁ። የተጠመቁትንም ሆነ ያልተጠመቁትን ልጆቹን ሁሉ ቸሩ እግዚአብሔር ይወዳቸዋል። እኔ የምናገራቸውን እያንዳንዳቸውን ቃላት ደግመህ ለማለት ፈቃደኛ ነህ?»

ዐይኖቻቸው ረጋ ብለው ሰፊው ገጻቸው በርኅራኄ ብሩህ አመለካከት የተሞላ ስለነበር፣ የጠየቁኝን እምቢ ለማለት ኃፍረት ተሰማኝና በርከክ ሲሉ እኔም እንደ



@BOOKALEM

እርሳቸው ተንበረከከሁ።

«አባታችን ሆይ፣ በሰማይ የምትኖር . . .»

በዐይኖቼ እንባዎች ተንቆረዘዙ። ርኅሩኅ አባት እንባዎቼን ሲመለከቱ አጫጭር ጣቶቻቸውን በጉንጮቼ ላይ አስቀመጡና አንድ ወፍራም እንባ ይዘው ወደ ከንፈራቸው በመውሰድ መጠጡ።

«የእኔ ልጅ እንባዎችህ እግዚአብሔር ለእኔ ሊሰጠኝ የቻላቸው ከፍተኛ በረከቶች ናቸው። አመሰግናለሁ» አሉና ብድግ ብለው ግንባሬን ሳሙኝ። እንደገና አልጋው ላይ ጎን ለጎን ተቀመጥን።

«ካሁን በፊት እንደዚህ ካለቀስክ ምን ያህል ጊዜ ሆኖሃል?»

«ዐሥራ አራት ዓመት»

«ዐሥራ አራት፣ ለምን?»

«እናቴ ሞታብኝ» እጄን ያዝ አደረጉና፣ «ለመሠቃየት ያደረሱህን በሙሉ ይቅርታ አድርግላቸው» ሲሉኝ፣ የማደርገውን ሳላውቅ እጆቼን አወናጨፍኩና ከተንጠልጣይ የብርድ ልብስ አልጋው ላይ እመር ብየ በክፍሉ መካከል ቆምኩ።

«እ፣ አላደርገውም! ያስ አይሆንም። ፍጹም ይቅርታ አላደርግም። አንድ ነገር እንድነግርዎት ይፈልጋሉ አባቴ? ሌሊቱንና ቀኑን በሙሉ፣ ማንኛዋንም ሰዓትና ደቂቃ የማሳልፈው ወደዚህ ያላኩኝን ሰዎች መቼና እንዴት እንደምገድል በማሰላሰል ነው።»

«የእኔ ልጅ፣ አሁን የምታስበውና የምትናገረው ይህንኑ ነው። ወጣት ነህ፣ በጣም ወጣት ነህ። እየሸመገልክ ስትሄድ ግን፣ የቅጣትንና የመበቀልን ሐሳብ ትተዋለህ።»

ከሠላሳ አራት ዓመታት በኋላ ከእርሳቸው ሐሳብ ጋር ተስማምቻለሁ።

«ምን ላደርግልህ እችላለሁ?» አሉ ቄሱ በድጋሚ።

«ሕግ ያፍርሱ።»

«የምን ሕግ?» ወደ ቁጥር ሰላሳ ሰባት ክፍል ይሒዱና ለዴጋ ጠ( ቃህን ወደ ኪየን ወህኒ ቤት እንዲያስልክህ ጠይቀው ብለው ይንገሩልኝ። የእኔንም ፤.ሬ እንዳልኩት ይንገሩት። ወደ ፈረንሣይ ጊየና ኮንቮይ የሚንቀሳቀሰው ከዚያ ወህኒ ቤት ስለሆነ፣ በተቻለ ፍጥነት ወደ እዚያ መሔድ አለብን። የመጀመሪያው ኮንቮይ ካመለጠን፣ ሌላ እስኪመጣ ድረስ ሁለት ተጨማሪ ዓመታት በግዞት መቆየታችን ነው። አባቴ፣ ከነገሩት በኋላ ወደዚሁ እንዲመለሱ»

«የማመካኘበት ምን ምክንያት ልጠቀም?»

«የዘወትር ጸሎት መጽሐፌን ረስቼ ነው ይበሉ። መልሱን እጠባበቃለሁ።»

«ወደ አስፈሪው የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ለመሔድ እንዴት እንደዚህ



@BOOKALEM

ተጣደፍክ?

እኚህን ተዘዋዋሪ የእግዚአብሔር ቃል ወኪል አቋም በመገምገም የማያጋልጡኝ መሆናቸውን ስለተማመንኩ፣ ‹ብፍጥነት ማምለጥ እንድችል ነው አባቴ› አልኳቸው። «አምናለሁ፣ እግዚአብሔር ይረዳሃል የእኔ ልጅ። ኑሮህንም እንደገና እንደምታድስ ይሰማኛል። የጥሩ አስተዋይነትና የጨዋ መንፈስ አለህ። ወደ ቁጥር ሠላሳ ሰባት ሔድና መልሱን ይገፍልህ እመጣለሁ።»

ጊዜ ሳያባክኑ ተመለሱ፣ ዴጋም ተስማምቶ ነበር።

ከአንድ ሳምንት በኋላ ከጧቱ አራት ሰዓት ላይ እኛ ሰባቶቻችን በጥበቃ ጣቢያው ክፍል መተላለፊያ በመስመር ተሰልፈን ነበር። ዘበኞችም ኃይላቸውን አጠናክረው እዚያው ነበሩ።

«አውልቁ!» ተባልን።

በዝግታ አወለቅን። ይቀዘቅዝ ነበር። አካላቴ ተጉረበረበ።

«ልብሶቻችሁን ከፊት ለፊታችሁ አስቀምጡ፣ ቀኝ ኋላ ዙሩና አንድ እርምጃ ወደ ኋላ ተመለሱ!» ከእያንዳንዳችን ፊት ለፊት አንድ ጥቅል አገኘን።

«ልበሱ!»

ከጥቂት ጊዜ በፊት ለብሸው የነበረ ካናቴና በሻካራና ግርር ባለ አንድ ነጭ ሸሚዝ፣ የሚያማምሩት ልብሶቼ፣ ሱሪዎቼና ጃኬቶቼ በከርዳዳ የዱቄት ከረጢት ጨርቅ ተተኩ። ጫማዎቼም ደብዛቸው ጠፍቶ በአንድ ጥንድ ነጠላ ጫማዎች ውስጥ እግሮቼን ደነቀርኳቸው። እስከዚያች ቀን ድረስ ሁኔታችን እንደማንኛውም ሰው ይመስል ነበር። ወደ ሌሎቹ ስድስቱ ሰዎች ተመለከትኩ። ምን ዐይነት ቀፋፊ ኖሯል! ልዩነታችን አከተመ። በሁለት ደቂቃ ውስጥ ወደ እሥረኛነት ተቀየርን።

«ወደ ቀኝ ዙር! በነጠላ ረድፍ፣ ተጠንቀቅ፣ ወደፊት ሒድ!»

ከሐያ አጃቢ ዘበኞዎቻችን ጋር ወጣንና እያንዳንዳችን በየተራ አንድ ጠባብ የፖሊስ ካሚዎን ውስጥ ታጎርን። ኪየን ወደሚገኘው (የቦሊያ) ወህኒ ቤት ጉዞ ቀጠልን።

## የኪየን ወህኒ ቤት

ወዲያው እንደ ደረስን ወደ አዛዡ ቢሮ ተወሰድን። ከፍታው ሦስት ጫማ በሆነ ሰገነት ላይ በሚያስፈራ ግርማ ከአንድ ጠረጴዛ በስተኋላ በኩራት ተቀምጧል።

«ተጠንቀቁ ! አዛዡ አሁን ንግግር ያደርጉላችኋል።»

«እስረኞች፣ ይህ ቦታ ወደቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት እስከትሔዱ ድረስ የምታርፉበት የመሸጋገሪያ ጣቢያ ነው። ወህኒ ቤት ነው። በማንኛውም ወቅት ጸጥታ አስፈላጊ ነው። ጎብኚዎች እንዲጠይቋችሁ አይፈቀድም። ደብዳቤ የለም። አሜን



@BOOKALEM

ብላችሁ ታዘዙ፡፡»

«አለበለዚያ ትንከታከታላችሁ፡፡ ለእናንተ የተዘጋጁ ሁለት መዝጊያዎች አሉ፡፡ አንደኛው መልካም ሥነ ምግባር ካሳያችሁ ወደ ቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ሲሆን፣ ሌላው ደግሞ ወደ መቃብር ጉድጓድ ነው፡፡ ለመጥፎ ሥነ ምግባር በጣም ኢምንት ቢሆንም እንኳን ቅጣቱ በውሃና በዳቦ ብቻ ለስድሳ ቀናት በቀዝቃዛ ግንብ ውስጥ መቆየት ይሆናል፡፡ እዚያ ሁለት ጊዜ በተከታታይ ከተቀጡት ውስጥ ማንም የተረፈ ሰው የለም፡፡ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷችኋል!»

ከስፓኝ ተባርሮ የነበረውን ፒየሮ ለፉን አነጋገረው፡፡

«ሙያህ ምን ነበር?»

«እንደ ስፔን ወታደሮች ሁሉ የሠለጠንኩት ከኮርማዎች ጋር ፍልሚያ በመግጠም ነበር፡፡»

አዛዡ በመልሱ ተናደደና እንደዚህ ሲል አጓራ፣ «ይህን ሰው ወዲያ ውሰዱልኝ!»

ወዲያውኑ አራት ወይም አምስት ወታደሮች እየደበደቡ በወሳንሳ ተሸክመው ወሰዱት፡፡ «እናንተ ግማታሞች፣ አምስት ሆናችሁ ለአንድ ሰው ዱላ ትጠቀማላችሁ? እናንት ቆሻሻ ዲቃላዎች!» እያለ ሲጮህ መስማት ችለን ነበር፡፡ ከዚያም ሊሞት እንደ ቆሰለ አውሬ «አህህ» ሲል ሰማን፡፡ በኋላ ምንም ነገር የለም፡፡ በሲሚንቶው ወለል ላይ የሚጎተት የአንድ ነገር ድምፅ ብቻ፡፡

አጋጣሚ ዴጋ ከእኔ ክፍል ቀጥሎ ያለው ደረሰው፡፡ በቅድሚያ ግን ቁመቱ ስድስት ጫማ ከአምስት ኢንች የሆነ፣ ቀይ ጸጉር ያለው አንድ ዓይናና ግዙፍ ሰው ጋር ተዋውቀን ነበር፡፡ በቀኝ እጁ አንድ አዲስ የበሬ ጅራፍ ይዟል፡፡ እስረኛ ቢሆንም በዝነኛ አሰቃይነቱ ዘበኞችን የሚያገለግል ባለሟል ነበር፡፡ እርሱ እስካለ ድረስ ወታደሮች ማንኛውንም ሰው መደብደብ ከመቻላቸውም ሌላ በዚያው ሳቢያ አንድ ሰው ቢሞት ራሳቸውን ስለማያጋልጣቸው በአስተዳደሩ ዐይን ከወንጀሉ ነጻ ይሆናሉ፡፡

በሕክምና ክፍሉ ለአጭር ጊዜ እንደ ሰነበትኩ ስለዚህ የሰው አውሬ ማወቅ ቻልኩ፡፡ እንደዚህ የመሰለውን ተግባር የሚካሒድለት ምርጥ ነፍስ ገዳይ በመመልመሉ የወህኒ ቤቱ አዛዥ እንኳን ደስ አለህ መባል ይገባዋል፡፡ የሥራ ልምዱ ድንጋይ ፈላጭነት ነበር፡፡ አንድ ቀን መኖሪያው ከሆነችው አንዲት ሰሜናዊ አነስተኛ ከተማ፣ ራሱን በራሱ ለመግደልና ሚስቱንም ጭምር ለማጥፋት አንድ ሐሳብ ይመጣለታል፡፡ ለዚህም እቅዱ የሚጠቀምበት አንድ ትልቅ ጉማጅ ፈንጅ ያዘጋጃል፡፡ በእንቅልፍ ላይ ከነበረችው ሚስቱ አጠገብ ያጋድምና (በቤቱ ውስጥ ስድስት ቤተሰቦች ነበሩ) አንድ ሲጋራ ለኩሶ በግራ እጅ በኩል በሚስቱና በእርሱ ጭንቅላት መካከል ያለውን የፈንጅ ክር ያቀጣጥላል፡፡



@BOOKALEM

የሚያሸብር ፍንዳታ አስተጋባ:: ውጤቱም የሚስቱ አካላት አንድ በአንድ እየተለቀመ ሲሰበሰብ፣ የቤቱ ግማሽ ጎን ተደረመሰ:: ከሦስት ልጆቹ ጋር አንዲት የሰባ ዓመት ባልቴትም ፍርስራሽ ተጭኗቸው ሞቱ:: ሌሎቹ ደግሞ በየደረጃው የሚቆሰል አደጋ ደርሶባቸዋል::

ራሱ ትሪቡሳርም አንዲት ጣትና አውራ ጣቱ ሲቀሩ፣ በከፊል የግራ እጁን የግራ ዐይኑንና ጆሮውን አጣ:: ጭንቅላቱም ላይ ቀዶ ጥገና የሚያስፈልገው ቁስል ደረሰበት:: አሁን ግን ወንጀለኝነቱ አንሶት፣ የወህኒ ቤቱ የሥነ ሥርዓት ኃላፊ ስለሆነ፣ ይህ ወፈፌ ባለመታደሉ ከመዳፉ ውስጥ የገቡለትን እስረኞች እየተከታተለ ደስ ያሰኘውን ድርጊት ይፈጽምባቸው ነበር::

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት አምስት . . . እዞራለሁ:: አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . እዞራለሁ:: እንግዲህ በግድግዳውና በክፍሉ መዝጊያ መካከል የማያቋርጠው የመሰለ ቀለል እርምጃ ተጀመረ::

ቀን በክፍል ውስጥ መተኛት አይፈቀድልህም:: ጧት ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ መብረቅ የመሰለ አንድ ፊሽካ ያባንንሃል:: መነሣት አልጋህን ማንጠፍ፣ መታጠብ ወይም መቆም፣ አለበለዚያም ከግድግዳው ጋር ከተያያዘችው ዱካ ላይ መቀመጥ ነበረብህ:: ለመጋደም አይፈቀድልህም! የቅጣት ሥርዓቱ ከፍተኛ የጠባይ ማረሚያ መሆኑ ነበር:: አልጋው ወደ ግድግዳው ይታጠፍና በዚያው ይቀራል:: በዚህ ዓይነት እስረኛው መጋደም ስለማይችል ይበልጥ በቀላሉ ሊጠበቅ ይችላል::

. . . አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . የዐሥራ አራት ሰዓት እርምጃ:: ይህንን የማያቋርጥ እንቅስቃሴ በፍጥነት ለመለማመድ ቢያስፈልግ፣ ጭንቅላትህን አቀርቅረህ፣ እጆችህን በስተጀርባህ አዙረህ፣ ስትራመድ በጣም ሳትፈጥን ወይም በጣም ሳትዘገይ፣ እርምጃህን በተመሳሳይ ርቀት መመጠን፣ እንዲሁ በግራ እግርህ በኩል በፍጥነት ከግድግዳው መጨረሻ ስትታጠፍ ሌላ ጊዜ ደግሞ በስተቀኝ በኩል መዞርን መማር ይኖርብሃል::

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . ከጥበቃ ጣቢያዎች ይልቅ እነዚህ ክፍሎች ቀለል ያሉ ስለነበሩ፣ ከሥነ ሥርዓት ክፍሉም ሆነ ከውጭ በኩል ጩኸቶች መስማት ትችላለህ:: በተጨማሪም እንደዚሁ በማዶ ካሉ ቀበሌዎችም ጭምር:: በምሽት ወቅት ሠራተኞች ቢራ በመቀማመስ ደስ ብሏቸው እያፏጩና እየዘፈኑ ከሥራ ወደ ቤታቸው ሲጓዙ ድምፃቸውን መስማት ትችላለህ::

አንድ ስጦታ አግኝቼ ነበር:: ይኸውም መስኮቴን በሸፈነው ጣውላ ቀዳዳ በኩል አንዳንድ ትላልቅ ዛፎችና በበረዶ የተሸፈነውን ቀበሌ፣ በሙሉዋ ጨረቃ አማካይነት ለማየት መቻል ነው:: የሚመስለው ልክ እንደ አንድ የልደት በዓል ካርድ



@BOOKALEM

ነበር። በነፋሱ ንቅናቄ ዛፎች የተሸከሙትን በረዶ ስላራገፉ በነጩ ላይ ጥቁር ጥላ ጥሎበታል። የገና በዓል ነበር። በወህኒ ቤቱ ውስጥ እንኳ በከፊል የልደት በዓል ተከብሯል። በሽግግር ላይ ላለነው እስረኞች አስተዳደሩ እንድ አስተያየት አድርጎ ነበር። ሁለት ቁራጭ ቸኮሌቶች ለመግዛት ተፈቀደልን። የምለው ሁለት ቁራጮች እንጅ፣ ሁለት ጉማጆች እንዳይመስላችሁ። በእነዚህ ሁለት የአውዢቤል ቁራጭ ቸኮሌቶች ነበር 1931 የዘመን መለወጫ ዋዜማየን ያከበርኩት።

አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት . . . የሕጉ መጥበቅ ልክ እንደሰዓት ፔንዱለም አድርጎኝ ነበር። በከፍሉ ውስጥ የማደርገው የወደኋላና ወደፊት ምልልስ በአጠቃላይ ሁለመናየን አስተካክሎታል። የሚከናወነው በሒሳብ ስሌት ነበር። ምንም ነገር፣ በክፍሌ ውስጥ የሚቀረኝ ባጠቃላይ ምንም ነገር አልነበረም። እስረኛ መበሳጨት የለበትም። በመስኮቱ ቀዳዳ ሳጮልቅ ብያዝ ኖሮ ከባድ ቅጣት ይደርስብኝ ነበር። በእርግጥም ለእነርሱ እኔ አንድ የቁም ሬሣ ስለሆንኩ ትክክል ናቸው። በየትኛው መብቴ ነው ተፈጥሮን በጨረፍታ በማየት የምደሰተው?

አንድ ጥቁር ቀጭን መስመር የተጋደመባት ውሃ ሰማያዊ ቢራቢሮ ውልብ ብላ ስታልፍ፣ አንዲት ንብ ደግሞ ከመስኮቱ ሳትርቅ ትጮሃለች። እነዚህ ጥቃቅን ነፍሳት ምን እየፈለጉ ኖሯል? ምናልባት ካልቀዘቀዛቸው በስተቀር በከረምቱ ፀሐይ ሰክረው ወደ ወህኒ ቤት መግባት ፈልገው ነው። በከረምቱ የአንዲት ቢራቢሮ መታየት ልክ ከሞት በኋላ ሕይወት እንደዘራች የሚቆጠር ነው። ለምን አልሞተችም ነበር? ንቢቱስ ቀፎዋን ለምን ለቀቀች? ምን የመሰሉ የሞኝ ደፋሮች ቢሆኑ ነው ወደ እዚህ የመጡ!

ትሪቡላር የወጣለት አረመኔ ነበር። በመካከላችን አንድ የሆነ ነገር ይፈጠራል የሚል ስሜት አደረብኝ፣ ትክክል ነበርኩ። እነዚያ ማራኪ ነፍሳት በጎበኙኝ ማግሥት ታመምኩ። ልቋቋመውም ጨርሶ ተሳነኝ። በብቸኝነት ታፍኜ ስለነበር ፣ ድምፅ ይሁን እንጂ የቁጣም ድምፅ ቢሆን እንኳ ለመስማትና አንድ ፊት ለማየት ፈለግኩ።

ራቁቴን እንደ ሆንኩ እንደ በረዶ በሚቀዘቅዘው መተላለፊያ አፍንጫዬን ለግድግዳው ትይዩ አድርጌ ዶክተሩን ለማየት በሰልፍ ተራቸውን ከሚጠባበቁት ስምንት ሰዎች ወስጥ ከመጨረሻ ሁለተኛ በመሆን ቆሜያለሁ። ሰው ለማየት መፈለጌ . . . ግሩም ሆኖ ተሣካልኝ። «ባለመደሻው ሰው» ከተባለው ከጁሎ ጋር ድምፄን አጥፍቼ በምነጋገርበት ወቅት ባለሟሉ ደርሶብን ማጅራቴን በአንድ ቡጢ ሲወግረኝ፣ ሕሊናዬን ልስት ምንም አልቀረኝ ነበር። ሲመጣ አይቼው ስላልነበር በምወድቅበት ጊዜ አፍንጫዬ ከግድግዳው ጋር ተላተመ። ደሜ ፊን ብሎ ሲወጣ ብድግ አልኩና ግብግብ ለመግጠም ተንገዳገድኩ። ግዙፉም የሚፈልገው ይህንኑ ነበር። መልሶ ዘረረኝ። አንድ ጠንካራ ጡጫ ሆዴ ላይ አቀመሰኝና፣ ከዚያም በበሬ ጅራፍ ይሞሽልቀኝ ጀመር። ይህም ለጁሎ



@BOOKALEM

የማይቋቋመው ነገር ሆነበት፡፡ ዘልሎ ተከመረበትና የጦፈ ትግል ተጀመረ፡፡ የሚደበደበው ጁሎ እስከሆነ ድረስ ዘበኞቹ ምንም ሳይነቃነቁ ቆሙ፡፡ ስለ እኔ ማንም ምንም ያስታወሰ አልነበረም፡፡ አንድ ዐይነት መሣሪያ ለመፈለግ አካባቢየን አማተርኩ፡፡ በኮሪደሩ የሚደረገውን ሁኔታ ለማየት ዶክተሩ በቢሮ ወንበሩ ላይ እንዳለ ወደፊት ሰገግ ሲል ድንገት አየሁት፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ፣ ከሚፈላ ውሃ ላይ፣ አንድ ግጣም ከፍት ከድን ሲል ልብ አልኩና ተመለከትኩ፡፡ በከሰሉ ፈርኔሎ ላይ ትልቅ ብረት ድስት የተጣደው የዶክተሩን ከፍል ለማሞቅ ነበር በእንፋሎቱ ፡፡ የብረት ድስቱን ጆሮዎች ያዝኩና ቢያቃጥለኝም ሳልለቅ በፍጥነት አንሥቼ ከሚፈላው ውሃ ጋር ባለሟሉ ፊት ላይ አሳረፍኩበት፡፡ ከጁሎ ጋር በመታገል ላይ ስለነበር እኔን አላየኝም፡፡ አንድ የሥቃይ ዋይታ አስተጋባ፡፡ በሚገባ አግኝቼው ነበር፡፡ ሦስቱን የሱፍ ሹራቦቹን አወልቃለሁ ብሎ ሲታገል ወለሉ ላይ ተንከባለለ፡፡ ሦስተኛው ላይ ሲደርስ ቆዳው ከሹራቡ ጋር አብሮ ተነሣ፡፡ የሹራቡ አንገት ጠባብ ስለነበር በጭንቅላቱ በኩል አወልቃለሁ ብሎ ሲታገል የደረቱ፣ የጉንጩና በከፊል የአንገቱ ቆዳ ከሱፉ ጋር ተጣብቆ ተነሣ፡፡ ብቸኛዋ ዐይኑም ስለ ተቀቀለች ያለጥርጥር ታውሮ ነበር፡፡ በመጨረሻ በኃፍረት ተውጦ፣ በደም ተለውሶና አካላቱ ጥሬ ሥጋ መስሎ በእግሩ ሲቆም፣ ከፍርንትቱ ላይ አንድ አደገኛ ቡጢ ለመስጠት ጁሎ ዕድል ገጠመው፡፡ ተኮራመተና በአፉ አረፋ እየደፈቀ ያስታውክ ጀመረ፡፡ የሚገባውን አግኝቷል፡፡ እኛንም የሚጠብቀን ቅጣት ሩቅ አይሆንም፡፡ ትዕይንቱን ሲመለከቱ የነበሩት ሁለት ዘበኞች እኛን ለመደብደብ በጣም ፈርተዋል፡፡ ለእርዳታ ተጣሩ፡፡ ከየአቅጣጫው ተሰበሰቡና በላያችን ላይ ዱላ እንደ በረዶ አዘነሙብን፡፡ በመጀመሪያው ድብደባ ሕሊናዬን ለመሳት ዕድለኛ ስለሆንኩ ምቶቹ አልተሰሙኝም፡፡

ሕሊናዬን ሳውቅ ከምድር በታች ሁለት ወለል ዝቅ ብሎ በውሃ በተጥለቀለቀ አንድ ጨለማ ግንብ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ራቁቴን ተጋድሜያለሁ፡፡ ቀስ በቀስ ስሜቴን ሳውቅ ቁስሎቼም ይሰሙኝ ጀመር፡፡ ያሰቃያሉ፡፡ ከጭንቅላቴ ላይ ቢያንስ ዐሥራ ሁለት እብጠቶች ነበሩ፡፡ ስንት ሰዓት ይሆን? ማወቅ አልቻልኩም፡፡ እዚህ ቦታ ቀንም ሆነ ሌሊት የሚባል የለም፡፡ በግድግዳው ላይ አንድ ቁርቆራ ሰማሁ፡፡ የመጣው ከሩቅ አካባቢ ነበር፡፡

ድም፣ ድም . . . ኪል፣ ኪል፣ ኪል . . . ቁርቆራዎቹ «የስልክ» አደዋወል ይመስላሉ፡፡ በመስመር ላይ ነኝ ለማለት ከፈለግኩ ሁለት ጊዜ መቆርቆር ነበረብኝ፡፡ እሺ ልቆርቁር፡፡ ግን በምን? በጨለማ ውስጥ አንድም ነገር ማየት አልቻልኩም፡፡ ድምፁ ማስተጋባት ስለማይችል ቡጢዎችም በቂ አልነበሩም፡፡ ትንሽ ብርሃን ስለነበረ፣ መዝጊያው መሆን አለበት ብዬ ወደ ገመትኩት አካባቢ ቀረብ አልኩ፡፡ ከፍርግርጉ ቋሚ መዝጊያው መሆን አለበት ብዬ ወደ ገመትኩት አካባቢ ቀረብ አልኩ፡፡ ከፍርግርጉ ቋሚ መዝጊያው የሚገኘው ከዚያ ጋር ተላተምኩ፡፡ በዳበሳ እንደ ደረስኩበት የጨለማው ግንብ መዝጊያ የሚገኘው ከዚያ



@BOOKALEM

ሦስት ጫማ ባሻገር ስለ ነበር፣ ቋሚ ፍርግርጉ ወደ እዚያ ለመድረስ እንደ ከለከለኝ ገመትኩ። የዚህም ቀያሽ ዓላማ ወደ አንድ አደገኛ እስረኛ ክፍል ውስጥ አንድ ሰው ቢገባ፣ እስረኛው የሚገኘው በወጥመድ ውስጥ ስለሆነ ሰውየውን ማግኘት እንዳይችል ነበር። ምንም ጉዳት ሳያደርስብህ ልትናገር፣ ውሃ ልትረጭበት ፣ ምግብ በላዩ ላይ ልትወረውርበትና ልትሰድበው ትችላለህ። በሌላው አንጻር ደግሞ ወደ እርሱ ለመጠጋት ቋሚ .ፍርግርጉን መክፈት ስለሚኖርብህ፣ ራስህን ለአደጋ ሳታጋልጥ ልትመታው አትችልም።

ቁርቆራው ቀጠለ። ከእኔ ጋር ለመገናኘት የሚታገለው ማን ይሆን? ሰውየው በእርግጥ አንድ መልስ ይጠብቃል። ከፍተኛ ጥረት በማድረግም ላይ ነበር። በጨለማው ውስጥ በመዘዋወር ላይ እንዳለሁ፣ ከብና ጠንካራ የሆነ አንድ ነገር እግሬን እንሸራትቶኝ በፊቴ ተደፍቼ ወደቅኩ። አንዷት የእንጨት ማንኪያ ነበረች። ያዝኳትና ለመመለስ ተዘጋጀሁ። ጀሮዬን ከግድግዳው ላይ ..ጥፌ እጠባበቃለሁ። ድም-ድም-ድም-ድም-ፓንግ። ቆመ። ድም-ድም አድርጌ እ..ፖ ዋለሁኑ። እነዚህ ሁለት ቁርቆራዎች፣ «ቀጥል እየሰማሁ ነው» ለማለት ነበር። ቁርቆራው ተጀመረ። ድም-ድም-ድም የንግግሮቹ ፊደሎች በፍጥነት ይኸጎደጎዱ ጀመር። ከኤ ይጀምርና በፒ ፊደል ያቆማል። አንድ ኃይለኛ ፓንግ ቀረቀርኩ። ይህም የፒ ፊደልን እንዲመዘግብ ልነግረው ነበር። ከዚያም አንድ ኤ፣ አንድ ፒ፣ አንድ አይ ወዘተ . . .

«እንዴት ይዞሃል ፓፒ? በእርግጥ ቻልከው? እኔ አ..ደኛው ..ንዴ ተሰብሯል» ይለኝ ነበር። ለካ ጁሎ ኖሯል።

አደጋውን ዘንግተን ከሁለት ሰዓት በላይ በስልካችን አወራን። በተመስጦ ተውጠን ነበር። ጭንቅላቴ በሙት በእ..ጡት ቢሸፈንም ቅሉ፣ በግልጽ እንዳልተፈነከትኩና ምንም እንዳልተሰበርኩ ..ገርኩት። እግሬን ይዘው ቁልቁል በደረጃው ሲያወርዱኝና ጭንቅላቴም ከእያንዳንዱ ደረጃ ላይ ሲነጥር ማየቱን ነገረኝ፡ እርሱ ፍጹም ሕሊናውን አልሳተም ነበር። ትሪቡላር ክፉኛ መቃጠሉና በአሥጊ ሁኔታ ላይ መሆኑ ለጊዜውም ቢሆን በመጠኑ አሳስቦት ነበር።

ሦስት ፈጣን ቁርቆራዎች ችግር ሊፈጠር መቃረቡን አስጠነቀቁኝ። እኔም አቆምኩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ መዝጊያው ተከፈተና አንድ ሰው ሲያጓራ ሰማሁ።

«ወደ ኋላ ተመለስ፣ አንተ ዲቃላ! ከክፍሉ ጥግ ሒድና በተጠንቀቅ ቆይ!» አዲሱ ባለሟል ነበር።

· «ስሜ ባቶን ነው። ስሚ ከሙያየ ጋር ይስማማል» አለና ጨለማው ግንብ ውስጥ እርቃነ ሥጋዬን እንደ ቆምኩ አንድ ትልቅ ፋኖስ በላዬ ላይ አበራብኝ።»

«የምትደርበው ነገር ያውልህ። ግን እንዳትንቀሳቀስ። ዳቦና ውሃም



@BOOKALEM

ይኸውልህ:: ሁሉንም በአንድ ጊዜ እንዳትበላ፣ ለሚቀጥሉት ሐያ አራት ሰዓቶች የምታገኘው ይህንኑ ብቻ ነው::»

አንድ የመጓጎር ጩኸት አሰማና ከዚያም ፋኖሱን ወደ ራሱ ፊት ቀረብ አደረገው:: ፈገግታ ያሳይ እንደነበር ተመለከትኩት:: የከፋት አልነበረም:: ከከንፈሮቹ ላይ አንደኛ ጣቱን አስቀመጠና ትቶልኝ ከነበሩት ዕቃዎች ላይ ዐይኑን ተከለ:: በኮሪደሩ ውስጥ አንድ ዘበኛ ኖሮ ነው እንጂ፣ ጠላቴ አለመሆኑን እንዳውቅለት ሊገልጽልኝ ፈልጎ ነበር::

በእርግጥም ጠላቴ አልነበረም:: በዳቦው ውስጥ አንድ ትልቅ ጉማጅ የተቀቀለ ሥጋና ከሱሪዎቹ ኪስ ደግሞ:- ይገርማል፣ ትላልቅ ጺጋዎች! አንድ ፓኬት ሲጃራና አንድ ማቀጣጠያ አገኘሁ:: እዚህ እነዚህን የመሰሉ ስጦታዎች ዋጋቸው በሚሊዮን ነበር:: ሁለት ሸሚዞችና ቁርጭምጭሚቴ የሚደርስ ከሰፋ የተሠራ አንድ የውስጥ ፒጃማም ሰጠኝ:: ባቶንን ፍጹም አልረሳውም:: ይህን ያደረገው ትሪቡላርን ስላሰወገድኩለት ወረታ ሊመልስልኝ ነበር:: ከግጭቱ በፊት ረዳት ባለሟል ብቻ ነበር:: አሁን ምስጋና ለእኔ ይድረሰኝና ሙሉውን ማዕረግ ይዟል።

«የስልኩን» ቁርቆራ አድራሿ ለማግኘት ታላቅ ትዕግሥት ስለሚጠይቅና ዘበኞቹም በጣም ሰነፎች በመሆናቸው ሊደርስበት የሚችለው ባለሟሉ ብቻ ስለነበር፣ ጁሎና እኔ ልባችን ያሰኘውን ያህል እንደሰትበታለን:: በሦስት ወይም በአራት ወራት ውስጥ ጉዞ የምንጀምር መሆናችንን ከእርሱ ተረዳሁ::

ከሁለት ቀን በኋላ ከጨለማው ግንብ ወጣንና እያንዳንዳችን በሁለት ዘበኞች ታጅበን ወደ አዛገሮቹ ቢሮ ተወሰድን:: ሦስት ሰዎች በመዝጊያው ትይዩ ከሚገኝ አንድ ጠረጴዛ ኋላ ተቀምጠዋል፣ አንድ ዐይነት ችሎት ይመስላል:: አዛዡ ሰብሳቢ ዳኛ በመምሰል፣ በመካከል፣ ረዳት አዛገፉና የዘበኞቹ ኃላፊ እንደ ረዳት ዳኞች ሆነው ተሠይመዋል::

«እህሳ፣ ወዳጆቼ እንግዲህ ለዚህ በቃችሁ! ስለራሳችሁ የምታስረዱት አላችሁ?»

ምናልባት የብርድ ሕመም ሳይዘው አልቀረም ይመስለኛል፣ ጁሎ ዐይኖቹ አብጠው ፊቱ በጣም ገርጥቶ ነበር:: ከንዱን ከተሰበረ አሁን ሦስት ቀን ሆኖታል:: በከፍተኛ ሥቃይ ላይ መሆን አለበት:: በጣም ቀስ ብሎ፤

«ክንዴን ተሰብሬያለሁ» አለ::

«ምስህን ነው ያገኘኸው፣ ሰዎችን ላለመደብደብ ይህ ትምህርት ይሆንሃል:: እዚህ ሲመጣ ዶክተሩ ያይልሃል:: ይህም በሳምንት ውስጥ እንደሚደረግልህ ተስፋ አለኝ:: ምናልባት ሥቃዩ አንዳንድ ነገር ስለሚያስተምርህ መቆየቱ ለአንተ ጥሩ



@BOOKALEM

ይሆናል፡፡ በተለይ እንደ አንተ የመሰለ ጠባይ ላለው አንድ ዶክተር ባስቸኳይ መቸም አትጠብቅም፡፡ ትጠብቃለህ እንዴ? ስለሆነም ጊዜ አግኝቶ እስኪመጣ ድረስ ጠብቅ፣ ከዚያም ያክምሃል፡፡ ይህንንም ስል ያለምንም ተጨማሪ መግለጫ ሁለታችሁንም ወደ ጨለማው ግንብ ከመላክ አያግደኝም፡፡»

የጁሎ ዐይን ከእኔ ጋር ግጥምግም ሲል፣ «ይህ የተቀናጣ መኳንንት የሌሎችን ሰዎች ሕይወት ለማፈን አስደናቂ ዘዴ አለው» የሚል ይመስል ነበር፡፡

ወደ አዛገፉ ዘወር አልኩና ትኩር ብየ ተመለከትኩት፡፡

ለመናገር የፈለግኩ መስሎት፣ «አንተ ለብያኔዎቼ ደንታ የለህም? አትቀበላቸውም?» አለ፡፡

«አይደለም ጌታዬ፣ የሚሰማኝ ጽኑ ፍላጎት በቀጥታ እፊትህ ላይ መትፋት ነው፡፡ ግን አላደርገውም፡፡ ምክንያቱም ምራቄን ለማቆሸሽ አልፈልግም፡፡»

ከመገረሙ የተነሣ ፊቱ አመድ መሰለና ምን እንደሚሠራ ግራ ገባው፡፡ ግን የወታደሮቹ ኃላፊ ዐውቋል፡፡ ዘበኞቹን ጠራ፡፡

«አንጠልጥላችሁ ውሰዱና ደህና አድርጋችሁ ተንከባከቡት! በአንድ ሰዓት ውስጥ እየዳኸ ሲሔድ ለማየት እጠብቃለሁ፡፡»

«እንክትክቱን እናወጣዋለን!»

ጫማዎቹን በሁለቱም በኩል ማለት ከላይና ከውስጥ በምላሱ አስጠርገዋለሁ፡፡ የሥራውን ስጡት፡፡ ሁለመናው የእናንተው ነው፡፡»

ሁለት ዘበኞች የግራ ክንዴን፣ ሌሎች ሁለት ደግሞ የቀኙን ጨመደዱኝ፡፡ ክንዶቹን በጀርባዬ አዙረው እጆቼ የትከሻዎቼን መጋጠሚያዎች እስኪነኩ ድረስ ጠመዘዙና ፊቴን ወደ መሬት ደፍተው አስተኙኝ፡፡ በእጅ ካቴና ታሰርኩና የግራ እጄ መካከለኛ ጣት ከቀኝ አውራ ጣቴ ጋር በመወጠሪያ ቪቴ አጣበቋቸው፡፡ ከዚያም የዘበኞቹ ኃላፊ ልክ እንደ አንድ አውሬ ጸጉሬን ጨምድዶ ወደላይ ሳበኝ፡፡

ወደ ተጨማሪ ሐተታ መግባት አያሻም፡፡ ማወቅ ያለባችሁ ብቻ ለዐሥራ አንድ ቀናት ካቴናዎቹን እንዳጠለቅኩ የፊጥኝ እንደ ታሠርኩ መቆየቴን ነው፡፡ ነፍሴን ለባቶን አደራ ሰጥቻለሁ፡፡ በየቀኑ የተለመደውን ቁራጭ ዳቦዎች ይወረውርልኛል፡፡ ግን በእጆቼ ስለማልጠቀም ልመገባቸው አልቻልኩም፡፡ በጭንቅላቴ ወደ ቋሚ ፍርግርጉ እየገፋሁ ባጋጫቸውም እንኳ አይሰበሩም፡፡ ግን ባቶን በሕይወት ለመቆየት የሚያስችሉኝ ተጨማሪ ቁርጥራጭ ዳቦዎች ይወረውርልኝ ነበር፡፡ በእግሮቼ ትናንሽ ቁልሎች አበጅና ከዚያም በሆዴ ተንጋልዬ ልክ እንደ ውሻ እበላቸዋለሁ፡፡ ቅንጣት ያህል እንኳ እንዳያመልጠኝ እያንዳንዷን ቁራጭ በሚገባ አኝካለሁ፡፡

በዐሥራ ሁለተኛው ቀን የእጅ ካቴናዎቼን አወለቁልኝ፡፡ ብረቱ ሥጋዬን ሰርስሮ



@BOOKALEM

ገብቶ ስለነበር በሚሸት ሥጋ ተሸፍኗል። በተለይ ኪሥቃዩ የተነሣ ተዳከምኩ። ይህም የዘበኞቹን ኃላፊ አስፈራው። መለስ ሲልልኝ ወደ ሕክምና ክፍል ተወሰድኩና በተፈላ ውሃ ታጠብኩ። የሕክምና ሠራተኛው የቲታነስ መከላከያ መርፌ እንዲሰጡኝ ደጋግሞ አሳሰበ። ከንዶቹ በድን ስለሆኑ ወደ ተለመደው አቅጣጫቸው መመለስ አልቻሉም። ለግማሽ ሰዓት በቅባት ከታሸሁ በኋላ ነበር በጎንና ጎን ቁልቁል ልዘረጋቸው የቻልኩት።

ወደ ክፍሌ እንደ ተመለስኩ፣ የዘበኞቹ ኃላፊ ዐሥራ አንዶቹን ቁራጭ ዳቦዎች ተመለከተና፣ «ግብግብ ልታደርግ ነው እንዴ! የሚገርም ነው፣ ግን ከዐሥራ አንድ ቀን ጾም በኋላም በጣም የከሣህ አትመስልም . . . » አለ።

«ብዙ ውሃ እጠጣለሁ ጌታዬ።»

«አሃ፣ ለዚህ ነዋ! ገባኝ። አሁን በብዛት መብላት ይገባሃል። ስለዚህ ጥንካሬህን መልሰህ ታገኛለህ» አለኝና ሔደ።

ሞኙ፣ ዐሥራ አንድ ቀን ሙሉ ምንም ነገር ስላልበላሁ፣ በአንድ ጊዜ ሁሉንም ጠራርጌ በመብላት በቁንጣን እንድሞትለት አስቦ ነበር።

ወደ ምሽቱ አቅራቢያ ባቶን ጥቂት ትምባሆና የሲጃራ መጠቅለያ ወረቀት ሸጎጠልኝ። ደጋግሜ በማጤስ ጢሱን በአንድ ያማይሠራ የሙቀት ማስተላለፊያ ቱቦ ውስጥ አቦንነው ጀመር። ቢያንስ ለአንድ ተግባር ተጠቀምንበት ማለት ነው። ትንሽ እንደቆየሁ ጁሎን ጠራሁት። እንደዚሁ እርሱም ለዐሥራ አንድ ቀን ያልበላሁ መስሎት ረጋ እንድል መከረኝ። ይሁንና አንዳንድ አሳባቂዎች መልእክቱን ያጋልጣሉ በሚል ፍርሃት ዕውነቱን ልነግረው አልደፈርኩም። በቆርቆሮ ቱቦ የተደበቀውን ገንዘብ በጥንቃቄ መያዜንም ጁሎ በየዋህነት ጠየቀኝ።

አዎ፣ ይዣት ነበር፣ ግን እንደዚያ በማድረግ ያሳለፍኩትን ሥቃይ መግለጽ አልፈልግም። ፊንጢጣዬ ቆስሎ እያሰቃየኝ ነበር።

ከሦስት ሳምንት በኋላ ከክፍላችን ወጣን። ጉዳዩ ለምን ኖሯል? በሣሙናና ሙቅ ውሃ ገላችንን ተዘናንተን ታጠብን። ወደ መኖር ዓለም እንደገና መመለሴ ለራሴው ተሰማኝ። ጁሎ እንደ ሕፃን ልጅ ፈነደቀ፣ ፒየሮ ለፋም ፊቱ በደስታ አንጸባረቀ።

ከጨለማው ግንብ ስንወጣ የመጀመሪያ ጊዜያችን ስለነበር፣ ይህ የሚካሔደው ጉዳይ ለምን እንደሆነ ለማወቅ መንገድ አጣን። ጸጉር አስተካካዩ እንዲገልጽልኝ ሹክ ብለው መልስ ሊሰጠኝ አልፈለገም።

አስቀያሚ ፊት ያለው አንድ የማላውቀው እስረኛ፣ «እንደሚመስለኝ ከጨለማው ግንብ መገላገላችን ነው። ተቆጣጣሪዎች ይመጡብናል ብለው ፈርተው ይሆናል። ዋናው ቁም ነገር በሕይወት መገኘታችን ነው» አለ።

እያንዳንዳችን ወደ ተለመደው ክፍላችን ተወሰድን። ከሰዓት በኋላ በዐርባ



@BOOKALEM

ሦስተኛው ቀን ከተሰጠኝ የመጀመሪያው ትኩስ ቮርባዬ ውስጥ አንድ ትንሽ ቁራጭ እንጨት አገኘሁ:: ከሥሯ በኩል፣ «በስምንት ቀን ውስጥ ጉዞ እንጀምራለን፣ ነገ ከትባት ይሰጣል» የሚል አነበብኩ::

ይህን የላከው ማን ይሆን? ወሬውን እንዲነግረን የፈለገ አንድ ቅን እስረኛ መሆን አለበት:: እንዳችን ካወቅን ሁሉም እንደሚያውቁ ገብቶት ነበር:: መልዕክቱ ወደ እኔ መምጣቱም በእርግጥ ጥሩ ዕድል ሆነ::

ለጂሎ ባስቸኳይ በስልክ አስታወቅኩ:: «ዜናውን ለሌላው አስተላልፍ::»

ሌሊቱን ሙሉ ስልኩ ሲዘዋወር አስማለሁ:: መልዕክቱን አንድ ጊዜ ከሰጠሁ በኋላ እኔ አቆምኩ:: አልጋየ በጣም ተመችቶኝ ስለነበር፣ ጣጣ ውስጥ ለመግባት አልፈለግኩም:: ሌላ ቢቀር በዚህች ቀን እንኳ ወደ ጨለማው ግንብ ከሚመለሱት ጋር ለመጓዝ ተካፋይ መሆን አልፈለግኩም::



@BOOKALEM

# ሁለተኛ ማስታወሻ

## *ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት በመንገድ ላይ፡-*
## *ቅዱስ ማርቲን ደ-ሬ*

ወደ ማታ ላይ፣ ባቶን ሦስት ሲጋራዎችና፣ «ፓፒዮ፣ ከእኔ የደስታ ትዝታዎች ጋር ከዚህ እንደምትሔድ ዐውቃለሁ:: ባለሟል ተብዬ ይሆናል፣ ግን በእስረኞች ላይ በተቻለኝ ሁሉ አነስተኛ ጉዳት ለመፈጸም እሞክራለሁ:: ሥራውን የተቀበልኩት ዘጠኝ ልጆች ስላሉኝ በፍጥነት ለመፈታት ስለቸኮልኩ ነው:: በጣም የባሰ ጭካኔ ውስጥ ሳልገባ ምሕረት ለማግኘት እንድችል እጥራለሁ:: ደህና ሁን:: መልካም ዕድል:: ኮንሸዩ ከነገ ወዲያ ይነሣል» የምትል መልዕክት ያዘለች አንዲት ቁራጭ ማስታወሻ አሾለከልኝ::

በሚቀጥለው ቀን በሠላሳ ቡድን እየሆንን በሥነ ሥርዓት ከፍሉ ኮሪደር ውስጥ ተሰበሰብን:: ለበሽታዎች መከላከያ ከትባት የሚያደርጉ የሕክምና ባለሙያዎች ከካየን መጥተው ነበር:: ለእያንዳንዳችን ሦስት ከትባቶችና ሁለት ሊትር ወተት ተሰጠን:: ዴጋ እኔ አጠገብ ቆሟል:: አንድ ጊዜ ከተከተብን በኋላ ተመልሰን ወደ ጨለማው ግንብ እንደማንገባ ስላወቅን የፀጥታ ማከበሩን ሕግ ጨርሶ ረሳነው:: ዘበኞቹ እያዩን ድምፃችንን ዝቅ አድርገን ስናወራም፣ ከከተማ በመጡት የሕክምና ሰዎች ፊት ምንም ነገር ለማለት አልደፈሩም::

ዴጋ ሐሳብ ገብቶት ነበር:: «ሁላችንንም በአንድ ጊዜ ለመውሰድ የሚበቃ ግልፕ ፋርጎዎች ያገኙ ይሆን? ሲል ጠየቀኝ::

«እንዴት እንደሚያደርጉ አላውቅም::»

«ቅዱስ ማርቲን ደ-ሬ በጣም ሩቅ ነው፣ ስለዚህ በቀን ስድሳ ሰዎች እንኳ ቢያጓጉዙ ዐሥር ቀን ይወስዳል:: እዚህ ብቻ ስድስት መቶ ያህል እንሆናለን::»

«ዋናው ነገር መከተባችን ነው:: ይህም ማለት በመዝገብ ላይ ስለገባን በፍጥነት ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት እንሔዳለን:: ደስ ይበለን ዴጋ፣ በአዲስ ሽግግር ላይ ነን:: በአንተ ስለምተማመን አንተም በእኔ መተማመን ትችላለህ::»

ትኩር ብሎ ተመለከተኝና ዐይኖቹ በደስታ በሩ:: እጁን በከንዴ ላይ ጣል አደረገና፣ «ፓፒ፣ በሕይወትም በሞትም» አለ:: በሸፍኑ ካሚወን ውስጥ ተጨናንቀን ከመታፈናችን በስተቀር ስለ ኮንሾዩ መዘርዘሩ ዋጋ የለውም:: ትንሽ አየር ለማስገባትም ሆነ መዝጊያዎቹን እንኳ ገርበብ አድርጎ ለመከፈት ዘበኞቹ እሻፈረን አሉ:: ላ-ሮሼል ስንደርስ ሁለት ሰዎች በአየር ማጣት ምክንያት ሞተው ነበር::

ቅዱስ ማርቲን ደ-ሬ፣ ደሴት ስለ ነበረችና ባሕሩን ለማቋረጥ አንድ ጀልባ



@BOOKALEM

መያዝ ስለሚኖርብን፣ በወደቡ ዳር የሚመላለሱት ሰዎች የምስኪኖቹን እስከሬን በማየት ታዛቢዎች ሆኑ፡፡ በከፋት አልተመለከቱንም፡፡ መጨረሻ ላይ ሲያስረክቡን የሞቱትንም ያሉትንም ጭምር ስለ ነበር፣ ፖሊሶቹ አስከሬኖቹን ከእኛ ጋር በጀልባው ላይ ጫኗቸው፡፡

መሻገሩም ረጅም ጊዜ አልወሰደም፣ ይሁንና ትንሽ ንፁሕ አየር ለመሳብ ዕድል አጋጠመን፡፡ «ማምለጥ ማምለጥ ይለኛል» ብለው ዴጋ ፈገግ አለ፡፡ አጠገባችን የቆመው ጁሎም እንደዚህ አለ፡-

«አዎ፣ በእርግጥም ይዳዳኛል፡፡ አብረን ለመሆን እንሞክር፡፡ በቅዱስ ማርቲን ደ-ሬ ለእያንዳንዱ ክፍል ዐሥር እሥረኞችን በመደዳው እያስነሱ ይወስዳሉ፡፡»

ጁሎ ተሳስቶ ነበር፡፡ በምንደርስበት ወቅት እርሱንና ሁለት ሌሎች ሰዎች ጠርተው ለብቻ አስቀመጧቸው፡፡ ሦስቱም ከቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት ቀደም ሲል ያመለጡ እስረኞች ስለሆኑ፣ ተይዘው ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ፈረንሣይ ተመልሰው መላካቸው ነበር፡፡

እኛ ክፍል ውስጥ ያለነው የዐሥር ሰዎች ቡድን የቆይታ ኑሮን ቀጠልን፡፡ ማውራትና ማጨስ ተፈቅዶልን ነበር፣ በጥሩ ሁኔታም ይመግቡናል፡፡ የምንፈራው ቢኖር በቆርቆሮ ቱቦ ለተደበቀው ገንዘብ ነበር፡፡ ያለ አንድ ምክንያት ድንገት አውልቅ ትባልና በጥብቅ ልትፈተሽ ትችላለህ፡፡ በመጀመሪያ እያንዳንዷ በስንዝር የምትለካ አካላትህ እስከ ውስጥ እግርህ ድረስ፣ ከዚያም ልብሶችህ፣ በመጨረሻም «ልበስ!» ትባልና ወደ ክፍልህ ትመለሳለህ፡፡

ኑሯችን እንደዚያ ነበር፣ መታሠሪያ ክፍሉ፣ የምግብ አዳራሹ፣ ለረጅም ሰዓት በሰልፍ እየሆንን የምናሳልፍበት መስከ፡፡ አንድ፣ ሁለት! አንድ፣ ሁለት! አንድ፣ ሁለት . . . በአንድ መቶ ሃምሳ ቡድን እንሰለፋለን፡፡ ሰልፉ ረጅም ስለነበረ የእንጨት ጫማዎቻችን ይንኳኳሉ፡፡ ፀጥታ ግዴታ ነበር፡፡ ከዚያ «ሰልፉ ተበትኗል!» ይባልና ሁሉም በየቢጤው በቡድን እየተከፋፈለ መሬት ላይ ይቀመጣል፡፡ በመጀመሪያ ከመላው ኮርሲካ፣ ማርሴይ፣ ቱሉስ፣ ብሪታኒ፣ ፓሪስ ወዘተ ... ዕውቅ የሆኑት አራዳዎች ይሰበሰባሉ፡፡ ከአርዴክም ቢሆን አንድ ሰው ነበር፣ እርሱም እኔ ነኝ፡፡ ለአርዴክ ተወክዬ መናገር ካስፈለገን፣ በዚያ አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰዎች የሚገኙበት ኮንቮይ ውስጥ ያለነው ሚስቱን ገድሎ የነበረ አንድ ፖሊስና እኔ፣ ሁለት ሰዎች ብቻ ነበርን፡፡ ለማጠቃለል ያህል፣ የአርዴክ ሰዎች ጥሩ ሰዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ ከአራዳዎቹ አባሎች ይልቅ ሌሎቹ ቡድኖች ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ለመሔድ ይበልጥ ፈቃደኞች ነበሩ፡፡ እነዚያ የቆይታ ቀኖች «የጥናት ወቅቶች» እየተባሉ ይጠራሉ፡፡ በዕርግጥም ነበሩ፣ በጥብቅ እንጠያቃለን፡፡

አንድ ጊዜ ከሰዓት በኋላ ፀሐይ ለመሞቅ ተቀምጬ እንዳለሁ፣ አንድ ሰው ወደ እኔ መጣ፡፡ መነጽር ያደረገ፣ አጭርና ኮሳሳ ነበር፡፡ ላስታውሰው ሞከርኩ፣ ግን



@BOOKALEM

ከዩኒፎርማችን አንጻር ችግር ሆነብኝ፡፡

«ፓፒዮ አንተ ነህ?»

«አዎ፣ እኔ ነኝ፡፡ ምን ትፈልጋለህ?»

«ወደ መጸዳጃ ቤት ና» አለኝና ሔደ፡፡

«ይኸ ኮርሲካዊ መሳይ ነው፣ አንድ የተራራ ወንበዴ ይመስላል፡፡ ምን ይፈልጋል?» አለ ዴጋ፡፡

«እኔም ለመረዳት የምፈልገው ይህንኑ ነው፡፡» ከግቢው መካከል ወደሚገኘው መጸዳጃ·ቤት ሔድኩና የምሸና መሰልኩ፡፡ ሰውየውም ከጎኔ ቆመና ወደ እኔ ሳይመለከት፣ «የፓስካል ማትራስ አማች ነኝ፡፡ ሲጎበኘኝ እንደመጣ፣ እርዳታ ካስፈለገኝ ወደ አንተ መጥቼ ስሙን እንዳነሣልህ ነግሮኛል» አለ፡፡

«አዎ፣ ፓስካል ጓደኛዬ ነው፡፡ ምን ትፈልጋለህ?»

«ከአሁን ወዲያ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦየን ለመያዝ አልቻልኩም፡፡ ተቅማጥ አምኛል፡፡ ዘበኞቹ ያገኙብኛል፣ ወይም አንድ ሰው ይሰርቃታል ብዬ ፈርቻለሁ፣ ማንን እንደማምን አላወቅኩም፣ እባክህ ፓፒዮ፣ ለትንሽ ቀን አንተ ያዝልኝ» አለና ከእኔ የበለጠ አንድ ትልቅ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ አሳየኝ፡፡ ይህን ብሎ የጠየቀኝ ለማውጣጣት ይሆናል ብዬ ፈርቼ ነበር፡፡ ሁለቱንም ለመያዝ አልችልም ብየ ብነግረው ደግሞ ሊያውቅብኝ ሆነ፡፡

ስለዚህ ለስለስ ብዬ፣ «በውስጥ ምን ያህል አለባት?» አልኩት፡፡

«ሐያ አምስት ሺ ፍራንክ፡፡»

ሌላ ቃል ሳልናገር የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዋን ተቀበልኩ፡፡ በጣም ንፁሕ ስለነበረች አንድ ሰው ሁለት ለመያዝ ይቻል እንደሆነ እየደነቀኝ በቀጥታ ከእርሱ ፊት በፊጋራየ ወደላይ ገፋኋት፡፡ ምንም ሐሳብ አልነበረኝም፡፡ ጥንሣሁና ሱሪየን መልሼ አጠለቅኩ፡፡ አላስቸገረኝም፡፡

ከመሔዱ በፊት «ሰሜ ኢኛስ ጋልጋኒ ነው፡፡ አመሰግናለሁ ፓፒዮ» አለ፡፡ ወደ ዴጋ ተመልሼ ሔድኩና ታሪኩን ነገርኩት፡፡

«በጣም አይከብድም?»

«አይከብድም፡፡»

«እሺ፣ እንግዲያውስ፡፡»

ከተቻለ ከጁሎ ወይም ከጊቱ ጋር፣ አለበለዚያም ካሁን በፊት አምልጠው ከነበሩ ሰዎች ጋር ግንኙነት ልናደርግ ሞከርን፡፡ ያ ቦታ ምን ይመስላል? የእሥረኛ አያያዛቸው እንዴት ነው? የገንዘብ መያዣ ቱቦህን እንዴት ትደብቃለህ? ወዘተ . . . ለሚለው ሁሉ መልስ ለማግኘት ጓጉተን ነበር፡፡ ዕድል የማያመጣው የለም፣ አንድ በጣም



@BOOKALEM

እንግዳ የሆነ ፍጡር ላይ ጣለን:: አባቱ ዘበኛ ሲሆን፣ ከባለቤቱ ጋር በደሳሊዩ ደሴቶች ኗሪ ነበር:: የተወለደው ከሦስቱ አንዱ በሆነችው በሮያሌ ደሴት ውስጥ ሲሆን፣ ሌሎቹ ቅዱስ ዮሴፍና የዲያብሎ ደሴት ይባላሉ:: ወይ ዕድል! ተመልሶ የሚሔደው እንደ ዘበኛ ልጅ ሳይሆን፣ እንደ አንድ እሥረኛ ሆኖ ነበር::

ቤት በመሰርሰር ዝርፊያ ዐሥራ ሁለት ዓመት ጽኑ እሥራት ተፈርዶበት ነበር:: ዕድሜው ዐሥራ ዘጠኝ ዓመት ሲሆን፣ ግልጽ ፊትና ጥርት ያሉ ብሩህ ዐይኖች ነበሩት:: በአጋጣሚ የፈጸመው ድርጊት መሆኑን ወዲያውኑ ለመገንዘብ ችለናል:: ስለ አራዳው ዓለም የሚያውቀው በጣም የተወሰነ ቢሆንም፣ ከፊታችን ለሚጠብቀን ኑሮ መረጃዎችን ለመስጠት ይጠቅመናል:: ለዐሥራ አራት ዓመት ስለ ቆየባቸው ደሴቶች ኑሮ ሁኔታ ነገረን:: ለምሳሌ እርሱን በደሴቱ ውስጥ አሳድጎት የነበረው አንድ የታወቀ ወመኔ እሥረኛ ሲሆን፣ የተወነጀለውም በሳሰከ ደ እር ውብ ዐይኖች መነሻ የጩቤ ፍልሚያ አድርጎ መሆኑን ተረዳን::

አንዳንድ ዋጋ ያላቸው ምስክሮችም ሰጠን:: ማምለጫችንን ማቀድ የሚኖርብን ከግራንዴቴሬ መሆን እንዳለበት እንጅ፣ ከደሴቲቱ አለመቻሉን፣ ከዚያም አደገኞች ተብለን መመዝገብ እንደማይኖርብን፣ ምክንያቱም በዚህ ስም ከጎደፍን ወደ አድራሻችን ቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ ወዲያው ስንደርስ፣ የቱን ያህል አደገኞች ናቸው ብለው እነርሱ በገመቱት መጠን ለዓመታት ወይም በዕድሜ ይፍታህ እዚያው ሊያስሩን እንደሚችሉና በአጠቃላይ በደሴቶቹ ከመቶ ውስጥ ከአምስት በላይ እንደማይታሡ ነበር:: ሌሎቹ በግራን ይቆያሉ:: ደሴቶቹ ጤናማ ነበሩ፣ ግራንዴቴሬ ግን ቀደም ብሎ ዴጋ እንደነገረን ከሆነ አንድን እስረኛ ቀስ በቀስ በዐፅሙ የሚያስቀር፣ ማንኛውም ዓይነት በሽታና ብዙ ዓይነት ድንገተኛ ሞት የሞላበት የታወቀ መዓተኛ ቦታ ነበር:: በደሴቶቹ ላለመታሠር ተስፋ አደረግን:: ግን በጉሮሮየ ላይ የሆነ ሽምቀቅ ተሰማኝ:: አደገኛ ተብዬ ተመዝግቤ ከሆነስ ምን ልሆን ነው? በወህኒ ቤቱ አዛዥና ትሪቡላር ላይ የፈጸምኳቸው ድርጊቶች ከዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ፍርዴ ጋር በጥሩ አቋም ላይ አያስገኙኝም::

ቅዱስ ማርቲን ደ-ሬ ከዳር እስከዳር በእሥረኞች ተጨናንቃለች:: ሁለት ዓይነት እሥረኞች ነበሩ፣ በስምንት መቶና በአንድ ሺ መካከል የሚገመቱ ሌቦችና ዘጠኝ መቶ ከባድ ወንጀለኞች:: ልማደኛ ወንጀለኛ ለመባል አንድ ከበድ ያለ ጥፋት መፈጸም፣ ወይም ቢያንስ አንድ ከባድ ጥፋት አድርጓል በመባል መከሰስ ይኖርብሃል:: ቅጣቱ ከሰባት ዓመት ጽኑ እሥራት እስከ ዕድሜ ይፍታህ ይደርሳል:: አንድ ወንጀለኛ በአመክሮ ከሞት ቅጣት ቢያመልጥ በቀጥታ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ያገኛሉ:: የልማደኛ ሌቦቹ ግን ከዚያ የተለየ ነበር:: አንድ ሰው ልማደኛ ሌባ የሚለው ከሦስት ወይም ከአምስት ውንጀላዎች በኋላ ነው:: የማይታረሙ ሌቦች ናቸውና ሕብረተሰቡም እንዴት ራሱን



@BOOKALEM

ሊጠብቅ እንደማይችል አንጃ፡፡ በሌላ አንጻር እንደዚህ የመሰለውን ተጨማሪ ዓይነት ቅጣት አንድ የሠለጠነ ሕዝብ በሥራ ላይ ማዋሉ ደግሞ አሳፋሪ ነበር፡፡ ልማደኞቹ ሌቦች ጊዜያዊ ናቸው፡፡ ዘወትር ሰለሚያዙ ፈዛዞች ነበሩ፡፡ በእኔ ጊዜ ልማደኛ ሌባ መሆንና የዕድሜ ይፍታህ እሥራት ተወራራሽ ነበሩ፡፡ ሕብረተሰቡን ያስቸግራሉ በሚል ምክንያት ብቻ እነርሱን ለማውደም የሚሯሯጥና ለመበቀል መብት ያለው ማንም ሀገር አይኖርም፡፡ እንደዚህ የመሰለው ከሰብአዊ ርኅራኄ ውጭ የሆነ ቅጣት ከሚጣልባቸው ይልቅ ቢታረሙ ይበጃል፡፡

አሁን በቅዱስ ማርቲን ደ ሬ ዐሥራ ሰባት ቀን ሆነን፡፡ ወደ ቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት የምትወስደን ጀልባ ስም «ላ-ማርቲኜ» መባሏን ተረዳን፡፡ አንድ ሺ ስምንት መቶ እስረኞች ልትሸከም ነው፡፡ በአምባው ውስጥ ከሚገኘው መስከ ስምንት ወይም ዘጠኝ መቶ የምንሆን እሥረኞች ተሰብስበን ፡፡ በዐሥር ረድፍ ተሰልፈን ግቢውን እንደ ሞላን ለአንድ ሰዓት ያህል ስንጠባበቅ ቆየን፡፡ በሩ ተከፈተና እኛ እናውቃቸው ከነበሩት ዘበኞች በጣም ልዩ የሆነ ልብስ የለበሱ በቡድን ሆነው ከውጭ በኩል መጡ፡፡ የለበሱት ውሃ ሰማያዊ የሚሊታሪ ቅድ ሆኖ አለባበሳቸውም ደስ ይላል፡፡ ፖሊሶችም አልነበሩም፣ ወታደሮችም አልነበሩም፡፡ ሁሉም ሰፊ ቀበቶዎች ታጥቀው በእነርሱ ላይ የሸጉጥ ማኅደሮች አንጠልጥለዋል፡፡ የሽጉጦቹንም እጀታዎች ማየት እንችላለን፡፡ ሰማንያ ይሆናሉ፡፡ አንዳንዶቹ በእጅጌዎቻቸው ላይ ጥብጣቦች ለጥፈዋል፡፡ ሁሉም ፊታቸው በፀሐይ የበለዘና በሠላሳ አምስትና በሃምሳ ዓመት መካከል ያሉ ይመስላሉ፡፡ ሽምገል ያሉት ርኅሩኆች ሲመስሉ፣ ወጣቶቹ ደግሞ በግብዝነት ስሜት ደረታቸውን አሳብጠዋል፡፡ የቡድኑ አዛዥ መኮንን በቅዱስ ማርቲን ደሬ የፖሊስ ኮሎኔል፣ የቅኝ ግዛት ልብስ በለበሱ ሦስት ወይም አራት ዶክተሮችና ነጭ ካባ በለበሱ ሁለት ቄሶች ታጅቦ ነበር፡፡ የፖሊሱ ኮሎኔል አንድ የድምፅ ማጉሊያ ወደ አፉ ቀረብ አደረገ፡፡ «ተጠንቀቅ!» የሚል ትእዛዝ ስንጠባበቅ ነበር፡፡ ግን በትእዛዙ ምትክ «በጥንቃቄ አዳምጡ» አለ ኮሎኔሉ፡፡ ቀጠለናም፣

«ከአንግዲህ ወዲያ ዋና መሥሪያ ቤቱ ካየን ከተማ የሆነው በፍትሕ ሚኒስቴር የፈረንሣይ ጊያናን በሚወከለው የቅጣት አስተዳደር ባለሥልጣኖች ዳኝነት ሥር ናችሁ፡፡ የወህኒ አዛገፉ ባሮ፣ እነኝህ የተሰለፉትንና ስማቸው መዝገብ ላይ የሰፈረውን ስምንት መቶ እስረኞች አስረክብዎታለሁ፡፡ ሁሉም መኖራቸውን አጣርተው በፊርማዎ ቢያረጋግጡልን?»

የስም ጥሪው ተጀመረ፡፡ «እከሌ እከሌ፣ አለሁ! እከሌ እከሌ፣ አለሁ! ወዘተ . . . » ሁለት ሰዓት ፈጀ፡፡ ሁሉም ነገር ተስተካከሎ ነበር፡፡ ከዚያም በሁለቱ አስተዳደሮች የተደረገውን የፊርማ ልውውጥ ለሥነ ሥርዓቱ በተዘጋጀች አንዲት ትንሽ ጠረጴዛ ላይ



@BOOKALEM

ሲከናወን ተመለከትን፡፡

ወህኒ አዛገፉ ባሮ፣ በብር ፋንታ የከር ጥልፍ ቢሆኑም፣ እርሱም እንደ ኮሎኔሉ ብዙ የማዕረግ ምልክቶች ነበሩት፡፡ እሱም በተራው የድምፅ ማጉሊያውን ያዘ፡፡ «ተጓዦች፣ ከአሁን ወዲያ የምትጠሩበት ስም ይሆናል፡፡ - ‹ተጓዥ እከሌ እከሌ› ወይም በተሰጣችሁ ማንኛውም መለያ ቁጥር መሠረት ‹ቁጥር ይህን ያህል› ይሆናል፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት ተገቢ ነው ብለው የማያምኑበትን ውሳኔ በሚያሳልፉ የውስጥ ፍርድ ቤቶችና በቅኝ ግዛት ወህኒ ቤቶች ልዩ ሕግና መመሪያ ሥር ናችሁ፡፡ በአሰቃቂው የቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ውስጥ በምትፈጽሙት ጥፋት መሠረት ራሱን ችሎ የሚሠራው ፍርድ ቤት፣ ከቀላል እሥራት አንሥቶ እስከ ሞት ቅጣት ድረስ በማንኛውም አኳያ ሊቀጣችሁ ይችላል፡፡ በእሥራትም ይሁን በግዞት እነዚህ የሥነ ሥርዓት ቅጣቶች የሚከናወኑት በአስተዳደሩ ሥር በሚገኙ ማናቸውም ቦታዎች ነው፡፡ ከፊታችሁ የምታዩዋቸው ፖሊሶች የሚጠሩት ዘበኞች እየተባሉ ነው፡፡ እናንተ ስትጠሯቸው ‹አቶ ዘበኛ› እያላችሁ መሆን አለበት፡፡ ከእራት በኋላ ለቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ከሚሆን ልብሶቻችሁ ጋር አንድ ሻንጣ ይሰጣችኋል፡፡ ማንኛውንም ነገር ተረድታችኋል፡፡ ነገ «ላ - ማርቲኜ» ላይ ትሣፈራላችሁ፡፡ ጉዞውን የምናደርገው አብረን ነው፡፡ በፈረንሣይ ውስጥ ከሚገኝ አንድ ጠባይ ማረሚያ ይልቅ የቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት የተሻለ ስለሆነ በመሔዳችሁ ሐዘን አይሰማችሁ፡፡ ማጤስ፣ መዝፈን፣ ካርታ መጫወትና መናገር ትችላላችሁ፡፡ መልካም ሥነ ምግባር እስካሳያችሁ ድረስ ሥቃይ ይደርስብናል ብላችሁ አትሥጉ፡፡ ማንኛውም ዓይነት የግል አለመግባባት ያላችሁ፣ ወደ ቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ደርሳችሁ እስኪታቃልሉ ድረስ እንድትታገሡ እጠይቃለሁ፡፡ በጉዟችን ወቅት ሥነ ሥርዓት በጣም ጥብቅ መሆን አለበት፤ ይህም ለምን እንደሆነ እንደምትረዱ አምናለሁ፡፡ ከእናንተ ውስጥ ጉዞውን ለመቀጠል ሕመም የሚሰማችሁ ካላችሁ ወደ ሕክምና ክፍል ሒዱና ኮንቮዩን በሚያጅቡ የሕክምና ሻምበሎች ልትታከሙ ትችላላችሁ፡፡ «መልካም ጉዞ እመኝላችኋለሁ፡፡» ሥነ ሥርዓቱ ተፈጸመ፡፡

«እንግዲህ፤ ምን ታስባለህ ዴጋ?»

«ወዳጄ ፓፒዮ፣ ትልቁ አደጋ የሌሎቹ እስረኞች ነው ብዬ ስነግርህ እርግጠኛ ነበርኩ፡፡ «ማንኛውም ዓይነት የግል አለመግባባት ያላችሁ ወደቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ደርሳችሁ እስኪታቃልሉ ድረስ ታገሡ» ያላት ጉዳይ ብዙ ስንክሳር ትናገራለች፡፡ መዓት ግድያዎች መኖር አለባቸው!»

«ስለዚህ ጉዳይ አትጨነቅ፡፡ እኔን ብቻ እመነኝ፡፡»

ፍራንሷ ላ-ፓሴን ፈለግኩና እንደዚህ ስል ጠየቅኩት፡፡

«ወንድምህ አሁንም የእሥረኛ ጤና ረዳት እንደሆነ ነው?»



@BOOKALEM

«አዎ፤ ልማደኛ አሥረኛ ነው፡፡»

«በተቻለ ፍጥነት ሒደና አንድ ጨቤ እንዲሰጥህ ጠይቀው፡፡ ገንዘብ ከፈለገ ስንት እንደሆነ ንገረኝና እከፍለዋለሁ፡፡»

ከሁለት ሰዓት በኋላ በጣም ጠንካራ የብረት እጀታ ያላት የአንዲት ጩቤ ባለቤት ሆንኩ፡፡ ሣንካዋ ትንሽ ረዘም ማለቷ ነው እንጂ የምታስደነግጥ መሣሪያ ነበረች፡፡

በግቢው መካከል ከሚገኘው መጸደጃ ቤት አጠገብ ቁጭ አልኩና የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን መልሼ መስጠት እንድችል ወደ ጋልጋኒ ላከሁ፡፡ ሆኖም ስፈውን ግቢ ሞልተው ከሚርመሰመሱት ስምንት መቶ ሰዎች መካከል እርሱን ለማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡ ከመጣን ጀምሮ ሉ-ጊቱን፣ ጁሎን ወይም ሳንቲኒን አላገኘናቸውም ነበር፡፡

የማኅበራዊ ኑሮ ጥቅሙ አብረን መኖራችን፣ ማውራታችንና የአንድ አዲስ ማኅበረሰብ አባል መሆናችን ነበር፡፡ አንድ ማኅበረሰብ ይሁን ብላችሁ ከጠራችሁት በጣም ብዙ ለመናገር፣ ለመስማትና ለማድረግ ይቻላል፡፡ ለማሰብ ግን ጊዜ አልነበረም፡፡ ያለፈው የብቸኝነት ኑሮዬ የአሁኑን ኑሮየን ምንኛ አደብዝዞትና ጋርዶት ኖሯል? ወህኒ ቤት ከደረስኩ በኋላ ማን እንደነበርኩና ለምን እንደ መጣሁ ማሰቡን እርግፍ አድርጌ ትቼ ለማምለጥ ብቻ ማተኮር እልዳለብኝ ተገነዘብኩ፡፡

ግን ተሳስቼ ነበር፡፡ ከሁሉም የበለጠ አንገብጋቢው ነገር በሕይወት መቆየት ነው፡፡ ለመሆኑ ፖሊሶቹ፣ ተቸዎቹ፣ ፍርድ ቤቱ፣ ዳኞቹ፣ ሚስቴ፣ አባቴና ጓደኞቼ ወዴት ይሆኑ? ሕያው ሆነው ተመለሱብኝ፡፡ እያንዳንዳቸውም በልቤ ውስጥ ቦታ ነበራቸው፣ ግን ወደ አልታወቀው አካባቢ የማደርገው ከፍተኛ የጉዞ ሽግግር መሸበርና፣ ከአዲስ ጓደኞች ጋር ከመለማመድ የተነሣ እንደ ወትሮው ተመሳሳይ ዋጋ አልሰጣቸውም፡፡ ይሁን እንጂ፣ አንድ ጊዜ ፍላጎት ኖሮኝ ለእያንዳንዳቸው መኖሪያ ያደረገሁትን የአእምሮዬን ጓዳ ስከፍት ሁሉም ቁልጭ ብለው ይታዩኛል፡፡

ጋልጋኒን ወደ እኔ እየመሩ አመጡት፡፡ በባዶ ዐይኑ ቀርቶ በወፍራሙ መነጥሩ እንኳ ለማየት አይችልም፡፡ ጤንነቱ የተሻሻለ ይመስላል፡፡ ወደ እኔ ቀረብ አለና ምንም ሳይናገር እጄን ጭምድድ አደረገኝ፡፡

«የገንዘብ መደበቂያ ቱቦህን መልሽ ልሰጥህ እፈልጋለሁ» አልኩና በማከታተል፣ «አሁን ደህና ነህ፣ ራስህ መያዝ ትችላለህ፡፡ በጉዞው ወቅት ለእኔ ከባድ ኃላፊነት ነው፣ ደግሞስ እርስ በርሳችን የትም ቦታ ባንቀራረብ ወይም በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ስንደርስ እንኳ ባንገናኝ፣ ምኑ ይታወቃል፡፡ ስለዚህ የሚሻለው ብትወስደው ነው፡፡»

ጋልጋኒ የከፋው ይመስላል፡፡

«እንግዲህ፣ ወደ መጸዳጃ ቤት ናና የገንዘብ መደበቂያ ቱቦህን ልስጥህ፡፡»

«ይቅርብኝ፣ አልፈልግም፡፡ አንተው ውሰደው፣ እንደ ገጸ በረከት ለአንተው



@BOOKALEM

ሰጥቻሃለሁ:: ሁሉም የአንተው ይሁን::»

«ለምን እንደዚህ ትላለህ?»

«ለገንዘብ መደበቂያ ቱቦየ ስል መገደል አልፈልግም:: በእርሱ ምክንያት ከምገደል ያለ ገንዘብ መኖርን እመርጣለሁ:: ከዚህም ሌላ የእኔን ገንዘብ ለማስቀመጥ ስትል ሕይወትህን አደጋ ላይ መጣል ይሉኝታ ማጣት ስለሆነ፣ ለአንተው እሰጥሃለሁ:: በዚህ መንገድ ሕይወትህን ለአደጋ ብታጋልጥ እንኳ ለገዛ ራስህ ጥቅም ይሆናል::»

«ፈርተሃል ጋልጋኒ:: የሚያስፈራሩህ አሉ እንዴ?»

«አዎ፣ ሦስት ዓረቦች ሁልጊዜ ከኋላየ እንደ ጅራት ይከተሉኛል:: ወደ አንተ ያልመጣሁበት ምክንያት በዚህ ነገር ሁለታችን እንደ ተመሳጠርን እነርሱ እንዲጠረጥሩ ስላልፈለግኩ ነው:: ቀንም ሆነ ሌሊት በማንኛውም ጊዜ ወደ መጸዳጃ ቤት ስሔድ፣ ከእነዚያ ጥላቢሶች አንዱ ይመጣና አጠገቤ ይቆማል:: ስለ ሁኔታው እምብዛም ሳላስተጋባ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ እንደሌለኝ ግልጽ ለማድረግ ሞከርኩ:: ግን ከመከታተል አልቦዘኑልኝም::

እርግጠኛ ነኝ አንድ ሰው እንደ ያዘልኝ ጠርጥረዋል:: ማን እንደሆነ አላወቁም፣ ግን መልሼ ስቀበል ለማየት ዙሪያውን ያንገራብቡብኛል::»

ጋልጋኒን ስመለከተው ተጨንቆ እንደነበር ተገነዘብኩ::

«የሚዘዋወሩት ከግቢው በየትኛው በኩል ነው?» ስል ጠየቅኩት::

«ከልብስ ማጠቢያውና ኩሽና ቤቱ አጠገብ::»

«መልካም፣ አንተ እዚህ ቆይና እኔ ወደዚያው እሔዳለሁ - ግን አይሆንም፣ አንተም ከእኔ ጋር ና::»

ጩቤየን ከኮፍያዬ አወጣሁና ስለቱን በቀኝ እጅጌዬ ውስጥ ወደላይ አስገብቼ እጀታዋን በእጄ ጨበጥኩ:: ወዲያው ተመለከትናቸው:: አራት ያህል ነበሩ:: ሦስት ዓረቦችና ጅራንዶ የተባለ አንድ ኮርሲካዊ:: ወዲያውኑ ነገሩ ገባኝ:: ኮርሲካዊው በአራዳዎች ጓደኞቹ ገሸሽ ስለተደረገ ነበር ወደ ዓረቦቹ የተጠጋው:: ጋልጋኒ የፓስካል ማትራስ አማች መሆኑንና እንደዚያም ከሆነ አንድ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ እንደሚኖረው ዐውቆ መሆን አለበት::

«ታዲያስ ሞከሬን?»

«ደህና ነኝ ፓፒዮ:: አንተስ እንዴት ነህ?»

«አለሁ . . . መቼስ! ወደእዚህ የመጣሁት ጋልጋኒ ጓደኛዬ መሆኑን ልነግራችሁ ነው:: አንድ ነገር በእርሱ ላይ ቢደርስ፣ ጉዳዩ መጀመሪያ የሚመለከትህ አንተን ጅራንዶን ነው:: የቀራችሁትንም ይከተላችኋል:: በፈለጋችሁት መንገድ ተርጉሙት::»

ሞከሬን ተነሣ:: በግምት ቁመቱ ስድስት ጫማ የሚሆን፣ እንደ እኔው ረጅምና



@BOOKALEM

አቋሙም የተደላደለ ነበር:: 'ለመጣላት ተዘጋጅቶ ነበር፣ · ሁለመናዋ የሚያብለጨልጨውን አዲስ ጩቤ መዘዝኩ:: በእጄ መዳፍ ውስጥ እንደያዝኩ፣ «ብትንቀሳቀስ ልክ እንደ ውሻ እገድልሃለሁ» አልኩት::

ሙሣሪያ በመያዜ ምክንያት በግልጽ ከመገረሙም ሌላ ቁርጠኛ የመሆኔና የጩቤውም ርዝመት ሰላስደነገጠው፣

«የተነሣሁት እኮ ላናግርህ እንጂ ለጥል አይደለም» አለ::

ይህ ዕውነት እንዳልነበረ ዐውቄአለሁ፣ ግን በጓደኞቹ ፊት ከኃፍረት እንዲድን እርሱን መርዳት ፍላጎቴ እስከሆነ ድረስ ተዝናንቶ እንዲያልፍ ፈቀቅ አልኩለት::

«እሺ፣ የተነሣኸው ለመናገር እስከሆነ ድረስ»

«ጋልጋኒ የአንተ ጓደኛ መሆኑን አላወቅኩም:: ወቅታዊ ትውውቅ መስሎኝ ነበር:: እንዴት እንደሆነ ታውቃለህ ፓፒዮ፣ ለማምለጥ ገንዘብ ማግኘት ሰላለብህ እዚህ ማንኛውም ሰው ከአንተ ይሰርቃል» አለ::

«መልካም፣ ሊሆን ይችላል፣ ለኑሮህ ለመታገል ማንኛውም መብት አለህ ሞከሬን:: ማስታወስ ያለብህ ብቻ ይህ የተከለከለ ቀበሌ መሆኑን ነው:: ሌላ አካባቢ አስስ::»

እጁን ዘረጋና ጨበጥኩት:: የክርስቶስ ያለህ፣ አልቆልኝ ነበር:: ሰውየውን ገድየው ቢሆን የሚቀጥለው ቀን እርግጠኛ ነኝ ከጉዞየ ተጨናግፌ ነበር::

ጋልጋኒ ከእኔ ጋር ተመለሰ:: «ስለዚህ ጉዳይ ለማንም ሰው እንዳትናገር:: ከዴጋ ጋርም ለመቀያየም አልፈልግም» አልኩት:: ጋልጋኒ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን እንዲወስድልኝ ለማሳመን ሞከርኩ::

«ከመሔዳችን በፊት ነገ» አለ:: ግን በሚቀጥለው ቀን ራሱን ሰለደበቀ፣ እነሆ ከሁለቱ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦዎች ጋር ወደ ቅኝ ግዛት እስቃቂ ወህኒ ቤት ጉዞ መነሣት ነበረብኝ::

በዚያች ሌሊት እኛ ከፍል ውስጥ ማንም አልተናገረም:: በፈረንሣይ አፈር ላይ ይህ የመጨረሻ ቀናችን መሆኑን ሁላችንም እያሰብን ነበር:: ፈረንሣይን እስከ መጨረሻው ለቅቀን ወደ አልታወቀ መሬትና ወደ አልተላመድነው ኑሮ መሔዳችን አባብቶን ነበር:: በቅኝ ግዛት ወህኒ ቤት ተወልዶ ከነበረው ወጣት ኮርሲካዊ በስተቀር በከፍላችን ውስጥ ከሚገኙት ዐሥራ አንድ ሰዎች ዐሥሩም ከታወቀው የአራዳ ዓለም የመጡ ነበሩ:: እነዚህ ሁሉ ሰዎች፣ በወቅቱ ከባድነትና ወሳኝነት ልባቸው ተንጠልጥሎ ነበር:: የሲጃራው ጢስ ከከፍሉ ውስጥ እየተነነ ወደ ኮሪደሩ ሲወጣ፣ ዐይኖችህን ለማዳን ከጢሱ ጉምጉምታች መቀመጥ ነበረብህ::

ያሳለፍኩት ኑሮ እንደ ተንቀሣቃሽ ፊልም ከፊት ለፊት ተተረተረ:: ፍቅር



@BOOKALEM

በተሞላበት ቤተሰብ ውስጥ ያሳለፍኩት የልጅነት ዘመኔ፣ ትምህርቴ፣ አስተዳደጌ፣ ጨዋነቴ፣ በመስኩ ላይ የነበሩት አበቦች፣ የፍራፍሬዎቹ ጣዕም፣ የአትክልት ቦታችን በብዛት የሚያፈራቸው ኮኮችና ፍራፍሬዎች፣ በየፀደዩ ከመዝጊያችን ፊት ለፊት የሚፈካው ባለሽቱ መዓዛ አበባ፣ የቤታችን ውጭና ልዩ በሆነው የቤተሰቦቼ እንቅስቃሴ የተሞላው የቤታችን ውስጥ፣ ይህ ሁሉ በአእምሮየ ተመዝግቧል:: ድምፅ ያለው አንድ ተንቀሳቃሽ ፊልም ነበር:: በጣም የምትወደኝን የምስኪኗ እናቴን ድምፅ ሰማሁ:: ከዚያም ሁልጊዜ የሚደባብሰኝንና የሚሳሳልኝን የአባቴን:: ከአትክልቱ ቦታ ወጥቼ እንድንጫወት የሚጠራኝ የከላራን (የአባቴ አዳኝ ውሻ ነበረች) ጩኸት፣ በደስታ ቀኖች ያጫወትኳቸው ጉብሎችና ልጃገረዶች:: ይህን ተንቀሳቃሽ ፊልም ለማየት አልጠየቅኩም ነበር:: ወደ ማይታወቀው ቦታ ለመሻገር በዚህ የቆይታ ምሽት እንዳለሁ፣ ሕሊናዬ በሰመመን መልክ ያመጣልኝ የሆነ አስማታዊ የፋኖስ ብልጭታ ነበር::

ዕድሜዬ ሐያ ስድስት ዓመት ሆኖ የተሟላ ጤንነት ነበረኝ:: በሆዴ ውስጥ የራሴን አምስት ሺ ስድስት መቶ ፍራንክና የጋልጋኒን ደግሞ ሐያ አምስት ሺ ፍራንክ ይገኛሉ:: ከእኔ ቀጥሎ ያለው ዴጋም ዐሥር ሺ ነበረው:: ጋልጋኒ ገንዘቡን እዚህ ተከላክሎ መያዝ ካልቻለ፣ በጀልባው ላይና ጊያና ውስጥ የበለጠ ችግር ስለሚሆን፣ የዐርባ ሺህ ፍራንክ ኃላፊነት በእኔ ላይ ወድቋል ለማለት እችላለሁ:: የገንዘብ መደበቂያውን ቱቦ ለመጠየቅ ያልመጣውም በዚሁ ምክንያት ነው:: ስለዚህ የእርሱንም ሆነ የእኔን በግዴታ የማኖር ኃላፊነት ከእኔው ራስ አይወርድም::

እርሱም ገንዘቡ ነውና ጥቅሙን ማግኘት አለበት:: በእርግጥ እኔም እንደዚሁ በተዘዋዋሪ መንገድ ጥቅም ቢኖረኝም ቅሉ፣ እርሱም ጥቅሙን እንዲያገኝ ማድረግ አለብኝ:: ዐርባ ሺ ፍራንክ ብዙ ነው:: ዘበኞችን፣ ያመለጡ እሥረኞችንና ለእሥረኞች ማምለጥ ተባባሪ የሚሆኑትን ሁሉ ለመደለል መንገዱን ያቃልለዋል::

እንደ ደረስኩ ወዲያውኑ ከዴጋና ጋልጋኒ ጋር ማምለጥ ነው:: የማተኩረው በዚሁ ይሆናል፣ በቃ በዚሁ ብቻ:: ጨቤየን ስነካት ቀዝቃዛው ብረት ተሰማኝና ደስ አለኝ:: እንደዚህ የመሰለች አንዷት ልብ የምትሞላ መሣሪያ በመያዜ በራስ መተማመን አደረብኝ:: ጠቃሚነቷን ያረጋገጥኩት ቀደም ሲል ከዐረቦቹ ጋር በፈጠርኩት ግጭት ነበር::

በግምት ከጧቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ላይ ከክፍላችን በስተውጭ በኩል በትልቁ ምልክቶች የተጻፉባቸው ጥቅጥቅ ያሉ ዐሥራ አንድ ጥቅሎች ተደርድረው አየሁ:: ከእነርሱ አንደኛው፣ «ሲ-ፒየሮ ፣ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት፣ ቁመቱ አምስት ጫማ ከዘጠኝ ኢንች፣ የልብስ መጠን ዐርባ ሁለት፣ የጫማው ቁጥር ስምንት፣ የመለያ ቁጥር 10» የሚል ይነበብበታል::



@BOOKALEM

ያ ሴ ፒየሮ፣ ፓሪስ ውስጥ በነፍስ ግድያ ተወንጅሎ ሐያ ዓመት ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ከቦርዶው ቀበሌ የመጣው ፒየር ለፉ ነበረ። ጥሩ፣ ጎበዝ፣ ቀጥተኛና የአራዳው ዓለም የሚመካበት መሆኑን በሚገባ ዐውቅ ነበር።

ፍርድ ቤቱን፣ ተችዎቹን፣ ዓቃቤ ሕጉንና የቀሩትንም ምሥል በሙሉ እንዲያሳየኝ አእምሮየን ጠየቅኩት። ወዲያውኑ ተቃወመኝ። ያገኘሁት መልስ ድፍን ያለና የማይታይ ነበር። ነገሩ ገባኝ። ባለፈው ወቅት በቦሊየ ጥበቃ ጣቢያ ብቻየን ሆኜ በጥሞና ሳሰላስላቸው ያለፉት ትዝታዎቼ ድቅን ይሉብኝ ነበር። እንዲመጡልኝ ካስፈለገ ብቻየን መሆን አለብኝ። ሙሉ በሙሉ ብቻየን። ይህንንም ማወቅ ሸከም ማቃለል ነበር። የሚጠብቀኝ የማኅበረሰብ ኑሮ አዲስ ፍላጎቶችን፣ አዲስ ሐሳቦችንና አዲስ ዕቅዶችን እንደሚፈጥር ተገንዝቤያለሁ።

ፒየሮ ለፉ ወደ ቋሚ ፍርግርፉ ቀረብ አለና፣ «እንዴት ይዞሃል ፓፒ?» ሲል ጠየቀኝ።

«አንተስ እንዴት ነህ?»

«ታውቃለህ፣ እኔ ሁልጊዜ ምኞቴ ወደ አሜሪካ መሔድ ነው። ግን ቁማርተኛ በመሆኔ ለጉዞ የሚሆነኝ በቂ ገንዘብ ለማጠራቀም ፍጹም አልሆነልኝም። ፖሊሶቹ ጉዞውን ያለክፍያ ሊያበረክቱልኝ ተስማምተዋል። ነገሩ ጥሩ መሆኑ መቼም አጠያያቂ አይሆንም፣ ፓፒዮ፣ እ?» አለ።

የሚናገረው ፍጹም ወደ ኋላ ሳይል በራሱ በሚገባ ተማምኖ ነበር።

«ይህ ወደ አሜሪካ የነጻ ጉዞ ያለጥርጥር ጥቅም አለው። ብፈረንሣይ የግዞት ወህኒ ቤት ውስጥ ዐሥራ አምስት ዓመት ከማጥፋት ይልቅ ወደቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መሔድን እመርጣለሁ።»

«ሁኔታዎች እስኪስተካከሉ ድረስ መታገል የሚኖርብን ይመስለኛል። እንደ ገመትኩት ከሆነ ካንተ ጋር እስማማለሁ። ተመልከት ፒየሮ፣ ያ የአንተ ምልክት ነው» አልኩት።

ሊያነብበው ጎንበስ አለና፣ «ይህን ልብስ ለመልበስ ጊዜ መውሰድ አልቻልኩም። እነዚያ ቀይ ጥብጣቦች ድንቆች አይደሉም? ፓኮውን ከኋቼ አሁኑኑ መልበስ እፈልጋለሁ። ማንም ሰው ፍጹም አይናገረኝም። ኑሮ ዞሮ የራሴው ናቸው» አለ።

«ይቅርብህ። እስኪነገረን ድረስ ቆይ። አሁን ረብሻ የምንፈጥርበት ወቅት አይደለም ፒየሮ። ሰላም እፈልጋለሁ» ስለው ገባውና ወደ ኋላ ገለል አለ።

ዴጋ ወደ እኔ ተመለከተና፣ «ወጣቱ ባልደረባዬ፣ እንግዲህ የመጨረሻው ሌሊታችን ነው። ነገ ውቢቱን ሀገራችንን እንለቃለን» አለ።



@BOOKALEM

«የእኛ ውብ ሀገር ውብ የሆነ ሕግ የላትም ዴጋ:: ጥፋተኞችን በተሻለ ሁኔታ የሚይዙ ምናልባት ግን፣ በጣም ውብ ያልሆኑ ሀገሮችን አናውቅ ይሆናል::» የቱን ያህል ወደ እውነቱ እንደተቀራረብኩ አላወቅኩም:: ወደፊት የሚሆነው ያስተምረኛል::

## ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መለቀቅ

የዐሥራ ሁለት ሰዓት ደወል ሲሰማ፣ አንዳንድ እሥረኞች ቡና አመጡልን:: ከዚያም አራት ዘበኞች መጡ:: አሁንም ሽጉጣቸውን በሽንጣቸው ላይ አንደ ገነደሩ ነጫጭ ለብሰዋል:: የብረት ቅብ ያላቸው አዝራሮቻቸው ያንጸባርቃሉ:: ከእነርሱ ወስጥ አንድ በግራ ክንዱ ክሣድ ላይ የv ምልክት ያላቸው ሦስት የወርቅ ጥብጣቦች ነበሩበት፣ ይሁንና በትከሻው ላይ ምንም ነገር የለውም::

«ተጓገሮች፣ ጣምራ እየሆናችሁ ወደ መተላለፊያው ሒዱ፣ እያንዳንዳችሁ አንድ ጥቅል ታገኛላችሁ:: - ስማችሁ በላዩ ላይ ተጽፎበታል:: አንሡና ከፊት ለፊታችሁ ይዛችሁ በኮሪዶሩ ትይዩ ቁሙ::»

ይህን ካደረግን በኋላ፣ «አውልቁ፣ ልብሶቻችሁን ሸከፉና ጃኬቶቻችሁ ውስጥ አስገብታችሁ በእጅጌዎቹ እሰሯቸው:: ጥሩ:: አንተ እዚያ ያለኸው፣ ጥቅሎቹን አንሣና ወደ ክፍል አስገባቸው:: አሁን አዲሶቹን ልብሶቻችሁን ልበሱ:: የውስጥ ሱሪና ካናቴራችሁን፣ ባለጥብጣብ ሱሪያችሁን፣ ጫማውንና ካልሲውን:: ሁሉም ሰው ተዘጋጀ?»

«አዎ ጌታዬ!»

«ጥሩ:: ዝናም ወይም ቅዝቃዜ የመጣ እንደሆነ.ሹራቦቻችሁን ከጥቅሉ ውስጥ አውጥታችሁ ያዙ:: ጥቅሎቻችሁን በግራ ትከሻችሁ! - በሁለት መስመር ተሰለፉና ተከተሉኝ::» የጥብጣብ መለከት ያለው ሰው ከፊት፣ ከጎንና ጎን አንዳንድ ዘበኛ፣ አራተኛ ከኋላ ተከትሎን፣ ትንሿ የሰልፈኛ ቡድን ወደ ግቢው ውስጥ አመራች:: ሁለት ሰዓት ሳይሞላ ስምንት መቶ እሥረኞች አሠልፈው ነበር:: ከዚያም ከእነርሱ ውስጥ እኔና ዴጋ፣ አምልጠው የተያዙት ሦስቱ፣ ማለት ጁሎ፣ ለጊቱና ሳንቲኒ የምንገኝበትን የዐርባ ሰዎች ቡድን ጠሩና ለይተው አወጡን:: በዐሥር ረድፍ ተሰልፈን ቆምን:: በእያንዳንዱ ረድፍ ጎን አንዳንድ ዘበኛ ቆመ:: እግር ብረት የለም፣ ካቴና የለም:: ከፊት ለፊታችን ሦስት ያርድ ርቀት ላይ ዐሥር ፖሊሶች ነበሩ:: ጠመንጃ እንደ ወደሩ ከፊት ለፊታችን በመሆንና አንዱ ፖሊስ ሌላውን በቀበቶው እየሳበ በመምራት መንገዳቸውን የቀጠሉት በኋሊዮሽ እርምጃ ነበር::

የአምባው ግዙፍ መዝጊያዎች ተከፈቱና ሰልፉ በዝግታ ወደፊት ይጓዝ ጀመር:: ከግቢው እንደወጣን፣ ከኮንቮዩ ጎን በመሆን እስከሚቀጥለው መዳረሻችን ለማጀብ



@BOOKALEM

አውቶማቲክ ጠመንጃ የወደሩ ፖሊሶች ተጨመሩ። እግረ መንገዳቸውንም በእኛ ጉዞ ተደንቀው የተሰበሰቡትን ሰዎች ወደኋላ እንዲያፈገፍጉ ለማድረግ ነበር። ግማሽ ጉዞ እንደ ሔድን አንድ ለስላሳ ፉጨት ሰማሁ። ቀና ስል፣ ኒኒታና አንቷን ዲ የተባለ አንድ የቅርብ ጓደኛዬ በአንድ ሕንፃ መስኮት ብቅ ብሎ አየሁት። የዴጋ ሚስት ፓውላና ጓደኛው አንቷን ጂሊቲ በሕንፃው ሌላ መስኮት በኩል ብቅ ብለው ነበር። ዴጋም አይቷቸዋል። በመስኮቶቹ ላይ ዐይናችንን እንደ ተከልን እስከ መጨረሻው ድረስ በመራመድ አለፍናቸው። ከዚያ ወዲያ ሚስቴንም ሆነ የማርሴይ ወደብ በቦምብ ስትደበደብ የሞተውን ወዳጄን አንቷንን አይቻቸው አላውቅም። ማንም ሰው አይናገርም። ፀጥታው ሙሉ በሙሉ ነበር። ይህን አሳዛኝ ወቅት ሕዝቡ፣ እሥረኞቹም ሆኑ ዘበኞቹና ፖሊሶቹም ጭምር በአርምሞ ይመለከቱ ነበር። እነዚህ ስምንት መቶ ሰዎች ከተላመዱት ኑሮ ለመጨረሻው ተለይተው መሔዳቸውን ማንኛውም ሰው ተረድቶታል።

ወደ መርከቡ ተሣፈርን። የመጀመሪያዎቹ ዐርባ ሰዎች በመርከቡ ምድር ቤት ዙሪያውን በብረት ምሰሶ ከተከበበ ወጥመድ ውስጥ ተወስደን ታሠርን። «ክፍል ቁጥር ፣ በልዩ ደረጃ የሚገኙ 40 ሰዎች፣ ጥብቅ ቁጥጥር» የሚል፣ አንድ ጽሑፍ ተሰቅሏል። ለእያንዳንዳችን ተንጠልጣይ አልጋ ታደለን። ለእርሱ መስቀያ የሚሆኑ ቀለበቶች በብዛት ተንጠልጥለዋል።

አንድ ሰው ድንገት ጎንተል አደረገኝ። ጁሎ ነበር። በዚህ ሁኔታ ከዐሥር ዓመት በፊት ተጉዞ ስለነበር ገመዶቹን ያውቃቸዋል።

«ፈጠን በል፣ ወደዚህ ና። ጓዝህን፣ ተንጠልጣይ አልጋህን ከምትዘረጋበት ጋንች ጋር አብረህ አስቀምጠው። ከሁለቱ መካፈቻዎች አቅራቢያ እዚህ ብንሆን ይሻላል። አሁን ተዘግተዋል። ወደ ባሕሩ ስንዘልቅ ግን ይከፈታሉ። ከማንኛውም ቦታ የተሻለ ቀዝቃዛ አየር እናገኛለን» አለ።

ከዴጋ ጋር አስተዋወቅኩት። በማውራት ላይ እንዳለን ከመካከላችን አንድ ሰው ጣልቃ ገባ። ጁሎ ሰውየውን ለመምታት ክንዱን መከተ። «ወደቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ከነነፍስህ ለመድረስ ከፈለግህ ወደዚያ ራቅ ብትል ይሻልሃል። ገባህ?

«አዎ!» አለ ያ ሰው።

«ለምን እንደሆነ ዐውቀሃል?»

«አዎ!»

«እሺ፣ በል ጥፋ ከዚህ» ብሎት ሰውየው ገለል አለ።

በዚህ የኃይል ትዕይንት ዴጋ ተደስቶ ነበር። ‹ከእናንተ ከሁለታችሁ ጋር እንቅልፍ መተኛት እችላለሁ» አለ።



@BOOKALEM

«ከእኛ ጋር በመሆንህ በባሕር ትይዩ መስኮቱ በተከፈተ አንድ ቪላ ቤት ውስጥ ከመኖር የተሻለ ሰላም አለህ፡፡»

ዐሥራ ስምንት ቀናት በወሰደው ጉዞ ውስጥ ቁምነገር ነው ተብሎ የሚገለጽ አንድ ድርጊት ብቻ ነበር፡፡ አንድ ሌሊት አንድ አጥንት የሚሰብር ኡኡታ አባነነን፡፡ በትክሻው መካከል ጩቤ የሰጠመበት አንድ ሰው ሞቶ ተገኘ፡፡ ያ የሚያስፈራው መሣሪያ ርዝመት ከስምንት ኢንች የበለጠ ስለነበር፣ ተንጠልጣይ አልጋውን ዘልቆ ነበር፡፡

በድንገት ሐያ አምስት ወይም ሠላሳ ዘበኞች ጠመንጃቸውን ወደ እኛ ደግነው፣ «ሁላችሁም ልብሳችሁን አውልቁ፣ ፍጥነት ይኑራችሁ!» ብለው ጮሁብን፡፡

ሁላችንም አወለቅን፡፡ የምንፈተሽ መሆኑን ገምቻለሁ፡፡ ጩቤየን በቀኝ ባዶ እግሬ ሥር ረገጥኩትና ክብደቴን ወደ ግራዬ አጋደልኩ፡፡ ስለቱ ወደ ውስጥ ይቆርጠኛል፡፡ ግን መሣሪያው በሚገባ ተደብቆ ነበር፡፡ አራት ዘበኞች ወደ ወጥመዱ ክፍል ገቡና ልብሶቻችንና ጫማዎቻችንን ይበረብሩ ጀመር፡፡ ከመግባታቸው በፊት መሣሪያዎቻቸውን ከውጭ በኩል ትተው የወጥመዱን መዝጊያ ከኋላቸው ሸጎሩት፡፡ ይሁንና ከወጥመዱ ክፍል ውጭ የቀሩት ዘበኞች ጠመንጃዎቻቸውን በእኛ ላይ ወድረዋል፡፡ «በመጀመሪያ እንቀሳቀሳለሁ የሚለው ሰው ሟች ነው» አለ ዋናው አዛዥ፡፡

የፍተሻው ውጤት ሦስት ጩቤዎች፣ ሁለት የተሣሉ ምስማሮች፣ አንድ የቆርኪ መከፈቻና አንድ የገንዘብ መደበቂያ የወርቅ ቱቦ ኣስገኘ፡፡ ስድስት ሰዎች እንደዚያው ራቁታቸውን እንዳሉ ወደ መርከቡ ወለል ተጠሩ፡. የካንቮዩ መሪ አዛዥ ባሮ ከሁለት ዶክተሮችና የመርከቡ ካፒቴን ጋር ደረሰ፡፡ ዘበኞቹ ከወጥመዱ ክፍል እንደወጡ ማንኛውም ሰው ትእዛዝ ሳይጠብቅ እንደገና ለበሰ፡፡ እኔም ጩቤየን አዳንኩ፡፡

ዘበኞቹ ከመርከቡ ወለል በስተኋላ አፈገፈጉ፡፡ አዛዡ ባሮ ከመካከል፣ ሌሎቹ ከደረጃዎቹ አጠገብ ነበሩ፡፡ ከእነርሱ ትይዩ በቀጥታ መስመር ራቁታቸውን የሆኑት ስድስት ሰዎች በተጠንቀቅ ቆመዋል፡፡ ሲፈትሽ የነበረ አንድ ዘበኛ፣ «የዚህ ዕቃ ባለቤት እርሱ ነው» አለ፡፡

«ትክክል ነው፡፡ የራሴ ነው፡፡»

«መልካም» አለና አዛዡ ባሮ በማከታተል፣ «በሞተሩ ክፍል ውስጥ እንደሆነ ጉዞውን ይፈጽማል» አለ፡፡

የመሣሪያዎቹ ባለቤቶች፣ የምስማሮቹ፣ የቆርኪ መከፈቻውና የጩቤዎቹ ታወቁና እያንዳንዳቸው ባለቤትነታቸውን አመኑ፡፡ ስለሆነም ራቁታቸውን እንደሆኑ በዘበኞች ታጅበው በደረጃው ወደ ላይ ወጡ፡፡ ሁለት ነገሮች ቀሩ አንድ ጩቤና ከወርቅ የተሠራች የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ፡፡ ግን ያለው አንድ ሰው ብቻ ነበር፡፡ ዕድሜው በግምት ሐያ አራት ዓመት የሚሆነው ሰውነቱ በሚገባ የተገነባ፣ ቁመቱ ስድስት ጫማ



@BOOKALEM

የሆነና ሰማያዊ ዐይኖችና የስፖርተኛ አካል ያለው አንድ ወጣት ነበር።

«ይህ የአንተ ነው። አይደለም እንዴ?» አለ ዘበኛው ከወርቅ ወደ ተሰራችው የገንዘብ መደበቂያ ቱቦ እያመለከተ።

«አዎ፣ የራሴ ነው።»

«በውስጧ ምን ያህል አለባት?» ሲል አዛዡ ባሮ ከወለሉ ላይ እያነሣት ጠየቀው።

«ሦስት መቶ የእንግሊዝ ፓውንድ፣ ሁለት መቶ ዶላርና ሁለት ባለ አምስት ካራት አልማዞች።»

«ደህና፣ እስኪ እንመልከተው።» ከፈታት። እኛ ምንም ነገር አላየንም። ግን፣ «ትክክል ነው። ማነው ስምህ?» ሲል ሰማነው።

«ሳልቨዲያ ሮሚዎ»

«ኢጣሊያዊ ነህ?»

«አዎ ጌታዬ»

«ለገንዘብ መደበቂያው የወርቅ ቱቦ አትቀጣም፣ ለጩቤው ግን አዎ።»

«ይቅርታ አድርግልኝ ጌታዬ፣ ጩቤው ግን የእኔ አይደለም።»

«እንደዚህ ብለህ አትመልስልኝ። ስማ፣ ያገኘሁት በጫማህ ውስጥ ነው» አለ ዘበኛው።

«እደግመዋለሁ፣ ጩቤው የእኔ አይደለም።»

«ታዲያ እኔ ውሸታም ነኝ?»

«አልወጣኝም፣ ተሳስተሃል።»

«መልካም፣ ታዲያ የማን ጩቤ ነው?»

«የእኔ አይደለም፣ የማውቀው ይህንኑ ብቻ ነው።»

«የተጣደ ድስት ውስጥ መቀቀል ካልፈለግህ የጩቤው ባለቤት ማን እንደሆነ ንገረን።»

«አላውቅም።»

«ልታሾፍብኝ አትሞክር። በጫማህ ውስጥ አንድ ጩቤ አግኝተን ባለቤቱ ማን እንደሆነ አታውቅም? ሞኝ ነው ብለህ ታስባለህ? ወይ የአንተ ነው አለበለዚያም እዚያ ያስቀመጠው ማን እንደሆነ ታውቃለህ።»

«የእኔ አይደለም፣ የማን እንደሆነ ለመናገር ደግሞ የእኔ ጉዳይ አይደለም። አዋሻኪ አይደለሁም። ከእንደ እናንተ ዓይነት ጥርቃሚዎች አንዱ መሰልኩህ እንዴ?»

«ዘበኛው በካቴና እሰረው። ለዚህ ብልግናህ ዋጋህን ታገኛለህ፣»

ሁለቱ መኮንኖች ቃላት ተለዋወጡ። የመርከቡ ካፒቴን ለአንድ የበታች



@BOOKALEM

መኮንን አንድ ትዕዛዝ ሰጠና ከዚያ ሔደ::

ከትንሽ ደቂቃዎች በኋላ፣ የጨው ውሃ የተሞላበት አንድ የእንጨት ባልዲና ውፍረቱ ከንድ የሚያክል ገመድ የያዘ አንድ ግዙፍ መርከበኛ ብቅ አለ:: ሮሚዮ እስከ መጨረሻው ድረስ በማጎንበስ ተንበርክኮ ታሰሯል:: መርከበኛው ገመዱን ባልዲው ውስጥ ነከረና ያለ የሌለ ኃይሉን በመጠቀም ምስኪኑን ሰው ከመቀመጫው እስከ ጀርባው ዝግ እያለ አግድም ይገርፈው ጀመር:: ከከንፈሩ አንድ ድምፅ አይወጣም፣ ግን ደሙ በመቀመጫው መውረድ ጀመረ:: እንደ መቃብር ቦታ ረጭ ባለው ፀጥታ ውስጥ አንዲት የተቃውሞ ጩኸት ከእኛ ክፍል በኩል «እናንተ ውሻዎች!» ስትል አስተጋባች::

እኛም ለሰበብ እንዲመቸን የፈለግነው ይህንኑ ስለነበር፣ «ነፍሰ ገዳዮች!» የውሻ ልጆች! ብስብሶች!» አልናቸው:: እነርሱ ዛቻቸውን በጨመሩ መጠን እኛም ጩኸታችንን ጨመርን:: ከዚያም አዛገፉ ድንገት እንደዚህ ሲል ጮኸ::

«የሞተሩን እንፋሎት ልቀቁባቸው!» ሽከርከሪቶቹ ተከፍተው የእንፋሎቱ ግፊት እየፈነዳ በደረቶቻችን ላይ ሲያርፍ ኃይሉ በወለሉ ላይ ይወረውረን ጀመር:: ተሸበርን:: የተቀቀሉት ሰዎች መጮህ አልቻሉም:: የቆየው ከአንድ ደቂቃ ያነሰ ነበር፣ ግን ማንኛውም ሰው ድንጋጤ ዋጠው::

«እናንተ ችግር ፈጣሪዎች፣ የሚገባችሁን እንዳገኛችሁ ተሰፋ አለኝ:: ምንም ነገር ይሁን እንፋሎቱን እከፍተዋለሁ:: ግልጽ ነው? አሁን ተነሡ!»

ከባድ ቃጠሎ የደረሰባቸው ሦስት ሰዎች ወደ ሕክምና ክፍል ተወሰዱ:: ሲገርፉት የነበረውንም ልጅ ወደ እኛ ክፍል መለሱት:: ከስድስት ዓመታት በኋላ ከእኔ ጋር በማምለጥ ላይ እንዳለ ለመሞት በቃ::

በዐሥራ ስምንት ቀን ውስጥ፣ ስለ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት መረጃዎች ለመቅሰም ሰፊ ጊዜ አግኝተን ነበር:: ጁሎ ከተነበየው ምንም ነገር የተለወጠ አልነበረም:: እንዲያውም በተሻለ ሁኔታ አብራርቶታል::

ለምሳሌ፣ ከባሕር በግምት ሰባ አምስት ማይል ርቀት ላይ ማሮኒ ከተባለ አንድ ወንዝ ቅዱስ ላውረን ደ ማሮኒ የተባለው መንደር እንደሚገኝ ገልጾልናል:: «ጠባይ ማረሚያው የሚገኘው እዚሁ መንደር ውስጥ ነው:: የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤቶች ዋና መሥሪያ ቤት ነው:: በየደረጃችን የሚከፋፍሉንም ከዚያ ቦታ ነው:: ልማደኞች እሥረኞች በቀጥታ የሚሔዱት ከዚያ ዘጠና አምስት ማይል ርቀ ከሚገኝ ቅዱስ ዮሐንስ ከተባለ ጠባይ ማረሚያ ነው:: የቀሩት በሦስት ቡድን ይከፈላሉ:: በጣም አደገኛ የሆኑት ወዲያው እንደ ደረስን ይጠራሉ:: ወደ ደሳሊዩ ደሴቶች እስኪዛወሩ ድረስ ሥነ ሥርዓት ክፍል ውስጥ ተቀምጠው ይጠባበቃሉ:: የቅጣታቸውን ዘመን እስኪጨርሱ የሚታሠሩት እዚያው ነው:: ደሴቶቹ ከቅዱስ ላውረን ሦስት መቶ ማይልና ከካየን ደግሞ ስድሳ



@BOOKALEM

ማይል ርቀት ላይ ነበሩ:: እሥረኞች በብዛት ወደ ዲያብሎስ ደሴት አይሔዱም፣ እዚያ የሚሔዱት የፖለቲካ እሥረኞች ናቸው::

«ሁለተኛው የአደገኛ እሥረኞች ቡድን የአትክልት ቦታዎችና፣ የእርሻ ሥራዎች ላይ ለመመደብ በቅዱስ ላውረን ይቆያሉ፣ አስፈላጊም ከሆነ በጣም መጥፎ ወደሆኑት ፎሬስትሴር፣ ሻርቢን፣ ካስኬድ፣ ክሪክ ሩዢና «ዐርባ ሁለት ኪሎ ሜትር» የሞት ካምፕ፣ ተብለው ወደ ሚጠሩ ሠፈሮች ይላካሉ::

«ከዚያም የተለመዱ ክፍልፍሎች አሉ:: የሚያገለግሉት በአስተዳደሩ ውስጥ ሲሆን፣ በኩሽና ቤቶች፣ መንደሩን ወይም ካምፑን በማጽዳት፣ ወይም እንደ አናጢነት፣ ቀለም ቀቢነት፣ ብረታ ብረት ሠራተኛነት፣ የኤሌክትሪክ ሠራተኛነት፣ ፍራሽና፣ ልብስ ሰፊነት፣ ልብስ አጣቢነት ወዘተ . . . ይሠራሉ::

«ለማንኛውም ዕውነቱ የሚታወቀው እዚያው በምንደርስበት ሰዓት ነው:: ከተጠራችሁና ወደ አንድ ክፍል ከተወሰዳችሁ፣ ወደ ደሴቶቹ ሔዳችሁ ልትታሠሩ ነው ማለት ነው:: ይህም ከሆነ ለማምለጥ ያላችሁን ምኞት ሙሉ በሙሉ አርግፍ አድርጋችሁ መተው ይኖርባችኋል ማለት ነው:: ከዚህ ለመዳን ብቸኛው መንገድ በፍጥነት ጉልበትህን ወይም ሆድህን ወግተህ ስትቆስል ነው፣ ከዚያም ወደ ሆስፒታል ይልኩሃል:: ከዚያ ማምለጥ ትችላለህ:: ግን የፈለገው ነገር ቢሆን ወደ ደሴቶቹ እንዳትሔድ:: ሌላው ተስፋ ደግሞ ወደ ደሴቶቹ የሚጓዘው ጀልባ ለመነሣት ካልቻኮለ፣ በሕክምና ክፍል ለሚሠራ አንድ የወህኒ ቤት ጤና ረዳት ገንዘብ ትሰጥና አንድ የተርፔንታይን መርፌ ይወጋሃል:: ወይም በሽንት የተነከረ የጸጉር ዘለላ ከቆዳህ ወስጥ እንዲከትልህና አካላትህን በቁስል እንዲነፈርቅ ማስደረግ ነው፣ ወይም ትንሽ ክብረ ሰማይ በአፍህ እንድትስብ ይሰጥህና ከዚያም ትኩሳትህ አንድ መቶ አራት ዲግሪ ሆኗል ብሎ ለዶክተሩ ይነግርልሃል:: እዚህ በምትቆይባቸው ጥቂት ቀናት ውስጥ እንደ ምንም ብለህ ሆስፒታል ለመግባት ተጣጣር::

«እንድትሔድ ካልተጠራህና፣ በዚህ ካምፕ ምሽግ ወደ ኋላ ከቀረህ፣ አንድ ነገር ለማድረግ ጊዜ ይኖርሃል:: ያም ቢሆን ግን፣ በካምፑ ውስጥ ሥራ ላለመያዝ ሞክር:: ለአሠሪው ጉቦ ብትሰጠው በመንደሩ ውስጥ የሠገራ ጽዳት ሠራተኛ፣ ወይም መንገድ ጠራጊ፣ አለበለዚያም ቦርጌሶች ከሚያካሒዱት አንድ የእንጨት መሰንጠቂያ ሞተር ቤት ውስጥ መሥራት ትችላለህ:: እግረ መንገድህን ለሥራ በምትመላለስበት ወቅት በመንደሩ ውስጥ ነጻ ወጥተው ከሚኖሩ እሥረኞች ወይም ቻይናውያን ጋር ለመገናኘት ዕድሉ ይኖርሃል፣ ስለሆነም የምታመልጥበትን ዘዴ ለማመቻቸት ዝግጅት ሊጀምሩልህ ይችላሉ:: በመንደሩ አካባቢ ከሚገኙት ካምፖች እንዳትጠጋ:: እዚያ ማንኛውም ሰው ቶሎ ይሞታል:: ማንም ሰው ሦስት ወር የማይቆይባቸው ካምፖች አሉ:: በቀን ሩብ



@BOOKALEM

ቀላድ ስፋት ያለው እንጨት በጫካው መካከል ያስቆርጡሃል፡፡»

በመላው ጉዟችን ውስጥ ጁሎ እነዚህን የመሳሰሉ ውድ መረጃዎች ሲያስከመኩመን ቆየ፡፡ ራሱም ተዘጋጅቶ ነበር፡፡ ተይዞ የተመለሰ እምላጭ እንደሚሆኑ መጠን፣ በቀጥታ ወደ ጨለማ ግንብ እንደሚሔድ ዐውቆታል፡፡ እንደዚሁም በጣም ትንሽ ሆና ኃይለኛ ስለት ያላትና ከማነሷም ብዛት በገንዘብ መደበቂያ ቀበቶ ውስጥ ያስቀመጣት እንዲት ሴንጢ ነበረችው፡፡ እንደ ወረድን ጉልበቱን ለመቁረጥ አቅዷል፡፡ ከዚያም ጀልባውን በመልቀቅ ላይ እንዳለ በሰው ሁሉ ፊት ከመረማመጃው ላይ ሲወድቅ ነበር፡፡ ከመሸጋገሪያው ድልድይ በቀጥታ ወደ ሆስፒታል እንደሚወስዱት ተስፋ አድርጓል፡፡ እንዳለውም ሆኖለት ነበር፡፡

## ቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ

አንዳንድ ዘበኞች በዕረፍት ላይ ስለነበሩ ልብሶቻቸውን ለመቀየር ቻሉ፡፡ በመለዮአቸው ፋንታ የቅኝ ግዛት ኬፓቸውንና ነጫጭ ዩኒፎርም ለብሰው ተመለሱ፡፡ «ወደያው መቃረባችን ነው» አለ ጁሎ፡፡ የሞተር ማናፈሻውን ስለዘጉት፣ ሙቀቱ በጣም ከፍተኛ ነበረ፡፡ በዚያው ውስጥ ጫካ ለማየት ቻልን፡፡ እንግዲህ ማሮኒ ደረስን፡፡ ድንግሉ መሬት በደማቅ አረንጓዴ ተክሎች የተሸፈነ፣ ጭቃማ ውሃ ነበረው፡፡ በመርከቡ ጡሩምባ አሞራዎች ሰለ ተረበሹ ሸሹ፡፡ አሁን የምንሔደው በጣም ዝግ ብለን ስለነበር፣ ረጅም ሆኖ ጥቅጥቅ ያለውን በአረንጓዴ ልምላሜ የተሸፈነ አካባቢ ጥርት አድርገን ለመመልከት ሰፊ ጊዜ አገኘን፡፡ ከዚያም በቆርቆሮ ጣሪያና በእንጨት የተሠሩትን የመጀመሪያዎቹን ቤቶች አየን፡፡ ከመዝጊያዎቻቸው ፊትለፊት ጥቁር ወንዶችና ሴቶች ቆመው መርከቡ ሲያልፍ ይመለከታሉ፡፡ በየጊዜው ሰው አየጫነ በመምጣት ሲቆምና ሲያራግፍ ማየት ለምደዋል፡፡ ለመቆም መቃረባችንን የነገሩን መርከቡ ያምባረቃቸው ሦስት ጡሩምባዎችና የሚፈታቱት ቡሎኖች ቅጭልጭልታ ነበር፡፡ ከዚያም ማንኛውም ድምፅ ጸጥ አለ፡፡ ከጸጥታው መስፈን የተነሣ የአንዲት ዝንብ ከንፎች ሲርገበገቡ እንኳ ለመስማት ይቻል ነበር፡፡

ማንም አይናገርም፡፡ ጁሎ ሱሪውን ከጉልበቱ ላይ ቀደደና ጫፉን ወደ ላይ ጠቀለለው፡፡ ሰውነቱን የሚቆርጠው ወደ መሸጋገሪያ ድልድዩ ሲደርስ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የደም ነጠብጣብ ምልክት እንዳይታይ ይረዳዋል፡፡ ዘበኞቹ መዝጊያውን ከፈቱና በሦስት ረድፍ አሠለፉን፡፡ ዴጋና እኔ፣ ጁሉ ከመካከል እንደሆነ አራተኛው መስመር ላይ ነበርን፡፡ እስከ ድልድዩ ድረስ ወጣን፡፡ ወቅቱ ከሰዓት በኃላ ስምንት ሰዓት ስለነበር፣ እንደእሳት የምትፋጀው ፀሐይ ዐይኔንና የተላጨ ጭንቅላቴን አንጫረረችኝ፡፡ በመርከቡ ወለል ላይ ተሰለፍንና ከዚያም ወደ መሸጋገሪያው ድልድይ አመራን፡፡



@BOOKALEM

የመጀመሪያው ሰው የመሸጋገሪያውን ድልድይ እንደነካ በጠቅላላው ጥድፊያ ሆነ፡፡ ዓዙን እኔ ያገዘኩለትና ጁሎ የጉልበቱን ቆዳዎች በሁለት እጁ ይዞ ጩቤውን ወደ ውስጥ በመሰግሰግ ሦስት ወይም አራት ኢንች ሥጋ ቆርጦ አወጣ፡፡ ከዚያም ጩቤውን አቀበለኝና ጥቅሉን ተሸከመ፡፡ የመሸጋገሪያውን ድልድይ እንደ ረገጥን ቁልቁል ተንከባለለና ወደቀ፡፡ እንሥተው ሲያዩት ተጎድቶ ስለነበረ ሁለት ቃሬዛ ተሸካሚዎች ጠሩ፡፡ የድራማው ጨዋታ ልክ እንደ ታቀደው ተከናውኖ ነበር፡፡

እኛን ለመመልከት ልዩ ልዩ ቀለም ያለው ሕዝብ ተሰብስቧል፡፡ ጥቁሮች፣ ክልሶች፣ ሕንዳውያን፣ ቻይናውያን፣ በዐፅማቸው የቀሩ ነጮች፣ (ምናልባት ነፃ የወጡ እሥረኞች ይሆናሉ) ወደ መሬት ወርደን ከሌሎቹ ጋር ስንሰለፍ እያንዳንዳችንን ይመለከቱናል፡፡ ከዘበኞቹ በስተጀርባ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሲቪሎች፣ የበጋ ቀሚስ የለበሱ ሴቶችና የቅኝ ግዛት ኬፕ የደፉ ልጆች ቆመዋል፡፡ እነርሱም የሚመለከቱት እንደዚሁ አዲሱን መጤ ነበር፡፡ ሁለት መቶ ስንሞላ ወደፊት በሰልፍ እንጓዛለን፡፡ ዐሥር ደቂቃ ያህል እንደ ተጓዝን አንድ ሕንፃ ፊትለፊት ደረስን፡፡ በግንቡ የእንጨት መዝጊያው ላይ «የቅዱስ ላውረን ዱ ማሮኒ ጠባይ ማረሚያ - ለ3000 ሰዎች የተተመነ» የሚል ተጽፎበት ነበር፡፡ በሩ ተከፈተና በዐሥር ረድፍ እንደ ተሰለፍን ገባን፡፡ «አንድ ሁለት፣ አንድ ሁለት፣ ተሰለፍ!» የእኛን መድረስ በዛ ያሉ እስረኞች ይመለከታሉ፡፡ በድንጋይ ላይ ቆመው እየተንጠራሩ ያዩን ነበር፡፡

ከግቢው መካከል ስንደርስ አንድ ዘበኛ፣ «ቁሙ! ጥቅሎቻችሁን ከፊት ለፊታችሁ አስቀምጡ! አንተ እዚያ ያለኸው ባርኔጣዎቹን አስተላልፍ!» ብሎ ጮኸ፡፡ ለእያንዳንዳችን አንድ የሰሌን ባርኔጣ ተሰጠን፡፡ ግሩም ነው እንፈልገዋለን፡፡ ከፀሐዩ ቃጠሎ የተነሣ ሁለት ወይም ሦስት ሰዎች ሕሊናቸውን ስተው ነበር፡፡ የጥብጣብ ማዕረግ ምልክት የለጠፈ አንድ ዘበኛ በእጁ አንድ የስም ዝርዝር ሊስት ይዞ ነበር፡፡ ዴጋና እኔ እርስ በእርሳችን ተያየን፡፡ ጁሎ ምን ተናግሮ እንደነበር ትውስ አለን፡፡ ላ ጊቱን ጠሩና፣ «በዚህ በኩል!» ብለው ሁለት ዘበኞች አጅበው ወሰዱት፡፡ ሳንቲኒን፣ ጅራሰሎንና ሌሎቹንም በዚሁ ዓይነት ወሰዷቸው፡፡

«ጁልስ ፒኛርድ!»

ጁልስ ፒኛርድ ቆስሏል፡፡ ሆስፒታል ውስጥ ነው» ተባለ፡፡

«እሺ፣ አሁን በጥንቃቄ አዳምጡ፡፡ ስማችሁን ስጠራ ጥቅሎቻችሁን በትከሻችሁ እንደያዛችሁ ከሰልፉ በመለየት ወደ ቢጫው ግንብ ፊት ለፊት ሔዳችሁ ትቆማላችሁ፡፡ ቁጥር አንድ ነው» አለ፡፡

እከሌ እከሌ፣ አቤት ወዘተ . . . ዴጋ፣ ካሪየና እኔ ከግንቡ ፊትለፊት ከተሰለፉት መካከል ነበርን፡፡ መዝጊያው ተከፈተና ርዝመቱ ሰባ ሜትር ከሆነ አንድ አዳራሽ ውስጥ



@BOOKALEM

ገባን፡፡ በመካከሉ ሰባት ጫማ ስፋት ያለው መተላለፊያና በግራና በቀኝ በአዳራሹ ርዝመት በተርታ የቆሙ የብረት ምሰሶዎች ነበሩ፡፡ ከአግዳሚዎቹ ወደ ግድግዳዎቹ የሸራ ተንጠልጣይ አልጋዎች ተዘርግተው እያንዳንዱ አልጋ ላይ አንድ ብርድ ልብስ ነበረበት፡፡ ወደ መረጥከው መሔድ ትችላለህ፡፡ ዴጋ ፒየሮ ለፉ፣ ሳንቶሪ፣ ግራንዴና እኔ ተርታውን አከታትለን ያዝንና፣ ወዲያውኑ ጓዛችንን ማሰናዳት ጀመርን፡፡ እስከ አዳራሹ መጨረሻ ሔድኩ፡፡ መታጠቢያ በስተቀኝ፣ መጸዳጃ ቤት በስተግራ አለው፡፡ የቧንቧ ውሃ የለም፡፡ በመስኮቶቹ ቋሚ ፍርግርጎች ጥግ ተለጠፍንና የሚቀጥለውን የእሥረኞች መድረስ እንመለከት ጀመር፡፡ ከጭንቀታችን ተገላግለናል፡፡ ለመታሰር-እንደማንሔድ ግልጽ ሆኖ ነበር፡፡ ምክንያቱም እዚህ አዳራሽ ውስጥ አብረን ሆነናል፡፡ ብንታሠር ኖሮ ጁሎ ነግሮን እንደነበረው ቀደም ብለን ወደ ልዩ ክፍሎች ውስጥ እንገባ ነበር፡፡

በምድር ወገብ ሲመሽም ሆነ ሲነጋ ቅፅበታዊ ነው፡፡ ዓመቱን በሙሉ ከቀን ወደ ሌሊት የምትሸጋገረው በአንድ ጊዜ በተመሳሳይ ወቅት ነው፡፡ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ከመቅፅበት ጨለማ ይሆናል፡፡ ስለሆነም በዐሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል፣ ሁለት ሽማግሌ እሥረኞች ሁለት የጋዝ ፋኖሶች አመጡና በጣራው ከሚገኝ አንድ ሜንጠ ላይ አንጠለጠሉ፡፡ የሚሰጡት ብርሃን በጣም ደብዘዝ ያለ ነበር፡፡ የምሽጉ ሦስት አራተኛ ሙሉ በሙሉ በጨለማ ተዳፈነ፡፡ ሦስት ሰዓት ላይ ማንኛውም ሰው ተኛ፡፡ የጉዞአችን ዜና አለፈና በሙቀት ተዋጥን፡፡ ለመተንፈስ አየር አልነበረም፡፡ ማንኛውም ሰው በካናቴራው ብቻ ቀረ፡፡ እኔ ከዴጋና ፒየሮ ለፉ መካከል ነበርኩ፡፡ ለትንሽ ጊዜ ተንሾካሾክንና ከዚያም እንቅልፍ ወሰደን፡፡

በሚቀጥለው ቀን ለቆጠራ የሰዓት ደወል ሲጮህ ገና ጨለማ ነበር፡፡ ሁሉም ሰው ተነሣና ፊቱን ታጥቦ ልብሱን ለበሰ፡፡ ቡናና አንድ ቁራጭ ዳቦ ተሰጥቶን ነበር፡፡ ከግድግዳው ጋር የተያያዘ አንድ ጣውላ ለመመገቢያ ገበታና ለጓዞቻችን መደርደሪያ አገለገለን፡፡ ሦስት ሰዓት ላይ ሁለት ዘበኞችና ማዕረግ የሌለው ነጭ ልብስ ብቻ የለበሰ አንድ ወጣት እሥረኛ ተያይዘው ገቡ፡፡ ሁለቱ ዘበኞች ኮርሲካውያን ስለነበሩ፣ ከሀገሮቻቸው ሰዎች ጋር በኮርሲካውያን ቋንቋ ይነጋገራሉ፡፡

ይህ በዚህ እንዳለ የሕክምና ክፍሉ የእሥረኛ ጤና ረዳት አዳራሹን መዞር ጀመረ፡፡ እኔ አጠገብ ሲደርስ፣ «እንደምን አለህ ፓፒ? አታስታውሰኝም እንዴ?» አለ፡፡

«አላስታውስህም፡፡»

«ሲየራ ነኝ፡፡ አልጀሪያዊው፡፡ በፓሪስ ዳንቴ ውስጥ ዐውቅሃለሁ፡፡»

«አሃ፣ አዎ፣ አሁን አስታወስኩህ፡፡ ግን የመጣኸው ከ1929 በፊት ነበር፡፡ አሁን 1933 ነው፡፡ እስካሁን እዚሁ ነህ?»

«አዎ፣ ከዚህ ቦታ ለመውጣት እንደዚህ ቀላል አይደለም፡፡ ለምን አምኛል



@BOOKALEM

ብለህ አታመለከትም? እርሱስ እንዴት ነው? ማን ነው?»

«ዴጋ፡፡ የእኔ ጓደኛ ነው፡፡»

«እርሱንም እንዲመረመር እመዘግበዋለሁ፡፡ አንተ ፓፒ ተቀማጥ አለብኝ በል፡፡ አንተ ሽማግሌው ሰው ደግሞ በአስም በሽታ ተለክፌያለሁ በል፡፡ በአምስት ሰዓት አያችኋለሁ፡፡ ላነጋግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡» በጣም እየጮኸ ዙረቱን ቀጠለ፡፡ «እዚህ የታመመ ሰው አለ?» አንድ ሰው ጣቱን ከቀሠረ፣ ወደ እዚያው ሔዶ ሊስት ውስጥ ይመዘግበዋል፡፡ ተመልሶ በእኛ በኩል ሲያልፍ በጣም የገረጀፈና በጸሐይ የበለዘ አንድ ሽማግሌ ዘበኛ አጅቦት ነበር፡፡

«ፓፒዮ፣ የሕክምና ክፍሉ ዘበኛ አለቃየን ባርቲሎኒን ላስተዋውቅህ እፈልጋሁ፡፡ አቶ ባርቲሎኒ፣ ይኸ ሰውና ያ እዚያ ማዶ ያለው፣ ሁኔታቸውን የነገርኩዎት ጓደኞቼ ናቸው፡፡»

«እሺ ሲየራ፣ በጉብኝቱ ወቅት እናመቻችላቸዋለን፡፡ በእኔ ላይ ጣለው፡፡»

በአምስት ሰዓት እኛ ዘንድ መጡ፡፡ ዘጠኝ ነበርን፡፡ በግንቦቹ መካከል ካምፑን አቋረጥንና አንድ የቀይ መስቀል ምልክት ያለበት አዲስ ነጭ ቀለም ከተቀባ ሕንፃ ደረስን፡፡ ወደ ውስጥ ገባንና በግምት ስድሳ የሚሆኑ ሌሎች ሰዎች ከሚገኙበት አንድ ማረፊያ ክፍል ውስጥ ተገኘን፡፡ በእያንዳንዱ ጥግ ዘበኞች ቆመዋል፡፡ ነጥብ የሌለበት ነጭ ሸርጥ ለብሶ ሲየራ ብቅ አለ፡፡ «አንተ፣ አንተና አንተ ወደ ውስጥ ሒዱ» አለ፡፡ የዶክተር መመርመሪያ ከሚመስለው ክፍል ውስጥ ገባን፡፡ ሲየራ ከሦስት ሽማግሌ ሰዎች ጋር በስፓኝ ቋንቋ ተነጋገረ፡፡ ከስፓኞቹ መካከል አንደኛውን ያኔውኑ አስታወስኩት፡፡ ፓሪስ ውስጥ በካፌ ዴ ማድሪድ መጠጥ ቤት ሦስት አርጀንቲናውያን ገድሎ የነበረ ፊርናንዴዝ የሚባል ሰው ነበረ፡፡ ትንሽ ቃላት ተለዋወጡና ወደ ዋናው አዳራሽ ወደሚከፈት አንድ ገላ መታጠቢያ ክፍል ሲየራ ይዞት ገባ፡፡ ከዚያም ወደ እኔ ተመልሶ መጣና፣ ፓፒዮ በጣም ደስ ስላለኝ ልቀፍህ፡፡ ለአንተና ለጓደኛህ አንድ ነገር ማድረግ ችያለሁ፡፡ እናንተ ሁለታችሁም እሥረኞች ናችሁ፡፡ ቆይ፣ ልናገር! አንተ ፓፒ፣ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራትና አንተ ዴጋ ደግሞ አምስት ዓመት ነው፡፡ ትንሽ ገንዘብ አላችሁ?»

«አዎ!»

«እያንዳንዳችሁ አምስት መቶ ፍራንክ ስጡኝና አንተ ፓፒ፣ ነገ ጧት ሆስፒታል እንድትገባ አደርጋለሁ፡፡ አንተ ዴጋ ደግሞ መዝገያ ቆርቁርና፣ አለበለዚያም ከሁለት አንዳችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ፣ ዘበኛውን ጥሩና ዴጋ በአየር ታፍኗል ብላችሁ ጤና ረዳቱን እንዲጠራላችሁ አመልክቱ፡፡ ለሌላው እኔ አስብበታለሁ፡፡ አንድ ነገረ ብቻ እጠይቅሃለሁ ፓፒዮ፡፡ ለማምለጥ ከፈለግክ ቀደም ብለህ አስጠንቅቀኝና እኔ እዚያው እገኛለሁ፡፡ ለእያንዳንዳችሁ አንድ መቶ ፍራንክ በማስከፈል በሆስፒታሉ ውስጥ አንድ



@BOOKALEM

ሳምንት ያቆዩዋችኋል:: ስለዚህ ፈጠን ብላችሁ መንቀሳቀስ ይኖርባችኋል:: ፌርናንዴዝ ከምታጠቢያ ክፍል ወጣና አምስት መቶ ፍራንክ ለሲየራ ሰጠው:: እኔም ወደ ውስጥ ገባሁና ስመለስ አንድ ሺህ ፍራንክ ሳይሆን አንድ ሺህ አምስት መቶ ፍራንክ ሰጠሁት:: ተጨማሪውን አምስት መቶ አልቀበልም አለ:: እኔም አልገፋፋሁትም:: «ገንዘቡ» ለዘበኞቹ ነው:: ለራሴ ምንም ነገር አልፈልግም፣ ጓደኞች ነን:: አይደለንም እንዴ?» አለ::

በሚቀጥለው ቀን ዴጋ ፌርናንዴዝና እኔ ሆስፒታሉ ውስጥ አንድ ሰፊ ክፍል ተገናኘን:: ዴጋ ሆስፒታል የገባው እኩለ ሌሊት ላይ ነበር:: የሕክምና ክፍል ጤና ረዳቱ ስሙ ቻታል የተባለ የሠላሳ አምስት ዓመት ሰው ነበር:: በእኛ በኩል ስላለው ሁኔታ ሲየራ ምስጢሩን በሙሉ አስረድቶታል:: ለዶክተሩ ሲያቀርበን፣ እኔን አሜባ የበጣጠሰኝ በማስመሰል አንድ የሠገራ ምርመራ ውጤት ሊያሳየው ነበር:: በዴጋ በኩልም ዶክተር ከመምጣቱ ዐሥር ደቂቃ ቀደም ብሎ ትንሽ ክብረ ሰማይ አቃጥሎ ፎጣ ጭንቅላቱ ላይ ጣል ባማድረግ ጢሱን ወደ ውስጥ እንዲስበው ነበር:: የፌርናንዴዝ ጉንጮች ቅትት ብለው አብጠዋል:: ያለማቋረጥ ለአንድ ሰዓት ከውጭና ከውስጥ በጣም በመርፌ ስለ ጠቀጠቃቸው፣ ዕብጠቱ ዐይኖቹን ሳይቀር ሸፍኖት ነበር:: ክፍሉ የሚገኘው ከሆስፒታሉ ሁለተኛ ፎቅ ላይ ሲሆን፣ ብዙዎቹ በደም ተቅማጥ የተያዙ፣ ሰባ ያህል ሕሙማን ይገኙበታል:: ጁሎ የት እንዳለ ጤና ረዳቱን ጠየቅኩት:: «ከመንገዱ ባሻገር ካለው ሕንፃ ውስጥ ነው፤ መልዕክት ወደ እርሱ እንዳደርስልህ ትፈልጋለህ?» አለ::

«ኦዎ ፓፒዮና ዴጋ እዚህ ናቸውና በመስኮት በኩል ብቅ ብለህ እንተያይ፣ ብለህ ንገረው::»

ጤና ረዳቱ እንደ ፈለገ መውጣትና መግባት ይችላል:: መዝጊያውን ሲቆረቁር አንድ ዐረብ ከፈተለት:: ዐረቡ እስረኛ ቢሆንም በቁልፍ ያዥነት እያገለገለ ዘበኞቹን ይረዳል:: ከመዝጊያው ጎንና ጎን ጠመንጃዎቻቸውን ከጭኖቻቸው ላይ አጋድመው ሦስት ዘበኞች ተቀምጠዋል:: መስኮቶቹ ቋሚ ብረቶች ስለነበሩ፣ እንዴት አድርገን እንደምንቆርጣቸው ጨንቆኛል:: በእኛና በጁሎ ሕንፃ መካከል በውብ አበቦች ያሸበረቀ አንድ የአትክልት ቦታ ነበር:: ጁሎ «ጎበዞች» ብሎ በቾክ የጻፈባት አንዲት ጠፍጣፋ ድንጋይ በእጁ እንደያዘ በመስኮቱ በኩል ብቅ አለ:: ከአንድ ሰዓት በኋላ ደግሞ ጤና ረዳቱ አንድ ደብዳቤ ከእርሱ አመጣልኝ::

«ወደ እናንተ ክፍል ለመምጣት እየሞከርኩ ነው:: ይህም ካልሠራ እናንተ ወደ እኔ ለመምጣት ሞክሩ:: በከፍላችን ውስጥ ጠላቶች አሉን በሉ:: ታዲያስ፣ ሆስፒታል ገባችሁ? በርቱ፣ በቀላሉ እናታልላቸዋለን::»

በቦሊየ እሥር ቤት ፈንድቶ በነበረው ግጭት አብረን ያሳለፍነው መከራ



@BOOKALEM

በመካከላችን አንድ ከፍተኛ መተሳሰር መሥርቷል:: ጁሎ በእንጨት መዶሻ የተካነ ነበር:: ለዚህም ነበር፣ «ባለ መዶሻው ሰው» የሚል ቅጽል ስም የተሰጠው:: አንዴ ምርጥ የሆኑ ጌጣጌጦች ለትዕይንት በመደብር መስኮት ላይ እንዳሉ አውቶሞቢሉን እያሽከረከረ በጠራራ ፀሐይ ወደ ጌጣጌጡ መደብር ያመራል:: አንድ ግብረ አበሩ መኪና ውስጥ ይቀመጥና ሞተሩን እያሠራ ይጠብቃል:: ከትልቁ መዶሻው ጋረ ጁሎ ይወጣና፣ በአንድ ምት መስኮቱን አንካክቶ ለማፈስ የቻለውን ያህል የጌጣጌጥ ሣጥኖች ጋፍፎ ወደ መኪናው ዘልሎ ይገባና፣ በከፍተኛ ፍጥነት ተፈትልኮ ይበርራል:: በሲሐቨር፣ በቱር፣ በአንገርስና በሊዮን ይህ ድርጊቱ ተሳከቶለት ነበር:: ከዚያም፣ ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ሲሆን፣ በፓሪስ የታወቀ አንድ ጌጣጌጥ መደብር ወስጥ ይገባና አንድ ሚሊዮን ፍራንክ የሚገመት ዋጋ ያላቸው ጌጦች ይዞ ይነጉዳል:: እንዴት ወይም በምን እንደተነቃበት ግን ፍጹም አልነገረኝም:: ሐያ ዓመት ተፈርዶበት ነበር:: በአራተኛው ዓመት መጨረሻ ላይ አመለጠ::

ሆስፒታል ውስጥ ከገባን አሁን አንድ ሳምንት ሆኖን ነበር:: ለሌላው ሳምንት ከፍያ ትላንት አንድ ሺ ፍራንክ ለቻታል ሰጠሁ:: ጓደኛ ለማፍራት ለሁሉም ሰው ትምባሆ እንጋብዛለን:: የማርሴይ ተወላጅ የሆነ ካሮራ የተባለ አንድ የስድሳ ዓመት ሽማግሌ እሥረኛ፣ ከዴጋ ጋር ጓደኝነት አበጇ:: እንደ አማካሪው አድርጎት ነበር:: «ብዙ ገንዘብ ካለህና በመንደሩ የሚገኙ ሰዎች ይህንን ካወቁ፣ (ለፈረንሣይኛ ጋዜጦች ምስጋና ይግባቸውና ማንኛውም ሰው ዜና ያገኝ ስለነበር) ነጻ የወጡት እሥረኞች ለገንዘብ መደበቂያ ቱቦህ ሲሉ ስለሚገድሉህ፣ አመልጣለሁ ብለህ ባትሞክር ይሻላል» እያለ ይመክረው ነበር:: ከካሮራ ጋር የሚያደርገውን ውይይት ዴጋ ለእኔ ደበቀኝ:: ሽማግሌው ሰው ሐያ ዓመት እዚሁ ተቸክሎ ጊዜውን ያጠፋ ከንቱ መሆኑ ግልጽ እስከሆነ ድረስ ዴጋ ማመን እንደማይኖርበት ብነግረውም ሊሰማኝ አልፈለገም:: ሽማግሌው በሚያነበንብለት ወሬ ዴጋ ተሰብኮ ስለነበር፣ ሐሳቡን ለማስለወጥ አስቸጋሪ ወቅት ገጠመኝ::

ጋልጋኒን ወደ እኔ እንዲልክልኝ አንድ ማስታወሻ ለሲየራ ላከሁ:: ብዙ ጊዜ አልወሰደም:: በሚቀጥለው ቀን ጋልጋኒ ከሆስፒታሉ ሌላ ከፍል ውስጥ ገባ:: እንዴት አድርጌ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን መልሼ ልስጠው? ለማምለጥ ዕቅድ ቢኖረው ነው ብሎ እንዲገምት ቻታልን ለማሳመን ለመጨረሻ ጊዜ ጋልጋኒን ማነጋገር እንደፈለግኩ ነገርኩት:: ዘበኞቹ ተረኝነት በሚለዋወጡበት ወቅት ልክ ለስድስት ሰዓት አምስት ጉዳይ ወደ እኔ ሊያመጣውና ሊያገናኘን ያሰበው ያለምንም ከፍያ ነበር:: ጋልጋኒ ስድስት ሰዓት ላይ በመስኮቱ በኩል ብቅ ሲል፣ የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን በቀጥታ እጁ ላይ አስቀመጥኩለት:: እዚያው እንደቆመ አለቀሰ:: ከሁለት ቀን በኋላ ባለ አምስት ሺ ፍራንክ ኖቶች የተጠቀለሉበት አንድ መጽሔትና «አመሰግናለሁ» የምትል አንዲት ቃል



@BOOKALEM

ላከልኝ፡፡

መጽሔቱን ያመጣልኝ ቻታል ገንዘቡን አይቷል፡፡ ምንም ነገር አላለም፣ ግን ትንሽ ላበረከትለት ሞከርኩ፡፡ አልቀበልም አለ፡፡

«ልናመልጥ ፈልገናል፣ እኛ ጋር መምጣት ትፈቅዳለህ?»

«አልፈልግም ፓፒዮ፡፡ ከሌሎች ጋር ተነጋግሬአለሁ፡፡ ጓደኛዬ ነጻ እስኪሆን ድረስ ከአሁን ጀምሮ ለአምስት ወራት ያህል ማምለጥ ልሞክር አልፈልግም፡፡ የእኛ ምርጫ በተጠናከረ ሁኔታ የሚዘጋጅና እርግጠኛ የሆነ ነው፡፡ እናንተ ለምን እንደ ቸኮላችሁ ገብቶኛል፡፡ የሆስፒታል ሕሙማኖች ናችሁ፡፡ ሆኖም እነዚህ ቋሚ ፍርግርግ ብረቶች በጣም አስቸጋሪ ሊሆኑባችሁ ነው፡፡ ስለምፈራ ልረዳችሁ አልቻልኩም፡፡ ራሴን አደጋ ላይ መጣል አልፈልግም፡፡ ጓደኛዬ እስኪዘጋጅ ድረስ እዚሁ ጸጥ ብዬ ለመጠበቅ ፈልጌያለሁ፡፡»

«በጣም ጥሩ ነው ቻታል፡፡ እንደዚህ በመሰለው ወቅት እርስ በርሳችን ግልጽ መሆን አለብን፡፡ ዳግመኛ አላነሣብህም፡፡»

«ግን ያም ቢሆን መልዕክቶችህን አደርሳለሁ፣ ምስጢርም አላከሃለሁ፡፡»

«አመሰግናለሁ ቻታል፡፡»

«በዚያ ሌሊት የአውቶማቲክ ጠመንጃ ሩምታ ተኩስ ሰማን፡፡ በሚቀጥለው ቀን ጧት ጁሎ አመልጠ መሔዱን ተረዳን፡፡ እግዚአብሔር ይከተለው፡፡ ግሩም ጓደኛዬ ነበር፡፡ አንድ ክፍት ቦታ አይቶ የተቻለውን ተጠቅሞበት መሆን አለበት፡፡

ከዐሥራ አምስት ዓመት በኋላ፣ በ1948 ወደ ሐይቲ ሔጄ ነበር፡፡ የሔድኩትም ከአንድ ቬኔዙዌላዊ ሚሊዮኔር ጋር ሕጋዊ ቁማር ማጫወቻ፣ ጠረጴዛዎቹን ለመከራየት ከድርጅቱ ፕሬዚዳንት ጋር ኮንትራት ለመፈራረም ነበር፡፡ አንድ ቀን ምሽት፣ ሻምፓኝ ስንጠጣ ከነበረበት የማታ ከበብ በመውጣት ላይ እንዳለን፣ ከእኛ ጋር ከነበሩት ኮረዳዎች ውስጥ እንደ ከሰል የጠቆረችና ደግሞ እንደ ማንኛውም ጥሩ የፈረንሣዊ ቤተሰብ የጠለቀ ዕውቀት ያላት ወጣት «አያቴ አንድ የታወቀች ጠንቋይ መነኩሲት ናት፡፡ የምትኖረው ከአንድ ሽማግሌ ፈረንሣዊ ጋር ነው፡፡ ያመለጠው ከካየን ሲሆን፣ ከእርሷ ጋር በጣም ረጅም ጊዜ ኖሯል፡፡ ሁልጊዜ እንደ ሰከረ ነው፡፡ ስሙ ጁልስ ማርቶው ይባላል» አለችኝ፡፡

ወዲያውኑ ጥርጣሬ ያዘኝ፡፡ «አሁኑኑ አያትሽን አሳይኝ፡፡»

የታክሲ ሾፌሩን በሐይቲ ቋንቋ አናገረችውና በከፍተኛ ፍጥነት ሸመጠጥን፡፡ በግ ያለ መብራት ያለው አንድ የማታ ከበብ ስናልፍ፣ «አቁም!» አልኩና ወደ መጠጥ ቤቱ ሔጄ፣ አንድ ጠርሙስ ፔርኖ፣ ሁለት ጠርሙስ ሻምፓኝ፣ ሁለት ጠርሙስ የሀገር ውስጥ ሩም ገዛሁ፡፡ «እንሒድ፡፡»



@BOOKALEM

ቀይ ለስላሳ የጡብ ክዳን ያላት አንዲት የምትሞቅ ትንሽ ጎጆ ፊት ለፊት ከባሕሩ ጠርዝ ላይ ቆምን፡፡ ባሕሩ እስከ ደረጃዋ ድረስ ያጥባት ነበር፡፡ ልጃገረዷ ስትቆረቁረ ሽበት የወረራቸው አንዲት ግዙፍ ጥቁር ሴት መዝጊያውን ከፈቱላት፡፡ ቁርጭምጭሚታቸው የሚደርስ አንድ የተንቧለለ ቀሚስ ለብሰው ነበር፡፡ ሁለቱ ሴቶች በሀገራቸው ቋንቋ ተነጋገሩ፡፡ ከዚያም አሮጊቷ፣ «ግቡ፣ ቤቱ የእናንተው ነው» አሉ፡፡

አንድ የናፍታ ፋኖስ፣ ያችን የጸዳች ጎጆ ብርሃን ሰጥቷታል፡፡

«ጁሎን ለማየት ትፈልጋለህ? ቆይ፣ እየመጣ ነው፡፡ ጁልስ! ጁልስ! አንተን ለማየት አንድ ሰው አለ፡፡»

የቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ዩኒፎርማችንን ያስታወሰኝን ሰማያዊ ጥብጣብ ያለበት ፒጃማ የለበሰና ባዶ እግሩን የሆነ አንድ ሽማግሌ ብቅ አለ፡፡

«በዚህ ውድቅት ሌሊት እኔን ሊያየኝ የሚፈልገው ማንነው ቡል ዶኒጅ? ፓፒዮ! ሊሆን አይችልም!»

አቀፈኝና፣ «ፋኖሱን ቀረብ አድርገው ቡል ዶኒጅ፣ የጥንቱ ጓደኛዬን ፊት ማየት እፈልጋለሁ፡፡ አዎ፣ አንተው ነህ፣ አንተ አሮጌ! በእርግጥም አንተው ነህ! እንኳን ደህና መጣህ፡፡ ቤቴ፣ ያለችኝ ትንሽ ገንዘብ፣ የሚስቴ የልጅ ልጅ፣ ሁሉም ያንተው ናቸው፡፡ የምትፈልገውን ለማዘዝ ትችላለህ፡፡ »

ፔርኖውን፣ ሻምፓኙንና፣ ሩሙን ጠጣን፡፡ አልፎ አልፎ ጁሎ ይዘፋፍናል፡፡

«አህ፣ እንዴት የመሰሉ ጊዜዎች አብረን አሳለፍን ባልንጀሬ? ጆብዱን የመሰለ ምንም ነገር የለምኮ! ኮሎምቢያን፣ ፓናማን፣ ኮስታሪካንና ጃማይካን አዳረስኩ፡፡ ከዚያ በኋላ መቼውንም ወንድ ከማያገኝት ግሩም ሴት ከቡል ዶ ኒጅ ጋር እዚህ ተቀመጥኩ፡፡ መች ትሔዳለህ? እዚህ ብዙ ትቆያለህ እንዴ!»

«አልቆይም፡፡ አንድ ሳምንት ብቻ፡፡»

«እዚህ ምን ልትሠራ ነው?»

«የቁማር ጠረጴዛዎቹን በኮንትራት እንዲሰጠኝ፣ ከካሲኖው ፕሬዚዳንት ጋር ለመዋዋል እየሞከርኩ፡፡»

«እስከ ዕድሜ ልክህ አንተን እዚህ አካባቢ ከማቆየት የበለጠ ሌላ ምንም ነገር አልወድም ባልንጀሬ፡፡ ግን ከዚያ የውሻ ልጅ ጋር ምንም ነገር አትሥራ፡፡ ጥሩ ንግድ ማንቀሳቀስህን ሲያይ በደቂቃ ያስገድልሃል፡፡»

«በአንቺ በኩል ደግሞ ቡል ዶ ኒጅ፣ ለቱሪስቶች የሚቀርበውን ሳይሆን ትክክለኛውን የአስማት ትርዒትሽን አዘጋጂ፡፡ ለጓደኛየ ዕውነተኛውን ነገር እንድትነግሪው እፈልጋለሁ፡፡»

ጁሎ እንዲያ አመለጠ፣ ግን ዴጋ ፈርናንዴዝና እኔ ገና በመጠባበቅ ላይ



@BOOKALEM

ነበርን፡፡ አልፎ አልፎ በመስኮቱ ላይ ያሉትን ቋሚ የብረት ፍርግርጎች እፈትሻቸዋለሁ፡፡ ዕውነተኞቹ የባቡር ሐዲድ ብረቶች ስለነበሩ በዚያ በኩል ምንም ማድረግ አልተቻለም፡፡ እንዲያውም ገና መዝጊያው አለ አይደል፡፡ ሌት ከቀን ሦስት ዘበኞች እዚያው ተመድበዋል፡፡ ጁሎ ካመለጠ ጀምሮ ቁጥጥሩ ጠብቋል፡፡ የዘበኞቹ መቀያየር ወዲያው ወዲያው ሆኗል፡፡ ዶክተሩም የቀድሞው ተግባቢነቱን አቀዝቅዟል፡፡ ቻታል ወደ ከፍል የሚመጣው መርፌ ለመውጋትና ሙቀት ለመለካት በቀን ሁለት ጊዜ ብቻ ነበር፡፡ ሁለተኛ ሳምንት አለፈና እንደገና ሁለት መቶ ፍራንክ ከፈልኩ፡፡

ዴጋ ከማምለጥ በስተቀር ስለ ማንኛውም ነገር ያወራ ነበር፡፡ ትላንት ጩቤየን አየና፣ «አሁንም ይዘሃታል? ለምን?» አለ፡፡

«የእኔንና የአንተንም ነፍስ የማተርፍ መስሎኝ» አልኩና በቁጣ መለስኩለት፡፡

ፌሬናንዴዝ የስፓኝ ዜጋ ሳይሆን አርጀንቲናዊ ነበር፡፡ በተፈተነ አስቸጋሪ ጊዜ የሠለጠነ፣ ደህና ሰው ነበር፡፡ ግን እርሱም እንደዚሁ በሽማግሌው ካሮራ ፍሬ ቢስ ወሬ ተሰብኮ ነበር፡፡ አንድ ቀን ለዴጋ እንደዚህ ብሎ ሲያወራው ሰማሁት፡፡

«እንደዚህ ሳይሆን ደሴቶቹ በጣም ጤናማ ቦታዎች ናቸው ይባላል፡፡ ሙቀታቸውም እስከዚህ አይደለም፡፡ እዚህ ወደ መጸዳጃ ቤት በመሔድ ብቻ በጀርሞች ትበከልና የደም ተቅማጥ ይይዝሃል፡፡»

እኛ ከፍል ከሚገኙት ሰባ ሰዎች አንድ ወይም ሁለት በየቀኑ በደም ተቅማጥ ይሞታሉ፡፡ የሚያስገርመው ደግሞ ሁሉም የሚሞቱት ማዕበሉ ጋብ በሚልበት ወቅት ከሰዓት በኋላ ወይም ሲመሽ ነበር፡፡ ጧት ምንጊዜም የሚሞት ሰው የለም፡፡ ለምን ይሆን? የተፈጥሮ ምስጢር?

በዚያው ሌሊት ከዴጋና ከፌርናንዴዝ ጋር መመካከር ነበረብኝ፡፡ ቁልፍ ያገኘ ዓረብ ሌሊት ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ወደ ከፍል ወስጥ እየገባ፣ አንሶላ ወደ ኋላ በመግፈፍ በጣም የጠናበትን በሽተኛ ይመረምራል ብየ ነገርኳቸው፡፡ እርሱን መምታትና ዩኒፎርሙን መልበስ፡ (እኛ ሁላችንም የለበስነው ፒጃማና ነጠላ ጫማ ብቻ ነበር) ቀላል ይሆናል፡፡ አንድ ጊዜ ከለበስኩ በኋላ ወደ ውጭ አወጣና ከአንደኛው ዘበኛ ጠመንጃውን በመንጠቅ በእነርሱ ላይ ወድሬ ወደ ከፍሉ ውስጥ እንዲገቡ በማስገደድ መዝጊያውን መሸንር ነው፡፡ ከዚያም በሆስፒታሉ ግንብ ላይ ወደ ወንዙ ዳር ዘልለን፣ ውሃው ውስጥ መግባትና በማዕበሉ እየተገፋን ማምለጥ፡፡ ከዚያ ወዲያ ደግሞ የሚሆነውን እናያለን፡፡ ገንዘብ እስካለን ድረስ አንድ ጀልባና ምግብ ገዝተን ወደ ባሕር ለመውጣት እንችላለን፡፡ ዕቅዱን ሁለቱም በየበኩላቸው ውድቅ አደረጉት፡፡ ችላ ማለታቸው ስለ ተሰማኝ በጣም ተስፋ ቆርጬ ነበር፡፡ ስለሆነም ቀኖቹ አለፉ፡፡



@BOOKALEM

አሁንም በሆስፒታሉ ሦስት ሳምንት ሊሆነን የቀረው ሁለት ቀን ነው:: ማምለጥ ለመሞከር የቀረን ጊዜ ቢበዛ ከዐሥር እስከ ዐሥራ አምስት ቀን ብቻ ነበር:: ዛሬ አንድ የሚታሰብ ቀን ነው:: ኅዳር 21/1933 ዮሐንስ ከሎሲዎ ወደ ክፍሉ ውስጥ መጣ:: በቅዱስ ማርቲን ጸጉር ማስተካከያ ቤት አንድ ሰው ሊገድለው ሞክሮ ነበር:: ለመታወር ተቃርቧል:: ዐይኖቹ ምርግ ብለው ተዘግተው በመግል ተሞልተው ነበር:: ወዳያው ቻታል እንደ ወጣልኝ እርሱ ዘንድ ሔድኩ:: ሌሎቹ እሥረኞች ከሁለት ሳምንት በፊት ወደ ደሴቶቹ ሒደዋል:: እርሱ ግን ወደ ኋላ ለመቅረት እንደ ተሳካለት ነገረኝ:: እነርሱ ለመሔድ ሦስት ቀን ሲቀራቸው አንድ ባለሥልጣን አስጠነቀቀኝ አለ:: የጉሎ ዘይት ፍሬ ዐይኖቹ ውስጥ አስገባና፣ በሚያብጡበት ጊዜ በቁስሉ ምክንያት ወደ ሆስፒታል ለመግባት ቻለ:: ለማንኛውም ነገር ወደ ኋላ የማይልና የማምለጥ ፍላጎት ያሳበደው ከመሆኑ የተነሣ ከተሳካለት ገድሎ እንኳ ለማምለጥ ወደኋላ አይልም:: ሦስት ሺ ፍራንክ ነበረው:: ዐይኖቹ በሙቅ ውሃ ከታጠቡ ወዲያው ጥርት አድርጎ ለማየት ይችላል:: የማምለጥ ዕቅዴን ገለጽኩለት:: ወደደልኝ፣ ግን ዘበኞቹን በድንገት የምናጠቃ ከሆነ እኛ ሦስት መሆን ይኖርብናል አለ:: የአልጋዎቹን እግሮች አውልቀን እያንዳንዳችን አንድ እግር ከያዝን፣ ሁሉንም በአንድ ጊዜ መምታት እንችላለን:: እርሱ እንደሚለው፣ ጠመንጃቸውን ብንነጥቃቸው እንኳ ቆርጠን እንደምንተኩስባቸው ስለማያምኑ፣ ቢያንስ ሐያ ያርድ ከማይርቀው ጁሎ ካመለጠበት ሕንጻ የሚገኙትን ዘበኞች ሊያስጠነቅቁ ይችላሉ::



@BOOKALEM

# ሦስተኛ ማስታወሻ

## የመጀመሪያው ማምለጥ

## ከሆስፒታሉ ማምለጥ

ዛሬ ማታ ዴጋን፣ ቀጥሎ ፌርናንዴዝን በነገር ወጥሬ ያዝኳቸው:: ዴጋ «በዕቅዱ ዕምነት የለኝም:: ግን ወደ ሆስፒታል በሕመምተኛነት የተመዘገብኩበት እንዲሰረዝልኝ የሚያስፈልገውን ገንዘብ እከፍላለሁ» አለ:: ይህን እርሱ ያቀደውን ሐሳብ ማሳካት የሚቻል እንደሆነ ለሲየራ ማስታወሻ ጽፌ እንድነግርለት ጠየቀኝ:: በዚያው ቀን ቻታል መልሱን ይዞ መጣ:: ማስታወሻዋ፣ «ሕመምተኞች መሆናችሁን ለማሰረዝ ለማንም ሰው ገንዘብ እንዳትከፍሉ:: ትእዛዙ የሚመጣው ከፈረንሣይ ስለሆነ፣ ማንም ቢሆን፣ ሌላው ቀርቶ የጠባይ ማረሚያው አዛዥ እንኳ ለመፍቀድ አይችልም:: ቁርጠኛ ከሆንክ ለማምለጥ መሞከር ትችላለህ፣ ግን «ማና» የተባለችው መርከብ ወደ ደሴቶቹ ከሔደች ከአንድ ቀን በኋላ ብቻ መሆን ይኖርበታል» ትላለች::

ወደ ደሴቶቹ ከመሔዳችን በፊት ስምንት ቀን ቀርቶን ስለነበር፣ ከሆስፒታሉ ከፍላችን ይልቅ ከዚያ ማምለጡ ይበልጥ የተሻለ መሆኑን ማሰብ ጀመርኩ:: የምፈልግ ከሆነ ከእኔ ጋር የሚነጋገርና አንድ ጀልባ ከሆስፒታሉ በስተጀርባ የሚያዘጋጅልኝ ነጻ የወጣ አንድ እሥረኛ እንደሚልክልኝ በዚያችው ማስታወሻ ሲየራ ገልጾልኝ ነበር:: ከሁለት ዓመት ቀደም ሲል የዶክተር ቦግራትን ማምለጥ ያቀነባበረ ስሙ ኢዮአስ የተባለ አንድ የቱሎስ ቀበሌ ተወላጅ ነበር:: እርሱን ለማነጋገር ስል ራጅ እነሣለሁ በማለት ወደ ሌላ ሕንፃ መሔድ ነበረብኝ:: ያ ክፍል የተሠራው ከሆስፒታሉ ሕንፃ ግድግዳ ጋር ተያይዞ ስለነበር፣ ነጻ ለወጡ እሥረኞች መገናኛ የምስጢር መሿለኪያ ነበረው:: ከሣንባዬ በታች ከተነሣሁ፣ ዶክተሩ ሊታየው ስለሚችል ራጅ ከመነሣቴ በፊት የገንዘብ መደበቂያ ቱቦየን ማውጣት እንዳለብኝ አስጠነቀቀኝ:: ኢዮአስን ወደ ራጅ ክፍል እንዲልክልኝና እኔም ከቻታል ጋር አብሬ ወደ እዚያ እንድላክ ለሲየራ አንድ ማስታወሻ አስተላለፍኩ:: ከነገ ወዲያ በሦስት ሰዓት እንደሚሆን በዚያው ሌሊት ሲየራ ነገረኝ::

በሚቀጥለው ቀን ዴጋና ፌርናንዴዝ ከሆስፒታል ለመውጣት አመለከቱ:: «ማና» በዚያን ዕለት ጧት ሔዳ ነበር:: ካምፕ ከሚገኙት ከፍሎቻቸው ለማምለጥ ምኞት አላቸው:: መልካም ዕድል እመኝላቸዋለሁ:: የእኔ ዕቅዶች ግን አልተለወጡም::

ኢዮአስን አገኘሁት:: ሁለት አስቀያሚ ጠባሳዎች በበለዘው ፊቱ ላይ አግድም የተሰመረበትና እንደ ተለበለበ ዓሣ ድርቅ ያለ፣ ነጻ የወጣ ሽማግሌ እሥረኛ ነበር:: ሁልጊዜ አንድ ዐይኑ ያለቅሣል:: አስቀያሚ ፊትና ዛላ ነበረው:: ዕምነት አላሳደረብኝም፣



@BOOKALEM

የዚህም እውን መሆን ወደፊት ሊረጋገጥ ነው፡፡ በጥድፊያ ተነጋገርን፡፡

«ለአራት ወይም ቢበዛ ለአምስት ሰዎች የምትሆን አንዲት ጀልባ ላዘጋጅልህ እችላለሁ፡፡ አንድ በርሜል ውሃ፣ ምግብ፣ ቡናና ትምባሆ፣ ሦስት መቅዘፊያዎች፣ ባዶ የዱቄት ከረጢቶች፣ ጥናውን የነፋስ ሸራና የአቅጣጫ ማስተካከያውን ሸራ የምትሰፋበት ክርና መርፌ፣ አንድ ኮምፓስ፣ አንድ ቅንጨራ፣ አንድ ጨቤና አምስት ሊትር ሩም፣ ይህን ሁሉ በሁለት ሺ አምስት መቶ ፍራንክ፡፡ በዚህ ሦስት ቀን ውስጥ ጨረቃ አይኖርም፡፡ ከአራተኛው ጀምሮ፣ የምትስማማ ከሆነ ለስምንት ተከታታይ ቀናት ከሌሊቱ አምስት ሰዓት እስከ ንጋቱ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ ጀልባ ውስጥ ሆኜ ልጠብቅህ፡፡ አንድ ጊዜ ጨረቃ ከታየች ከመጀመሪያው ሳምንት በኋላ መጠበቁን አቆማለሁ፡፡ ጀልባዋ ልክ ከሆስፒታሉ ግንብ በስተጀርባ ትሆናለች፡፡ ከስድስት ጫማ ርቀት ላይ ሆነህ እንኳ ልታያት ስለማትችል፣ ግንቡን እየዳሰስክ ራስህን ምራ» አለ፡፡

እ.መንከትም፣ ግን ያም ሆኖ እሺ አልኩ፡፡

«የገንዘቡስ ጉዳይ እንዴት ነው?» አለ ኢዮአስ፡፡

«በሲየራ በኩል እልክልሃለሁ፡፡»

ሳንጨባበጥ ተለያየን፡፡ ጥሩ ጅምር አልነበረም፡፡

በዘጠኝ ሰዓት ቻታል ገንዘቡን ለሲየራ ለመስጠት ወደ ካምፕ ሔደ፡፡ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ፍራንክ ነበር፡፡ አደገኛ እንደሆነ ቢታየኝም ለጋልጋኔ ምስጋና ይግባውና ይህን ገንዘብ ቁማር እንደተጫወትኩበት አቆጥረዋለሁ፡፡ ብቻ እሱስ ቢሆን ሁሉንም ገንዘብ በሩም ባይጨርሰው አይደል?

ክሎሲዎ ከመጠን በላይ ፈንድቆ ነበር፡፡ በራሱ፣ በእኔና በዕቅዱ ሙሉ በሙሉ ተማምኗል፡፡ አንድ ነገር ብቻ አሳስቦታል፡፡ ዐረቡ በምሽት አይመጣም፣ በሚመጣበት ጊዜ ግን አዘውትሮ ቀደም እያለ ነበር፡፡ አንድ ተጨማሪ ሦስተኛ ሰው ማን ይሆን የሚለውም ሌላው ችግር ነበር፡፡ ከኒስ ቀበሌ የመጣ ቢያጂ ዖተባለ አንድ ኮርሲካዊ ነበር፡፡ ከ1929 ጀምሮ በቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ውስጥ ቢሆን፣ እሁንም አንድ ሰው ገድለሃል በሚል ጥርጣሬ በከፍተኛ ጥበቃ ሥር ይገኛል፡፡ ክሎሲዎና እኔ እርሱን ማነጋገር ነበረብን፡፡ መቼ እናነጋግረው በማለት በመወያየት ላይ እንዳለን፣ በግምት ዐሥራ ስምንት ዓመት የሚሆነው አንድ ልጅ ወደ እኛ መጣ፡፡ ልክ እንደ ልጃገረድ ቆንጆ ነበር፡፡ ስሙ ማቹሬ ይባላል፡፡ በአንድ የታክሲ ሾፌር ግድያ የተነሣ የሞት ቅጣት ከተፈረደበት በኋላ፣ በዕድሜው ምክንያት (በዚያን ጊዜ ዐሥራ ሰባት ዓመቱ ነበር፡፡) ወደ ዕድሜ ይፍታህ ተሻሽሎለት ነበር፡፡ የተከሰሱት የዐሥራ ስድስትና የዐሥራ ሰባት ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሁለት ልጆች ነበሩ፡፡ ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ እያንዳንዳቸው የታክሲውን ሾፌር መግደላቸውን በማመን ቃላቸውን ሰጡ፡፡ ግን ሾፌሩ የተመታው



@BOOKALEM

በአንድ ጥይት ብቻ ነበር። በፍርድ ቤት ያሳዩት ሥነ ምግባር እሥረኞቹን በሙሉ ስሜታቸውን በሐዘን መስጦታል።

ማቼሬ ወደ እኛ ቀረብ አለና የልጃገረድ ድምፅ በመሰለ አነጋገር የሲጃራ ማቀጣጠያ ጠየቀን። አራት ሲጃራዎችና አንድ ሣጥን ክብሪት በስጦታ መልክ ወረወርኩለት። ከመሽኮርመም ፈገግታ ጋር አመሰገነኝ። እኛም አሰናበትነው።

ክሎሲዎ በድንገት፣ «ፓፒ ድነናል። ያን ዐረብ እኛ እንደ ፈለግን አዘውትሮ ወደዚህ መምጣት የሚችልበትን ዘዴ ዐወቅኩ፣ እጃችን ውስጥ ገብቷል» አለ።

«እንዴት አስብክ?»

«ቀላል ነው። ማቼሬና ዐረቡ የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው አያጠራጥርም። ልጁ ማድረግ ያለበት እንዳልታይ እፈራለሁ እያለ ልክ እኛ በምንፈልግበት ሰዓት ዐረቡ እንዲመጣ ማመቻቸት ብቻ ነው።»

«እስኪ እንሞክረው።»

ማቼሬ ዘንድ ስሔድ እንደገና በሌላ የመሽኮርመም ፈገግታ ተቀበለኝ። የመጀመሪያው ፈገግታ ስሜቴን ቀስቅሶታል ብሎ ገምቷል። በቀጥታ እንደዚህ አልኩት። «አንድ ጊዜ ላነጋግርህ እፈልጋለሁ። ወደ መጸዳጃ ቤት እንድትመጣ» ተያይዘን እንደሔድን እንዲህ አልኩት። «አሁን የምነግርህን አንዷን ቃል ለሌላ ሰው ብትተነፍስ ሟች ሰው ነህ። እንደዚህ ነው . . . » ስል ዕቅዳችንን በዝርዝር ነገርኩትና ምን ያህል ገንዘብ እንደሚጠይቅ፣ ወይም ከእኛ ጋር ማምለጥ የሚፈልግ ከሆነ ጠየቅኩት።

«ከእናንተ ጋር ማምለጥ እፈልጋለሁ።»

ተስማማን። ለዚህም እጅ ለእጅ ተጨባበጥን። ለመተኛት ሔደ፣ ከሎሲዎ ጋር ትንሽ ቃላት ከተለዋወጥን በኋላ እኔም ተኛሁ። በሚቀጥለው ሌሊት በስምንት ሰዓት ማቼሬ ከመስኮቱ አጠገብ ተቀመጠ። ዓረቡ መጠራት አላስፈለገውም። በገዛ ራሱ መጣና ድምፃቸውን ዝቅ በማድረግ አወሩ። በዐሥር ሰዓት ማቼሬ ወደ አልጋው ሔደ። እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ አንድ ዐይናችንን እንዳጨለቅን በአልጋችን ውስጥ ቆየን። ዓረቡ ወደ ክፍል ገብቶ ሁለት ጊዜ ሲፈትሽ፣ አንድ ሰው ሞቶ አገኘ። መዝጊያውን ቆረቆረና ወዲያውኑ ሁለት ቃሬዛ ተሸካሚዎች መጥተው አስከሬኑን ወሰዱ። አስከሬኖች ጠቃሚነታቸው ከሌሊቱ በማንኛውም ሰዓተ ዓረቡ እንደልቡ ወጣ ገባ እንዲል ማስቻላቸው ነው። የእኛን ምክር በመከተል ማቼሬ በሚቀጥለው ሌሊት በአምስት ሰዓት አንድ ቀጠሮ ሰጠው። ቁልፍ ያገዞም ዓረብ በቀጠሮው ሰዓት ከተፍ አለና በልጁ አልጋ በኩል ሲያልፍ ሊቀሰቅሰው እግሮቹን ሳብ አድርጎ አለፈ። ማቼሬ ተከተለው። ከዐሥራ አምስት ደቂቃ በኋላ ቁልፍ ያዡ ተመለሰና በቀጥታ ወደ መዝጊያው ሔዶ ወጣ። በዚያው ወቅት ማቼሬም ምንም ሳይናገር ወደ አልጋው ተመልሶ ሔደ።



@BOOKALEM

በሚቀጥለው ምሽት እንደዚሁ ሆነ፡፡ ግን ውድቅት ሌሊት ላይ ነበር፡፡ ማንኛውም ነገር የሚከናወነው ልክ እንደ ሕልም ይመስል ነበር፡፡ በማንኛውም ጊዜ ልጁ ከጠየቀው ዓረቡ ይመጣል፡፡

ኅዳር 27/1933 ከሰዓት በኋላ ዐሥር ሰዓት ላይ ሁለቱን የአልጋ እግሮች ለመፈንከቻ አዘጋጀኹ፤ ከሲየራ የሚደርሰኝን ቃል እጠባበቅ ጀመር፡፡ ጤና ረዳቱ ቻታል መጣ፡፡ ግን አንድም ማስታወሻ አልያዘም፡፡ ያለው፣ «ኢየሱስ በተጠቀሰው ቦታ እየጠበቃችሁ ነው፡፡ መልካም ዕድል ብዬ እንድነግራችሁ ፍራንሷ ሲየራ ልኮኛል» ብቻ ነበር፡፡ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ ማቹሬ ለዐረቡ «ከግማሽ ሌሊት በኋላ እንድትመጣ» አለው፡፡

ዐረቡም እንደተባለው አደርጋለሁ አለ፡፡ ልክ ግማሽ ሌሊት ሲሆን ተዘጋጅተን ነበር፡፡ ዐረቡ ስድስት ሰዓት ከሩብ ላይ መጣ፡፡ ማቹሬም ተከተለው፡፡ የአልጋየን እግር ሳወልቅ በሚወድቅበት ወቅት አንድ ድምዕ አሰማብኝ፡፡ ክሎሲዎ ግን ምንም ድምፅ አልነበረውም፡፡ እኔ መዝጊያውን ተከልዬ ልቆምና ክሎሲዎ ደግሞ የዐረቡን ስሜት ለመሳብ በቀጥታ ወደ እርሱ ሲሔድ ነበር፡፡ ከሐያ ደቂቃ ቆይታ በኋላ ማንኛውም ነገር በጣም እየተቀላጠፈ ሔደ፡፡ ዐረቡ ከመጸዳጃ ቤት ሲወጣ ክሎሲዎን በማየቱ ደነቀውና፣ «በዚያ ሌሊት በክፍሉ መካከል ምን እያደረግክ ነው? ወደ አልጋህ ተመለስ» አለው፡፡

ከዚያም ጭንቅላቱ ላይ አፈጋሁበትና ምንም ድምዕ ሳያሰማ ተፈነገለ፡፡ ቶሎ ብየ ጫማዎቹንና ልብሶቹን አጠለቅኩ፡፡ ወደ አልጋ ሥር ጎተትነውና ሙሉ በሙሉ ወደ ውስጥ ከመግፋታችን በፊት ማጅራቱ ላይ አንድ ሌላ ምት ደገምኩት፡፡ አሁን ያለጥርጥር ሕሊናውን ስቷል፡፡

በክፍሉ ውስጥ ካሉት ሰዎች ማንም የተንቀሳቀሰ የለም፡፡ ማቹሬና ክሎሲዎ የሆስፒታል ፒጃማቸውን እንደለበሱ ተከትለውኝ በቀጥታ ወደ መዝጊያው አመራሁ፡፡ ስቆረቁር ዘበኛው ከፈተ፡፡ የአልጋውን ብረት አምዘገዘግኩና በቀጥታ ጭንቅላቱን ነረትኩት፡፡ ከእኛ ፊት ለፊት ያለው ሌላ ዘበኛ ካርባይኑን ጣለው፡፡ ተኝቶ መሆን አለበት፡፡ እንቅስቃሴ ከማድረጉ በፊት እርሱንም ነረትኩት፡፡ ከእኔዎቹ ማንም ድምፅ ያሰማ የለም፡፡ የክሎሲዎ ግን በወለሉ ላይ ከመዘርጋቱ በፊት «እህ!» አለ፡፡ የእኔ ሁለቱ ዘበኞች ገና በወንበሮቻቸው ላይ ሲሆኑ፣ ሦስተኛው ግርር እንዳለ ተዘርግቶ ነበር፡፡ ትንፋሻችንን ዋጥ አድርገን ይዘናል፡፡ በእኛ ግምት «እህ» የምትለዋ የዘበኛው የመጨረሻ ድምዕ በመላው ዓለም ተሰምታብናለች፡፡ በእርግጥ በቂ ጩኸት ነበር፡፡ ይሁንና ማንም አልተንቀሳቀሰም፡፡ መጀመሪያ ክሎሲዎ፣ በመካከል ልጁ፣ እኔ ከኋላ ሆነን የሦስቱንም ካርባይኖች አነሣንና እንደተጋደሙ ትተናቸው ሔድን፡፡ የደበዘዘ መብራት ባለበት ደረጃ ቁልቁል ሸመጠጥን፡፡ ክሎሲዎ የአልጋውን እግር ወደ ኋላ ጥሎት ነበር፡፡ የእኔን ጠመንጃ



@BOOKALEM

በቀኘ፣ የአሊጋወን እግር በግራ እጄ ይዤዋለሁ:: ከደረጃው በታች ምንም ነገር የለም:: አካባቢያችን በሌሊቱ ድቅድቅ ጨለማ የተዋጠ ነበር፡፡ ከወንዙ ቀጥሎ ያለውን ግንብ ለማግኘት አተኩረን መመልከት ነበረብን:: የቻልነውን ያህል በከፍተኛ ፍጥነት እንራመዳለን:: አንድ ጊዜ ወደ ግንቡ ከደረስኩ በኋላ በእጆቼ በመደገፍ የቁም ዕረፍት አደረግኩ:: ክሎሲዎ ወደ ላይ ተንጠለጠለና በግንቡ ላይ ተንፈራጥጦ ማቹሬን፣ ከዚያም እኔን ጎትቶ አወጣን:: በሌላው በኩል ተንሸራትተን ወረድን:: ክሎሲዎ አንድ ጉድጓድ ውስጥ ስለገባ እግሩን ተሰበረ:: ማቼሬና እኔ ያለችግር ዘለልን:: ከመዝለላችን በፊት ጠመንጃዎቹን ጥለናቸው ስለነበር፣ ያለችግር በእግራችን ቆምን:: ክሎሲዎ ግን እቆማለሁ ብሎ ቢሞክር አልቻለም:: ጉልበቴን ተሰብሬአለሁ አለን:: ማቹሬን ከክሎሲዎ ጋር ተውኩና በእጄ እየዳበስኩ ወደ ግንቡ ማዕዘን አቅጣጫ መሮጥ ያዝኩ:: በጣም ጨለማ ከመሆኑ የተነሣ ወደ ግንቡ መጨረሻ መድረሴን ስላላወቅኩ፣ በፊቴ ጧ ብዬ ወደቅኩ:: ከወንዙ በታች አንድ ድምፅ ሰማሁ::

«አንተ ነህ?»

«አዎ፣ ኢዮአስ ነህ?»

«አዎ»

አንድ ከብሪት ለኮስ:: ወንዙ ውስጥ ገባሁና እያንቦጫረቅኩ እርሱ ወደሚገኝበት አመራሁ:: ሁለት ሰዎች ነበሩ::

«መጀመሪያ አንተ ግባ፣ ማንኛው ነህ?»

«ፓፒዮ»

«እሺ»

«ኢዮአስ፣ ወደ ላይ ተመልሰን መሔድ ሊኖርብን ነው:: ከግንቡ ላይ እዘላለሁ ሲል ጓደኛየ ቅልጥሙን ተሰብሯል::»

«እንግዲህ ይህን መቅዘፊያ ውሰድና ቅዘፍ::» ሦስቱንም መቅዘፊያዎች ወደ ውሃው አጠለቅንና በመቅዘፍ በእኛና በጓደኞቼ መካከል ያለውን የአንድ መቶ ያርድ ርቀት ጀልባዋ በፍጥነት አጠናቀቀች:: ምንም ነገር ካለማየታችን የተነሣ እናገኛቸዋለን ብየ ከገመትኩበት አካባቢ ስደርስ

«ክሎሲዎ!» ብዬ ተጣራሁ::

«ስለ ክርስቶስ አትናገር:: ሴንፍሊ፣ የሲጃራ ማቀጣጠያህን ተጠቀም» አለ ኢዮአስ:: ትንሽ ብልጭታ ቦግ ሲል እነ ክሎሲዎ አዩን:: ክሎሲዎ በጥርሶቹ መካከል አንድ ፉጨት አሰማ:: ልክ እንደ አባባ ፉጨት ጥርት ብሎ የሚሰማ የሊዮን ቀበሌ ፉጨት ነበረ:: እስከምንቀራረብ ድረስ ማፏጨቱን ቀጠለ:: ሴንፍሊ ወጣና የክሎሲዎን ከንድ ደግፎ ወደ ጀልባው አመጣው:: ከዚያም ማቹሬ ተንጠለጠለ፣ በመጨረሻ ሴንፍሊ



@BOOKALEM

ወጣ:: አምስት ነበርን፣ ስለሆነም ውሃው ወደ ጀልባዋ አፍ ጠርዝ ሊደርስ የቀረው ጥቂት ነበር::

«ያለ አንድ ማስጠንቀቂያ ማንም ሰው እንዳይነቃነቅ:: ፓርዮ መቅዘፍህን አቁም:: መቅዘፊያውን በጉልበቶችህ አግድም አስቀምጥ:: እንሒድ ሌንፍሌ!» አለ ኢዮአስ::

በማዕበሉ እየተረዳች ጀልባዋ ወደ ጨለማው ውስጥ ጠለቀች:: የአንድ ማይል ሲሶ በወንዙ ቁልቁል እንደወረደን የጠባዩ ማረሚያውን ከልል አለፍን:: ወደ ወንዙ መካከል እንደገባን፣ ማዕበሉ በማይታመን ፍጥነት ተሸከመን ነጎደ:: ሌንፍሌ መቅዘፊያውን አቁሞ ነበር:: ኢዮአስ ደግሞ፣ መቅዘፍ ሳይሆን የመቅዘፊያውን እጀታ ከጭኑ ጋር ጥብቅ አድርጎ በመያዝ የጀልባዋን አቅጣጫ ለመቆጣጠር ይጥራል::

ከዚያም ኢዮአስ እንደዚህ አለ:: «አሁን ሲጋራ ማጨስ እንችላለን:: እንደማስበው ሁሉም ነገር የተሳካ ይመስለኛል:: እርግጠኞች ናችሁ ምንም ሰው አልገደላችሁም?»

«አይመስለኝም::»

«እግዚአብሔር ይይልህ ኢዮአስ! ያታለልከኝ አንተ ነህ!» አለ ሌንፍሌ:: «አንተ ያልከው ቀላል ማምለጥ ነበር:: አሁን እንዳየሁት ግን የሕሙማን ሩጫ ነው::»

«ትክክል ነው፣ ሕሙማን እሥረኞች ናቸው:: አልነገርኩህም ሌንፍሌ፣ ምክንያቱም አትረዳኝም ነበር፣ እኔም አንድ ሌላ ሰው ማግኘት ነበረብኝ:: ተዝናና:: ከተያዝን ኃላፊነቱን በሙሉ እኔ እወስዳለሁ::»

«እንዳልከው ይሁን ኢዮአስ:: አንድ ሙቶ ፍራንክ ከፍለኸኛል ብየ አንድ ሰው ቢገደል ወይም ቢቆስል አንገቴን ለአደጋ ልሰጥ አልፈልግም::»

«ሌንፍሌ፣ ለሁለታችሁም አንድ ሺ ፍራንክ በተጨማሪ አበረክትላችኋለሁ» አልኩ::

«እንግዲያስ ደህና ነው ጓዴ:: ማሰብህም ተገቢ ነው:: እናመሰግናለን:: መንደሩ ውስጥ በረኃብ መሞታችን ነው:: ወህኒ ቤት ከመሆን ይልቅ የሚብሰው ነጻ መውጣቱ ነው:: በወህኒ ቤት ውስጥ ሌላው ቢቀር በየቀኑ ምግብና ልብስ ታገኛለህ::»

«ብዙ ተጎድተሃል እንዴ ጓዴ?» ሲል ኢዮአስ ከሎሲዎን ጠየቀው::

«እስከዚህ ከባድ አይደለም:: ግን በሰባራው ቅልጥሜ እንዴት አድርጌ ልሔድ ነው ፓፒዮ?» አለ ከሎሲዎ::

«እስኪ እናያለን:: ወዴት ነው የምንሔደው ኢዮአስ?»

«ለወንዙ ጫፍ ዐሥራ ሁለት ማይል ሲቀረን፣ ከምትገነጠል አንዲት ጠባብ ጅረት ውስጥ እሸሽጋችኋለሁ:: ዘበኞቹና ሰው አዳኞቹ ፍለጋቸውን ተስፋ ቆርጠው



@BOOKALEM

እስኪተዉት ድረስ እዚያ ስምንት ቀን ያህል ትቆያላችሁ:: በዛሬው ሌሊት በማሮኒ ወንዝ ወርዳችሁ ወደ ባህር ዘልቃችኋል ብለው ሊያስቡ ይችላሉ:: አዳኞቹ የሚጠቀሙባቸው ጀልባዎች ሞተር አልባ ናቸው:: ምናልባት በአካባቢው ስለሚቀርቡ እሳት ማንደድ፣ መነጋገርና መሳል አደገኛ ይሆናል:: ዘበኞቹ የሚጠቀሙበት ባለሞተር ጀልባ ግን በጣም ትልቅ ከመሆኑ የተነሣ ወደ ጅረቷ ዘልቆ መቃናት ስለማይችል የሚሯሯጡት በመሬት ነው::»

ሌሊቱም ወገግ አለ:: ከረጅም ፍለጋ በኋላ በመጨረሻ ኢዮአስ ብቻ ከሚያውቃት የመሸሸጊያ ሥፍራ ስንደርስ፣ ከጧቱ አንድ ሰዓት ሊሆን ተቃርቦ ነበር:: ሙሉ በሙሉ ጫካ ውስጥ ነበርን:: አጫጭር የሆኑትን ቁጥቋጦዎች ጀልባዋ እያስተኛቻቸው ካለፍን በኋላ፣ እንደገና ቀጥ ብለው ይቆሙና አንድ ወፍራም መጋረጃ ይሆናሉ:: አንድ ጀልባ የሚያንሳፍፍ በቂ ውሃ እዚህ አለ ብሎ ለማወቅ ጠንቋይ መሆንን ይጠይቃል:: ወደ በሸሎዋ ገባን:: ከዚያም መንገዳችንን የዘጉብንን ቅርንጫፎች በመመንጠር ወደ ጫካዎቹ ውስጥ ሰርገን ለመግባት ከአንድ ሰዓት በላይ አጠፋን:: ድንገት አንድ ቦይ የመሰለ ቦታ ውስጥ ገባንና ቆምን:: የበሸሎው ዳር ንጹሕና አረንጓዴ ሆኖ የዛፎቹ ቅጠሎች በጣም ሰፋፊ ስለሆኑ፣ ከውፍረታቸውም የተነሣ የፀሐይዋን ብርሃን እያስተላልፉም ነበር። በዚህ ማራኪ አረንጓዴ አጎበር ሥር ፍጹም ሰምተናቸው የማናውቅ በሺህ የሚቆጠሩ አራዊት ይኖራሉ:: «ስምንት ቀን የምትቆዩት እዚህ ነው:: በሰባተኛው ቀን ተመልሼ ስንቃችሁን አመጣላችኋለሁ» አለ ኢዮአስ:: ጥቅጥቅ ያለውን ጫካ ገላለጠና ስድስት ጫማ ርዝመት ያላት አንዲት ትንሽ ጀልባ ከሁለት መቅዘፊያዎች ጋር ጎትቶ አወጣ:: ማዕበል ሲነሣ ወደ ቅዱስ ላውረን መልሳ የምትወስደው ጀልባ ይህች ነበረች::

ጅረቷ ዳር ተዘርግቶ ለነበረው ክሎሲዎ አንድ ነገር ማድረግ የሚቻለው አሁን ነበር:: የለበሰውም ፒጃማውን ብቻ ስለሆነ ባቶቹ ራቁታቸውን ናቸው:: ለማጀያ የሚያገለግሉን ደረቅ ቅርንጫፎች በቆንጨራችን ቆረጥንና ሰነጣጠቅን:: ሌንሮ እግሩን ሲሰብለት ክሎሲዎ በከባድ ላብ ተዘፈቀ:: ድንገት ክሎሲዎ፣ «አቁም! አሁን የሚያመኝ በመጠኑ ነው:: አጥንቱ ከቦታው መግባት አለበት» አለ:: ስንጥሮቹን አሰናዳንና ጀልባው ውስጥ ባገኘነው አዲስ የቃጫ ገመድ አሠርናትው፣ ሥቃዩ በረደለት:: ቀደም ሲል ኢዮአስ ለእኛ ያዘጋጃቸው አራት ሸሚዞች፣ አራት ሱሪዎችና አራት የሱፍ ሹራቦች ይዞ ነበር:: ማቹሬና ክሎሲዎ ለበሷቸው:: እኔ የዓረቡን ልብሶች እንደ ለበስኩ ቆየሁ:: ትንሽ ሩም ጠጣን:: ከተነሣን ጀምሮ ሁለተኛው ጠርሙስ መሆኑ ነበር:: ሞቅ አደረገን:: ከፉኛ በቢንቢዎች በመነደፋችን አንድ ፓኬት ትምባሆ ለመሠዋት ተገደድን:: ውሃ ከተሞላ ጠርሙስ ውስጥ ዘፈዘፍንና ፊታችንን፣ እጆቻችንና እግሮቻችንን ለቀለቅናቸው:: ስርሥሮ



@BOOKALEM

ከሚገባው እርጥበት የሱፍ ሹራቦቹ ሙቀት ጠበቀን፡፡

«መሔዳችን ነውኮ፡፡ ቃል የገባህልንን አንድ ሺ ፍራንክ አታመጣም?» አለ ሌንፍሌ፡፡

ለትንሽ ጊዜ ገለል አልኩና አንድ ባለ አንድ ሺ ፍራንክ አዲስ ኖት ይዤ ተመለስኩ፡፡

«ደህና ሁኑ፡፡ ለስምንት ቀን ከዚህ እንዳትንቀሳቀሱ፣ በሰባተኛው እንመለሳለን፡፡ በስምንተኛው ወደ ባሕር ትወጣላችሁ፡፡ በምትቆዩበት ጊዜ የነፋስ ሸራችሁን፣ የአቅጣጫ ማስተካከያ መሣሪያችሁን በመጠገን ጀልባዋን አዘጋጁ፡፡ ከበስተኋላ ያለውን የጀልባዋን መሪ አስተካክላችሁ፣ ማንኛውንም ነገር በቦታው አስቀምጡ፡፡ ከዐሥር ቀን በኋላ ካልመጣን ታስረናል ማለት ነው፡፡ እነዚያን ዘበኞች ማጥቃታችሁ ብዙ ችግር ማስከተሉ አይቀርም፡፡»

ከዚያም ክሎሲዎ ካርባይኑን በግንቡ ሥር እንዳልተወው ነገረን፡፡ ከግንቡ ላይ ሆኖ ሲወረውረው ወንዙ ቅርብ መሆኑን በዚያ ወቅት ባለማስተዋሉ ነው እንጂ ወደ ውሃው ውስጥ መውደቅ አለበት፡፡ አዳኞቹ መሣሪያ ታጥቀናል ብለው ስለሚያስቡ አለመገናኘቱ ጥሩ ነው አለ ኢዮአስ፡፡ አሁን ትንሽ መዝናናት እንችላለን፡፡ የሚይዙት ሽጉጥና ገጀራ ብቻ ስለሆነ፣ እኛም መሣሪያ እንዳለን ከጠረጠሩ እኛን ለማደን መንገዳቸውን አሳብረው አይወጡም፡፡ ይሁንና በአጋጣሚ ከተገኘን ጀልባዋን ትተን ደረቅ መሬት እስከናገኝ ድረስ ጅረቷን ተከትለን ሽቅብ መውጣት ይኖርብናል፡፡ ከዚያም የሰሜንን አቅጣጫ እየጠበቅን በኮምፓስ በመመራት መሔድ አለብን፡፡ ከሁለት ወይም ከሦስት ቀናት በኋላ ቫርቬን ተብላ ከምትጠራው ካምፕ ለመድረስ ጥሩ ዕድል ይኖረናል፡፡ አንድ ጊዜ እዚያ ከደረስን ለአንድ ሰው ጉርሻ ሰጥተን የት እንዳለን ለኢዮአስ እንዲነግርልን ማድረግ ነው፡፡

ሁለቱ ሽማግሌ ተባባሪዎቻችን ሔዱ፡፡ ከትንሽ ደቂቃ በኋላ ጀልባቸው ተሠወረች፡፡ ምንም ነገር ማየትና መስማት አልቻልንም፡፡ የቀኑ ብርሃን ጫካውን ሰርጎ የሚገባው በጣም ልዩ በሆነ መንገድ ነበር፡፡ በላዩ ላይ ፀሐይ የምታርፍበትና ጨረሯ ግን ተጣርቶ የማይወርድበት አንድ ጃንጥላ ውስጥ ያለን ይመስል ነበር፡፡ መሞቅ ጀመረ፡፡ ማቹሬ፣ ክሎሲዎና እኔ ብቻችንን ቀረን፡፡ እየተያየንም እንሣሣቅ ጀመረ፡፡ ጥቂት ቅሬታ ቢኖረን በክሎሲዎ ቅልጥም መሰበር ነበር፡፡ ግን ዙሪያውን በታሠረለት እንጨት ምክንያት ደህና ነኝ አለ፡፡ ቡና ብናፈላለት የሚሻለው መሆኑን ነገረን፡፡ ወዲያው አዘጋጀንለት፡፡ እሳት አነደድንና እያንዳንዳችን በወየበ ስኳር የጣፈጠ ጥቁር ቡና ጠጣን፡፡ የሚያረካ ነበር፡፡ ካለፈው ሌሊት ጀምሮ ኃይላችንን በብዛት አባክነን ስለነበር፣ ጓዛችንን ለመመርመርም ሆነ ጀልባዋን ለመፈተሽ አቅም አላገኘሁም፡፡ ያ በኋላ ሊደርስ ይችላል፡፡



@BOOKALEM

ቁም ነገሩ ነፃ፣ ነፃ፣ ነፃ መሆናችን ነበር፡፡ ወደ ቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት የደረስነው ልክ ከሠላሳ ሰባት ቀን በፊት ነበር፡፡ ማምለጡ ከተሳካ የዕድሜ ልክ እሥራት ቅጣት ፎጣም ረጅም ላይሆን ነው፣ «ከቡር ፕሬዚዳንት፣ ፈረንሣይ ውስጥ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ማከተሚያው እስከ መቼ ይሆን?» አልኩና በሣቅ ፈነዳሁ፡፡ እንደኔ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የተፈረደበት ማቹሬም እንደዚሁ ቀጠለ፡፡ «አሁን አትንጫጩ፡፡ ኮሎምቢያ ገና ሩቅ ስለሆነ ይህች ጀልባ እስከዚህም ለባሕር ጉዞ ዋጋ ያላት አትመስለኝም» አለ ክሎሲዖ፡፡

አልመለስኩለትም፣ ምክንያቱም ይህች ጀልባ ወደ አስተማማኙ ግባችን እንደምታደርሰን እስከ መጨረሻዋ ደቂቃ ድረስ አምኜ ስለነበር ነው፡፡ ተሳስቼ እነደነበር ስረዳ ግን፣ ጓደኞቼን አሸብራለሁ በሚል ሥጋት ምንም ነገር ለማለት አልደፈርኩም፡፡ እንደዚሁም ኢዮአስ በሚገባ የተስተካከለች ናት ብሎ እሰካሰበና በተለይም ለማምለጥ የሚጠቀሙባቸው ጀልባዎች ምን ዓይነት እንደሆኑ እኔም እሰካላወቅኩ ድረስ የምፈልገውን ዓይነት እንዲሠራልኝ መመሪያ ለመስጠት አልቻልም ነበር፡፡

የመጀመሪያውን ቀን ያጠፋነው በማውራትና ከዚህ ምኑም የማይታወቅ ጫካ ጋር በመለማመድ ነበር፡፡ ዝንጀሮዎችና ትናንሽ የሸኮኮ ዝርያዎች ከጭንቅላታችን በላይ ትንግርታዊ አክሮባት ይሠራሉ፡፡ አንድ የዱር አሳማዎች መንጋ ወደ ጅረቱ ለመታጠብና ለመጠጣት መጣ፡፡ ቢያንስ ሁለት ሺህ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚያም ወደ ውሃው ውስጥ በመግባት የተንጠለጠሉትን ሐረጎች እየበጣጠሱ ይዋኙ ጀመር፡፡ ከወዴት እንደ መጣች እግዚአብሔር ይወቅላትና አንዲት አዞ ከተፍ ብላ ከእነርሱ ውስጥ የአንዷን እግር ያዘች፡፡ ዓሣማዋ፣ ሌሎቹ ዓሣማዎች በአዞዋ ላይ እየተንጠላጠሉ ግዙፍ የሆነ አፏን ዳርና ዳር በመንከስ ይታገሏት ጀመር፡፡ አዞዋ በየጊዜው ጅራቷን ባወናጨፈች ቁጥር አንድ ዓሣማ አየር ላይ ይሽቀነጠራል፡፡ ከእነርሱ ውስጥ አንዷ ሞተችና ሆዷን ወደ ሰማይ ገልብጣ ተንሣፈፈች፡፡ ወዲያውኑ ጓደኞቿ እርሷን ለመብላት ተሰበሰቡ፡፡ ጅረቱን ደም አጥለቅልቆት ነበር፡፡ አዞዋ ወደ ውሃው ጠልቃ እስከትጠፋ ድረስ ትዕይንቱ ሐያ ደቂቃ ፈጀ፡፡ ዳግመኛ ፈጽሞ አላየናትም፡፡

ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ወስዶን አደርን፡፡ ጧት ቡና አፍልተን ከጠጣን በኋላ ሹራቤን አውልቄ ጀልባው ውስጥ ባገኘሁት አንድ ትልቅ የማርሴይ ሳሙና አጠብኩ፡፡ ማቹሬ በራሴው ጩቤ ጉንጩን እየቆራረጠ ጺሜን ላጨኝ፡፡ ቀጥሎ ክሎሲዖንን ላጨው፡፡ ማቹሬ ራሱ ግን ጺም አልነበረውም፡፡ ሹራቤን ለመልበስ ብድግ ሳደርግ፣ የጥቁር ሐምራዊ የሆነ አንድ ግዙፍ ሸረሪት ከላዩ ላይ ዱብ አለ፡፡ ጫፎቻቸው ትናንሽ የፕላቲኒየም ኳሶች በመሰሉ ቀጫጭንና በጣም ረጅም ጸጉሮች የተሸፈነ ነበር፡፡ ቢያንስ አንድ ፓውንድ የሚመዝን መሆን አለበት፡፡ ቀፈፈኝና ጨፈለኩት፡፡ የውሃውን በርሜል



@BOOKALEM

ጨምሮ ማንኛውንም ነገር ከጀልባው ውስጥ አራገፍን፡፡ ውሃው የወይን ጠጅ መስሎ ነበር፡፡ እንዳይበላሽ በማለት ኢዮአስ ብዙ ፐርማንጋኔት ጨምሮበት መሆን አለበት፡፡ የከብሪት እንጨቶችና አንድ መጫሪያ ጥብቅ ብለው በተዘጉ ጠርሙሶች ውስጥ አገኘን፡፡ ኮምፓሱ ከልጅ መጫወቻ አሻንጉሊት የማይሻል ነበር፡፡ የጀልባው ምሰሶ ከፍታ ሁለት ያርድ ተኩል በቻ እስከሆነ ድረስ፣ የዱቄት ከረጢቶቹን በአግድመት አቅጣጫ በማድረግ ለማጠናከር ያህል የከፈቱን ዙሪያ በገመድ ሰፋነው፡፡ ሦስት ማዕዘን የሆነች አንዲት ትንሽ የአቅጣጫ ማስተካከያ ቢጤ መሣሪያ ሠራሁ፡፡ የነፋስ አቅጣጫ ለመከተል ትረዳናለች፡፡

ምሰሶውን ለመትከል በምንዘጋጅበት ወቅት የጀልባው ሥር ጠንካራ አለመሆኑንም ተመለከትኩ፡፡ የምነሰው መትከያ ጉድጓድ በጠቅላላው ተበልቶ ነበር፡፡ መሪውን ይደግፈው በነበረው እርፍ ውስጥ ቪቴዎቹን ለማሰር ሳስገባ እንጨቱ እንደቅቤ የቦከቦከ ስለነበር በቀጥታ ወደ ውስጥ ጠለቀ፡፡ ጀልባዋ የበሰለበሰች ነበረች፡፡ ያ የውሻ ልጅ ኢዮአስ ወደ ሞታችን ልኮናል፡፡ ይህን ከእነርሱ ለመሸሸግ መብት ስለማይኖረኝ፣ ሌሎቹም እንዲመለከቱት አደረግሁ፡፡ ምን ማድረግ ይሻለናል? ኢዮአስ ሲመለስ አንድ የተሻለች ጀልባ እንዲፈልግ እንጠይቃለን፡፡ መሣሪያውን እንግፈፈውና፣ ከዚያም እኔ ገጀራና ጨቤ ታጥቄ ሌላ ጀልባ ለመፈለግ ከእርሱ ጋር ወደ መንደሩ እንሔዳለን፡፡ ራሴን ለትልቅ አደጋ ማጋለጥ መሆኑ ይሰማኛል፡፡ ያም ሆኖ በዚያች የሬሣ ሣጥን ውስጥ ወደባሕር ከመግባት የከፋ አይሆንም፡፡ በቂ ምግብ የሚሆነን ማለት አንድ ትልቅ ጠርሙስ ዘይትና፣ አንድ ሣጥን ዱቄት ነበረን፡፡ በዚህም ረጅም ጉዞ ለመሸፈን እንችላለን፡፡ በተረፈ ግን፣ በዛሬው ጧት አንድ እንግዳ ትርዒት ተመለከትን፡፡ ግራጫ ፊት ያላቸው የዝንጀሮ መንጋዎች ጸጉራማ ከሆኑ ጥቁር ፊት ካላቸው ዝንጀሮዎች ጋር ጦርነት ገጠሙ፡፡ ጦርነቱ በመፋፋም ላይ እንዳለ ማቹሬ ጭንቅላቱን አንድ ዝንጣይ ቅርንጫፍ ስለመታው የትልቅ ፍሬ ያህል አብጦ ነበር፡፡

እዚህ ከመጣን አምስት ቀንና አራት ሌሊት ሆነን፡፡ ዛሬ ማታ ዶፍ የሆነ ዝናም ጣለ፡፡ በጫካ የሙዝ ቅጠሎች አንድ መጠለያ ሠራን፡፡ እንደ ቫርኒሽ በሚያሙለጨልጩት ቅጠሎች ላይ ውሃው ወዲያው እየተንኳለለ ስለሚወርድ ከእግሮቻችን በስተቀር ደረቅ ነበርን፡፡ ጧት ቡናየን በመጠጣት ላይ እንዳለሁ፣ ኢዮአስ ምን ዓይነት ተንኮለኛ እንደነበር አሰብኩ፡፡ ይህችን የበሰበሰች ጀልባ በመስጠት በሞኝነታችን ተጠቀመብን! ለአምስተ መቶ ወይም ለአንድ ሺ ፍራንክ ሲል ሦስት ሰዎችን ወደ ዕውነተኛ ሞት ይልካል፡፡ ሌላ ጀልባ እንዲሰጠን ካደረግን በኋላ እርሱን ካልገደልኩ መቸውንም ይገርመኛል፡፡

ትንሿን ዓለማችንን የአሞራዎች ጩኸት አሸበራት፡፡ እንደዚህ ለመሰለው የሚሰቀጥጥና ደም የሚያረጋ ጩኸት መንሥዔው ምን እንደሆነ ማቹሬ ገጀራ ይዞ



@BOOKALEM

እንዲፈልግ ነገርኩት፡፡ ከአምስት ደቂቃ በኋላ ተመለሰና እንድከተለው ጠራኝ፡፡ በግምት አንድ መቶ ሃምሳ ያርድ ርቀት ላይ ካለ ቦታ ስንደርስ፣ ከአንድ ትልቅ እውራ ዶሮ በእጥፍ የሚበልጥ ዥግራ ወይም ዳክዬ የሚመስል በአየር ላይ ተንጠልጥሎ አየሁኝ፡፡ በገመድ ሸምቀቆ ቢያዝም፣ ጥፍሮቹ አንድ ቅርንጫፍ ላይ የሙጥኝ ብለው ነበር፡፡ ትዕግሥት አስጨራሽ ጩኸቱን ለማቆም በአንድ የገጀራ ውዝግዝግ አንገቱን ቀላሁት፡፡ ከብደቱ ቢያንስ ዐሥራ አራት ፓውንድ እንደሚሆን ገመትኩ፡፡ ልንበላው ወሰን፡፡ ግን ወጥመዱ እዚያ የተቀመጠው በአንድ ሰው መሆኑ ስለማይቀር ከእርሱ ሌላ ተጨማሪ ሕይወት መኖር እንዳለበት ገመትን፡፡ ዙሪያውን ለመቃኘት ሔድንና አንድ አስደናቂ ነገር ተመለከትን፡፡ ከቅጠሎችና ከሐረጎች የተተበተበ ዐሥራ ሁለት ኢንች ከፍታ ያለው አንድ ወጥመድ አግድም ተዘርግቶ ነበር፡፡ አለፍ አለፍ እያሉ በሮች ሲኖሩት፣ በእነርሱም ላይ ማሳሳቻ ጭራሮዎች ተረብርበባቸው ከመዳብ ሽቦ የተሠሩ ሸምቀቆዎች ተቀምጠባቸው ነበር፡፡ እንደ ገመትኩት ከሆነ አውሬው ወደ ወጥመዱ ውስጥ ሮጦ ከገባ በኋላ መሹለኪያ ለመፈለግ በዚያ ላይ እንዲራመድ ነበር፡፡ በሩን ሲያገኝና ወደ ውስጥ ለመግባት ሲጀምረ ሸምቀቆው እግሮቹን ስለሚይዙት አዳኙ መጥቶ እስኪያገኘው ድረስ ወጥመድ ውስጥ የገባው እንስሳም ሆነ ወፍ በአየር ላይ ይንጠለጠላል፡፡

ይህ እንግዲህ ሰላምን የሚያሳጣ ግኝት ነበረ፡፡ ወጥመዱ በሚገባ የተሠራና ፍጹም አዲስ ስለሚመስል፣ የመጋለጥ አደጋ ላይ እንደሆንን ተሰማኝ፡፡ እሳት ማንደድ የለብንም፡፡ ወጥመዶቹን የሚጠብቅ አንድ ዘበኛ ለማቆም ወሰንን፡፡ ጀልባዋን በዛፍ ቅርንጫፎች ሥር ደበቅንና ስንቃችንንም በጫካው ውስጥ ሸሸግን፡፡

በሚቀጥለው ቀን አራት ሰዓት ላይ በጥበቃ ተረኝነት ላይ ነበርኩ፡፡ ጅግራም ሆነ ሌላ ነገር፣ ያን አሞራ ባለፈው ሌሊት በልተነዋል፡፡ መረቁ ግሩም ነበር፣ ሥጋውም ይጥማል፡፡ እያንዳንዳችን ሁለት ሣህን ሙሉ በላን፡፡ እዚህ በጥበቃ ላይ እንደነበርኩ እያንዳንዳቸው ትላልቅ ቁራጭ ቅጠሎች ወደ አንድ ግዙፍ ኩይሣ የሚያመላልሱ ግዙፍና ጥቋቁር ጉንዳኖች አጋጠሙኝና በአድናቆት ተዋጥኩ፡፡ ጉንዳኖቹ ቁመታቸው ከግማሽ ኢንች በላይ ሲሆን፣ የሚቆሙትም በቅልጥሞቻቸው በጣም ቀጥ ብለው ነበር፡፡ ቅጠሎቻቸውን ወደሚቆርጡበት አትክልት ተከተልኳቸውና አንድ ሰፊ ድርጅት ይመስል በሥራ ላይ እንዳሉ ተመለከትኩ፡፡ በመጀመሪያ ቁራጮቹ ብቅ ይላሉ፡፡ መቀረጣጠፍ ካልሆነ በስተቀር ምንም ነገር አይሠሩም፡፡ ከእነዚያ የሙዝ ኮባዎች የመሰሉ ሰፋፊ ቅጠሎች ውስጥ እየገቡ በከፍተኛ ፍጥነት በመከርተፍ በሚያስገርም ጥበብ እኩል በሆነ መጠን ይቆራርጡና ወደ መሬት ይጥሏቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ዘራቸው ተመሳሳይ ሆኖ ግን ትንሽ ለየት ያሉ የጉንዳን ሰልፈኞች ከሥር በኩል ነበሩ፡፡ በአገጮቻቸው ጎንና ጎን ቁልቁል የወረደ አንድ ግራጫ መስመር ነበረባቸው፡፡ እነዚህ ጉንዳኖች ግማሽ ከብ



@BOOKALEM

ሠርተው ተሸካሚዎቹን ይቆጣጠሩ ነበር፡፡ ተሸካሚዎቹ በሰልፍ ሆነው ከቀኝ በኩል ይመጡና ከዚያም ወደ ኩይሳቸው አቅጣጫ በስተግራ በኩል ያመራሉ፡፡ መጀመሪያ ከዚያ ይሸከሙና በኋላ በሰልፍ ይገባሉ፡፡ ግን አልፎ አልፎ ጭነታቸውን ተሸክመው ወደ ሰልፉ ለመመለስ ከሚያደርጉት ጥድፊያ የተነሣ የትራፊክ መጨናነቅ ነበር፡፡ ሆኖም ሠራተኞቹ ጉንዳኖች የተወሰነ ቦታቸውን እንዲይዙ ‹የፖሊስ› ጉንዳኖች እየገፉ ተርታ ያስገቧቸዋል፡፡ ምን ዐይነት ከባድ ጥፋት ፈጽሞ እንደነበረ ግልጽ ባይሆንልኝም ከሠራተኞቹ ጉንዳኖች አንደኛውን፣ ሁለት የፖሊስ ጉንዳኖች ከሰልፉ ውስጥ ጎትተው አወጡና አንደኛው ጭንቅላቱን በጥሶ ሲጥለው፣ ሌላው ደግሞ ከወገቡ ላይ ሰውነቱን ለሁለት ቆረጠው፡፡ ከዚያም ፖሊሶቹ ሁለት ሠራተኛ ጉንዳኖች አቆሙና ቁርጥራጭ ቅጠሎቻቸውን አውርደው በአግሮቻቸው ጉድጓድ አስቆፈሯቸው፡፡ በመጨረሻም የተገደለው ጉንዳን ሦስት ከፍሎች፣ ማለት ጭንቅላት፣ ደረትና የቀረውም ተጨማምሮ ተቀበረና አፈር ለበሰ፡፡

ይህችን ትንሽ ዓለም ተመልከቼ ፖሊሶቹ ቁጥጥራቸውን የሚያከናውኑት እስከ ኩይሳው መጨረሻ ድረስ ይሆናል በማለት በጠቅላላው በአድናቆት ተመስጬ በመከታተል ላይ እያለሁ ነበር አንድ ድምፅ፣ «እንዳትንቀሳቀስ አለበለዚያ ትሞታለህ፡፡ ቀኝ ኋላ ዙር» ሲል የሰማሁት፡፡ ከወገቡ በላይ ራቁቱን ሆኖ ካኪ ቁምጣ ሱሪ የለበሰና ቀይ ቆዳ ቦት ጫማ ያደረገ፣ ረሽ ጠመንጃ የያዘ አንድ ሰው ቆሞ ነበር፡፡ የዐይኖቹ ዙሪያና አፍንጫው ደማቅ ሰማያዊ በሆኑ ውቅራቶች የቸኘርጎረጎረ፣ በጣም ወፍራም ሆኖ ቁመቱ መጠነኛ፣ ፀሐይ ያበለዘው ራሰ በራ ነበር፡፡ ግንባሩ መካከል አንድ የትኋን ምሥል ተወቅሯል፡፡

«መሣሪያ ታጥቀሃል?»

«የለኝም፡፡»

«ብቻህን ነህ?»

«አይደለሁም፡፡»

«ስንት ናችሁ?»

«ሦስት፡፡»

«ወደ ጓደኞችህ ውሰደኝ፡፡»

«አልችልም፣ ምክንያቱም ከእነርሱ አንደኛው ካርባይን ስላለው አስተሳስብህን ከማወቄ በፊት እንድትገደል አልፈልግም፡፡»

«አሃ! እንግዲያውማ ሳትንቀሳቀስ ዝግ ብለህ አውራኝ፡፡ ሦስቱ ከሆስፒታል ያመለጣችሁት ናችሁ?»

«አዎ»



@BOOKALEM

«ፓፒዮ የሚባለው የትኛው ነው?»

«እኔ ነኝ።»

«መልካም የእናንተ ማምለጥ በመንደሩ ውስጥ ለብጥብጥ ምክንያት ሆኗል! ነፃ ከወጡት እስረኞች ከፊሎቹ እንደገና ወህኒ ቤት ውስጥ ናቸው።» ቀረብ አለና የጠመንጃውን አፈ ሙዝ ወደ መሬት ዘቅዝቆ እጁን እየዘረጋ «ባለውቅራታሙ ብራቶን እኔ ነኝ። ስለ እኔ ሰምተሃል?» አለ።

«አልሰማሁም። ግን ከአዳኞቹ ወገን እንዳልሆንክ ገብቶኛል።»

«ልክ ነህ። አሞራዎች ለመያዝ እዚህ ወጥመድ አስቀምጣለሁ። እናንተ ካልሆናችሁ ድመት አውርዶ በልቶት መሆን አለበት።»

«እኛ ነበርን።»

«ትንሽ ቡና ትፈልጋለህ?» አለና በጀርባው ከተሸከመው ጥቅል አንድ ፔርሞስ አወጣና አንድ ጉንጭ ሰጥቶኝ ለራሱም ትንሽ ጠጣ።

«ና ጓደኞቼን ላገናኝህ» አልኩት

ተከትሎኝ መጣና ከእኛ ጋር ተቀመጠ። ካርባይን በመያዛችን ለቅቄበት ስለነበረው ፍርሃት ሣቀ። «ካርባይን ይዛችሁ ማምለጣችሁን አዳኞቹ ከዐወቁ ስለማይከታተሏችሁ ነው ያመኗችሁ» አለ።

ጊያና ውስጥ ለሐያ ዓመታት እንደኖረና ከአምስት ዓመታት በፊት ከእሥር ቤት መለቀቁን ተረከልን። ዕድሜው ዐርባ አምስት ዓመት ነበር። በሞኝነት ፊቱን በውቅራት አኸሮጎርጉሮት ስለነበር ወደ ፈረንሣይ እመለሳለሁ የሚለውን ሐሳብ እርግፍ አድርጎ ለመተው ተገድዷል። የጫካውን ኑሮ በመውደዱም ውሎው በዚሁ አካባቢ ነበር። የእባብና፣ የአቦ ሸማኔ ቆዳዎች፣ ቢራቢሮዎች መሰብሰብና ከዚያም ይበልጥ እኛ በልተነው የነበረውን ዓይነት አሞራ የመሰሉ ከነነፍሳቸው ይይዝ ነበር። ከሁለት መቶ እስከ ሁለት መቶ ሃምሳ ፍራንክ ይሸጣቸዋል። ልከፈለው ብየ ሰጠሁት፣ ግን በቁጣ አልቀበልም አለ። ከዚያም ስለ አሞራው ሁኔታ ነገረን። «ይህ የዱር አሞራ ወይም የዶሮ ዘር ሰው ፍጹም አይቶ እንደማያውቅ ግልጽ ነው። ይሁንና አንዱን በምይዝበት ጊዜ ወደ መንደር እወስድና የዶሮ ርቢ ላለው ሰው እሸጠዋለሁ። የእርሱ ዓይነት አሞሮች በጣም ተፈላጊዎች ናቸው። እየውልህ፣ ክንፉን አትሰብርም። ምንም ነገር አታደርገውም። ቀኑ እንደመሸ ብቻ ዶሮዎች ቤት ወስደህ አስቀምጠው። በሚቀጥለው ቀን ጧት መዝጊያውን ከፍተህ ሲካካዎቹና አውራ ዶሮዎቹ ሲወጡ ዶሮዎቹን የሚቆጥር በመምሰል ከፊት ለፊታቸው ቆሞ ታየዋለህ። ከእነርሱ ጋር አብሮ በመልቀም በአካባቢው ጫካ ላይና ታች እያለ ለመጠበቅ ይከተላቸዋል። እንደ አንድ ጥሩ የውሻ ዘበኛ ማለት ነው። ምሽት ሲመጣ በዶሮዎቹ ቤት መዝጊያ ይቆምና ይቆጣጠራል። ምናልባት አንድ ወይም ሁለት



@BOOKALEM

ዶሮዎች ቢኀድሉ እንዴት እንደሚያውቅ ራሱን የቻለ ምስጢር ነው፣ ፍለጋ ይሔዳል፡፡ እንዳገኛቸውም፣ ሲካካም ትሁን አውራ ዶሮ ወደ ቤት የመመለሻ ሰዓት መሆኑን ለማስተማር ሲል በሹል ከምቢው እየጠቀጠቀ ወደ ማደሪያቸው ያሰግራቸዋል፡፡ አይጦችን፣ እባቦችን፣ አይጠመንጦችን፣ ሽረሪቶችን ትላትሎችን ይገድላል፡፡ እንደዚሁም አንዲት ጭልፊት ሰማይ ላይ ከታየች፣ በዚያው ወቅት እሱ ጭልፊቷን ወደ ሰማይ አንጋጦ እየተመለከተ ዶሮዎቹ እንዲደበቁ ያጣድፋቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ ፍጹም አይኮበልልም፡፡»

ልክ እንደ ማንኛውም ተራ አውራ ዶሮ ነበረ ይህን ታሪከኛ አሞራ የበላነው፡፡

ኢዮአስ፣ ሌንፍሌና ሠላሳ ያህል ነፃ እሥረኞች በቅዱስ ላውረን ፖሊስ ጣቢያ እሥር ቤት ውስጥ ገብተው ስለእኛ ማምለጥ እየተመረመሩ መሆናቸውን ብሪቶኑ ነገረን፡፡ ዓረቡም እንደዚሁ ተባባሪ ይሆናል በሚል ጥርጣሬ አንድ ክፍል ወስጥ ተዘግቶበት ነበር፡፡ ያደነዘዙት ሁለት ምቶች ለጉዳት አላደረሱትም፣ ግን ዘበኞቹ ጭንቅላታቸው በመጠኑ አብጦ ነበር፡፡ «እኔ እስረኞችን ለማስመለጥ ተባባሪ እንደማልሆን ሁሉም ሰው ስለሚያውቅ ማንም አያስቸግረኝም» አለና፣ ኢዮአስ ግን መናጢ መሆኑን ነገረን፡፡ በበኩሌም ስለ ጀልባዋ ሁኔታ ሳጫውተው ሊያያት ይችል እንደሆነ ጠየቀኝ፡፡

ሲመለከታት፣ «ያ የውሻ ልጅ! የላካችሁ ወደ ሞት ነበር! ይህች ጀልባ በባሕር ላይ አንድ ሰዓት አትቆይም፡፡ የመጀመሪያው ትልቅ ማዕበል ለሁለት ይከፍላታል፡፡ ምንም ነገር ይሁን በዚህች ተልካሻ ጀልባ እንዳትሔዱ፡፡ ራስን በራስ መግደል ይሆናል» ብሎ ጮኸ፡፡

«ታዲያ ምን እናድርግ?»

«ገንዘብ አላችሁ?»

«አዎ!»

«ምን እንደምታደርጉ እነግራችኋለሁ፤ እንዲያውም እረዳችኋለሁ ማለቱ ይመረጣል፡፡ በእርግጥም መረዳት ይገባችኋል፡፡ የማደርገውም ያለ ምንም ክፍያ ነው፤ ምክንያቱም አንተና ጓደኞችህ ሲሳካላችሁ ለማየት እፈልጋለሁ፡፡ ከሁሉ በፊት፣ የፈለገው ነገር ይሁን ወደ መንደሯ አትሒዱ፡፡ አንድ ጥሩ ጀልባ ለማግኘት ወደ ፒገን ደሴት ማምራት ይኖርባችኋል፡፡ በደሴቷ ውስጥ ሁለት መቶ ያህል ቆማጦች ይኖራሉ፡፡ ሐኪምም ሆነ ሌላ ማንም ጤነኛ ሰው ምንጊዜም ወደዚያ አካባቢ አይሔድም፤ ዘበኞች የሉም፡፡ በየጊዜው ጧት በሁለት ሰዓት ለሐያ አራት ሰዓታት የሚበቃ የምግብ ራሽን አንድ ጀልባ ያመጣላቸዋል፡፡ የሆስፒታሉ ጤና ረዳትም አንድ ሣጥን መድኃኒት ለሌሎች ሁለት ጤና ረዳቶቹ ያስረክባል፡፡ እነርሱም እንደዚሁ ቆማጦች ናቸው፡፡ የደሴቷን



@BOOKALEM

ነዋሪዎች የሚያከሙት እነርሱ ብቻ ናቸው። ምን ጊዜም ወደ ደሴቷ የሚሔድ ዘበኛ የለም፣ ሰው አዳኝ የለም፣ ቄስ የለም፣ ማንም ሰው ወደዚያ ዝር አይልም። ቆማጦቹ የሚኖሩት ራሳቸው በሠሯቸው ትናንሽ የሣር ጎጆዎች ውስጥ ሲሆን፣ በሕብረት የሚሰበሰቡበት አንድ የጋራ አዳራሽ አላቸው። የዘወትር ምግባቸውን ለማሟላት ዶሮዎችና ዝዮች ያረባሉ። ከደሴቷ ውጭ ምንም ነገር በግልጽ አይሸጡም። ግን ከቅዱስ ላውረን፣ ከቅዱስ ዮሐንስና በዳቾ ጊያና አልቢና ውስጥ ከሚገኙ ቻይናውያን ጋ የኮንትሮባንድ ንግድ ያካሒዳሉ። ሁሉም ነፍስ ገዳዮች ናቸው። ብዙውን ጊዜ እርስ በርሳቸው አይገዳደሉም። ይሁንና ከደሴቷ ውጭ ሲሔዱ ብዙ ወንጀሎች ይፈጽሙና ከዚያ በኋላ ለመሰወር ይመለሳሉ። ለዚህ ተልዕኳቸው ከጎረቤት መንደር የሰረቋቸው ጥቂት ጀልባዎች አሏቸው። እስከፊ ወንጀል የሚፈጽሙት ደግሞ ጀልባ ለማግኘት ነው። ከፒገዮን ደሴት በሚመጣው ወይም በሚሔደው በማንኛውም ነገር ላይ ዘበኞቹ ይተኩሳሉ። ቆማጦቹም ጀልባዎቻቸው እንዳይታዩ ድንጋይ በመሙላት ማስቀመጥና እንደገና ሲያስፈልጓቸው ጠልቀው በመውረድ ቋጥኞቹን ገልብጠው ጀልባዎቹ ወደ ላይ እንዲንሳፈፉ ማድረግ ነው። ከየትኛውም የፈረንሣይ ክፍልና ከማንኛውም ዓይነት ጎሣ የተውጣጡ ሕዝቦች በደሴቷ ውስጥ ይገኛሉ። ይህች የእናንተ ጀልባ ጥሩነቷ ለማሮኒ ወንዝ ብቻ ያውም ጭነት ሳታበዛ ሲሆን ወደ ባሕር ለመውጣት ግን፣ አንድ ሌላ ሻል ያለ መፈለግ አለባችሁ። ለዚህም የሚመረጠው ቦታ የፒገዮን ደሴት ነው።»

«እዚያ እንዴት እንደርሳለን?»

«እንደዚህ ነው - ወንዙን ወጥተን ደሴቷን ለማየት እስከምንችል ድረስ ከእናንተ ጋር አብሬ እሔዳለሁ። ብቻችሁን ፍጹም ልታገኟት አትችሉም፣ ወይም ልትሳሳቱ ትችሉ ይሆናል። ከወንዙ አፍ ስድሳ ማይል ስለሚሆን ወደ ኋላ መመለስ ይኖርባችኋል። ከቅዱስ ላውረን ባሻገር ሐያ ማይል ይሆናል። ጀልባየን ከእናንተ ጋር እናቆራኛታለን። በተቻለ መጠን እስከትቃረቡ እሸኛችሁና ከዚያ በኋላ በራሴ ጀልባ ሆኜ ወደ ኋላ እመለሳለሁ። ከዚያም ወደ ደሴቷ ታመራላችሁ።»

«ለምን ከእኛ ጋር ወደ ደሴቷ መምጣት አትችልም?»

«አ፣ የእግዚአብሔር ያለህ፣ ወደ ፒገዮን ደሴት ከምትመለሰው የአስተዳደሩ ጀልባ የመሸጋገሪያ ድልድይ እግሬን ለማሣረፍ ሞከሬ ነበር። ጠራራ ቀን ስለነበር በዚያ ጊዜ ያየሁት ይሰቀጥጠኛል። ስለዚህ ይቅርታ አድርግልኝና ፓፒዮ፣ በዚያች ደሴት ላይ ዳግመኛ ፍጹም እግሬን አላሣርፍም። ምን እንደሚሰማኝ መሸሸግ ስለማልችል ከምጠቅማችሁ ይልቅ ይበልጥ ጉዳት አደርስባችኋለሁ።»

«መቼ እንሔዳለን?»

«ሲመሽ።»



@BOOKALEM

«አሁን ስንት ሰዓት ነው?»

«ዘጠኝ ሰዓት፡፡»

«እሺ፡፡ ለትንሽ ጊዜ እተኛለሁ»

«አይሆንም፡፡ አትተኛ፡፡ ጀልባዋን መጫን ይኖርብሃል፡፡»

«አይሆንም፡፡ የምሔደው ጀልባዋ ባዶ እንደሆነች ነው፡፡ ከዚያ በኋላ እዚህ ቆይቶ ጓዛችንን ወደሚጠብቀው ከሎሲዎ ተመልሼ እመጣለሁ፡፡»

«አይቻልም፡፡ ይህን ቦታ በጠራራ ቀን እንኳ ቢሆን እንደገና በጭራሽ አታገኘውም፡፡ በተጨማሪ፣ ምንጊዜም ቢሆን በቀን ወንዙ ላይ እንዳትታይ፡፡ አሁንም ገና እየፈለጓችሁ ነው፡፡ ወንዙ አሁንም ገና በጣም አደገኛ ነው፡፡»

ምሽት መጣ፡፡ ጀልባውን ለመፈለግ ሔደና ከእኛ ጋር አቆራኘናት፡፡ ከሎሲዎ መሪውን ከያዘው ብራቶን ቀጥሎ፣ ማቼሬ በመካከል፣ እኔ ደግሞ ከፊት በኩል ተቀመጥኩ፡፡ ጅረቷን ለመውጣት ችግር ስለነበረብን፣ ወደ ወንዙ አፍ በምንደርስበት ወቅት ጨለማ ጋረደ፡፡ የቀይ ቡናማ የሆነች ግዙፍ ፀሐይ ከባሕሩ ባሻገር ትንቀለቀል ነበር፡፡ ግርማ ሞገስ ያለው ወንዝ ሐምራዊና ብር የሚመስሉ ጨረሮችን እያፈናጠቀ ባሕሩን ለመገናኘት ሲገሠግሥ ከፊት ለፊት እስከ ዐሥራ ሁለት ማይል ርቀት ግልጽ ሆኖ ማየት ቻልን፡፡

«ማዕበሉ በርዷል፡፡ በአንድ ሰዓት ውስጥ ግን እያየለ ስለሚመጣ ወደማሮኒ ለመውጫ እንጠቀምበታለን፡፡ በዚህ ዘዴ ያለብዙ ድካም ወደ ደሴቷ እንደርሳለን» «ወደፊት ግፉ፣ ወደ ወንዙ መካከል እንድንገባ በኃይል ቅዘፉ፡፡ ሲጃራ ማጨስ የለም፡፡» አለ ብራቶ፡፡ ወዲያው ጨለመ፡፡

ውሃውን በመቅዘፊያዎቹ እየሰነጣጠቅን ከማዕበሉ ጋር ተፈተለክን፡፡ ብራቶና እኔ በተመሳሳይ ቅኝት ስንስብ ማቼሬም የተቻለውን ይሞክራል፡፡ ወደወንዙ መካከል እየገፋን በገባን መጠን የሚነሣው ማዕበልም እየጨመረ መሔዱ ተሰማን፡፡ አሁን በፍጥነት እንንሣፈፍ ጀመር፡፡ ማዕበሉ እየጠነከረ በሔደ መጠን እኛንም በፍጥነት ይገፋን ነበር፡፡ ከስድስት ሰዓት በኋላ ወደ ደሴቷ በጣም ስለተቃረብን፣ በቀጥታ ወደ እርሷ አመራን፡፡ ደሴቲቱ ከሞላ ጎደል በወንዙ መካከል፣ ትንሽ ወደ ቀኝ ሲል የምትገኝ አንዲት ጥቁር ነጥብ ትመስላለች፡፡ ዝግ ባለ ድምፅ ብራቶ፣ «ያች ናት» አለ፡፡ በጣም ጨለማ ሌሊት ባይሆንም እንኳ ከውሃው በላይ ባለው ጭጋግ ምክንያት ከሩቅ ሆኖ እኛን ለማየት አስቸጋሪ ነበር፡፡ እየተጠጋን መጣን፡፡ የቋጥኞቹ ገመገም ግልጽ ሲሆን፣ ብራቶ ወደ ጀልባው ተዛወረና በፍጥነት ፈትቶ፣ «መልካም ዕድል ልጆች!» ሲል ሹክ አለን፡፡

«እናመሰግናለን፡፡»

«ምንም አይደል፡፡»



@BOOKALEM

ብራቶኑ መሪው ላይ ስለሌለ ጀልባዋ እንዳጋደለች ወደ ደሴቷ አመራች:: እንድትዞር ለማድረግ ሞከርኩ፣ ግን አልቻልኩም:: ወደ ውሃው ቁልቁል የተንጠለጠሉ ቅጠላቅጠሎች ጥግ እየገፋ ማዕበል ወሰደን:: ከድንጋጤ የተነሣ ወደ ኋላ ስቀዝፍ፣ በዚያ ፍጥነት በቅጠሎችና በቅርንጫፎች ፊንታ ከቋጥኞች ላይ ዐርፈን ቢሆን ኖሮ፣ እንከትከታችን ወጥቶ ማንኛውም ነገር ባበቃልን ነበር:: ማቹሬ ወደ ውሃው ውስጥ ዘለለና ጀልባዋን ጎትቶ ጥቅጥቅ ካለው ጫካ ሥር አበታት:: አንድ ኩባያ ሩም ተከፋፈልንና ሁለቱን ጓደኞቼን ጀልባው ላይ ትቼ፣ ብቻየን አሻቅቤ በውሃው ዳር ተቃናሁ:: ጫካዎቹን ወደ ኋላ እየመነጠርኩና መንገድ ላይ ባሉት ቅርንጫፎች ላይ የዱቄት ከረጢት ጨርቅ ትልታዮች በማሰር ኮምፓስ እንደያዝኩ መራመዴን ቀጠልሁ:: ከፊት ለፊቴ አንዲት ስልምልም ያለች መብራት ከማየቴ ወዲያው ድምፅ ሰማሁ፣ ከዚያም ሦስት የሣር ጎጆዎች ብቅ አሉ:: እንዴት መቅረብ እንዳለብኝ እስካላወቅኩ ድረስ ወደፊት እየተንቀሳቀስኩ እነርሱው እንዲያገኙኝ ወሰንኩ:: አንድ ሲጋራ አቀጣጠልኩ:: መብራቱ ብልጭ እንዳለ አንዲት ትንሽ ውሻ ወደ እኔ እየጮኸች መጣችና ባቴ ላይ ቦጨቀችኝ:: ብቻ ቆማጣ እንዳትሆን ብዬ አሰብኩ:: ታዲያ ደደብነቴ እንጂ ውሾችን ለካስ ቁምጥና አይዛቸውም ኖሯል!

«ማነው? . . . ማነህ ማርሴል ነህ እንዴ?

«ያመለጥኩ እስረኛ ነኝ::»

«እዚህ ምን ታደርጋለህ? ልትዘርፈን ነው? ከበርቴዎች መሰልንህ እንዴ?»

«አይደለም:: እርዳታ እፈልጋለሁ::»

«በነፃ ነው ወይስ በከፍያ?»

«አንዴ ዝም በል እንጅ ላሹዌት!»

ከጎጆዋ ውስጥ አራት ጥላዎች ብቅ አሉ::

«ረጋ እያልክ ተጠጋ ወዳጄ:: እርግጠኛ ነኝ ባለካርባይኑ ሰው ነህ:: ይዘኸው ከሆነ ከመሬት ላይ አስቀምጠው፣ እኛን የምትፈራበት ምንም ነገር የለም::»

«አዎ፣ እኔ ነኝ:: ግን ካርባይኑን አሁን አልያዝኩትም» በመጠኑ ቀረብ አልኩ:: አሁን ተጠግቼ ነበር፤ ግን ጨለማ ስለሆነ አቋማቸውን ማጣራት አልቻልኩም:: በየዋህነት እጄን ዘረጋሁ:: ማንም አልተቀበለኝም:: እንደዚህ የመሰለ ሰላምታ እዚህ እንደማይደረግ በጣም ዘግየት ብሎ ገባኝ:: ሊበክሉኝ አልፈለጉም::

«ወደ ጎጆዋ እንግባ» አለ ላሹዌት::

ጠረጴዛ ላይ በተቀመጠ አንድ ዘይት ፋኖስ ትንሿ ከፍል ታበራለች::



@BOOKALEM

«ተቀመጥ።»

በአንዲት ዱካ ላይ ተቀመጥኩ። ላሹዌት ሦስት ተጨማሪ ፋኖሶች አቀጣጠለና አንደኛውን በቀጥታ እኔ ፊት ለፊት ከሚገኘው አንድ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠው። የኮከነት ዘይቱ ጢስ የሚያንገሸግሽ ሽታ ነበረው። አምስቱም ቆመው ስለነበር መልካቸውን መለየት አልቻልኩም። እኔ ግን እነርሱ በፈለጉት ሁኔታ ከፋኖሱ ፊት ለፊት ነበረ የተቀመጥኩት።

ላሹዌትን ዝም በል ብሎ ተናግሮ የነበረው ድምፅ፣ «ላአንጎዊ፣ ወደ ዋናው አዳራሽ ሒድና፣ እዚያ እንድናመጣው ይፈልጉ እንደሆን አለቆቻችንን ጠይቅ። መልሱን ወዲያው ይዘህ ተመለስ። በተለይም ቶሲያ ፈቃደኛ መሆኑን እንድታረጋግጥ። ዕንቁላሎች እንድትውጥ ከማድረግ በስተቀር እዚህ ምንም የምትጠጣው ነገር ልንሰጥህ አንችልም» አለና፣ ዕንቁላል የተሞላበት አንድ ቅርጫት ከፊት ለፊቴ አስቀመጠ።

«ይቅርብኝ። አመሰግናለሁ።»

ከዚያም ከእነርሱ ውስጥ አንደኛው ወደ አጠገቤ መጥቶ ተቀመጠ። በዚህም የመጀመሪያውን ቆማጣ መመልከቴ ነበር። በጣም ያስቅቃል። ዘወር ላለማለት ወይም ስሜቴን ላለማሳየት ጥረት ማድረግ ነበረብኝ። ሥጋውን አጥንቱም ሳይቀር ሙሉ በሙሉ አፍንጫው ተቦጭቆ ሒዷል። ከፊቱ መካከል አንድ ቀዳዳ ብቻ አለው። ለማለት የፈለግሁት፣ ሁለት ቀዳዳዎች ሳይሆኑ፣ ያለው ጠገራ ብር የሚያክል አንድ ሰፊ ቀዳዳ ነው። በተጨማሪ ከቀኝ በኩል ያለው የታችኛው ከንፈሩ ተቦጭቆ ስለሔደ፣ ከላይኛው አገጩ ቁልቁል የወረዱ ሦስት ረጃጅም ቢጫ ጥርሶች ገጥጠዋል። በፋሻ የተጠቀለለ እጁን ጠረጴዛው ላይ አጋድሞታል። የቀኝ እጁ ነበር። ከግራ እጁ ውስጥ በተረፉት ሁለት ጣቶቹ አንድ ወፍራምና ረጅም ሲጃራ ይዟል። ቀለሙ አረንጓዴ ስለነበር የጠቀለለው በከፊል ከበሰለ የትምባሆ ቅጠል ሳይሆን አይቀርም። የግራ ዐይኑ ብቻ የዐይን ቆብ ነበረው። የቀኝ ዐይኑ ቆብ ከቦታው ጠፍቶ አንድ የተጠረመሰ ጠባሳ ከዐይኑ ጀምሮ በግንባሩ ላይ በመጋደም ወደ ተቆጣጠረው ግራጫ ጸጉሩ ውስጥ አልፎ ጉኗል።

«እንረዳሃለን። እዚህ አካባቢ ቆይተህ እንደ እኔ እንድትሆን አልፈልግም» አለ በተነፋነፈ ድምፅ።

«አመሰግናለሁ።»

«ስሜ የሐንስ ፕር ነው። ወደ ቅኝ ግዛት አስቃቂ ወህኒ ቤት መጀመሪያ ስመጣ ከአንተም ቆንጆ፣ ጤነኛና ጠንካራ ሰው ነበርኩ። ዐሥር ዓመታት እንዴት እንዳደረገኝ ተመልከት።»

«ማንንም የሚያከምህ ሰው የለም?»

«አዎ። የቹዋልሙግራ ዘይት መርፌ ራሴን በራሴ መውጋት ከጀመርኩ



@BOOKALEM

አንሥቶ በጣም ተሸሎኛል፡፡ ተመልከተው፡፡» ጭንቅላቱን አዞረና በግራው በኩል አሳየኝ፡፡ «እዚህ ላይ እየደረቀ ነው፡፡»

ለዚህ ሰው ከፍተኛ ሐዘን ተሰምቶኝ የጓደኝነት ምልክት ለማሳየት ጉንጩን ልነካ ስንቀሳቀስ፣ ወደ ኋላ አፈገፈገና፣ «ለመንካት ስላልተጠየፍከኝ አመሰግናለሁ፣ ግን ቆማጣን ፍጹም መንካት ወይም በእርሱ ሣህን መብላትና መጠጣት የለብህም» አለ፡፡ ይህ ሰው እንድመለከተው አደፋፍሮኝ ስለነበር ከቆማጣዎቹ ሁሉ የማስታውሰው የእርሱን ፊት ነው፡፡

«እንግዳው የታል?» ሲል፣ ከድንክ ብዙም የማይሻል አንድ በጣም አጭር ሰው በበሩ ተመለከትኩ፡፡ «ቶሲያንና ሌሎቹም ሲያዩት ይፈልጋሉ፡፡ ወደ ማዕከሉ አምጡት፡፡»

ዮሐንስ ፐር ብድግ አለና፣ «ተከተለኝ» አለ፡፡ ሁላችንም በጨለማው ውስጥ ጉዞ ጀመርን፡፡ አራት ወይም አምስት የሚሆኑት ከፊት ለፊት፣ እኔ ከዮሐንስ ፐር ቀጥዬ፣ ሌሎች ተጨማሪዎች ሰዎች ከኋላ ነበሩ፡፡ ከሦስት ደቂቃ በኋላ የደበዘዘች ጩረታ ብርሃን ወደምትታይበት ገላጣ ቦታ ደረስን፡፡ የደሴቷ ከፍተኛው ደልዳላ ቦታ ነበር፡፡ በመካከሉ አንድ ቤት አለ፡፡ ከሁለቱ መስኮቶች በኩል ብርሃን ይታያል፡፡ ሐያ የሚሆኑ ሰዎች የእኛን መምጣት ይጠባበቃሉ፡፡ መዝጊያው አጠገብ እንደ ደረስን እኛን ወደ ውስጥ ለማሳለፍ ወደ ኋላ አፈግፍገው ቆሙ፡፡ ምድጃ ከሚመስል ቦታ ተመሳሳይ ቁመት ባላቸው አራት ትላልቅ ድንጋዮች ተከብቦ እንጨት ይነድበት ከነበረና ርዝመቱ ሠላሳ ጫማና ስፋቱ ሃያ ሁለት ጫማ ከሆነ አንድ ክፍል ውስጥ ነበር የገባሁት፡፡ አዳራሹ ብርሃን የሚያገኘው ከሁለት ትላልቅ ፋኖሶች ነበር፡፡ ከነጭ ፊቱ ላይ ጥቋቁር ዐይኖች ያፈጠጡበት ዕድሜው የማያስታውቅ አንድ ሰው ከድንጋይ ዱካዎቹ በአንደኛው ላይ ተቀምጧል፡፡ ከእርሱ በስተጀርባ አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ደግሞ ሌሎች አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ነበሩ፡፡

«ቶስያን ኮርሲካዊው ነኝ፣ ፓፒዮ መሆን አለብህ፡፡»

«ነኝ፡፡»

«ልክ እንደእናንተ ከቅኝ ግዛት አሰቃቂ ወህኒ ቤት ወሬውም ፈጥኖ ይጓዛል፡፡ ካርባይንህ ወዴት አለ?»

«ወደ ወንዙ ወርውረነዋል፡፡»

«የት?»

«እኛ ከዘለልንበት ከሆስፒታሉ ግንብ ትይዩ፡፡»

«እንግዲያ መልሶ ለማግኘት ይቻላላ?»

«እንደዚያ ይመስለኛል፡፡ እዚያ ውሃው በጣም ጥልቅ አይደለም፡፡»



@BOOKALEM

«እንዴት ዐወቅከው?»

«የቆሰለውን ጓደኛየን ወደ ጀልባ ለመሸከም በውስጡ ሔደንበት ነበር።»

«ምን አጋጥሞት ነው?»

«ቅልጥሙን ተሰብሮ»

«ምን አድርገህለታል?»

«ቅርንጫፎች ስነጣጥቄ አሥሬለታለሁ።»

«ሥቃይ እየተሰማው ነዋ?»

«አዎ።»

«ወዴት ነው?»

«ጀልባ ውስጥ።»

«የመጣሁት ለእርዳታ ነው ብለሃል፣ ዕርዳታው ምን ዐይነት ነው?»

«የተሻለች ጀልባ።»

«እኛ ጀልባ እንድንሰጥህ ትፈልጋለህ እንዴ?»

«የምገዛበት ገንዘብ አለኝ።»

«ጥሩ፤ እንግዲያው የእኔን እሸጥልሃለሁ። አዲስ የሆነች ከፍተኛ ጀልባ ናት። ባለፈው ሳምንት ከአልቢና ሰርቂያት ነው። ጀልባ ሳትሆን ውቅያኖስ አቋራጭ መርከብ ናት። የሚጎድላት አንድ ነገር ብቻ ነው፣ ወለል። ግን በሁለት ሰዓት ውስጥ ጥሩ ዓይነት እንገጥምላታለን። ሲያስፈልግህ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር ታሟላለች። አንድ መሪ፣ ከጠንካራ እንጨት የተሠራ አንድ ባለዐሥራ ሦስት ጫማ ተራዳና አንድ አዲስ ከባድ የነፋስ ሸራ አላት። ለዚህች ምን ትከፍለኛለህ?»

«አንተ ምን ያህል እንደምትፈልግ ንገረኝ። እዚህ የዕቃዎች ዋጋ ስንት እንደሚያወጣ አላውቅም።»

«ካለህ ሦስት ሺ ፍራንክ። ከሌለህ ነገ ሌሊት ሔደህ ካርባይኑን ፈልግና በለውጡ ጀልባዋን እሰጥሃለሁ።»

«አልፈልግም። መከፈሉን እመርጣለሁ።»

«እሺ። በሺያጩ ተስማምተናል። ቡና አምጡልን ላፑስ!»

እኔን ለመውሰድ መጥቶ የነበረው ከድንክ የማይሻለው ላፑስ፣ ከምድጃው በላይ ከሚገኘው ግድግዳ ላይ ወደ ተሠራ አንድ ቁምሣጥን ሔደና አዲስ በሚያንጸባርቅ ንፁሕ ጎድጓዳ ሣህን ላይ ጠርሙስ ውስጥ የተቀመጠ ቡና ቀድቶ ምድጃው ላይ ጣደ። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሣህኑን አነሣና በኩባያዎቹ ቀዳ። ቶሲያን ከኋላው ወደ ተቀመጡት ሰዎች ሰገግ ብሎ ኩባያዎቹን አደለ። «አትሥጋ፣ ይህ ሣህን ለእንግዶች ብቻ ነው። በእርሱ የሚጠጡ ቆማጦች የሉም» በማለት ላፑስ ጎድጓዳ ሣህኑን አቀበለኝ።



@BOOKALEM

ሣህኑን ተቀበልኩና ጠጣሁ:: ከዚያም ጉልበቴ ላይ አሣረፍኩት:: በዚያው ወቅት አንዲት ጣት በሣህኑ ላይ መጣበቋን ተመለከትኩ:: ይህን በማይበት ጊዜ ነበር ላፑስ፣ «ወይ መከራ፣ ደግሞ አንድ ሌላ ጣት ጣልኩ:: ወዴት አባቷ ሔደች?» ያለው::

«ይህችውና» አልኩና ሣህኑን አሳየሁት::

መንጭቆ አነሣና አሳቱ ውስጥ ወረወራት:: «መጠጣት ትችላለህ:: የያዘኝ ደረቅ ቁምጥና ነው:: የማልቀው እየተቀራረጥኩ ነው፣ ግን አልሸትም፣ አስተላላፊም አይደለሁ» አለ:: የሚጠበስ ሥጋ ጠረን አወደኝ:: የእርሱው ጣት መሆን አለባት::

«ዝቅተኛ ማዕበል እስከሆነ ድረስ ቀኑን ሙሉ እዚሁ መዋል አለብህ:: ሒድና ለጓደኞችህ ንገራቸው:: የተሰበረውን ጓደኛህን ከጎጆዎቹ ወደ አንደኛዋ አምጣው:: ያላችሁን ማንኛውንም ነገር ከጀልባ ውስጥ አውጡና አስቀምጡት:: እዚህ ሊረዳችሁ የሚችል ማንም ሰው የለም:: ለምን እንደሆነም ይገባሃል» አለ ቶሲያን::

ወደ ባልደረቦቼ ተመለስኩና ክሎሲዎን ተሸክመን ወደጎጆዋ አመጣነው:: ከአንድ ሰዓት በኋላ ማንኛውም ነገር ከጀልባዋ ወጥቶ በጥንቃቄ ተቀመጠ:: ጀልባዋንና በተጨማሪ አንድ መቅዘፊያ በስጦታ እንድናበረክትለት ላፑስ ጠየቀኝ:: ሰጠሁትና እርሱ ከሚያውቀው አንድ ልዩ ቦታ ሊደብቃት ወሰዳት:: ሌሊቱ በፍጥነት ሔደ:: ሦስታችንም ቶሲያን በላከልን አዲስ ብርድ ልብሶች ተጠቅልለን ጎጆዋ ውስጥ ተኛን:: ብርድ ልብሶቹ ከፋብሪካ ሲወጡ በተጠቀለሉበት ወፍራም ወረቀት ውስጥ እንዳሉ ነበር:: እንደዚያ እንደተጋደምን ወደ ደሴቷ ከመጣን ጀምሮ ምን እንዳደረግኩና ከቶሲያን ጋር የቀናኘን የሽያጭ ስምምነት ለክሎሲዎና ለማቹሬ በዝርዝር አወራኋቸው::

«እንግዲህ ለማምለጥ በእርግጥ ስድስት ሺ ፍራንክ ሊያስወጣን ነው:: ግማሹን እኔ እከፍላለሁ ፓፒዮ፣ ወይም ያለኝን ሦስት ሺ» አለ ክሎሲዎ አፉ እንዳመጣለት::

«እዚህ ያለነው ስለገንዘብ ለመጨቃጨቅ አይደለም:: ገንዘብ እስካለኝ ድረስ እኔ እከፍላለሁ:: ከዚያ ደግሞ እናያለን::»

ሌሊት ብቻችንን ነበርን:: ሲነጋ ቶሲያን ወደእኛ መጣ:: «እንደምን አደራችሁ:: ወደ ውጭ ለመውጣት አትፍሩ:: እዚህ ማንም የሚያስቸግራችሁ ሰው የለም:: በወንዙ ላይ ስለሚንቀሳቀሱት የፖሊስ ጀልባዎች በደሴቷ አናት ከሚገኝ አንድ የካካዎ ዛፍ ላይ ሆኖ የሚጠባበቅ ሰው አለ:: እስካሁን ምንም አላየንም:: አንድ ነገር ሲያይ ወደ ታች ይመጣና ይነግረናል:: ካስፈለጋችሁ ፓፓያ ራሳችሁ ቁረጡ::

«የወለሉ ጉዳይ ከምን ደረሰ ቶሲያን?» አልኩት::

«የሕክምና ከፍሉን መዝጊያ ነቅለን እንገጥምለታለን:: የተሠራው ከወፍራምና ጠንካራ እንጨት ነው:: ወለሉ ሁለት ጣውላዎች ይፈልጋል:: ማታውኑ ጀልባዋን ወደ



@BOOKALEM

ላይ አውጥተናታል:: መጥተህ ተመልከታት::» ·

ሔድን:: ርዝመቷ ዐሥራ አምስት ጫማ የሆነ፣ አንድ የተራዳ መትከያ ጉድጓድና ሁለት አግዳሚ መቀመጫዎች ያሏት አዲስና ድንቅ የሆነች ጀልባ ነበረች:: ከባድ ስለነበረች ማቹሬና እኔ ሆነን ለመገልበጥ አቅቶን ነበር:: እንደዚሁም የነፋስ ሸራውና ገመዶቹም አዲስ ነበሩ:: ለበርሚል ውሃ መስቀያ የሚሆኑ ቀለበቶች ከጎን ይገኛሉ:: መሥራት ጀመርን:: በረጅም ቪቴዎችና በአራት የብረት ማገሮች በጥብቅ የተሠራ አንድ ጠንካራ ወለል ከፊት እስከ ኋላ ድረስ ከሰዓት በኋላ ተገጠመላት::

ቆማጦቹ ዙሪያችንን ከብ ሠርተው በፀጥታ ይመለከታሉ:: ምን ማድረግ እንደሚኖርብን ቶሲያን ይመራናል:: እኛም እንታዘዛለን:: በቶሲያን ፊት ላይ ምንም የቁስል ምልክት የለበትም:: በእርግጥም እንደማንኛችንም እንከን የሌለበት ይመስላል:: ግን ሲናገር በአንድ በኩል ያለው ፊቱ፣ ማለት የግራው ብቻ የሚንቀሳቀስ መሆኑን ተገነዘብኩ:: የእርሱም እንደዚሁ ደረቅ ቁምጥና መሆኑን ነገረኝ:: ከቀኝ እጁ ጀምሮ ግማሽ አካላቱ በድን እንደሆነና የቀኝ ባቱም በቅርብ ተቆርጦ እንደሚወድቅ ይጠብቃል:: የቀኝ ዐይኑ ልክ እንደ ጠርሙስ አንድ ቦታ የተተከለ ነበር:: ሊያይበት ይችላል፣ ግን ሊያንቀሳቅሰው አይችልም::

ማንም ሰው ይህን አሳዛኝ ዕድላቸውን ባያየው ምኞቴ ነው::

በመሥራት ላይ እያለሁ ከቶሲያን ጋር አወራ ነበር:: ሌላ ማንም የሚናገር ሰው የለም:: ሆኖም ከብረት ማዕዘኖች አንዱን ለማንሣት ስል ከመካከላቸው አንዱ፣ «አትንካቸው:: እንደኛውን ብረት እነቅላለሁ ስል ራሴን ቆርጬ ስለነበር ደሙን ለመጥረግ ብሞክርም አልተቻለኝም» አለ::

ሌላው ቆማጣ በላዩ ላይ ሩም አፈሰሰበትና በእሳት አቃጠለው:: ከዚያም እየደጋገመ እንደዚሁ አደረገ:: «አሁን ልትጠቀምበት ትችላለህ» አለ ሰውየው በመሥራት ላይ እንዳለ:: ቶሲያን ከሰዎቹ ለአንደኛው እንደዚህ አለው:: «አንተ ብዙ ጊዜ ከደሴቷ ውጪ ተመላልሰሃል:: ፓፒዮና ጓዶቹ ግን እንግዶች ናቸው:: ታዲያ እንዴት እንደሚያደርጉ አሰኪ ምከራቸው::»

«ዛሬ ማዕበሉ ፀጥ እንዳለ ይቆይና በዘጠኝ ሰዓት ላይ እየገፉ መሔድ ይጀምራል:: በዐሥራ ሁለት አካባቢ እስከ ወንዙ አፍ ድረስ ያለውን ስድሳ ማይል በሦስት ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለመሸፈን የሚረዳችሁ ኃይለኛ ማዕበል ይነሣል:: ከዚያም ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ጀልባችሁን ከአንድ ጠንካራ ዛፍ ጋር ደህና አድርጋችሁ በማሠር ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት የሚነሣውን ማዕበል መጠበቅ ይኖርባችኋል:: ይህም ማዕበል እስከ ንጋቱ ዐሥራ ሁለት ሰዓት ይቀጥላል:: ግን በዚያ ወቅት አትንቀሳቀሱ፣ ማዕበሉ ፍጥነት የሚጨምረው ቀስ በቀስ ነው:: በዐሥር ሰዓት ተኩል ወደ ወንዙ መካከል



@BOOKALEM

ግቡ። የሠላሳ ማይል ጉዟችሁን ለመፈጸም ከመንጋቱ በፊት አንድ ሰዓት ተኩል ይኖራችኋል። የመጨረሻ ዕድላችሁ ይህ ነው። ፀሐይ በዐሥራ ሁለት ሰዓት ብቅ ስትል ከባሕሩ ደርሳችሁ ጉዞ ትቀጥላላችሁ። ዘበኞቹ እንኳ ቢያዩዋችሁ፣ ሊይዟችሁ አይችሉም። ምክንያቱም በባሕሩና ወንዙ መገናኛ ላይ የሚደርሱት ማዕበሉ ሲመለስ ስለሆነ የአሸዋ ክምር ያግዳቸዋል። ሲያልፉት ስለማይችሉ እናንተ ይሳካላችኋል፣ ሀልውናችሁን የሚወስነው ይህን ግማሽ ማይል ቀድማችሁ መገኘት ነው። ይህች ጀልባ አንድ የነፋስ ሸራ ብቻ አላት። የእናንተስ ጀልባ ምን አላት?»

«አንድ ዋና የነፋስ ሸራና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራ።»

«ይህች ከባድ ጀልባ ናት። ከፊት ጀምሮ እስከ ምሰሶው የሚዘረጋ አንድ ባለ ሦስት ማዕዘን ሸራና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራ፣ እንዲሁም ሁለት ተጨማሪ ሸራዎች አሏት። ሸራዎቻችሁን በሙሉ ወጥራችሁ በቀጥታ ወደ ማዕበሎቹ ውስጥ ግቡ። ከወንዙና ከባሕሩ መገናኛ ላይ ሞገዱ ሁልጊዜ ከባድ ስለሚሆን፣ ጀልባዋን ለማርጋት ጓደኞችህን ከጀልባዋ ሥር ለጥ ብለው እንዲጋደሙ አድርግና አንተ መሪውን ግጥም አድርገህ በእጆችህ ጨብጥ። ገመዱን ከባትህ ላይ እንዳታስር። ግን በቀለበቱ ውስጥ አሳልፍና አንድ ጊዜ በእጅህ ላይ ጠምጥመህ ያዘው። የነፋሱ ኃይልና የማዕበሉ መጠን ተጨማምሮ የሚገለብጣችሁ መስሎ ቢታይህ ብዙም አትጨነቅ። ጀልባዋ በገዛ ራሷ ወዲያውኑ ሚዛኗን ትጠብቃለች። አትቁም። ዋናውን የነፋስ ሸራ ወደ ነፋስ አቅጣጫ አድርግና የሦስት ማዕዘኑንና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራውን ሳታወርድ መጓዝህን ቀጥል። ባሕሩ ፀጥ ሲል የነፋስ ሸራውን ለማውረድ ጊዜ ይኖርሃል። ከዚያም እንደገና ከሰቀልከው በኋላ መንቀሳቀስ ቀጥል። ለመሆኑ የጉዞህን አቅጣጫ ታውቀዋለህ?»

«አላውቀውም። የማውቀው ቢኖር ቬኔዙዌላና ኮሎምቢያ በስተሰሜን ምዕራብ በኩል መሆናቸውን ብቻ ነው።»

«ልክ ነህ። ግን ወደ ጠረፍ እንዳትመለስ ተጠንቀቅ። ከኛ ትይዩ ያለችው የዳች ጊያና እስረኞችን ሁሉ መልሳ ለፈረንሣይ ታስረክባለች። የእንግሊዝ ጊያናም እንደዚሁ ታደርጋለች። ትሪኒዳድ ግን አትመልሳችሁም። ሆኖም ከዚያ መቆየት የሚቻለው ሁለት ሳምንት ብቻ ነው። ቬኔዙዌላ ለአንድ ወይም ለሁለት ዓመት በመንገድ ሥራ ብርጌድ ውስጥ ካሠረቻችሁ በኋላ ትመልሳችኋለች።

በጥሞና አዳመጥኩት። በየጊዜው ከደሴቷ መውጣቱን ነገረኝ። ቆማጣ ስለሆነም በአጭር ትእዛዝ ዘወትር እየተባረረ ይመለስ ነበር። ከእንግሊዝ ጊያናዋ ጆርጅ ታውን ግን ፍጹም ርቆ እንዳልሔደ ተናገረ። በባዶ እግሩ ስለነበር ለማየት እንደቻልኩት ጣቶቹን በማጣቱ ነው እንጅ በግልጽ ቆማጣ የሚባል አልነበረም። የነገረኝን መመሪያዎች እንድደግማቸው ቶሲያን ጠየቀኝና አንድ ስሕተት ሳላደርግ ቃል በቃል



@BOOKALEM

መለስኩለት፡፡ በዚህ ነጥብ ላይ እንዳለን ዮሐንስ ፐር፣ «በተንጣለለው ባሕር ላይ ምን ያህል ጊዜ ማጥፋት ይኖርበታል?» አለው፡፡

በቀጥታ ራሴ መለስኩለት፡፡ «ለሦስት ቀናት ያህል ወደ ሰሜን ምሥራቅ እጓዛለሁ፣ ማለትም ወደ ሰሜን አቅጣጫ ከሚሔደው የውሃ አዙሪት ጋር፡፡ በአራተኛው ቀን ግን ወደ ሰሜን ምዕራብ አመራለሁ፡፡»

«ጎበዝ» አለ ቆማጣው፡፡ «ባለፈው ጊዜ እኔም እንደዚሁ ነበር ያደረግኩት፡፡ ወደ ሰሜን ምሥራቅ ለመሔድ ሁለት ቀን ብቻ አጠፋሁና እንግሊዝ ጊያና ደረስኩ፡፡ ወደ ሰሜን አቅጣጫ ሦስት ቀን ከተጓዝክ፣ ሰሜናዊ ትሪኒዳድን ወይም ባርባዶስን ታልፍና ቬኔዙዌላን እያካለልክ ሳታውቀው ኮሎምቢያ ወይም ኩራሶ ትደርሳለህ» አለ፡፡

«ጀልባህን ምን ያህል ነው የሸጥካት ቶሲያን?» ሲል ዮሐንስ ፐር ጠየቀው፡፡

«ሦስት ሺ፡፡ በጣም ብዙ ነው እንዴ?»

«አይደለም፡፡ ለዚህ አይደለም የጠየቅኩህ፡፡ ለማወቅ ብቻ ፈልጌ ነው፡፡ ገንዘቡን ታገኘለህ ፓፒዮ?»

«አዎ፡፡»

«የሚተርፍ ይኖርሃል?»

«የለኝም፣ ያለን ይኸው የጓደኛየ የክሎሲዎ ሦስት ሺ ፍራንክ ብቻ ነው፡፡»

«ሽጉጤን ትገዛኛለህ ቶሲያን?» አለና ዮሐንስ ፐር በማከታተል፣ «እነዚህን ጓዶች ለመርዳት እፈልጋለሁ፡፡ ምን ያህል ትከፍለኛለህ?» አለ፡፡

«አንድ ሺ ፍራንክ» አለና ቶሲያንም፣ «እኔም እንደዚሁ ልረዳቸው፣ እፈልጋለሁ ሲል ሐሳቡን ገለጸ፡፡

«ለማንኛውም ዕርዳታችሁ እናመሰግናለን» አለ ማቱሬ ወደ ዮሐንስ ፐር እየተመለከተ፡፡

«እናመሰግናለን» አለ ክሎሲዎም፡፡

እኔ ግን፣ በውስጤ ኃፍረት ስለ ተሰማኝ፣ «አይሆንም፣ መቀበል አልችልም፡፡ በምንም ምክንያት» አልኩ፡፡

ዮሐንስ ትኩር ብሎ ወደ እኔ ተመለከተና፣

«በዕርግጥ ምክንያት አለ እንጂ፡፡ ሦስት ሺ ፍራንክ ብዙ ገንዘብ መሆኑን ዐውቃለሁ፡፡ ያም ሆኖ ይህች ጀልባ ከፍተኛ ስለሆነች፣ ቶሲያን ለእናንተ በዚህ ዋጋ የሸጠላችሁ ቢያንስ ሁለት ሺ ፍራንክ ከስሮ ነው፡፡ ስለዚህ እኔም እንደዚሁ አንድ ውለታ ልውልላችሁ የማልችልበት ምክንያት የለም» አለ፡፡

ከዚያም አንድ በጣም ስሜት የሚነካ ጉዳይ ተከናወነ፡፡ ላሹዊት አንድ ባርኔጣ ከመሬት ላይ አስቀመጠና ቆማጦቹ ሁሉ እየመጡ ብሮችና ሳንቲሞች ይወረውሩ ጀመር፡፡



@BOOKALEM

ከየአቅጣጫው በመምጣት የመጨረሻው ዝቅተኛ ሰው ሳይቀር አንድ ነገር ያስቀምጣል:: አሁን በዕርግጥ አፍሬ ነበር:: ትንሽ የተረፈ ገንዘብ እንዳለኝ አሁን እንዴት አድርጌ ልነግራቸው እችላለሁ? ወይ አግዚአብሔር፣ ምን አጋጣሚ ነው! በዚህ በጎ አድራጎት መካከል ይህን መናገሩ ደግሞ ውርደት ነበር:: ከዚያም፣ ቅንጣት ጣት ያልነበረውና እጆቹ ተጎንድሸው የተጎማመደ አንድ ጥቁር የቲምበክቱ ተወላጅ እንደዚህ አለ:: «ገንዘብ ለእኛ ኑሮ አይረዳንም:: ለመቀበል ኃፍረት አይሰማችሁ:: ሁሉንም የምንጠቀምበት ለቁማር መጫወቻ፣ ወይም አንዳንድ ጊዜ ከአልቤና ወደ እዚህ የሚመጡ የቆማጣ ኮረዳዎችን ለመደለያ ብቻ ነው::» ይህ አነጋገር ኃፍረቴን ስላስወገደልኝ ገንዘብ እለኝ ማለቱን አርግፍ አድርጌ ተውኩት::

ቆማጦቹ የቀይ መስቀል ምልክት ባለበት አንድ ቅርጫት ውስጥ ሁለት መቶ የተቀቀሉ እንቁላሎች ሞልተው ሰጡን:: በዚያን ቀን ጧት ከዕለቱ የመድኃኒት ራሽን ጋር መጥቶላቸው የነበረው ያው ቅርጫት ነበር:: በተጨማሪ ቢያንስ እያንዳንዳቸው ስድሳ ፓውንድ የሚመዝኑ ሁለት ኤሊዎች ከነነፍሳቸው፣ የትምባሆ ቅጠሎች፣ ሁለት ፓኮ ከብሪትና አንድ መጫሪያ፣ መቶ ፓውንድ የሚመዝን አንድ ከረጢት ሩዝ፣ ሁለት ኬሻ ከሰል፣ ከሕክምና ክፍል የተወሰደች አንዲት ፔርሙዝና አንድ ደምበኛን ነዳጅ ሰጡን:: በዚህ ጎስቋላ ማኅበረሰብ ውስጥ ያለ ማንኛውም ሰው በእኛ አሥጊ ሁኔታ ስሜቱ ተነክቶ ሊረዳን ፈለገ:: የእኛ ማምለጥ ለእነርሱ እንደሆነላቸው ይመስሉ ነበር:: ጀልባዋ በመጀመሪያ እኛ ዐርፈንበት ወደ ነበረው አካባቢ ተጎተተች:: በባርኔጣው ውስጥ ያለውን ገንዘብ ሲቆጥሩት ስምንት መቶ ዐሥር ፍራንክ ሆነ:: የቶሲያን ያለብኝ ዕዳ አንድ ሺ ሁለት መቶ ፍራንክ ብቻ ነበር:: የገንዘብ መደበቂያ ቱቦውን ከሎሲዎ ሰጠኝና በሁሉም ሰው ፊት ከፈትኳት:: አንድ ባለ አንድ ሺ ፍራንክ ኖትና እያንዳንዳቸው ባለ አምስት መቶ ፍራንክ አራት ኖቶች ይዛለች:: ለቶሲያን አንድ ሺ አምስት መቶ ፍራንክ ሰጠሁትና ሦስት መቶ ፍራንክ መልስ በመስጠት ላይ እንዳለ፣ ‹ያውልህ፣ ሽጉጡንም ውሰድ:: ስጦታ ነው:: ብቸኛ ዕድልህ ይህ ነው:: በመሣሪያ ዕጦት ምክንያት በመጨረሻ ጊዜ ዕድልህ እንዲኮላሽ አልፈልግም:: ግን ለከፋት እንደማትጠቀምበት ተስፋ አደርጋለሁ» አለ::

በቅድሚያ እርሱን፣ ከዚያም ሌሎቹን በሙሉ እንዴት አድርጌ እንደማመሰግናቸው አቃተኝ:: ጤና ረዳቱ በአንድ ትንሽ ሣጥን ውስጥ ጥጥ፣ አልኮል፣ አስፐሪን፣ ፋሻ፣ አዮዲን፣ መቀስና ማጣበቂያ አዘጋጀልን:: አንድ ቆማጣ ደግሞ፣ ሁለት ትንንሽ የተላጉ የስብራት ማሰሪያ ጣውላዎችና ከፋብሪካቸው ታሽገው እንደወጡ የሚገኙ ሁለት የፋሻ ጥቅሎችን በማምጣት የክሎሲዎን ማሰሪያ እንድንለውጥ ረዳን::

ዐሥራ አንድ ሰዓት ገደማ ዝናም መጣል ጀመረ::



@BOOKALEM

«ዕድሉ አጋጠማችሁ፡፡ ዝናቡ አዳኞቻችሁ እናንተን ከማየት ይገታቸዋል፡፡ በግማሽ ሰዓት ቀድማችሁ የመነሣት ዕድል ይኖራችኋል ማለት ነው፡፡ ቅድሚያ ስለሚሰጣችሁ አሁን መሔድ ትችላላችሁ፡፡ ጧት ላይ ወደ ወንዙ አፍ ቶሎ እንድትቃረቡ ያደርጋችኋል» አለ ዮሐንስ ፐር፡፡

«ሰዓቱን እንዴት ዐውቀዋለሁ?»

«ማዕበሉ በሚነሣበት ወይም በሚበርድበት ወቅት ነው፡፡»

ጀልባዋ ተንሣፈፈች፡፡ ከቀድሞዋ በጣም የተለየች ነበረች፡፡ ይህች ጀልባ የእኛን ጭነት ሁሉ ተሸክማ ከውሃው መስመር በላይ ያዐሥራ ስድስት ኢንች ከፍታ ነበራት፡፡ ከወንዙ እስካልወጣን ድረስ ስለማንጠቀምበት ምሰሶው በነፋስ ሸራው ተጠቅልሎ ከጀልባዋ ሥር ተቀመጠ፡፡ መሪውንና መቅዘፊያውን ከማዘጋጀታችንም በላይ ለእኔም የምቀመጥበት አንድ የሣር ትራስ አገኘሁ፡፡ ከጀልባዋ ሥር፣ በእኔና በውሃው በርሜል መካከል ለከሎሲዎ ብርድ ልብሶች ደለደልንለት፡፡ ማቹሬም ከሥር በኩል ከፊት ለፊት ተቀመጠ፡፡ በዚያቸኛዋ ጀልባ ፍጹም ያልነበረኝ መተማመን አሁን ከመቅፅበት በዚህችኛዋ አደረብኝ፡፡

አሁንም ገና እየዘነመ ነበር፡፡ ስለሆነም በወንዙ መካከል ቁልቁል መውረድ ይኖርብኛል፡፡ ሆኖም ወደ ዳቸ ጊያና አቅጣጫ ትንሽ ወደ ግ . .ንማድላት ነበረብኝ፡፡ «ደህና ሁኑ፡፡ ተንቀሳቀሱ!» አለ ዮሐንስ ፐር፡፡

«መልካም ዕድል» አለና ቶሲያን ጀልባዋን አንድ ጊዜ በኃይል በእግሩ ገፋት፡፡

«አመሰግናለሁ ቶሲያን፣ አመሰግናለሁ ዮሐንስ፣ ሁላችሁንም ፣ እጅግ በጣም አመሰግናለሁ!»

ተመላሽ ማዕበል ፍጥነት ከጀመረ ከሁለት ሰዓት ተኩል በፊት በመሆኑና አሁንም የሚንቀሳቀሰው በኃይል ስለነበረ፣ ወዲያው ከመነሣታችን ርቀት ተጓዝን፡፡

ዝናሙ ስለጨመረ ከፊት ለፊታችን ሠላሳ ጫማ ርቀት እንኳን ማየት አልቻልንም፡፡ ከበታቻችን ሁለት ትንንሽ ደሴቶች ስለነበሩ፣ ማቹሬ ከጀልባዋ ፊት ሰገግ በማለት በአካባቢው የቋጥኝ ምልክቶች መኖራቸውን በዐይኖቹ ይቃኛል፡፡ ምሽት መጣ፡፡ አንድ ትልቅ ዛፍ በዝግታ ጉዞ ከእኛ ጋር በወንዙ ቁልቁል ይወርዳል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ በቅርንጫፎቹ መሰናከልነት ችግር ገጥሞን ነበር፡፡ ግን በፍጥነት ራሳችንን አላቀቅንና የትኮላ ፍጥነታችንን ቀጠልን፡፡ ሲጃራ አጨስንና ትንሽ ሩም ጠጣን፡፡ ሩም የተሞላባቸው በሰሌን የተሸፈኑ ስድስት የኪያንቲ ጠርሙሶች ቆማጦቹ ሰጥተውናል፡፡ ዝም ብለን ጠጣን እንጂ፣ የቆማጦቹን አስቃቂ አካለጎዶሎነት ከእኛ ውስጥ ማንም ያነሣ አልነበረም፡፡ የምናወራው ቢኖር ስለ ርኅሩኅነታቸው፣ ቸሮታቸውና፣ ጨዋነታቸው፣ እንደዚሁም ከውቅራታሙ ብሪቶን ጋር ለመገናኘት ስላበቃን ዕድል ነበር፡፡ ዝናሙ እየከበደ ሔደ፡፡



@BOOKALEM

እስከ አጥንቴ ድረስ በስብሼ ነበር፡፡ ሆኖም የሱፍ ሹራቦቻችን ጥሩ ከመሆናቸው የተነሣ በጣም ብንርስም ሙቀት አልተለየንም፡፡ በቅዝቃዜ የተኮማተረው በመሪው ላይ ያለው እጄ ብቻ ነበር፡፡

«አሁን በሰዓት ከሐያ አምስት ማይል የበለጠ እየተጓዝን ነው» አለ ማቹሬ፡፡

«ምን ያህል ርቀት ተጉዘናል ብለህ ትገምታለህ?»

«በደቂቃ ውስጥ እነግርሃለሁ» አለና ከሎሲዎ፣ «አንድ ጊዜ ቆይ ሦስት ሰዓትና ዐሥራ አምስት ደቂቃ» አለ፡፡

«እየቀለድክ ነው፡፡ እንዴት ዐወቅከው?»

«ከተነሣን ጀምሮ ያለማቋረጥ ሦስት ሦስት ሴኮንዶች ለየብቻ እቆጥር ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ሦስት መቶ መጨረሻ አንድ ቁራጭ ካርቶን እቀዳለሁ፡፡ እስከ አሁንም ሠላሳ ዘጠኝ ቁራጮች ቀድጃለሁ፡፡ እያንዳንዳቸው ሦስት መቶ ሴኮንዶች አምስት ደቂቃ እስከሆኑ ድረስ ከተነሣን ጀመሮ ሦስት ሰዓት ከሩብ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ካልተሳሳትኩ በስተቀር በሚቀጥለው ዐሥራ አምስት ወይም ሐያ ደቂቃ ቁልቁል መውረዳችን ቀርቶ ወደ መጣንበት ተመልሰን መውጣት ይኖርብናል፡፡»

ወንዙን እያካፈልኩ ለማቋረጥና ወደ ዳች ጊያና ጠረፍ ለመጠጋት መሪውን ወደ ቀኝ ገፋሁ፡፡ ልክ ከቁጥቋጦ ጋር ልንላተም ስንል ማዕበሉ ቆመ፡፡ ወደላይም ሆነ ወደፊት አልተንቀሳቀስንም፡፡ አሁንም ገና እየዘነመ ነበር፡፡ መነጋገር አቆምን፣ ማጨስ አቆምን፡፡ «አንድ መቅዘፊያ ግፉ» ብዬ ሹክ አልኩ፡፡ መሪውን በቀኝ ጭኔ ሥር በመያዝ እኔም እቀዝፋለሁ፡፡ ቁጥቋጦውን መንጥረን ቅርንጫፎች ሳብንና ከሥሩ ተጠለልን፡፡ የደኑ ውስጥ ሙሉ በሙሉ ጨለማ ነበር፡፡ ወንዙም ደፍርሶ በከባድ ጭጋግ ተሸፍኗል፡፡ በማዕበሉ ዳግመኛ መቀስቀስ ምልክት ካልሆነ የወንዙ መጨረሻና የባሕሩ መጀመሪያ የት እንደሆነ መናገር አይቻልም፡፡

## ታላቁ አስቸጋሪ ጉዞ

ማዕበሉ እንዴ ከተነሣ የሚቆየው ለስድስት ሰዓት ያህል ነበር፡፡ እስኪነሣ ድረስ ደግሞ አንድ ሰዓት ተኩል መጠበቅ ሊኖርብን ነው፡፡ ይህም ማለት እንቅልፍ ከወሰደኝ የሰባት ሰዓት የመኝታ ጊዜ ነበረኝ፡፡ አሁን ካልተኛሁ በባሕር ላይ ምን ጊዜ እተኛለሁ?

በበርሜሉና በአግዳሚው መቀመጫ መካከል እንደ ድንኳን አድርጎ ማቹሬ አንድ ብርድ ልበስ ዘረጋልኝና፣ በግሩም ሁኔታ ተከልየ ለጥ አልኩ፡፡ ሕልም የለም፡፡ ዝናም ወይም የእኔ አለመመቻቸት፣ ምንም አልረበሸኝም፡፡ ማቹሬ ቀስቅሶ እንዲህ እስከሚለኝ ድረስ ተኛሁ፡፡

«ጊዜው የተቃረበ ይመስለኛል ፓፒ፡፡ ማዕበሉ መመለስ ከጀመረ ረጅም ጊዜ



@BOOKALEM

ነው፡፡»

ጀልባዋ በወንዙ ቁልቁል አፈተለከች፡፡ የማዕበሉ እንቅስቃሴ ጣቶቼን ይሰማኛል፡፡ የሚንቀሳቀሰው በጣም ፈጥኖ ነበር፡፡ ዝናሙ አቆመ፡፡ ከወንዙ ፊትለፊት በሦስት መቶ ጫማ ላይ የሚንሳፈፉትን የሣር ግብስብሶች፣ ዛፎችና የማይለዩ ጥቁር ቅርፆች የሩብ ጨረቃ ብርሃን ግልጽ አድርጋ አሳየችኝ፡፡ በወንዙና በባሕሩ መካከል ያለውን ክልል ለመለየት ሞከርኩ፡፡ እኛ በነበርንበት አካባቢ ነፋስ የለም፡፡ በወንዙ መካከል ይኖር ይሆን? ጠንካራ ይሆን? የወንዙን መጨረሻና የባሕሩን መጀመሪያ መለየት የምችለው ወደ ሰማይ በመመልከት ብቻ ነበር፡፡ ከአሰብነው በላይ በጣም ርቀን ቁልቁል መጥተን ስለነበር እንደሚመስለኝ ቢበዛ የምንርቀው ከወንዙ አፍ ከስድስት ማይል በላይ አይሆንም፡፡ አንዳንድ ሙሉ ጉንጭ ሩም ከለበስን፡፡ ምሰሶው ወዴት መቆም እንዳለበት ለማረጋገጥ የጀልባዋን ዙሪያ ቃኘሁ፡፡ አነሣነውና በአግዳሚው ወንበር ከሚገኘው ቋቱ ውስጥ አስገብተን ገጠምነው፡፡ የነፋስ ሸራውን ሰቀልኩ፣ ግን ከተራዳው ላይ እንደ ተጠቀለለ ተውኩት፡፡ ባለ ሦስት ማዕዘን የአቅጣጫ ማስተካከያውን ሸራም በምንፈልግበት ወቅት እንዲወጥራቸው ለማቼሬ አዘጋጅቼለት ነበር፡፡ የነፋስ ሸራውን ለመዘርጋት ማድረግ ያሉብኝ ከምሰሶው ጋር የተጠቀለለበትን ገመድ መተርተር ብቻ ነበር፡፡ ይህንንም ከተቀመጥኩበት ሳልነሣ ማድረግ እችላለሁ፡፡ ማቼሬ ከፊት በኩል አንድ መቅዘፊያ፣ እኔ ከኋላ ሌላ ይዣለሁ።

ከወንዙ ዳር ስድሳ ጫማ እንደ ራቅን ማዕበሉ የሦስት መቶ፣ ያርድ ያህል ቁልቁል ወሰደን፡፡ ወዲያውኑ ነፋስ ገፋና ወደ ወንዙ መካከል አደረሰን፡፡

«የነፋስ ማስተካከያ ሸራዎቹን አንሣና ሁለቱም በሚገባ ጠብቀው መታሠራቸውን አረጋግጥ!»

ነፋስ ሞላቸውና ጀልባዋ ልክ እንደ ፈረስ ወደፊት ተፈተለከች፡፡ ወንዙ ድንገት በፀሐይ ብርሃን የተጥለቀለቀው ገምተነው ከነበረበት ጊዜ ዘግይቶ ነበር፡፡ የፈረንሣይ ጠረፍ በግምት አንድ ማይል ከሩብ በስተቀኛችን፣ የዳችን ጠረፍ በግምት ግማሽ ማይል በስተግራችን በቀላሉ መለየት እንችላለን፡፡ እየተነሣ የሚወድቀው ነጭ አረፋ ከፊት ለፊታችን በጣም ግልጽ ሆኖ ይታየን ነበር፡፡

«የክርስቶስ ያለህ! ስለ ሰዓቱ ተሳስተን ነበርኮ» አለ ክሎሲዎ፡፡

«ልናስተካክለው እንችላለን ብለህ ታስባለህ?»

«አላውቅም፡፡»

«ማዕበሉ እንዴት ከፍተኛ እንደሆነ ተመልከት! ሞገዱ ተመልሶ ነበር እንዴ?»

«ሊሆን አይችልም፡፡ ቁልቁል የሚንሳፈፍ ነገር አያለሁ፡፡»

«የምንወጣው አይደለም፡፡ ጊዜ የለንም» አለ ማቼሬ፡፡



@BOOKALEM

«ዝም በልና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራዎቹን አጥብቀህ ያዝ፡፡ አንተም ክሉሲዮ እንደዚሁ ዝም በል፡፡»

ድው . . . ድው . . . ተኩስ ተከፈተብን፡፡ ተኩሱ ከየት እንደመጣ በሁለተኛው ዙር መመልከት ቻልኩ፡፡ ዘበኞቹ አልነበሩም፡፡ ተኩሱ የመጣው ከዳች ጠረፍ በኩል ነበር፡፡ ዋናውን የነፋስ ሸራ ስሰቅለው በፍጥነት ነፋስ ሞላና በጣም በመወጠሩ የእጄን አንጓ ገንጥሎ ሊወስደው ተቃርቦ ነበር፡፡ ጀልባዋ ዐርባ አምስ ዲግሪ ከአፍንጫዋ ቀና ብላ ተነሣች፡፡ በጣም ቀላል ስለነበር የቻልኩትን ያህል የነፋሱን ኃይል ለመቆጣጠር ሞከርኩ፡፡ ድው . . . ድው . . . አለና ከዚያ ጸጥ አለ፡፡ ወደ ፈረንሣይ ጠረፍ አቅራቢያ አዘንብለን ኖሯል፡፡ ተኩሱም ያቆመው ለዚሁ ኖሯል፡፡ ከቁጥጥራችን ውጪ በሆነ ፍጥነት ወደ ፊት ተገፋን፡፡ ሳይቆም ከፈረንሣይ ጠረፍ አካባቢ ከሚገኘው የባሕሩና የወንዙ መገናኛ አፍ ተደንቅረን ዐረፍነው፡፡ ሰዎች ወደዚያው አቅጣጫ ሲሯሯጡ አየን፡፡ ገመዱን በተቻለኝ መጠን በዝግታ ነተትኩ፡፡ ዋናው የነፋስ ሸራ አሁን ከፊት ለፊቱ ቀጥ ብሏል፡፡ የነፋስ አቅጣጫ ማስተካከያ ሸራው በገዛ ራሱ ተስተካከለ፣ ባለ ሦስት ማዕዘን ሸራውም እንደዚያው፡፡ ጀልባዋ ሦስት አራተኛ ዙራ ተሽከረከረች፡፡ የነፋስ ሸራውን ዘረጋሁና ከነፋሱ ቀድመን እየሮጥን የወንዙንና የባሕሩን መጋጠሚያ ለቀቅን፡፡ ክርስቶስ! ተሣክቶልን ነበር! ከዐሥር ደቂቃ በኋላ የመጀመሪያው የባሕር ማዕበል ቢጋረጥብንም በቀላሉ በላዩ ላይ ተንሳፈን አለፍን፡፡ በወንዙም ላይ ሸው ስትል ትበር የነበረችው ጀልባችን አሁን በሞገዱ ላይ ብቅ ጥልቅ ትል ጀመረ፡፡ በከፍተኛዎቹ ማዕበሎች ላይ የምንንጠሳጠለው ልክ ጢብ ጢብ እንደሚጫወት ልጅ በቅልጥፍና ነበር፡፡ ንዝረት የለም፣ የመሰበር ድምፅ አይሰማም፣ ብቻ ጀልባዋ በማዕበሉ ትነሣና እንደገና ትወርዳለች፡፡ አንድ ማዕበል ካለፈች በኋላ ባሕሩን ስትመታ የምታሰማው ዘጭ የሚል ድምፅ ብቻ ነበር፡፡

«ይኸው! ይኸው! ተሳካልን!» አለ ክሉሲዮ ሳንባዎቹ እስኪሰነጠቁ ድረስ በመጮኸ፡፡

በአስቸጋሪዎቹ ፈተናዎች ላይ የተጎናጸፍነውን ድል እንድናከብር ቸሩ ፈጣሪ ግሩም የፀሐይ ጮራ ፈነጠቀልን፡፡ ማዕበሎቹ ተመሳሳይ ንቅናቄአቸውን ቀጠሉ፡፡ እየራቅን በሔድን መጠን የጀልባዋ መንጠር እየቀነሰ ሔደ፡፡ ውሃው በጣም ጭቃማ ነበር፡፡ ከፊት ለፊታችን በሰሜን በኩል ባሕሩ ጠቁሯል፣ ዘግይቶም ወደ ሰማያዊነት ይለወጣል፡፡ ኮምፓስ መመልከት አላስፈለገኝም፡፡ ፀሐይዋ በቀኝ ትከሻየ በኩል ነበረች፡፡ የነፋስ ሸራውን ዘርግቸው በከፊል ስለሞላ፣ አሁን ጀልባዋ ቀና ማለቷን ቀንሳ በቀጥታ መሥመር ከነፋሱ ፊት እየሮጠች ነበር፡፡ ታላቁ አስቸጋሪ ጉዟችን በመካሔድ ላይ ይገኛል፡፡



@BOOKALEM

ከሎሲዎ ቀና አለና ተቀመጠ። የሚካሔደው ምን እንደነበር ማየት ፈልጓል። ጀርባውን በበርሜሉ ትይዩ አድርጎ ከእኔ ፊትለፊት እንዲቀመጥ ማቼሬ ደገፈው። አንድ ሲጃራ ጠቀለለና አቃጥሎ አቀበለኝ፣ ከዚያ ሦስታችንም አጨስናት።

«ዙሪያውን ሩም ቅዳ፣ ለድላችን እንጠጣ» አለ ከሎሲዎ። ማቼሬ በሦስት የብረት ኩባያዎች ለቀቅ አድርጎ ቀዳና ለድላችን! ለጤናችን! ተባባልን። ማቼሬ ከእኔ በግራ በኩል ተቀምጦ ስለነበር ሁላችንም እንተያያለን። ፊቶቻቸው በደስታ በርተዋል። የእኔም እንደዚያው መሆን አለበት።

«ወዴት ነው የምትጓዘው ካፒቴን?» ሲል ከሎሲዎ ጠየቀኝ።

«እግዚአብሔር ፈቃዱ ቢሆን፣ ወደ ኮሎምቢያ።»

«እግዚአብሔርማ ከኛ ጋር ነውና ፈቃደኛ ይሆናል!» አለ ከሎሲዎ። ፀሐይዋ በፍጥነት ወጣች። ልብሳችንም ጊዜ ሳይፈጅ ደረቀ። የሆስፒታል ፒጃማችንን ወደ ዐረቦች ዐይነት ጥምጣም ቀየርናቸው። በሚረጥቡበት ወቅት ቀዝቃዛ ስለሚሆኑና ጭንቅላት ላይ ስለሚጣበቁ የፀሐዩን ሐሩር ይከላከሉልን ነበር። ባሕሩ የሚያንጸባርቅ፣ ሰማያዊ፣ ማዕበሎቹም ሰፊና ረጅም ሆነው ለጀልባ ጉዞ ይመቻሉ። ነፋሱ ኃይሉን እንደጨመረ ስለሆነ ከጠረፉ በከፍተኛ ፍጥነት ራቅን። ከአረንጓዴው ገመገም በራቅን መጠን ምሥጢርነቱ እየጎላ ከአድማሱ ላይ ደበዘዘ። ዛሬ ይህንኑ ስመለከት ነበረ አንድ ማዕበል ከተፍ ብሎ ኃላፊነቴን ያስገነዘበኝ።

«ትንሽ ሩዝ ልቀቅል ነው» አለ ማቼሬ።

«አንተ ብረት ድስቱን ስትይዝ፣ እኔ ምድጃውን እይዛለሁ» አለ ከሎሲዎ። የነዳጅ ደምበጃን ማንም ሰው እንዲያጨስ ከማይፈቀድበት ቦታ ተሰትሮ ነበር። ሩዙን በዘይት ሲቀቅለው ሽታው ግሩም ነበር። ከሁለት ጣሳ ሠርዲኖች ጋር አደባልቀን ትኩሱን በላነው፣፣ በዚያ ላይ ጥሩ ቡና ጨመርንበት። «አንድ አንድ ጉንጭ ሩም?» አሉ ሁለቱም። አይሆንም አልኩ። በጣም ሙቀት ነበር። ከሎሲዎ ለእኔ ሲጃራ መጠቅለሉንና ማቃጠሉን ቀጠለ። ከፀሐይዋ አቅጣጫ በግምት ከጧቱ አራት ሰዓት እንደሚሆን ገመትን። በባሕር ላይ የቆየነው አምስት ሰዓት ብቻ ነበር። ከሥራችን ያለው ውሃ በጣም ጥልቅ መሆኑ ያስታውቃል። ማዕበሎቹ ለጥ ያሉ ስለነበሩ የምንሰነጣጥቃቸው ያለ አንድ ድምፅ ነበር። ደስ የሚል ቀን ሆነ።

በቀን ኮምፓስ እንደማያስፈልገን ተገነዘብኩ። አልፎ አልፎ ግን ከኮምፓሱ መርፌ ጋር የፀሐይዋን አቅጣጫ እያዛመድኩ በዚያ ሁኔታ እመራለሁ። ግን የፀሐይዋ ነጸብራቅ ዐይኔን ጎዳኝ። አንድ ጥቁር መነጽር ለማግኘት ባለመሞከሬ አዘንኩ።

«ሰውዬ፣ ካንተ ጋር ሆስፒታል በመገናኘቴ ዕድለኛ ነኝ!» አለ ከሎሲዎ ድንገት።

«አንተ ብቻ አይደለህም። እኔም አንተን በማግኘቴ ዕድለኛ ነኝ።» ስለእኔ



@BOOKALEM

ዴጋ፣ ፌርናንዴዝ ... አስታወስኩ፡፡ እሺ ብያቸው ቢሆን ኖሮ፣ እነርሱም በዚህ ጊዜ ከእኛ ጋር እዚሁ ይሆኑ ነበር፡፡

«እኔ ብቻ አይደለሁም» አለ ክሎሲዎ፣ «ማቹሬ ባይኖር ኖሮ በምትፈልገው ጊዜ ዐረቡን ወደ ክፍሉ ውስጥ ማምጣት ችግር ይሆንብህ ነበር፡፡»

«አዎ፣ በእርግጥም ማቹሬ ጠቃሚ ነበርክ፡፡ ጎበዝና ብልህ ልጅ ስለሆንክ ከእኛ ጋር በመምጣትህ ደስ ብሎኛል፡፡»

«አመሰግናለሁ» አለና ማቹሬ «ካለኝ አቋምና ከዕድሜዬ አንጻር ሁላታችሁም በእኔ ላይ እምነት ስለጣላችሁብኝ አመሰግናለሁ፡፡ እስከወዲያኛው በዚሁ ለመጽናት እሞክራለሁ» አለ፡፡

«ፍራንሷ ሲየራም ከእኛ ጋር መሆን በቻለ ነበር፡፡ ጋልጋኒም» አልኩ፡፡

«ነገሮች በመለዋወጣቸው፣ ይህ ሊሆን አልቻለም ፓፒዮ፡፡ ኢዮአስ ቀና ሆኖ ጥሩ ጀልባ ቢሰጠን ኖሮ ከተሸሸግንበት ቦታ ሆነን ልንጠብቃቸው በቻልን ነበር፡፡ ለማምለጡ ኢዮአስ ሊረዳቸው በቻለና ሌላውን እኛ ማድረግ በቻልን ነበር፡፡ ሌላው ቢቀር አንተን ስለሚያውቁህ፣ ያልሞከርከው አቅቶህ መሆኑን ይገነዘቡታል፡፡»

«ጨዋታችንን ሳንለቅ፣ ከሆስፒታል ከፍተኛ ጥበቃ ክፍል እንዴት ልትገባ ቻልክ ማቹሬ?»

«ሆስፒታሉ እንዴት እንደገባሁ እኔም አላወቅኩም፡፡ ወደ ዶክተሩ የሔድኩበት ምክንያት ጉሮሮዬ ስለ ቆሰለና በተጨማሪ አካባቢውን ለመቃኘት ነበር፡፡ ዶክተሩ ሲያየኝ፣ ካርድህ ሆስፒታል መግባት አለበት ይላል አለኝ፡፡ ‹ለምን? ዶክተር?፡፡ ሆስፒታል ይግባ ማለት ምን ማለት ነው?› ስል ጠየቅሁት፡፡ ‹ግድየለም፣ ወደ ሆስፒቲል ሒድ› ተባልኩ፡፡ በዚሁ የተነሣ ሆስፒታል ውስጥ ተቀመጥኩ፡፡»

«ውለታ አድርጎልህ ነበራ?» አለ ክሎሲዎ፡፡

«እንደዚህ ስትል ስሜቱን ገምተህ ነው? ይህን ጊዜ ያ መልከ መልካምና የዋህ የሚመስለው ልጅ ለካስ እንደዚህ የዋዛ አልነበረም፡፡ እምልጦ ለመሔድ ወኔ ነበረው› በማለት ራሱን በራሱ መውቀሱ አይቀርም» ብዙ የማይረቡ ወሬዎች አወራን፡፡ «ማን ያውቃል ጁሎን እናገኘው ይሆናል፡፡ አሁንም ገና በጫካው ውስጥ ካልተሸሸገ በስተቀር በጣም ርቆ መሔድ አለበት» አልኩ፡፡

«በምለቅበት ወቅት፣ የምገኝበትን አድራሻ አልገለጽኩም ስል ከትራሴ ሥር እንዲት ማስታወሻ አስቀምጫለሁ» አለ ክሎሲዎ፡፡ ሁላችንም በሣቅ ፈነዳን፡፡

ለአምስት ቀናት ያለ ችግር ተጓዝን፡፡ ቀን ሲሆን አቅጣጫችንን በፀሐይ እናስተካከላለን፣ ሌሊት በኮምፓስ እንጠቀማለን፡፡ በስድስተኛው ቀን ፍንትው ያለች ፀሐይ ወጣችና ሰላምታ አቀረበችልን፡፡ ባሕሩም ድንገት በረደና በራሪ ዓሣዎች



@BOOKALEM

በአጠገባችን ይመላለሱ ጀመር፡፡ ደከምኝ ነበር፡፡ በዚያ ሌሊት በእንቅልፍ እንዳልወድቅ ለመጠባበቅ የጨው ውሃ በተነከረ ጨርቅ ማቹሬ ፊቴን ያረጥብልኝ ነበረ፡፡ ግን ወዲያው እንቅልፍ ይጥለኛል፡፡ ከዚያም ከሎስዮ፣ አሁን ማዕበሉ እረጭ በማለቱ በእርግጥ መተኛት እንደምችል ነገረኝ፡፡ ባለ ሦስት ማዕዘኑን ሸራ ብቻ እንደ ተሰቀለ ትተን፣ የነፋስ ሸራውንና የአቅጣጫ ማስተካከያ ሸራውን አወረድን፡፡ ከፀሐይ ለመከላከል ከበላይ ያለውን ሸራ ተከለልኩና ከጀልባዋ ሥር ልክ እንደ ግንድ ተጋደምሁ፡፡ ማቹሬ ነቅንቆ ቀሰቀሰኝ፡፡ «ገና ወደ ቀትር አካባቢ ነው፣ ግን የቀሰቀስኩህ ነፋሱ በመነሣት ላይ ስለሆነ ነው፡፡ ከአድማሱም በኩል ማንኛውም ነገር እየጠቆረ በመምጣት ላይ ይገኛል» አለኝ፡፡ በድግ አልኩና መሪውን ጨበጥኩ፡፡ ብቸኛው ባለ ሦስት ማዕዘን ሸራ ለጥ ባለው ባሕር በፍጥነት አስፈተለከን፡፡ ከበስተጀርባዬ በስተምሥራቅ አቅጣጫ ሰማዩ ጠቁሮ ነበር፣ የነፋሱም ኃይል እየጨመረ ሔደ፡፡ ፍጥነት ለመጠበቅ ያህል ሁለቱ የነፋስ ማስተካከያዎች በቂ ናቸው፡፡ የነፋስ ሸራውን በምሰሶው ዙሪያ ጠቀለልኩ፡፡

ሐጥብቃችሁ ያዙ፡፡ ሞገድ እየመጣ ነው፡፡»

ትላልቅ የዝናም ነጠብጣቦች መውረድ ጀመሩ፡፡ አንድ አስቀያሚ ቁልል ደመና ወደ እኛ አቅጣ ያስገመግም ነበር፡፡ ዐሥራ አምስት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ እኛ ዘንድ ደረሰ፡፡ ቁጠኛ ነፋስ ገፈተረን፡፡ አንዳች ልከፍት የያዛቸው ይመሥል ማዕበሎቹም አረፋቸውን ይደፍቁ ጀመር፡፡ አንድም ነገር ማየት አለቻልንም፡፡ ዶፍ ይጥላል፣ ፀሐይዋም ተሰወረች፡፡ ማዕበሉ ጀልባዋን ሲመታት የሚቆጠቁጠው የውሃ ዐረፋ እየተፈናጠረ ፊቴን አኮማተረው፡፡ ነጎድጓዱን፣ መብረቁን፣ ዝናሙን፣ ማዕበሎቹንና በአካባቢያችን የሚወርደውን ነፋስ፣ ተፈጥሮ ባላት ኃይል ሁሉንም ፈትታ የለቀቀችብን ሞገድ ነበር፡፡ እውነተኛው ዓውሎ ነፋስ ነበር የተነሣው፡፡ ልክ አንድ ቁራጭ ካርድ መስላ ጀልባዋ ከከፍተኛ ቦታ ጥልቅ ወደ ሆነ አዘቅት፣ ከጥልቀቱም የተነሣ ፍጹም ተመልሰን እንወጣለን ብየ ወደማላስብበት ታሽቆለቁላለች፡፡ ያም ሆኖ ከሚያስገርመው ማሽቆልቆል ውስጥ በእያንዳንዱ አዲስ የማዕበል ጫፍ ተመልሰን ወደ ላይ እንገናለን፡፡ መሪውን በሁለቱም እጆቼ ጨመደድኩና ሊሰብራት የተቃረበውን ትልቅ የማዕበል እብጠት መቋቋም መቻል አለብኝ በማለት በላዩ ላይ ሰንጥቄ ለማለፍ ጀልባዋን አዘጋጀኋት፡፡ ምናልባት በጣም በፍጥነት መሪውን በማዞር ይሆናል፣ ከፍተኛ መጠን ያለው ውሃ ወደ ጀልባዋ ውስጥ ገባና በውሃ ተጥለቀለቀች፡፡ ሠላሳ ሊትር ያህል ሆኗ ታች ሳንሰምጥ አንቀርም፡፡ ትዕግሥቴ አለቀና ምን እንደማደርግ ሳላውቅ የሚቀጥለውንም ማዕበል በጎን በኩል ለማለፍ ራሴን ለጥፋት ጋበዝኩ፡፡ ያም ሆነና ጀልባዋ በጎኗ እንደ መተኛት ብላ ማዕበሉን ስታልፍ ገብቶ የነበረው ብዛት ያለው ውሃ ፈሰሰ፡፡

«ጎበዝ» አለና ከሎሲዎ፣ «በትክክል ገመዶቹን ማዘዝ ይውቅህበታል ፓፒዮ!



@BOOKALEM

ጀልባዋን ባዶ ለማድረግ በአቋራጭ ዘዴ ተጠቀምክ» አለ::

«አትጠራጠር» ብየ መለስኩለት:: ግን በእኔ ልምድ ማጣት የተነሣ ልንሰምጥ ተቃርበን እንደነበር ተረድቶ ይሆን!» የሚል ሃሳብ ጫረብኝ::

ከማዕበሎቹ ጋር መታገሌን ወይም አቅጣጫ ማስተካከሌን ለማቆም ወሰንኩ:: ጀልባዋ በተቻለ መጠን ረጋ እንድትል በማድረጉ ላይ አተኮርኩ:: ማዕበሎቹን ወደ ጎን በማሳለፍ ቁልቁል እየወረደች ወደላይ እንድትወጣ አደረግኋት:: ከአንድ ጠቃሚ ግኝት መድረሴንና አደጋውም ከመቶ ዘጠና እጅ መቃለሉን ወዲያውኑ ተገነዘብኩ::

ምንም እንኳ ነፋሱ እንደ ቀጠለ ቢሆንም፣ ዝናሙ ስላቆመ አሁን ወደፊትና ወደ ኋላ በግልጽ ለማየት ችያለሁ:: ከኋላችን ፈካ ብሎ ከፊታችን ደግሞ የጠቆረ፣ ሁለት ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ የአየር ጠባይ መካከል ነበር ያለነው::

በዐሥራ አንድ ሰዓት ሁሉም ነገር አለፈ:: ማዕበሉም በረደ፣ ነፋሱም እንደ ተለመደው ረጋ፣ ፀሐይዋም እንደገና ወጣች:: ሸራውን ሰቀልኩና በዕድላችን በጣም እየተደሰትን እንደገና ጉዞ ጀመርን:: ጀልባው ውስጥ ቀርቶ የነበረውን ውሃ በብረት ድስታችን እየቀዳን አፈሰስነው:: ብርድ ልብሶቻችንንም ምሰሶው ላይ ሰቀልንና ነፋሱ ወዲያውኑ አደረቃቸው:: ከዚያም የሩዝና የዱቄት ምሳ በዘይት አዘጋጀን:: በወፍራም ቡናና በአንዳንድ ደህና ጉንጭ ሩም አሳረግን:: ፀሐይዋ ለመጥለቅ ተቃርባ በሰማያዊው ባሕር ላይ እሳት የመሰለ ብርሃኗን ረጨችበት:: በጣም ያምር ነበር:- የቀይ ቡናማው ሰማይ፣ ከከፊል ወደ ባሕሩ ጠልቃ በትልቁ ቢጫ ምላሷ ሰማዩን የምትልስ የምትመስለው ፀሐይ፣ መጠነኛዎቹ ነጫጭ ደመናዎችና ራሱ ባሕሩ ውብ ትርዒቶች ነበሩ:: ማዕበሎቹ ከሥር በኩል ሰማያዊ ቢሆኑም እንደሚያርፉባቸው የፀሐይ ጨረሮች አረፋዎቻቸው አረንጓዴና ቀይ፣ ሐምራዊ ወይም ቢጫ ይሆናሉ::

አንድ የማይናቅ ሰላም ተሰማኝ:: ከዚህም ሰላም ጋር በራስ መተማመን አደረብኝ:: ሁኔታዎችን በሚገባ ለመቆጣጠር ቻልኩ:: የአጭሩ ጊዜ ሞገድ ብዙ አስተምሮኛል:: ኃይለኛ ባሕር ውስጥ እንዴት መገለባበጥ እንደሚቻል በገዛ ራሴው ለምጃለሁ:: ሌሊቱንም በጸጋ እንኳን ደህና መጣህ ለማለት ችያለሁ::

«ታዲያስ፣ ከሎሲዎ፣ ከጀልባዋ ውሃ ያፈሰስኩበትን ዘዴ ወደድከው?»

«ጓደኛዬ፣ ይህን ባታደርግና ጎናችንን አንድ አዲስ ማዕበል ቢመታን ኖሮ አልቆልን ነበር:: ሻምፒዮን ነህ::»

«ይህን የተማርከው ባሕር ኃይል ውስጥ ነበር?» አለ ማቹሬ::

«አዎ፣ ሌላው ቢቀር ለአንዳንድ ነገሮች ባሕር ኃይል ጥሩ ነው» አልኩት:: መስመራችንን አሳስተን ርቀን መሆን አለብን:: በዚያ ነፋስና እነዚያ ማዕበሎች ውስጥ ከአራት ሰዓት ቆይታ በኋላ ይህ ቢፈጸም የሚያስደንቅ ነገር አይሆንም:: ወደ ሰሜን



@BOOKALEM

ምዕራብ ለመሔድ መሪውን ማስተካከል ነበረብኝ። ለመስነባበቻ ያህል ፀሐይዋ ሐምራዊ ጨረሯን ለመጨረሻ ጊዜ ፈንጥቃ ስትጠልቅ፣ ጨለማው ወረረን።

ያለምንም ችግር ሌላ ተጨማሪ ስድስት ቀኖች ተጓዝን። በአንዳንድ አነስተኛ የነፋስ ግፊትና ዝናም ከሦስት ሰዓት ላልበለጠ ጊዜ ከመንብኖታችን በስተቀር ከመጀመሪያው ሞገድ ደረጃ የሚመጣጠን ፈተና ፈጽሞ አላጋጠመንም።

አሁን ከጧቱ አራት ሰዓት ነበር። አንድም የነፋስ ሽውታ የለም። ባሕሩ መስታወት መስሏል። አራት ሰዓት ያህል ተኛሁ። በምኝታበት ጊዜ ፊቴ እየተለበለበ ነበር። ከከንፈሮቼና ከአፍንጫየ ቆዳዬ ተነሥቷል። የቀኝ እጄም ተገሽልጧል። የማቹሬና የከሎሲዎም እንደዚሁ ሆኖ ነበር። ፊቶቻችንንና እጆቻችንን በቀን ሁለት ጊዜ ዘይት እንቀባቸዋለን፣ ግን ይህ በቂ አልሆነም። የምድር ወገብ ፀሐይ ወዲያውኑ ታደርቀዋለች።

ከፀሐይዋ አቅጣጫ እንደ ተረዳሁት፣ አሁን ከሰዓት በኋላ ስምንት ሰዓት ነበር። ምግብ ብጤ ቀማምሰኩና ከዚያም ባሕሩ ረጋ ባለበት ወቅት ጥላ እንዲሆነን በማለት የነፋስ ሸራውን አስተካከልን። ማቹሬ ሣህኖቹን ያጥብበት ከነበረው አካባቢ ዓሣዎች ተሰበሰቡ። ገጀራችንን እንሣሁና ትንሽ የሩዝ ፍሬዎች እንዲበትንላቸው ለማቹሬ ነገርኩት። ሩዙ በሞገድ ወቅት ረጥቦ ስለነበር በቆልት መሆን ጀምሯል። ሩዙ በተበተነበት አካባቢ ዓሣዎች ተሰበሰቡና ከእነርሱ አንደኛው ጭንቅላቱን ከውሃው በላይ ሲያወጣ ደህና አድርጌ በገጀራው ቀላሁት። ወዲያው ሆዱን በአየር ላይ ገለበጠ። ያ ዓሣ ሐያ አምስት ፓውንድ መመዘን አለበት። በጨው ውሃ አጥበን ቀቀልንና ከታፒዎካ ዱቄት ጋር በዚያኑ ምሽት በላነው።

አሁን በባሕር ላይ ዐሥራ አንድ ቀን ሆኖን ነበረ። በጠቅላላው በዚህ ጊዜ ውስጥ አንድ ጀልባ ብቻ ከአድማሱ በጣም ራቅ ብሎ አይተናል። የትኛው ቦታ እንሆን እያልኩ ራሴን መጠየቅ ጀመርኩ። በዓለም አቀፍ ባሕሮች ላይ መሆናችን ግልጽ ነበር። ግን ከትሪኒዳድ ወይም ከሌሎቹ የእንግሊዝ ደሴቶች ጋር ያለን መቀራረብ የቱን ያህል ይሆን? ያንንስ የሰይጣን ጆሮ አይስማው በቀጥታ ከፊት ለፊታችን እያደር እያደገ የሚሔድ አንድ ጥቁር ነጥብ ነበር። ትልቅ መርከብ ይሆን ወይስ አነስተኛ ጀልባ? ጀልባ ነበር፣ ግን የሚመጣው ወደ እኛ አቅጣጫ አልነበረም። ከእኛ መስመር ባሻገር ሲንቀሳቀስ አሁን ግልጽ ሆኖ ማየት ቻልን። ሆኖም እየቀረበ መጣ፣ ግን በማዕዘን በኩል ነበር። የጉዞ መስመሩ ሊያቀርበው አይችልም። ነፋስ ካለመኖሩና የነፋስ ሸራዎቹም ስለተመለሱ የሚያየን አይመስልም። ከዚያ ድንገት አንድ የጡሩምባ ድምፅ ተምባረቀና ሌሎች ሦስት ደግሞ ተከታተሉ። ጀልባው መስመሩን አሳብሮ በቀጥታ ወደ እኛ ገሠገሠ።



@BOOKALEM

«እስካልተጋጨን ድረስ» አለ ክሮሲዎ፡፡

«አደጋ አይኖርም፡፡ ባሕሩ እንደ መስታወት የለሰለሰ ነው፡፡»

አንድ ነዳጅ ጫኝ መርከብ ነበር፡፡ እየቀረበ ሲመጣ በመተላለፊያው ላይ የተሰበሰቡትን ሰዎች ማየት ቻልን፡፡በዚህች ‹የወፍ ጎጆዋቸው› ውስጥ ሆነው እነዚህ ሦስት ዕብዶች በውቅያኖስ መካከል ምን እያደረጉ ይሆን ብለው መገረም አለባቸው፡፡ በጥንቃቄ እየቀረቡን ሲመጡ፣ የመርከቡን መኮንኖች፣ አንዳንድ የመርከቡን ሠራተኞች፣ ዝጉርጉር ቀሚስ የለበሱ ሴቶችንና ባለቀለም ሸሚዝ የለበሱ ወንዶችን ወደ መተላለፊያው ሲሰባሰቡ ለማየት ቻልን፡፡ በግልጽ እንደሚታየው መንገደኞች ናቸው፡፡ በዘይት ጫኝ መርከብ ላይ መንገደኞች ማየት ያልተለመደ ነገር ይመስላል፡፡ አሁን መርከቡ በጣም ቀርቦ ስለነበር ካፒቴኑ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ተጣራ፡፡

«ከወዴት ናችሁ?»

«ፈረንሣይ ጊያና»

«ፈረንሣይኛ ትናገራላችሁ?» አለች አንዲት ሴት፡፡

«አዎ እመቤቴ፡፡»

«ምን እያደረጋችሁ ነው?»

«እግዚአብሔር ይወቅ . . .»

ሴትየዋ ከካፒቴኑ ጋር ተነጋገረችና እንደዚህ አለች፡፡ «ካፒቴኑ ወደ መርከቡ መጥታችሁ እንድትሣፈሩ ይጋብዛችኋል፡፡ ጀልባችሁንም ወደ ወለሉ ላይ ስቦ ያወጣላችኋል፡፡»

«እናመሰግናለን ብለሽ ንገሪው፣ ግን በጣም ተመችቶናል፡፡»

«እርዳታ አትፈልጉም?»

«ያመለጥን እሥረኞች ስለሆንን፣ በእናንተ አቅጣጫ አንሔድም፡፡»

«ወዴት ነው የምትሔዱት?»

«ማርቲኒከና ከዚያ ባሻገር፡፡ የት እንዳለን አላወቅነውም፡፡ ወደ እንቲይ ደሴቶች የሚወስደን የትኛው አቅጣጫ እንደሆነ ልትነግሩን ትችላላችሁ?

«የእንግሊዝኛ የባሕር መስመር ካርታ ማንበብ ትችላለህ?»

«አዎ፡፡»

ከትንሽ ጊዜ በኋላ አንድ የእንግሊዝኛ ካርታ፣ አንድ ካርቶን ሲጃራ፣ ዳቦና አንድ የበግ እሮስቶ ሰደዱልን፡፡

«ካርታውን ተመልከተው» ካርታውን ተመለከትኩና ከዚያም፣ «ወደ እንግሊዝ እንቲይስ ለመጓዝ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ አንድ ሩብ መዞር ይኖርብኛል፡፡ ልክ ነው?» አልኩ፡፡



@BOOKALEM

«እዎ።»

«ምን ያህል ማይል ይሆናል?»

«በሁለት ቀን ውስጥ መድረስ ትችላለህ» አለ ካፒቴኑ።

«ለማገኛውም እናመሰግናለን፣ ደህና ሁኑ።»

«ስለባሕር ተጓዥነት ወኔያችሁ ካፒቴኑ እንኳን ደስ አላችሁ ይላችኋል!»

«በድጋሚ እናመሰግናችኋለን። ደህና ሁኑ!» ከዚያም መርከቡ ሊታከከን ተቃርቦ በዝግታ አለፈን። እንዳይገለብጠን በማለት የቻልኩትን ያህል ለመራቅ ጠመዘዝኩ። ልክ በዚያ ወቅት አንድ መርከበኛ ከወለሉ ላይ ሆኖ መለዮውን ሲወረውራት በቀጥታ በጀልባዋ መካከል ወደቀች። ከሁለት ቀን በኋላ ትሪንዳድ ስንደርስ ይህችን በወርቅ የተጠለፈችና መልሕቅ ያላት መለዮ ደፍቼ ነበር።

## ትሪንዳድ

ጠረፏን ለማየት ከመቻላችን በጣም ቀደም ብሎ መሬት መድረሳችንን አንድ የአሞራዎች በረራ አበሠረን። በላያችን እያንዣበቡ ሲመጡ ከጧቱ አንድ ሰዓት ተኩል ይሆን ነበር። « ተሳክቶልናል! ተሳክቶልናል ጓደኞቼ! የመጓመሪያው የማምለጥ ምዕራፍ ማከተሙ ነው። ያውም ከባዱ ክፍል። ረጅም ዕድሜ ለ!ፀ!ታችን!» ከደስታችን ጉዛት አንደ ሕፃናቶች ሆንን። ፀሐይ ያቃጠለው ፊታችንን ለማለስለስ የመርከቡ ሰዎች ሰጥተውን የነበረውን የኮኮስ ቅባት ለደፍነው። ወደ ሦስት ሰዓት ገደማ መሬት አየን። በእርጋታ በሚንከባለለው ባሕር የሚጓዘው ቀዝቀዝ ያለ ነፋስ ወደዚያው አቅጣጫ በፍጥነት አስጠጋን። ከሰዓት በኋላ ዐሥር ሰዓት ላይ ነበር ወደ መሬት በመጠጋታችን የአገሩን አቀማመጥ አስተካክለን ለማየት የቻልነው። በረጅሙ ደሴት ባሕር ጠርዝ ላይ በመቀራረብ ተደርድረው የሚታዩት ነጫጭ ቤቶችና የኮከናት ዛፎች ቁንጮዎች ለጠረፉ ጉልላት ሆነውታል። አቤቶቹ ውስጥ ሰው ይኑርባቸው አይኑርባቸው ወይም ሥፍራዋ በትክክል ደሴት ትሁን ወይም ልሣነ ምድር ገና መለየት አልቻልንም። እኛ ወደምናመራበት የባሕር ዳር አቅጣጫ የሚሯሯጡትን ሰዎች ከመለየታችን በፊት ሌላ አንድ ሰዓት ሆነ። ሐያ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሕዝብ ተሰበሰበ። የትንሿ መንደር ነዋሪ ሁሉ እኛን ለመቀበል ወደ ባሕሩ ዳር ግልብጥ ብሎ ወጣ። በኋላ እንደ ተረዳነው የቦታዋ ስም ሳንፌርናንዶ ነው።

ከባሕሩ ዳር ሦስት መቶ ያርድ ርቀት ላይ መልህቅ ጥዬ ወዲያው ቆነጠጠልኝ። ይህን ያደረግኩት በአንድ በኩል የሰዎቹን አዝማሚያ ለመመልከት በሌላ በኩል የባሕሩ ወለል ኮራል ከሆነ ጀልባዋን ለአደጋ ከማጋለጥ ለማዳን ስል ነበር። የነፋስ ሸራዎቹን አወረድንና ጠበቅን። አንዷት ትንሽ ጀልባ ወደ እኛ አቅጣጫ መጣች።



@BOOKALEM

በውስጧ ሁለት የሚቀዝፉ ጥቁሮችና የቅኝ ግዛት መለያ ያደረገ አንድ ነጭ ነበር::

« ወደ ትሪኒዳድ እንኳን ደህና መጣችሁ» አለ ነጩ ጥርት ባለ ፈረንሣይኛ::

« አመሰግናለሁ ጌታዬ እዚህ ከባሕሩ ሥር ኮራል ነው ወይስ አሸዋ?»

« አሸዋ ነው:: ያለምንም አደጋ እስከ ባሕሩ ዳር ድረስ መሔድ ትችላላችሁ::»

መልህቁን ወደ ላይ ሳብንና ማዕበሎቹን በዝግታ ወደ ዳር ገፋን:: ዐሥር ሰዎች ወደ ውሃው ውስጥ እየተሯሯጡ ጀልባዋን በአንድ ግፊት ወደ መሬት ያወጧት ገና አፈር ሳንነካ ነበር:: መላው ሁኔታችንን ተመለከቱ፣ ተንከባከቡን፣ ጥቁር ሴቶች፣ ቻይናውያንና ሕንዶች የአክብሮት አቀባበል አደረጉልን:: ከእነርሱ ጋር እንድንቆይ ማንኛውም ሰው መፈለጉን ነጩ ገለጸልን:: ማቹሬ በአፍ ሙሉ አሸዋውን ዘገነና እንደ መሳም አለ:: ይህም ተመልካቾቻችንን አስደነቀ:: ስለ ክሎሲዎ ሁኔታ ለነጩ ሰው ገለጽኩለትና በባሕሩ ዳር ከሚገኘው መኖሪያ ቤቱ አሸከሞ አስወሰደው:: እስኪነጋ ማንኛውንም ነገር ጀልባዋ ውስጥ መተው እንደምንችልና ማንም ሰው ምንም ነገር እንደማይነካ ገለጸልን:: ሁሉም ሰው፣ «ካፒቴን» እያለ ስለ ጠራኝ ይህ አዲስ የወጣልኝ የክርስትና ስም አሣቀኝ:: በእንግሊዝኛም ቋንቋ በትንሽ ጀልባ ረጅም ጉዞ ያደረገን ሰው፣ «ጎበዝ ካፒቴን?» ይላሉ::

ምሽት መጣ:: ለጥበቃ ያህል ጀልባችንን ትንሽ ራቅ አድርገን በመግፋት ከአንድ ከፍ ካለ ጀልባ ጋር ማቆራኘት ይቻል እንደሆነ ጠየኩ:: ከዚያም እንግሊዛዊውን ተከተልኩና ወደ ቤቱ አመራሁ:: ትንሽ ደረጃዎችና ባለወንፊት መዝጊያ ያለው በእንግሊዝ ሀገር በየቦታው የሚታዩትን ቪላዎች ይመስላል:: ማቹሬ ከእኔ ኋላ፣ እኔ እንግሊዛዊውን ተከትየ ገባን:: ወደ ውስጥ እንደገባሁ፣ ክሎሲዎ ባለመደገፊያ ወንበር ላይ ተቀምጦ እግሮቹን አንፈራጦ ሁለት ሴቶች እያሟሟቁ ይንከባከቡት እንደነበረ አየሁ::

እንግሊዛዊው፣ «ሚስቴና ልጄ» አለና አስተዋወቀን:: «እንግሊዝ ሀገር በትምህርት ላይ የሚገኝ አንድ ወንድ ልጅም አለኝ::»

«ወደ ቤታችን እንኳን ደህና መጣችሁ» አለች ሚስቱ በፈረንሣይኛ::

«እባካችሁ ተቀመጡ» አለች ልጅቱ ሁለት ከቀርከሃ የተሠሩ ወንበሮች እያቀረበች::

«እናመሰግናለን፣ እባካችሁ ለእኛ ብላችሁ አትቸገሩ::»

«ለምን? ከየት እንደመጣችሁ ስለምናውቅ አትሥጉ፣ እደግመዋለሁ፣ ወደ ቤታችን እንኳን ደኅና መጣችሁ::»

ሰውየው ጠበቃ ሲሆን፣ ስሙ ቦውን ይባላል:: መሥሪያ ቤቱ በግምት ሐያ አምስት ማይል ከምትርቅ ፖርት ኦፍ ስፔይን ከተባለች የትሪኒዳድ ዋና ከተማ ውስጥ ነበር:: በሻይ፣ በወተት፣ በኬክ፣ በቅቤና በማርማላታ አስተናገዱን:: እንደ ነፃ ሰዎች



@BOOKALEM

የሆንባት የመጀመሪያዋ ምሽት ስለነበረች ፈጽሞ አልረሳትም፡፡ ጉዞው እንዴት እንዳለፈና ስንት ቀን እንደ ፈጀብን፣ እዚህ መድረሳችንን ለፖሊስ የምናሳውቅ ነገ ይሁን ወይስ በሌላ ቀን፣ ከሎሲዎ ሥቃይ የሚሰማው እንደሆነ፣ ደብዳቤ የምንጽፍላቸው ቤተሰቦች፣ ሚስቶች ወይም ልጆች እንዳሉን ብቻ ካልሆነ በቀር፣ ሌላ ዓይነት ወይም ስላለፈው ታሪካችን አንድም ጥያቄ አላቀረቡልንም፡፡ ልንጽፍላቸው ከፈለግን ደብዳቤዎቹን እነርሱ እንደሚልኩልን ገለጹልን፡፡ እንዴት አድርጌ ልናገረው፡፡ እነዚህ እንግሊዛውያን ቤተሰቦችና ከነሕፃ ጠረፍ ያጋጠሙን ሰዎች፣ ሁሉም እንደኛ ላሉ ለሦስት ተባራሪዎች ያደረጉልን መስተንግዶ ልዩ ነበር፡፡ ሚስተር ቦውን ወደ አንድ ዶክተር ስልክ ደወለና በሚቀጥለው ቀን ከሎሲዎን ወደ ክሊኒኩ አምጥቶ ራጅ እንደሚያስነሣውና ምን እንደሚያስፈልገው እንዲመረምረው ነገረው፡፡ ከዚያም ሚስተር ቦውን ፖርት ኦፍ ስፔይን ወደሚገኘው የወታደራዊ በጎ አድራጎት ድርጅት ኃላፊ ወደ ነበረው ካፒቴን ስልክ ደወለ፡፡ ካፒቴኑም በበጎ አድራጎት የእንግዶች ማረፊያ አንድ ክፍል እንደሚያዘጋጁና በሚያስፈልገን ጊዜ መምጣት እንደምንችል፣ ጀልባችንም ጥሩ ከሆነች ለመሔድ ስንዘጋጅ ስለምታስፈልገን ማስቀመጥ እንዳለብን ገለጸለት፡፡ ከባድ ወንጀለኞች ወይም ለማደኛ ሊቦች መሆናችንን ጠየቀንና ከባድ ወንጀለኞች መሆናችንን ስንመልስለት ጠበቃው ደስ ያለው መሰለን፡፡

«ገላህን መታጠብና ጺምህን መላጨት ትፈልጋለህ?» ስትል ልጃገረዷ ጠየቀችኝና፣ «እባክህ እምቢ እንዳትል፣ ምንም ችግር የለውም፡፡ መታጠቢያ ቤቱ ውስጥ የሚያስፈልጉህን ማናቸውንም ነገሮች እንደምታገኝ ተስፋ አደርጋለሁ» አለች፡፡

ወደ መታጠቢያ ቤት ገባሁና ገላየን ታጥቤ ጺሜን ከተላጨሁ በኋላ የቴኒስ ጫማ፣ ነጭ ካልሲ፣ ነጭ ሸሚዝና ቡላ ሱሪ ለብሼ ብቅ አልኩ፡፡

አንድ የሕንድ ዜጋ መዝጊያ ቆረቆረ፡፡ ለማቹሬ አንድ የሆነ ጥቅል አምጥቶ ነበር፡፡ ዶክተሩ የእርሱም መጠን በእኔ ልክ ይሆናል ብሎ በመገመት ሊሆን ይችላል ልብስ ልኮለት ነበረ፡፡ ግን ኮሳሳው ማቹሬ እንዳይለብሰው ችግር ሆነበት፡፡ ምክንያቱም ጠበቃው ቤት ውስጥ ካለነው ከሦስታችን እንደ እርሱ ቀጫጫ አልነበረም፡፡ ሰውዬው ሕንዶች እንደሚያደርጉት እጅ ነሣና ሔደ፡፡ እንደዚህ የመሰለ ርኅራኄ ሲገጥመን ምን ለማለት እንችላለን? በልቤ ውስጥ የታመቀውን ስሜት ለመግለጽ አልችልም፡፡ ከሎሲዎ ቀደም ብሎ ተኛ፡፡ ከዚያም የቀረነው አምስታችን በልዩ ልዩ ርዕሶች ላይ ብዙ ሐሳቦች ተለዋወጥን፡፡ እነኛን የደስ ደስ ያላቸውን ሁለት ወይዛዝርት ያስገረመው ኑሯችንን እንደገና ለማቃናት እንዴት እንዳቀድን እየነገርናቸው ነው፡፡ የወደፊቱንና የወቅቱን ብቻ ካልሆነ ስላለፈው ምንም ወሬ አልተነሣም፡፡ ትሪኒዳድ ያመለጡ እስረኞችን ለማቆየት ባለመፍቀዷ ሚስተር ቦውን አዘነ፡፡ እንዲፈቀድልን ቀደም ሲል ጠይቆ እንደነበርና ግን



@BOOKALEM

ፍጹም እንዳልቻለ ነገረን:: ልጅቷ ልክ እንደ አባቷ በጣም የተጣራ ፈረንሣይኛ ትናገራለች:: ስትናገርም አፏን ያዝ እያደርገውም ነበር:: ዕድሜዋ በዐሥራ ሰባትና በሐያ መካከል ሆኖ ፊቷ በብጉር የተሸፈነ ጸጉረ ወርቃማ ወጣት ነበረች::

«ገና ወጣት ስለሆንክ ዕድልህ ወደፊት ነው:: ለመታሠር የበቃኸው ምን አድርገህ እንደሆነ አላውቅም፣ ለማወቅም አልፈልግም:: ግን በዚህች አነስተኛ ጀልባ ባሕር ለማቋረጥ ያለህ ቆራጥነትና ይህን የመሰለ ረጅምና አደገኛ ጉዞ ማድረግህ፣ ነፃ ለመውጣት ከፍተኛ ወኔ እንዳለህ ያሳያል:: ይህም እንደማስበው ከሆነ ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኝ ነው» አለችኝ::

በሚቀጥለው ጧት እስከ ሁለት ሰዓት ድረስ ተኛን:: ገበታው ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶአል:: ሚስተር በውን ወደ ፖርት ኦፍ ስፔይን መሔዱንና የእኛን የወደፊት ዕድል በሚመለከት አስፈላጊውን መረጃ እስኪሰበስብ ድረስ እስከ ሰዓት በኋላ እንደማይመለስ ወይዘዝርቱ ነገሩን::

እንደ እውነቱ ከሆነ ይህ ሰው ሦስት ያመለጡ ወንጀለኞች እቤቱ ትቶ ወደ ውጭ ሊሔድ መቻሉ ለእኛ ትልቅ ዋጋ ያለው ትምህርት ነበር:: «እንደ ማንኛውም ትክክለኛ ሰው ተመልከቻችኋለሁ:: ከተዋወቅን ዐሥራ ሁለት ሰዓቶች ብቻ ቢያልፉም፣ ከልጄና ከባለቤቴ ጋር እቤት እንድተዋችሁ በቂ እምነት አድሮብኛል:: ከዚህ በኋላ በቤቴ ውስጥ መጥፎ ምግባር ለመፈጸም ትችላላችሁ ብዬ አላምንም:: ስለሆነም ልክ እንደ ቀድሞ ጓደኞቼ እዚሁ ትቻችኋለሁ» የሚል ይመስላል:: ይህ ዕምነቱ በከፍተኛ ደረጃ ስሜታችንን ነካው::

ገና አዲስ ሕይወት ባልጀምርም ወደዚያው እያዘገምኩ ነበር:: አዲስ ከብር መላበሴ፣ ንፁሕ ሆኜ መቆጠሬ፣ ተዘፍቄበት ከነበረው ቆሻሻ በአንድ ሌሊት የተላቀቅሁ አንድ ልዩ ሰው ስለመሆኔ ማረጋገጫ ሆነኝ:: በእግር ብረቶች ማቃጨል የበታችነት ስሜት የሚያድርበት እሥረኛ፣ ነፃ ሆኖ እንኳ በዐይነ ቁራኛ እጠበቃለሁ ብሎ የሚከበው ጭንገግ፣ ያየሁት ያለፍኩበት፣ የተሠቃየሁበትና ማንኛውም እኔነቴን የበከለው፣ ያበሰበሰኝና አደገኛ ያደረገኝ፣ ላይ ላዩን ታዛዥ ብመስልም በውስጤ የታመቀው አሥጊው አደገኛነቴ ሁሉ በተአምር እልም ብሎ ጠፋ:: በጥብቅና የሚያገለግለውን አቶ በውን፣ አመሰግነዋለሁ:: በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ አንድ አዲስ ሰው ስላደረገኝ አመሰግነዋለሁ::

ዐይኖቿ ልክ በአካባቢያችን እንዳለው ባሕር ሰማያዊ የሆኑት ባለወርቃማ ጸጉር ኮረዳ፣ አባቷ ቤት ጎን ከሚገኘው የኮከነት ዘንባባ ሥር አብራኝ ተቀምጣ ነበረ:: ቀይ ፣ ቢጫና ሐመራዊ የሆኑት በወቅታቸው የፈኩ አበቦች፣ የአትክልት ቦታውን የማራኪ ሥነ ግጥም ማመንጫ አድርገውት ነበር::

«ሚስተር ሔንሪ» ብላ ጠራችኝ! አንድ ሰው ሚስተር ብሎ ከጠራኝ ምን ያህል ረጅም ጊዜ ሆኖኝ ነበር! «ትላንት ኔባባ እንደ ነገረህ በእንግሊዛውያን ባለሥልጣኖች ደደብነትና የማይረባ አመለካከት፣ ያሳዝነናል፣ እናንተ እዚህ ለመቆየት አልቻላችሁም:: ለማረፍ ያህል ብቻ ሁለት ሳምንት ይሰጣችሁና ከዚያም እንደገና ወደ ባሕር መሔድ ሊኖርባችሁ ነው:: ጀልባችሁን እንዳየኋት ከፊታችሁ ለሚጠብቃችሁ ረጅም ጉዞ በጣም ትንሽና በጣም ቀላል እንደሆነች ለመገንዘብ በቅቻለሁ:: ከእኛ ይበልጥ እንግዳ ተቀባዮችና ተግባቢዎች ወደሚገኙበት አገር እንድትደርሱ እንመኛለን:: ሁሉም የእንግሊዝ ደሴቶች ከዚህችኛዋ ደሴት ተመሳሳይ ናቸው:: የምለምናችሁ፣ የሚቀጥለው ጉዞችሁ አንድ ሥቃይ ቢያስከትልባችሁ፣ በእነዚህ ደሴቶች ሕዝቦች ላይ ቅሬታ እንዳትይዙባቸው ነው:: ኃላፊዎቹ እነርሱ አይደሉም:: ትእዛዙ የሚመጣው ከእንግሊዝ አገር ነው፣ እናንተን ከማያውቋችሁ ሰዎች ነው:: የአባቴ አድራሻ 101 ኩዊን ስትሪት፣ ፖርት ኦፍ ስፔይን፣ ትሪኒዳድ ነውና እባካችሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ቢሆን ትንሽ ቃላት ጻፉልንና ስለ ደህንነታችሁ እንወቅ::»

እንደገና ስሜቱ ተነካና ምን እንደምናገር ተደናገረኝ:: ማዳም ቦውንም ወደ እኛ መጣች:: አረንጓዴ ዐይኖችና ቡና ቀለም ጸጉር ያላት፣ ዐርባ ዓመት አካባቢ የሚሆናት በጣም ውብ ሴት ነበረች:: ፈካ ያለ አረንጓዴ ነጠላ ጫማ አድርጋ፣ ሳሳ ባለው ነጭ ቀሚሷ ላይ አንድ ነጭ መታጠቂያ ሸብ አድርጋ ነበር::

«ባለቤቴ እስከ ዐሥራ አንድ ሰዓት አይመለስም:: ያለ አንድ አጃቢ ፖሊስ ወደ ዋና ከተማዋ እንድትሔዱ ፈቃድ ሊያወጣላችሁ እየሞከረ ነው:: በተጨማሪ የመጀመሪያ ሌሊታችሁን በፖርት ኦፍ ስፔን ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ እንዳታሳልፉ ለመከላከል ይፈልጋል:: ቅልጥሙን የተሰበረው ጓደኛችሁ የእኛ ወዳጅ ወደሆነ አንድ ዶክተር ክሊኒክ በቀጥታ ይሔዳል:: እናንተ ሁለታችሁ ደግሞ ወደ በጎ አድራጎት የእንግዶች ማረፊያ ልትሔዱ ነው::»

አትክልቱ ቦታ ማቹሬም ተቀላቀለን:: ጀልባዋን ለመመልከት ሔዶ እንደነበርና በሚያደንቋት የመንደሩ ኗሪዎች የመከበቧንም ዜና ጨምሮ ነገረን:: ምንም የተነካ ነገር አልነበረም:: ግን በሚያተኩሩበት ወቅት ኗሪዎቹ ከመሪው ሥር አንዲት ጥይት አይተው ኖሮ፣ ከእነርሱ ውስጥ አንደኛው መታሰቢያ ሊያደርጋት መውሰድ ይችል እንደሆነ ጠይቆ፣ ማቹሬ፣ «ካፒቴን፣ ካፒቴን» ብሎት ነበር:: ማቹሬ የካፒቴኑን ፈቃድ መጠየቅ ይኖርብኛል ማለቱ እንደነበረ ኗሪዎቹ ገብቷቸዋል:: በተጨማሪ ኤሊዎቹን ለምን እንደማገለቅቃቸው ጠይቀውታል::

«ኤሊዎች አሏችሁ እንዴ?» ብላ ልጃገረዷ ጠየቀችኝና፣ «እስኪ ሔደን እንያቸው!» አለች::



@BOOKALEM

ወደ ጀልባዋ ሔድን:: በመንገድ ላይ እንዳለን በዓለም ላይ ሁሉ የተለመደ ነገር ይመስል አንዲት ሕፃን ሕንዳዊ ልጃገረድ እጇን ልትጨብጥ አቆመችኝና በእንግሊዝኛ፣ «እንደምን ዋላችሁ» አለች:: በጠቅላላው የተሰበሰበው መንደርተኛም «እንደምን ዋላችሁ» አለ:: ሁለቱን ኤሊዎች አወጣሁና፣ «ምን እናድርጋቸው? ወደ ባሕሩ መልሰን እንልቀቃቸው ወይስ በአትክልትሽ ቦታ ልታሰቀምጪያቸው ትፈልጊያለሽ?» አልኳት ልጃገረዷን::

«ከቤታችን ጀርባ አንዲት ትንሽ ኩሬ አለች:: ስለዚህ እዚያ ኩሬ ውስጥ እንከተታቸውና ለእናንተ ጉብኝት መታሰቢያ ይሁኑን» አለች::

«መልካም፣ እንግዲያው የምናደርገው ይህንኑ ነው::» ኮምፓሱን፣ ትንሽ ትንባሆ፣ የውሃውን በርሜል፣ ጨቤዬን፣ ገጀራውን፣ ቆንጨራውን፣ ብርድ ልብሱንና ቶሎ ብዬ በብርድ ልብሴ ውስጥ የደበቅኩትንና ማንም ሰው ያላየውን ሸጉጤን ብቻ በማስቀረት ማንኛውንም ጀልባዋ ውስጥ ማግኘት የቻልኩትን ነገር በሙሉ ለሰዎቹ አከፋፈልኩ::

ሚስተር ቦውን በዐሥራ አንድ ሰዓት ደረሰ:: «ክቡራን፣ ማንኛውም ነገር ተሳክቷል:: ወደዋናው ከተማ ራሴ አደርሳችኋለሁ:: መጀመሪያ ሚስተር ክሎሲዎን እናወርድና ከዚያም ወደ እንግዶች ማረፊያ እንሔዳለን::»

ክሎሲዎን ከአውቶሞቢሏ የኋላ ወንበር አስቀመጥነው:: ልጃገረዷን ደህና ሁኝ ስል ነበር እናቷ አንድ ሻንጣ ተሸክማ በመምጣት፣ «እባካችሁ እነዚህን የባልተቤቴን ስጦታዎች ውሰዱ:: መልካም ምኞታችንን ያስታውሳሉ» ያለችን::

«እናመሰግናለን፣ በጣም እናመሰግናችኋለን» አውቶሞቢሏ ተንቀሳቀሰች::

ለዐሥራ ሁለት ሩብ ጉይ ከክሊኒኩ ደረስን:: የተሠየመው በ«ቅዱስ ጊዮርጊስ» ስም ነበር:: ጤና ረዳቶች ክሎሲዎን እነሡና ቃሬዛ ላይ በማድረግ አንድ የሕንድ ዜጋ አልጋ ላይ ሆኖ ይጠባበቀው ከነበረበት ክፍል ውስጥ አስገቡት:: ዶክተሩ ወደ ውስጥ መጣና መጀመሪያ ቦውንን፣ ከዚያም ሌሎቻችንን ጨበጠን:: ፈረንሣይኛ አይናገርም፣ ግን ለክሎሲዎ ጥሩ ሕክምና እንደሚደረግለትና እኛም ዘወትር በፈለግንበት ወቅት እየመጣን ልናየው መቻላችንን በአንድ አስተርጓሚ አማካይነት ገለጸልን:: ወደ ቦውን አውቶሞቢል ተመለስንና ከተማውን አቋረጥን:: በመብራቶቹ፣ በመኪናዎቹ በብስክሌቶቹ ተደነቅን:: የዚህችን የእንጨት ቤቶች ከተማ አውራ መንገዶች፣ ነጮች ጥቁሮች፣ ሕንዶችና ቻይናውያን አጣብበውታል:: የበጎ አድራጎት እንግዶች ማረፊያ የሚገኘው ደማቅ መብራት ካለው አደባባይ «የዓሣ ገበያ» የሚል ጽሑፍ ከሠፈረበት አንድ መደብር አጠገብ ነበር:: የሕንፃው ምድር ቤት ከድንጋይ የተሠራ ሆኖ፣ የተቀረው ከጣውላ ነበር:: የበጎ አድራጎቱ ድርጅት ካፒቴንና መላው አባሎቹ ወንድም ሆነ ሴቱ



@BOOKALEM

ሳይቀር ተቀበሉን:: በመጠኑ ፈረንሣይኛ ይናገራሉ:: ግን ማንኛውም ሰው የሚያነጋግረን እኛ በማይገባን የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነበር:: ፈገግ ከሚለው ፊታቸውና ሰላምታ ከማይለያቸው ዐይኖቻቸው አኳያ ርኅሩኅ ቃላት እንደሚያፈልቁ ገብቶናል::

ሦስተኛው ፎቅ ላይ ወደሚገኝና ሦስት አልጋዎች ወዳሉት አንድ ክፍል ወሰዱን:: ከእኛ ጋር የሚመጣ ከሆነ ሦስተኛው አልጋ ለክሎሲዎ መሆኑ ነበር:: ከክፍሉ ጋር አብሮ የተያያዘ አንድ የገላ መታጠቢያ ቤት ከሣሙናና ፎጣዎች ጋር ነበር:: ካፒቴኑ ክፍላችንን ካሳየን በኋላ፣ «ከአሁን በኋላ ግማሽ ሰዓት ያህል ቆይተን አንድ ሰዓት ሲሆን፣ ሁላችንም አብረን እራት እንበላለን» አለ::

«እናመሰግናለን፣ ግን አልራበንም::»

«በከተማው መዘዋወር ከፈለጋችሁ ሁለት የአንቲይ ዶላር ይኸውላችሁ:: ስለዚህ ቡና፣ ወይም ሻይ ወይም ጀላቲ መግዛት ትችላላችሁ:: ግን መንገዱ እንዳይጠፋችሁ:: ወደ ቤት ለመመለስ ስትዘጋጁ የሚያስፈልጋችሁን ታክሲ አስቁማችሁ ‹ሓባከሀ ወደ በጎ አድራጎት ድርጅት› ማለት ብቻ ነው::»

ከዐሥር ደቂቃ በኋላ ወደ አውራ ጎዳናው ወጣን:: ማንም ሰው ሳያተኩርብን፣ ማንም ሰው ጉዳይ ሳይለን፣ ከሁሉም ሰዎች ጋር እየተጋፋን በእግር መንገዶቹ ላይ መጓዝ ጀመርን:: በአንድ ከተማ ውስጥ የመጀመሪያዎቹን ነፃ እርምጃዎቻችንን በማድረጋችን ተደንቀን በሰፊው ተነፈስን:: የማይናቅ ስፋት ባላት አንዲት ከተማ ውስጥ በነፃ እንድንራመድ ስለተፈቀደልን ይበልጥ ደስታችንን አደነደነው::ታዲያ በተጨማሪ በእኛ ላይ የጣሉብንን እምነታቸውን ፍጹም ላለመጣስ ሐቀኝነትም አደረብን:: ማቹሬና እኔ ዝግ እያልን በሕዝቡ መካከል እንጓዛለን:: ከሰዎች ጋር ለመጠጋት፣ ለመነካካትና ከእነርሱ እንደ አንዱ ነዋሪ ለመሆን እምርናል:: አንድ መጠጥ ቤት ውስጥ ገባንና ሁለት ቢራዎች ጠየቅን:: እንደዚያ ለማለት ብዙ የሚያዳግት አይመስልም:: «ሁለት ቢራ እባክሽ::» አፍንጫዋ ላይ የወርቅ ጌጥ ያደረገች አንዲት የሕንድ ኮረዳ ካመጣችልን በኋላ፣ «ግማሽ ዶላር ጌቶች» ማለቷ አስደነቀን:: ፈገግ ስትል ሉል የሚመስሉ ጥርሶቿ፣ ቦግ ያሉት የጥቁር ሐምራዊ ትላልቅ ዐይኖቿ፣ በትከሻዋ የተንዘፋለለው ጥቁሩ ጸጉሯ፣ የጡቶቿን ውበት ለማሳየት በከፊል የተገለጠው ደረቷ፣ ለሌላው ሰው የተለመዱ ተራ ነገሮች ቢመስሉም ለእኛ ግን ትንግርታዊና አስማታዊ መሰሉን:: አትቸኩል ፓፒ! እየቀለድክም መሆን አለበት፣ ዕውነት አይደለም! በቅርቡ በቁምህ የተቀበርህ ወንጀለኛ፣ የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት የተፈረደብህ እሥረኛ ነበርክ፣ አሁን ደግሞ አንድ ነፃ ሰው በመሆን ላይ ትገኛለህ!

ማቹሬ ከፈለ:: የዶላር ግማሽ ብቻ ተርፎት ነበር:: ቢራው እርኪና ቀዝቃዛ ነበር:: «ሌላ እንጨምር ይሆን?» ሲል ጠየቀኝ::



@BOOKALEM

ሁለተኛ ዙር ማዘዝ ብልህነት አልመሰለኝም:: «ስማ፣ አንድ ሰዓት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ነፃ ሆንህና ልትሰክር ትፈልጋለህ እንዴ?»

«ተው እንጂ ፓፒ፣ እታጋንነው! ሁለት ቢራዎች መውሰድኮ መስከር አይባልም::»

«ላይሆን ይችላል፣ ግን ደስታን በአንድ ጊዜ ተስገብግበን መጨረስ ትክክል ነው ብዬ አልገምትም:: በየጊዜው አንድ አንድ እያልን እየቆጠብን መቅመስ አለብን እንጂ መስገበገብ አይኖርብንም:: በተጨማሪ ገንዘቡ የእኛ አይደለም::»

«እሺ ልክ ነህ:: መጠቀም የሚኖርብን በቁጠባ ይሁን፣ ተገቢ ነው::»

መጠጥ ቤቱን ተውንና ከአንዱ የከተማው ዳር እስከ ሌላው በተዘረጋው የዋተርስ አውራ ጎዳና ቁልቁል ወረድን:: በከተማዎቹ ታክሲዎች፣ በበቅሎዎች በሚሳቡ ትናንሽ ጋሪዎች፣ በካሚዎኖች፣ በሲኒማ ቤቶች በሚንቦገቦጉት የመብራት ምልክቶችና የማታ ክበቦች፣ በሕንዶችና በጥቁር ኮረዳዎች ዐይኖች ከመጠን በላይ እየተደነቅን ድንገት ሳናውቀው በወደቡ አካባቢ ደረስን:: ከፊትለፊታችን መብራት ያላቸው ጀልባዎች፣ እንደ ፓናማ፣ ሎስ አንጀለስ፣ ቦስተን፣ ኩዊቤክ፣ የመሳሰሉ የዝነኛ ወደቦችን ስም የያዙ የመንገደኞች መርከቦችና፣ ከሐምቡርግ፣ ከአምስተርዳም፣ ከሎንዶን የመጡ ዕቃ ጫኝ መርከቦች ተገጥግጠዋል:: ወደቡ ከዳር እስከዳር በመጠጥ ቤቶች፣ በሴተኛ አዳሪዎችና በሆቴል ቤቶች ተጨናንቋል:: በውስጣቸው ወንዶችና ሴቶች ጥቅጥቅ ብለው ሲጠጡ፣ ሲዘፍኑና እየተጯጯሁ ሲጨቃጨቁ በድንገት እኔንም ከእነዚህ ሰዎች ጋር ተቀላቀል የሚል የማልቋቋመው ከፍተኛ ፍላጎት አደረብኝ:: ስድነት ሊመስል ይችል ይሆናል፣ ግን ስሜትን በጣም ፈንቅሎ የሚማርክ ነበር:: ከመጠጥ ቤቶቹ በአንደኛው ደጃፍ ላይ በበረዶ የታጀሉ የአይስተሮች፣ ሽሪምፖች፣ የከላሞች . . . እለ የተባለ የባሕር ውስጥ ምግብ በያይነቱ ተላላፊውን ለማስጎምጀት ለትዕይንት ተደርድሮ ነበር:: ቀይና ነጭ ጨርቅ የለበሱት ገበታዎች ብዙ ሰዎችን እንደሚያስተናግዱ እኛም እንድንቀመጥ ይጋብዙሉ:: ጠያይምና ደስ የሚል መልክ ያላቸው ኮረዳዎች ባለደማቅ ቀለምና ሰውነት የሚያሳዩ ስስ ቀሚሶቻቸውን ለብሰው ይበልጥ አንድንደሰት ይገፋፉናል:: ከእነርሱ መካከል ወደ አንዷ ሔድኩና፣ «የፈረንሣይ ገንዘብ ተቀባይነት አለው?» ብየ የአንድ ሺ ፍራንክ ኖት ሰጠኋት:: «አዎ እመነዝርልሃለሁ:: እሺ::» ኖቱን ተቀበለችና ወደ ሚጯጯኸው ክፍል ወስጥ ገብታ ቆየች:: ከዚያም ተመልሳ «ወደዚህ ና» አለችና ገንዘብ ተቀባዩ ዘንድ ወሰደችኝ:: ቻይናዊ ነበር::

«ፈረንሣዊ ነህ?»

«አዎ»

«አንድ ሺ ፍራንክ ለመመንዘረ ነው?»



@BOOKALEM

«አዎ»

«ሁሉንም በአንቲይ ዶላር ነው?»

«አዎ»

«ፓስፖርት?»

«የለኝም»

«የመርከበኛ መታወቂያ ካርድ?»

«የለኝም»

«የይለፍ ወረቀት?»

«የለኝም»

«እሺ።» ከኮረዳዋ ጋር አንድ ሁለት ቃላት ተነጋገረ። የከፍሉን ዙሪያ ቃኘች። የወርቅ ጥልፍና መልህቅ ያለው የእኔን የመሰለች ኬፕ የደፋ አንድ መርከበኛ መሳይ ሰው ዘንድ ሔደችና ወደ ገንዘብ ተቀባዩ ይዛው መጣች።

«መታወቂያ ካርድህን?» አለው ቻይናዊው።

«ይኸው።»

ቻይናዊው ኮስተር ብሎ በእርሱ ስም አንድ የምንዛሪ ፋክቱር አዘጋጅና አስፈረመው። ከዚያም ኮረዳዋ ከንዱን ይዛ እየመራች ወደ መቀመጫው መልሳ ወሰደችው። ምን መደረግ እንዳለበት ቀደም-ብሎ የለመደ ኖሯል። ባለ ሃምሳ ዶላር አንድ ኖትና የሁለት ዶላር ኖቶች፣ በጠቅላላው ሁለት መቶ ሃምሳ የአንቲይ ዶላር ተቀበልኩ። ለኮረዳዋ አንድ ዶላር ጉርሻ ሰጠሁ። ወደ ውጭ ወጥተን ከጠረጴዛዎቹ በአንደኛው ላይ ተቀመጥንና የጎመገንለትን የባሕር ምግብ ከተመገብን በኋላ፣ በደረቅ ነጭ የወይን ጠጅ አወራረድነው።



@BOOKALEM

# አራተኛ ማስታወሻ

## የመጀመሪያው ማምለጥ (ይቀጥላል)

## ትሪኒዳድ

በእንግሊዞች ከተማ ያሳለፍኳትን ያችን የመጀመሪያ የነፃነት ሌሊት ልክ ትላንት እንደሆነች ሳስታውሳት እኖራለሁ:: በልባችን ብርሃንና ሙቀት ተሞልተን ከሚደሰተውና ከሚስቀው ሕዝብ ጋር በየቦታው ዞርን:: መጠጥ ቤቶቹ በመርከበኞችና እነርሱን ለማጥመድ አሰፍስፈው በሚጠባበቁ ኮረዳዎች ተሞልተው ነበር:: እነዚህ ግን በፓሪስ በሊ ሐቭር ወይም በማርሴይ እንዳሉት ሞጋጎች ዐይናቻቸው በጉጉትና በጮሌነት የፈጠጡ አራዳዎች አልነበሩም:: የትሪኒዳድ ኮረዳዎች የተለያዩ መልኮች ነበራቸው:: ወደ ብጫነት የሚያደሉ ቻይናውያን ጠቆር ያሉ አፍሪቃውያን እንደዚሁም የሸንኮራ አገዳና የኮከነት ተክል ለማልማት ዘሮቻቸው ቀደም ብለው ተግዘው የነበሩ የሕንድ ጠያይምና ባለ ሐር ጸጉር ሴቶች የቻይናውያንና የሕንድ ድብልቅና በአፍንጫዎቻቸው ላይ የወርቅ ቀለበቶች የሚያንጠለጥሉ ጭምር ነበሩ:: ከዚያም በሮማውያን ገጽታቸው ላይ የሚንቦገቦጉ ትላልቅ ጥቁር ዐይኖችና እንደ መዳብ የሚያበሩ ፊቶች ያሏቸውና « እንዴት እንደ ተስተካከሉ እስኪ ተመልከቷቸው» የሚሉ የሚመስሉ ወደፊት የተወጠሩ ጡቶች የሚያስመዘግቡ የላቲን ዝርያዎችም አሉ:: እነዚህ ሁሉ ጸጉሮቻቸውን በልዩ ልዩ ቀለማት አበባዎች የሚያስጌጡ ኮረዳዎች ስሜታቸው የሚቀሰቅሰው ለወራዳ ተግባር ወይም ለንግድ አልነበረም:: በእርግጥ የሚደሰቱበት ሞያ እንዳልነበረና ገንዘብም በኑሯቸው ውስጥ ዓቢይ ነገር እንዳልሆነ ሁኔታቸው ይነግራል::

ማቹሬና እኔ ልክ ከመብራት ጋር የሚጋጩ ጥንድ የእሳት እራት ቢራቢሮዎች መሰለን ከመጠጥ ቤት ወደ መጠጥ ቤት ስንናወዝ ቆየን:: ደማቅ መብራቶች ከሚገኙባት አንዲት ትንሽ አደባባይ ብቅ ስንል አንድ ቤተክርስቲያን ላይ ሰዓት አየሁ:: ከሌሊቱ ስምንት ሰዓት ሆኗል:: መመለስ ነበረብን:: ፈርለቀቅን:: ወደ እንግዶች ማረፊያ በሁለት ዶላር የሚወስደን አንድ ታክሲ ጠራሁ:: በጣም ኃፍረት እየተሰማን ስንገባ፤ ዕድሜዋ በሐያ አምስትና በሠላሳ መካከል የሆነ ቡናማ ጸጉር ያላት የበጎ አድራጎቱ ድርጅት አባል የሆነች ሴት በሰላምታ ተቀበለችን:: እንኳን ደህና መጣችሁ አለችና ለስሜት በሚጥሙ ቃላት በእንግሊዝ ቋንቋ ጥቂት አውርታን ከዚያም የከፍላችንን ቁልፍ ስትሰጠን መልካም ሌሊት ተመኘችልን:: ወደ አልጋችን ውስጥ ገባን:: ከሻንጣዬ ውስጥ አንድ ፒጃማ አገኘሁ:: መብራቱን ላጠፋ ስል ነበር ማቹሬ እንደዚህ ሲለኝ የሰማሁት:: « እንደዚህ በአጭር ጊዜ ውስጥ ይህን ሁሉ የሰጠንን አምላክ ማመስገን



@BOOKALEM

የሚኖርብን አይመስልህም? ምን ታስባለህ ፓፒ?»

« አንተው የራስህን ሾምላክ አመስግንልኝ:: ታላቅ ወዳጅ ነው:: ለእኛ በጣም ግሩም እንደሆነልን ሐቅ ነው:: ደህና እደር::» ከዚያም መብራቱን አጠፋሁ::

ይህ ትንሣኤ ይህ ከተቀበርኩበት መቃብር ያመለጥኩበትና ከዓለም ሕዝቦች ጋር የተቀላቀልኩበት አጋጣሚ በጣም አስፈንድቆኝ ስለነበር መተኛት አልቻልኩም:: በዐይኖቼ ላይ እንደ ሕልም በግ እልም የሚሉ ድብልቅልቅ ስሜቶች ድቅን አሉብኝ፡- ቻሎቱ፣ ማረፊያ ጣቢያው፣ ቆማጦቹ፣ ቅዱስ ማርቲን ደ ሬ ፣ ትሪቡላር፣ ኢዮአስ፣ ሞግዱ - ባለፉት ዓመታት አልፌባቸው የነበሩት አገሮች በሙሉ ልክ እንደ ባሌ ዳንስ ተጫዋቾች እየተከታተሉ ወደ አእምሮዬ ለመግባት ይታገሉ ነበር:: ትዝታዎቼን ለመርሳት ሞከርኩ:: ግን ልረሳቸው አልቻልኩም:: እንግዳ የሆነብኝ ሌላው ነገር ደግሞ እነዚህ ትዝታዎች ከዱር ዓሣማዎቹ ጩኸት ከእሞራዎቹ ጫጫታ ከነፋሱና ከማዕበሎቹ ውሽንፍር ትተናቸው ከመጣነው መጠጥ ቤቶች ውስጥ ከሰማኋቸው የሕንዶች ቫዮሊን የሙዚቃ ድምፆች ጋር መቀላቀላቸው ነበር::

በማግሥቱ እስከ ረፋዱ ተኛሁ:: በአራት ሰዓት መዝጊያው ተቆረቆረ ሚስተር ቦውን ነበር:: ፈገግ እያለ « እንደ ምን አደራችሁ:: ገና አልጋ ላይ ናችሁ እንዴ? ዘግይታችሁ መሆን አለበት:: ጥሩ ጊዜ አሳለፋችሁ?» አለ::

« እንደምን አደሩ:: አዎ አምሽተን ነው የመጣነው እባክዎ ይቅርታ ያድርጉልን::»

« በምን የተነሣ? ካሳለፋችሁት ሕይወት አኳያ አድራጎታችሁ በትክክል ተገቢ ነው:: እንደ ነፃ ሰዎች የሆናችሁበትን የመጀመሪያዋን ምሽታችሁን መጠቀም ነበረባችሁ:: የመጣሁት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይገኙችሁ ልሔድ ነው:: ወደ ሀገሪቱ ያለሕጋዊ ፈቃድ መግባታችሁን በግንባር ቃል ለመስጠት እዚያ መሔድ አለባችሁ:: ያ ፎርማሊቲ ከተጠናቀቀ በኋላ ጓደኛችሁን ለማየት እንሔዳለን:: ቀደም ብለው ዛሬ ጧት ራጅ አንሥተውታል:: ውጤቱን በፍጥነት እናውቃለን::»

ልብሳችንን ለበስንና ሚስተር ቦውንና ካፒቴኑ ከሚቆዩበት የምድር ቤት ወረድን::

«እንደምን አደራችሁ ጓደኞቼ» አለ ባልተስተካከለ ፈረንሣይኛው::

«ሁላችሁም እንደምን አደራችሁ:: ደህና ናችሁ?» ስትል አንዲት የበጎ አድራጎቱ የሴት መኮንን ተናገረችና፣ «ፖርት አፍ ስፔይን ተወዳጅ ሆና አገኛችኋት?» ብላ ጠየቀችን::

«አዎ፣ እንዴ! በጣም ግሩም ጊዜ አሳለፍን»

ቡና ጠጣንና ከእንግዶች ማረፊያው እስከ ፖሊስ ጣቢያው ሁለት መቶ ያርድ



@BOOKALEM

የነበረውን ርቀት በእግራችን ተጓዝን፡፡ ያለምንም ልዩ አመለካከት ፖሊሱ ሰላምታ አቀረበልን፡፡ ካኪ ዩኒፎርም የለበሱ ሁለት ጥቁር ዘበኞች መሀል አለፍንና ከፍተኛ ግርማ ያለው አንድ ቢሮ ውስጥ ገባን፡፡ ካኪ ሸሚዝና ቁምጣ ሱሪ የለበሰ፣ በሜዳሎች የተንቆጠቆጠ፣ ዕድሜው በግምት ሐምሳ ዓመት የሚጠጋው አንድ መኮንን ብድግ ብሎ በፈረንሣይኛ ቋንቋ አነጋገረን፡፡ «እንደምን አደራችሁ፡፡ እባካችሁ ተቀመጡ፡፡ ኦፊሺያል የሆነውን ቃላችሁን ከመቀበላችን በፊት ትንሽ ጥያቄዎች ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ፡፡»

«ዕደሜያችሁ ስንት ነው?»

«ሐያ ስድስትና ዐሥራ ዘጠኝ፡፡»

«ምን ነበር ወንጀላችሁ?»

«ነፍስ መግደል፡፡»

«ምን ያህል ተፈረደባችሁ?»

«የዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት፡፡»

«እንግዲያስ በአንደኛ ደረጃ ነፍስ መግደል ነበራ?»

«አይደለም ጌታዬ፣ የእኔ ሁለተኛ ደረጃ ነበር፡፡»

«የእኔ አንደኛ ደረጃ ነበር» አለና ማቹሬ በማከታተል፣ «ዕድሜዬ ግን ዐሥራ ሰባት ዓመት ብቻ ነበር» አለ፡፡

«በዐሥራ ሰባት ምን እንደምታደርግ ቷውቃለህ» አለና መኮንኑ በማከታተል፣ «እንግሊዝ ውስጥ ቢሆን ኖሮ ትሰቀል ነበር፡፡ ይሁንና የፈረንሣውያንን ሕግ እንግሊዛውያን ባለሥልጣኖች ሊተቹበት አይገባም፡፡ ወንጀለኞቻቸውን ወደ ፈረንሣይ ጊያና መላካቸውን ግን አንስማማበትም፡፡ ፈረንሣይን ለመሰለ አንድ ሥልጡን ሀገር ይህ ድርጊት ኢሰብአዊና ክብርን የሚያቃልል ነው፡፡ ግን እናዝናለን፡፡ በትሪኒዳድም ሆነ በማናቸውም የእንግሊዝ ደሴቶች ውስጥ ለመቆየት አትችሉም፡፡ የሚሰጣችሁን የጊዜ ገደብ ለማስረዘም በሕመም ወይም በሌላ ምክንያት ሰበብ ለመፈለግ እንዳትሞክሩ፡፡ ከእኛ ጋር እንድንተማመን መጠየቅ ይኖርብኛል፡፡ ለዐሥራ ስምንት ቀናት ፖርት ኦፍ ስፔን ውስጥ ለመቆየት ነፃ ናችሁ፡፡ እንደሚታወቀው እንዲት ጥሩ ጀልባ አላችሁ፡፡ ጥገና ቢያስፈልጋት የእንግሊዝ ባሕር ኃይል ሠራተኞች ይሠሩላችኋል፡፡ ለጉዟችሁ የሚያስፈልጋችሁ ማንኛውም ምግብና ከዚህም ሌላ አንድ ጥሩ ኮምፓስና አንድ የባሕር መስመር ካርታ ይሰጣችኋል፡፡ አንዳንድ የደቡብ አሜሪካ ሐገሮች እንደሚቀበሏችሁ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ለፈረንሣይ ባለሥልጣኖች ሊልኳችሁ እስከሚወስኑበት ጊዜ ድረስ ታሥራችሁ በመንገድ ሥራ ብርጌድ ውስጥ ስለምትመደቡ ወደ ቬኔዙዌላ እንዳትሔዱ፡፡ ወንጀላችሁ ከባድ ሊሆን ይችላል፣ ግን ይህ ደግሞ ሕይወታችሁ እስከዘለዓለም ተበላሸ ማለት አይደለም፡፡ ወጣትና ጤነኛ ከመሆናችሁም ሌላ ጨዋ ልጆች ትመስላላችሁ፡፡



@BOOKALEM

ስለሆነም ካለፋችሁበት ሁኔታ አንፃር ቋሚ ሽንፈትን ለመቀበል እንደማትፈልጉ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ራሱ እዚህ ድረስ መምጣታችሁም አለመፈለጋችሁን ይመሰክራል፡፡ ኃላፊነት የሚሰማው የሕብረተሰብ አባል እንድትሆኑ ለመርዳት እጄን ስዘረጋ ደስ ይለኛል፡፡ መልካም ዕድል! ማንኛውም ችግር ቢገጥማችሁ በፈረንሣይኛ ልታነጋግሩት የምትችሉት አንድ ሰው ስለሚኖር በዚህ ስልክ ቁጥር ደውሉ፡፡

ደወል አንቃጨለና አንድ ሲቪል ሰው ወደ እኛ መጣ፡፡ ብዙ ፖሊሶችና ሲቪሎች ታይፕ ከሚመቱበት አንድ ክፍል ውስጥ ተወሰድንና ከመካከላቸው አንዱ ቃላችንን ተቀበለ፡፡

«ወደ ትሪኒዳድ ለምን መጣችሁ?»

«እግረመንገዳችንን ለማረፍ ነበር፡፡»

«ከወዴት ነው የመጣቸሁት?»

«ከፈረንሣይ ጊያና፡፡»

«በምታመልጡበት ወቅት፣ የፈጸማችሁት ወንጀል ነበረ? ጉዳት የደረሰበት ወይንም የገደላችሁት ሰው ቢኖር?»

«ከባድ ጉዳት የደረሰበት ሰው አልነበረም፡፡»

«እንዴት ወጣችሁ?»

«ከመልቀቃችን በፊት ዐውቀነዋል፡፡»

ዕድሜያችንን፣ በፈረንሣይ ሕግ የቅጣታችንን ደረጃ፣ ሌላ ሌላውንም በሙሉ አስረዳነው፡፡ ከዚያም ቃል ተቀባዩ እንደዚህ አለ፡፡ «እስከ ዐሥራ ስምንት ቀናት ድረስ እዚህ ለመቆየት ትችላላችሁ፡፡ በዚያ ወቅት ማንኛውንም የምትፈልጉትን ለማድረግ ነፃነት አላችሁ፡፡ ማረፊያችሁን ከቀየራችሁ አስታውቁን፡፡ የሃምሳ አለቃ ዊሊ እባላለሁ፡፡ አድራሻዬ ከሁለት ስልክ ቁጥሮች ጋር ይኸውላችሁ፡፡ አንደኛው የታወቀው የፖሊስ ባልደረባነቴ ቁጥር፣ ሌላው የግል ቁጥሬ ነው፡፡ አንድ ነገር አጋጥሟችሁ ዕርዳታ ቢያስፈልጋችሁ ወዲያውኑ ደውሉልኝ፡፡ ለዕምነታችን ዋጋ እንደምትሰጡት እርግጠኞች ነን፡፡ መልካም ሥነ ምግባር እንደምታሳዩ አምናለሁ፡፡»

ከትንሽ ጊዜ በኋላ ሚስተር በውን ወደ ክሊኒኩ ይዞን ሔደ፡፡ ከሎሲዎ እኛን በማየቱ ደስ ብሎት ነበር፡፡ በከተማ ስላሣለፍነው ምሽት ምንም ነገር አልተናገርንም፡፡ የነገርነው ቢኖር እንደፈለግን ለመውጣትና ለመግባት ነፃ መሆናችንን ብቻ ነበር፡፡ ይህም አስደነቀውና፣ «ያለ ምንም አጃቢ?» አለ፡፡

«አዎ፣ ያለ ምንም አጃቢ»

«እነዚህ እንግሊዞች ቀልደኛ ሰዎች ናቸው ጃል፡፡»

በውን ዶክተሩን ለመፈለግ ሄዶ ስለነበር አሁን ከእርሱ ጋር ተመለሰ፡፡



@BOOKALEM

«ስብራቱን የጠገነው ማነው?» ሲል ክሎሲዎን ጠየቀው።

«እኔና እዚህ የሌለ አንድ ሌላ ሰው» አልኩ።

«ጥሩ ስለጠገናማችሁት እንደገና ማስተካከል አያስፈልገንም፤ የተሰበረው አጥንት ከቦታው ገብቷል። አንድ የብረት ምርኩዝ እንሠራልህና በመጠኑ እየተራመድክ ለመዘዋወር ትችላለህ። እዚህ መቆየት ትፈልጋለህ፣ ወይስ ከጓደኞችህ ጋር ለመሔድ?»

«ከእነርሱ ጋር ለመሔድ።»

«መልካም ነው። ነገ ጧት መሔድ ትችላለህ። »

በእጅጉ አመሰገንነው። ዶክተሩና ሚስተር ቦውን በየፊናቸው ሔዱ። እኛም የቀረውን ጧትና ከቀትር በኋላ በከፊል ከክሎሲዎ ጋር አሳለፍን። የማቀዝቀዣ መሣሪያ አየሩን በሚያናፍስበትና መስኮቱ ወለል ብሎ በተከፈተ የእንግዳ ማረፊያ ክፍላችን ወስጥ እንደገና በማግሥቱ ስንሰባሰብ ደግሞ ከመጠን በላይ ደስታችን ጋለ። በአዲሶቹ ልብሶቻችን ውበትና ሙሉ ጤነኞች በመሆናችን ራሳችንን የምሥራች አልነው። ግን ውይይቱ ወደ አለፈው ታሪካችን ሊያዘነብል ሲል እንደዚህ አልኩ።

«ስለ ወደፊቱና ስለአሁኑ ብቻ ማሰብ እንጂ፣ ያለፈውን መርሳት አለብን። ለምሳሌ፣ ወዴት መሔድ ይኖርብናል - ወደ ኮሎምቢያ? ፓናማ? ኮስታሪካ? ይበልጥ ሊቀበሉን የሚችሉት የትኞቹ ሀገሮች እንደሆኑ ቦውንን መጠየቅ ይገባናል።»

ወደ ቦውን ቢሮ ስልክ ደወልኩ፤ እዚያ አልነበረም። ሳን ፈርናንዶ ወደሚገኘው ቤቱ ደወልኩ፤ ልጁ መለሰች። ለትንሽ ጊዜ እንደተነጋገርን፣ «ሚስተር ሔንሪ፣ ልክ ከእናንተ ማረፊያ አጠገብ ከሚገኘው ከፈረንሣውያን ገበያ ተነሥተው ሳንፈርናንዶ የሚመላለሱ አውቶብሶች አሉ። ለምን መጥታችሁ ከሰዓት በኋላ እዚህ አትቆዩም። እባካችሁ እንደዚያ አድርጉ። እጠብቃችኋለሁ» አለች።

ስለሆነም ክሎሲዎ በመጠኑ ሚሊታሪ የሚያስመስለውን አዲሱን ቡናማ ቀለም ልብስ እንደለበሰ ሽክ ብሎ፣ ሦስታችንም በሙሉ ወደ ሳን ፈርናንዶ ተነሣን።

ያን የመሰለ የሞቀ መስተንግዶ ተሰጥቶን ወደ ነበረበት ቤት እንደገና ስንመለስ መንፈሳችንን ደስታ ሞላው። ሁለቱ ሴቶች ስሜታችንን ተረድተውት መሆን አለበት፣ «ውድ ወዳጆቻችን፣ ወደ ራሳችሁ ቤት ተመለሣችሁ» አሉን። ስለሆነም አሁን የሚጠሩን በመጀመሪያ ስሞቻችን፣ እንደመሆኑ «ሔንሪ፣ ስኳር ላድርግልህ?» ወይም «አንድሬ፣ (የማቹሬ ስም ነበር) ተጨማሪ ነገር ትፈልጋለህ?» በማለት ነበር።

«የተወደዳችሁ ማዳም ቦውንና ሚስስ ቦውን፣ እግዚአብሔር ለጋስነታችሁንና ሩኅሩኅነታችሁን ተገንዝቦ፣ ከዚያች ቀን ጀምሮ በደስታ እንድትኖሩ፣ ውለታችሁን ሁሉ መልሶላችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።»

በጠረጴዛው ላይ አንድ ካርታ ዘረጋንና ዕቅዶቻችንን ነደፍን። መንገዶቹ ረጅም



@BOOKALEM

ነበሩ:: ሳንታ ማርታ ወደ ተባለችው የመጀመሪያዋ የኮሎምቢያ ወደብ ሰባት መቶ ሐያ ማይል፣ ወደ ፓናማ አንድ ሺ ሁለት መቶ ማይል፣ ወደ ኮስታሪካ አንድ ሺ አምስት መቶ ማይል::

በውን ተመሰሰ:: «ቆንሲሎቹ ዘንድ በሙሉ ስልክ ደውዬ መልካም ዜና ሰምቻለሁ» አለን፣ «ለማረፍ ያህል በኮራሰ ለትንሽ ቀናት መቆየት ትችላላችሁ:: ኮሎምቢያ ስለአመለጡ ወንጀለኞች መመሪያ አላወጣችም:: ቆንሲሉ እስከሚያውቀው ድረስ እስካሁን ኮሎምቢያም ሆነ ፓናማ ውስጥ ወይም የትኛውም ቦታ በባሕር የደረሰ ወንጀለኛ ከቶውንም የለም::»

«አንድ ሐሳብ አለኝ» አለች የሚስተር በውን ልጅ ማርጋሬት:: «ግን በጣም ሩቅ ነው ቢያንስ አንድ ሺ ስምንት መቶ ማይል::»

«ቦታው ወዴት ነው?» ሲል አባቷ ጠየቃት::

«እንግሊዝ ሆንዱራስ:: አገረገዢው የክርስትና አባቴ ስለሆነ ምናልባት እዚያ እርዳታ ታገኙ ይሆናል::»

ወደ ጓደኞቼ ተመለከትኩና፣ «ጉዞ ወደ እንግሊዝ ሆንዱራስ» አልኩ:: በምዕራብና በደቡብ፣ ጓቴማላ፣ በሰሜን፣ ሜክሲኮ የሚያዋስናት የእንግሊዝ ይዞታ ነች::

በማርጋሬትና በእናቷ እርዳታ ካርታ ላይ መስመራችንን እየነደፍን የከሰዓት በኋላውን ጊዜ አሳለፍን:: የመጀመሪያ ማረፊያ ስድስት መቶ ማይል ላይ በኮራሶ:: ሁለተኛ ማረፊያ - ከኮራሶ መንገዳችን ላይ ከሚያጋጥመን ማንኛውም ደሴት ላይ:: ሦስተኛ ማረፊያ - እንግሊዝ ሆንዱራስ::

በባህር ላይ ምን እንደሚያጋጥመን ፍጹም ማወቅ ስለማይቻል የጣሳ ምግቦች ሣጥን መያዝ እንዳለብን ተወሰነ:: ሥጋ፣ አትክልቶች፣ ማርማላታ፣ ዓሣ ወዘተ . . . ይህም ከፖሊሶቹ የተሰጡንን ስንቆች ማጠናከሪያ እንዲሆን ነበር::

የሳልቫቶሬ ሁለገብ መደብር ስንቃችንን በስጦታ መልክ ለማበርከት ደስተኛ እንደሚሆን ማርጋሬት አንድ ሐሳብ አቀረበችና፣ «ግን ፣ እነርሱ ካልፈለጉም እማማና እኔ እንገዛላችኋለን» አለች::

«አይሆንም፣ በምንም ምክንያት» አልኩ::

«ዝም በል ሔንሪ»

«አይሆንም፤ አልፈቅድልሽም:: የራሳችን ገንዘብ አለን:: ለዕቃዎቹ ራሳችንን በቀላሉ መክፈል እየቻልን የእናንተን ሩኅሩኅነት ለማሚጠጥ መሞከር ለእኛ ነውር ይሆንብናል::»

ከታላቁ ጉዟችን በፊት አንድ የመጨረሻ ጉብኝት ለማድረግ ቃል ገብተን ተለያየን::



@BOOKALEM

በየምሽቱ ዐሥራ አንድ ሰዓት ላይ ወደ ከተማ እንወጣለን:: በጣም እንቅስቃሴ ባለበት አደባባይ አንድ አግዳሚ ወንበር ላይ ከሎሲዎን እናስቀምጥና አንዳችን በከተማ ስንዘዋወር፣ ሌላው ከእርሱ ጋር ለመሆን ማቹሬና እኔ ተራ እንለዋወጣለን:: እዚህ ከመጣን አሁን ዐሥር ቀን ሆነን:: ለዚያ ለብረት ምርኩዝ ምስጋና ይግባውና ከሎሲዎ ያለ ችግር በመጠኑ ይራመዳል:: በከተማ ታክሲዎች ወደ ወደብ መሔድ በብዙዎቹ መጠጥ ቤቶች ዘንድ እንደ ደንበኞች ታይተን ነበር:: ፖሊሶቹም ሰላምታ ያቀርቡልናል:: ምን እንደነበርንና ከወዴት እንደመጣን ማንኛውም ሰው ዐውቋል:: ይሁንና አንድም ሰው ስለዚህ አይገልጽም:: የተለማመድናቸው መጠጥ ቤቶች ለምግብና ለመጠጥ ከመርከበኞቹ ይልቅ ለእኛ የሚያስከፍሉን በቅናሽ ዋጋ ነበር:: ኮረዳዎቹም እንደዚሁ ያደርጋሉ::

አብዛኛውን ጊዜ ኮረዳዎቹ ከመርከበኞች፣ ከመኮንኖችና ከቱሪስቶች ጋር ሲቀመጡ ሣያሰልሱ ይጠጣሉ፣ በተቻለ መጠን ብዙ እንዲሰከሩም ያደርጓቸዋል:: በመጠጥ ቤቱ ዳንስ በሚኖርበት ወቅት በመጀመሪያ ብዙ መጠጥ ካልገዛላቸው በስተቀር ፍጹም ከአንድ ሰው ጋር አይደንሱም:: ከእኛ ጋር ግን የተለየ ነበር:: ከእኛ ጋር ረጅም ጊዜ ይቀመጣሉ፣ ካልገፋፋናቸው በስተቀር መጠጥ አይወስዱም:: ያንንም ሲቀበሉ ዝነኛውን የእነርሱን መጠጥ ሳይሆን አንድ ቢራ ወይም ዕውነተኛውን ውስኪ በሶዳ ነበር:: ሁኔታችንን እንዳወቁና እንዳዘኑልን የሚገልፁበት መንገድ በመሆኑ ይህም አስደሰተን::

ጀልባዋ ፖርት ኦፍ ስፔይን ከሚገኘው የእንግሊዝ ባሕር ኃይል ሰፈር ገብታለች:: ወለሏ ተጠናክሮና በጠርዟ ላይ ሌላ ሰድስት ኢንች ተጨምሮላት ታድሳ ነበር:: በጥሩ ቅርፅ የምትገኝ ትመስላለች:: ምሰሶውን በቀላልና በከፍተኛ ዓይነት ሌላ ምሰሶ ተከተው፣ ለአቅጣጫ ማስተካከያ እንጠቀምባቸው የነበሩትንም የዱቄት ከረጢቶች በጠንካራና ቀለም በተነከሩ የንፋስ ሸራዎች ለውጠውልናል:: አንድ የባሕር ሐይል መኮንን የተስተካከለች አንዷት ኮምፓስ አበረከተልኝና በካርታ ላይ አቅጣጫችንን እንዴት እንደምንቀይስ አሳየኝ:: የኮራሶ መስመራችን በሰሜን ሆኖ አንድ ነጥብ ወደ ምዕራብ ሲል ይሆናል::

ካፒቴኑ «ታርፖን» ከምትባል አንድ የማሠልጠኛ መርከብ አዛዥ ከሆነ የባሕር ኃይል መኮንን ጋር አስተዋወቀኝ:: በሚቀጥለው ቀን ጧት በሁለት ሰዓት ከወደቡ ለልምምድ ልገኝ እችል እንደሆነ ፈቃደኝነቴን ጠየቀኝ:: ነገሩ ግራ ገብቶኝ ነበር፣ ግን ተስማማሁ:: በሚቀጥለው ቀን ጧት ማቹሬና እኔ ወደ ባሕር ኃይል ሠፈር ሔድን:: አንድ መርከበኛ አጀበንና ጥሩ ነፋስ አግኝተን ወደ ባሕር ወጣን:: ለሁለት ሰዓት እንደተለማመድን ድንገት አንድ የጦር መርከብ ብቅ አለ:: ሙሉ ማዕረግ ልብሳቸውን



@BOOKALEM

እንደለበሱ ሠራተኞቹና መኮንኖቹ ሁሉ በመርከቡ ወለል ላይ ተሰልፈው ነበር። እኛን በማሳለፍ ላይ እንዳሉ «ሁ ራ» ብለው ጮሁና መለዮዋቸውን ሁለት ጊዜ አወረዱ። አንድ ዐይነት የክብር ሰላምታ ኖሯል፣ እኔ ግን ምን ማለት እንደሆነ ቅንጣት ታክል ግንዛቤ አልነበረኝም። የጦር መርከቡ ቆሞ ወደነበረበት ሥፍር ተመለስን። የእኛንም እንደዚሁ አቆምንና መርከበኛው እንድንከተለው አንድ ምልክት አሳየን። ወደ ጦር መርከቡ ስንወጣ አዛገፉ ከድልድዩ ላይ ተቀበለን። ከመድረሳችን አንድ የፊሽካ ድምፅ አስተጋባና ከመኮንኖቹ ጋር ከተዋወቅን በኋላ፣ በተጠንቀቅ ቆመው የነበሩ አሩጩ መኮንኖች በፊት ለፊታችን በሰልፍ አለፉ። አዛገፉ በእንግሊዝኛ ቃላት ገለጻ ካደረገ በኋላ ሰልፉ ተበተነ። አዛገፉ ለተማሪዎቹ ሲገልጽላቸው የነበረውና ከእነርሱም የክብር ሰላምታ ያገኘነው ይህችን በመሰለች ትንሽ ጀልባ ያን ያህል ረጅም ጉዞ ማድረጋችንና አሁንም ገና ይበልጥ አደገኛና ረጅም ጉዞ ለማድረግ በመነሣት ላይ መሆናችን እንደነበር አንድ ወጣት መኮንን አስረዳን። ለተደረገልን ክብር መኮንኑን አመሰገንን። ሦስት የመርከበኛ ጃኬቶች አበረከቱልን። ጥቁር ሆነው ጠንካራ ዚፕና የራስ ቆብ ያላቸው ነበሩ። ደሴቲቷን ለመልቀቅ ሁለት ቀናት ሲቀረን፣ ከሳምንት በፊት የታሠሩ ሦስት ልማደኛ ሌቦችን እንድንወስድለት የፖሊሱ አዛዥ ትብብር የጠየቀ መሆኑን ሰተር በውን አሜወተን። ደሴቷ ላይ ሲቀሩ የቻሉት ወደ ቬኔዙዌላ ወይም ሌላ ሀገር የሔዱ ጓደኞቻችን ትተውን ነው ይላሉ። ሐሳቡን አልወደድኩትም፣ ግን እምቢ ለማለት ደግሞ ከሚገባው በላይ እንክብካቤ ተደርጎልናል። የመጨረሻ መልስ ከመስጠቱ በፊት ከእነዚህ ሦስት እሥረኞች ጋር ለመገናኘት ጠየቅኩ። አንድ የፖሊስ መኪና መጣልኝና ከአዛገፉ ጋር ለመወያየት ሔድኩ። እርሱም መጀመሪያ በደረስንበት ወቅት ጠይቆን የነበረው መኮንን ነበር። ሃምሳ አለቃ ዊሊ አንደ አስተርጓሚ ሆነ።

« አንድ ውለታ ብታደርጉልን ደስ ባለን ነበር።»

« የሚቻል ከሆነ፣ በደስታ»

« እዚህ እሥር ቤት ውስጥ ሦስት ፈረንሣውያን ልማደኛ ሌቦች አሉን። ጓደኞቻችን እዚህ ትተውን ሔዱ ይላሉ። ጀልባቸውን ራሳቸው ያሰመጡ መስሎናል፣ እነርሱ ግን መቅዘፍ እንኳ አናውቅም ይላሉ። እኛ ሁኔታው ተማታብን፣ አንድ አዲስ ጀልባ እንድንሰጣቸው እየጣሩ መስሎናል። መሔድ ይገባቸዋል፣ ግን እዚህ ለሚመጣው የመጀመሪያ የፈረንሣይ መርከብ መልሼ ላስረክባቸው አልፈለግኩም።»

« ጌታዬ ፣ እኔ እወስዳቸዋለሁ። ግን መጀመሪያ ከእነርሱ ጋር መነጋገር እፈልጋለሁ። ሦስት እንግዶችን አጠቃልሎ መውሰድ አደገኛ መሆኑን እርስዎም መገንዘብ አለብዎት።»

« ገብቶኛል። ዊሊ፣ ሦስቱን ፈረንሣውያን ወደ እሥር ቤቱ ግቢ



@BOOKALEM

አውጧቸው::» ብቻየን ላነጋግራቸው ስለፈለግኩ ሃምሳ አለቃ ዊሊ ገለል እንዲልልኝ ጠየቅኩት::

«ልማደኛ ሌቦች ናችሁ?»

«አይደለንም፣ ከባድ ወንጀለኞች ነን::»

«ታዲያ ለምን ልማደኛ ሌቦች ነን አላችሁ?»

«ከአንድ ትልቅ ወንጀል ይልቅ ብዙ ትንሽ ወንጀሎች የሠራን መሆናችንን ከዐወቁ የተሻለ እንክብካቤ እናገኛለን ብለን ተስፋ በማድረግ ነበር:: ግን ስሕተተኞች ነን:: አንተስ ምንድን ነህ?»

«ከባድ ወንጀለኛ»

«አላወቅህም?»

«በመጨረሻው ኮንቮይ ነው የመጣሁት:: ስሙ፣ ሦስታችሁን በእኛ ጀልባ እንድንወስዳችሁ የምትፈልጉ ከሆነ እንድጠይቃችሁ የፖሊሱ አዛዥ ነግሮኛል:: እኛም ሦስት ነን:: እርሱ የሚለው፣ እኔ ካልወሰድኳችሁ በስተቀር በዚያ በሚያልፈው የመጀመሪያው የፈረንሣይ ጀልባ አሣፍራቸዋለሁ ነው:: ምን ይመስላችኋል?»

«ወደ ባሕር ዳግመኛ ለመውጣት ያልፈለግንበት ምክንያቶች አሉን::»

«ከእናንተ ጋር የሔድን እንመስልና፣ ከዚያም ከደሴቷ መጨረሻ ትታችሁን እናንተ መንገዳችሁን አትቀጥሉም እንዴ?»

«አይሆንም፣ እንደዚያስ ማድረግ አልችልም::»

«ለምን አይሆንም?»

«ምክንያቱም ሩኅሩኅነታቸውን በዚህ መልኩ መልሶ አጸፋ መክፈል አስነዋሪ መንገድ ነው::»

«ለእንግሊዛውያን ከማሰብህ በፊት ለእኛ ማሰብ ይኖርብሃል::»

«ለምን?»

«ምክንያቱም አንተም ራስህ እሥረኛ ነሃ?»

«ያ ሊሆን ይችላል፣ ግን ብዙ ዓይነት የተለያዩ እሥረኞች አሉ:: ምናልባትም ከእኔና ከእንግሊዛውያኑ ይልቅ፣ በአንተና በእኔ መካከል የበለጠ ልዩነት ይኖራል:: ወሳኙ የአመለካከት ሁኔታ ነው::»

«ታዲያ ለፈረንሣውያን ባለሥልጣኖች እንዲያስረክቡን ልትነግራቸው ነዋ?»

«አይደለም:: ግን ኩራሶ ከመድረሳችን በፊት እንደማላወርዳችሁ ነው::»

«እንደገና ጉዞ መቋቋም አልችልም» አለ ከእነርሱ ውስጥ አንዱ::

«ስማ፣ በመጀመሪያ የእኛን ጀልባ ተመልከታት:: ምናልባት የቀድሞዋ ጀልባችሁ አሮጌ ትመስለኛለች»



@BOOKALEM

«እሺ፣ እስኪ እንሞክራ»

«መልካም፣ ጀልባዋን ለመመልከት እንዲፈቅድላችሁ አዛገፑን እጠይቀዋለሁ፡፡»

ከሃምሳ አለቃ ዊሊ ጋር አብረን ወደ ወደቡ ሔድን፡፡ አንድ ጊዜ ጀልባዋን ከተመለከቱ በኋላ ሦስቱ ጓደኞች እምነት ያደረባቸው መሰሉ፡፡

## አዲስ ጉዞ

እኛ ሦስታችንና ሦስቱ እንግዶች ከሁለት ቀን በኋላ ጉዞ ጀመርን፡፡ ወሬው እንዴት እንደ ነፈሰላቸው አላውቅም፣ ከቦውን ቤተሰቦችና ከወታደራዊው በጎ አድራጎቱ ኃላፊ ጋር የመጠጥ ቤቶቹ አሥራ ሁለት ያህል ኮረዳዎች እኛን ለመሸኘት መጡ፡፡ ከኮረዳዎቹ አንዷ ለመሸነባበቻ አንድ ጊዜ ስትስመኝ፣ ማርጋሬት እየሣቀች፣ «ሔንሪ፣ ለካ ቀልጣፋ ወንድ ኖረሃል!» አለች፡፡

«ሁላችሁም ደህና ሁኑ፡፡ ዳግመኛ ባናያችሁም በልባችን ውስጥ አንድ ትልቅ ቦታ እንዳላችሁ አስታውሱ፡፡ ፍጹም አንረሳችሁም፡፡»

ከሰዓት በኋላ በዐሥር ሰዓት ተንቀሳቀስን፡፡ ጊዜ ሳንፈጅ ከወደቡ ወጣንና እኛን ለመሸኘት መጥተው የነበሩትን ቡድኖች ለመጨረሻ ጊዜ ለመመልከት ቆምን፡፡ አሁንም ነጭ መሐረቦች እያውለበለቡልን ነበር፡፡ የኮ-ስ ሸራዎቻችንን ነፋስ ሞላቸው፣ በመነሻችንና በመድረሻችን መካከል ከሚያጋጥሙን በሚሊዮን ከሚቆጠሩ ማዕበሎች ውስጥ የመጀመሪያውን በድፍረት ተጋፈጥነው፡፡

ጀልባችን ወስጥ የእኔና የማቹሬ ሁለት ጩቤዎች ነበሩ፡፡ ቆንጨራው ከክሎሲዎ አጠገብ ነበር ያለው፣ ገጀራውም እንደዚያው ነበር፡፡ ከእነርሱ መካከል ግን ማንም እንዳልታጠቀ እርግጠኞች ነበርን፣ ለማንኛውም ቢሆን ነገሮችን ለመቆጣጠር ቢያንስ ሁለታችን ዘወትር መንቃት ይኖርብናል፡፡ ፀሐይ ልትጠልቅ አቅራቢያ የማሠልጠኛው መርከብ መጣና ለግማሽ ሰዓት ሲያጅበን ቆየ፡፡ ከዚያም ሰላምታ ሰጥቶን ሔደ፡፡

« ማነው ስምህ?»

« ሌፉው»

« ስንተኛ ኮንቪይ?»

« ሐያ ሰባተኛው፡፡»

« ቅጣትህ?»

« ሐያ ዓመት»

« የአንተስ ማን ይባላል?»

« ካርጉሬ ሐያ ዘጠነኛው ኮንቪይ፡፡ ብሪቶን ነኝ፡፡»



@BOOKALEM

« ብሪቶን ሆነህ ጀልባ መቅዘፍ እንዴት አታውቅም?»

« ስሜ ዱፈልስ ነው፡፡ ከአንገር ቀበሌ ነኝ፡፡ በችሎት ላይ አንድ ጸያፍ ነገር በመናገሬ ምክንያት ዕድሜ ልክ ጽኑ እሥራት ተፈረደብኝ፡፡ ያ ባይሆን ኖሮ ቢበዛ ዐሥር ዓመት በተፈረደብኝ ነበር፡፡ በሐያ ዘጠነኛው ኮንቮይ ነበርኩ፡፡»

« የተናገርከው ምን ብለህ ነበር?»

« ያማ እንደዚህ ነበር፡፡ ሚስቴን በካውያ ገደልኳት፡፡ ለፍርድ በቀረብኩበት ወቅት ከተችዎቹ አንደኛው ለምን በካውያ እንደ መታኋት ጠየቀኝ፡፡ ‹ለምን እንደሆነ እኔም አላውቅም፤ ግን ልብስ በሚገባ መተኮስ ባለመቻሏ በካውያው ገደልኳት› አልኩት፡፡ ከባድ ቅጣት ሊያስከትልብኝ የቻለው ያ አስቀያሚ ንግግር መሆኑን ጠበቃዬ ገለጸልኝ፡፡»

« ያመለጥከው ከየት ነበር?»

« ከካስኬድ፡- ከቅዱስ ላውረን በግምት ሃምሳ ማይል የምትርቅ የሚካ ካምፕ ነች፡፡ ከዚያ ለማምለጥ ቀላል ነበር፤ ምክንያቱም ብዙ ነጻነት ነበረን፡፡ የነበርነው አምስታችን ስለሆን ቀላል ነበር፡፡»

« አምስት ስትል ምን ማለትህ ነው? ሁለቱ ወዴት ሔዱ?»

የኃፍረት ዝምታ ረጭ አለ፡፡

በመጨረሻም ከሎሲዎ « ስሙ ጓደኞቼ ሁላችንንም የሚያገባን ጉዳይ ይሆናል፡፡ ለማወቅም መብት አለን» አለ፡፡

« እኔ እነግራችኋለሁ» ብሎ ብሪቶኑ ጀመረ፡፡ « እርሱ እንዳለው ሁሉ ስንነሣ አምስት ሆነን ነበር፡፡ ግን ሁለቱ የጎደሉት የካኒስ ቀበሌ ሰዎች ስለነበሩ ዓሣ አጥማጆች ነን ብለው ነገሩን፡፡ ለማምለጡ ዝግጅት ምንም ነገር አልከፈሉም ግን ጀልባ በመቅዘፍ እየረዱን እናካክስላችኋለን አሉን፡፡ ታዲያ ወደ መንገድ ስንገባ ከእነርሱ ውስጥ አንዳቸውም ስለጀልባ ቀዘፋ ምንም ነገር አያውቁም፡፡ ሐያ ጊዜ ልንሰጥም ተቃርበን ነበር፡፡ ወደ ጠረፍ ተጠጋን መጀመሪያ ዳች ጊያና ከዚያም እንግሊዝ ጊያና በመጨረሻም ትሪኒዳድ፡፡ በጆርጅታውንና በትሪኒዳድ መካከል ጀልባ መቅዘፍ እችላለሁ ያለውን አንደኛውን ገደልኩት፡፡ ድርሻውን ስላልከፈለና ጥሩ ጀልባ ቀዛፊ ነኝ ብሎ ስለዋሸ ሰውየው የሚገባውን አግኝቷል፡፡ ሌላው ደግሞ ገና ለገና እገደላለሁ ብሎ ስለፈራ በአንድ ሞገድ መካከል የጀልባውን እርፍ ለቀቀና ወደ ባሕር ዘለለ፡፡ የምንችለውን ሁሉ ጥረት አደረግን ብዙ ጀልባዋ ልትሰምጥ ተቃረበች፡፡ በመጨረሻም ከአንድ ቋጥኝ ጋር ተጋጨንና ዕድለኞች ሆነን ከዚያ ውስጥ ለመትረፍ ቻልን፡፡ እምላለሁ ዕውነቱ ይኸው ነው ሌላ ምንም ነገር የለም ሐቅ ነው፡፡»

« ልክ ነው» አሉ ሌሎቹ ሁለቱ፡፡ « ሁኔታው ይኸው ነው፡፡ ሰውየው መገደል



@BOOKALEM

እንደሚገባው እኛ ሁላችንም ተስማምተናል:: አንተስ ምን ይመስልሃል ፓፒዮ?»

« እኔ ፍርድ ለመስጠት አልተዘጋጀሁም::»

« ግን አንተ ብትሆን ምን ታደርገው ነበር?» ሲል ብሪቶት አጥብቆ ጠየቀኝ::

« ስለሁኔታው አስብበታለሁ:: እርግጡን ለማወቅ ራስህ የታሪኩ ተካፋይ መሆን ይኖርብሃል:: አለበለዚያ የትኛው ልክ እንደሆነ ለመናገር አትችልም::»

« እኔ ብሆን እገድለው ነበር:: በርሱ ውሸት የተነሣ የሁሉም ሕይወት ሊጠፋ ነበርኮ» አለ ክሎሲዮ::

« እሺ ዳግመኛ ስለዚህ ጉዳይ አናውራ:: ግን አሁንም ገና በመፍራት ላይ መሆናችሁ ተሰምቶኛል:: ወደ ባሕር የተመለሳችሁት እነርሱ ሒዱ ብለው ስላስገደዷችሁ ብቻ ነው ልክ ነው?

« ልክ ነው» ሲሉ ሁሉም በአንድነት መለሱ::

« እንግዲያው እሺ:: ግን የፈለገው ነገር ቢሆን ማንም ሰው መርበትበት የለበትም:: ሌላው ቢቀር መፍራታችሁን አታስታውቁ:: ፍርሃት ቢገባችሁም እንኳን አትፍሩ ይህች ጥሩ ጀልባ ነች ማንነቷን በሚገባ አስመስክራለች:: ከበድ ያለ ጭነት አለን:: ግን ከፈፋ የስድስት ኢንች ከፍታ ስለአለው የተጨመረውን ጭነት በሚገባ ይችላል::»

ትንሽ ቡና ቀማመስንና ሲጃራ አጨስን:: በምንነሣበት ወቅት ጥሩ ምግብ በልተን ስለነበር እስከሚቀጥለው ቀን ላለመብላት ወስነናል:: ከቅዱስ ላውረን ሆስፒታል ከፍላችን ለማምለጥ ከተነሣንበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ዐርባ ሁለት ቀናት መሆኑን ልማደኛው መዘክር መዝጋቢያችን ክሎሲዮ ገለጸልን:: ከዚያ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሦስት ውድ ዕቃዎች ባለንብረት ሆኜአለሁ:: ትሪኒዳድ የገዛሁት ውሃ የማያበላሸው አንድ የእጅ ሰዓት ጥንድ ማንገቻ ያለው አንድ በጣም አስተማማኝ ኮምፓስ ባለፕላስቲክ መስታወትና አንድ ጥቁር መነጽር:: ክሎሲዮና ማቹሬም እያንዳንዳቸው የማርከበኛ መለዮ ነበራቸው:: ከዶልፊን መንጋዎች ጋር ሁለት ጊዜ ያህል ከመገናኘታችን በስተቀር የመጀመሪያዎቹን ሦስት ቀናት ምንም ችግር አልገጠመንም:: በቁጥር ስምንት የሆኑ መንጋዎች በጀልባዋ ሊጫወቱባት ተነሡ:: ሁላችንም ላብ አጠመቀን:: በቅድሚያ ውስጥ ለውስጥ እየታከኳት ከፊቷ ወደ ላይ ብቅ አሉና እንደገና ከጀልባዋ ሥር በጎኗ በኩል አግድም አለፉ:: በሌላው ጨዋታ ደግሞ ሦስት ዶልፊኖች ሦስት መዓዘን በመሥራት አንዱ ከፊት ሁለቱ ከኋላ በመሆን በትክክል ሰልፍ ገቡ:: በሚያስፈራ ፍጥነት ወደ እኛ ይሸመጥጡና እላያችን ላይ ሊወጡብን ሲቃረቡ ወደ ጀልባዋ ሥር በመጥለቅ በሌላ አቅጣጫ ብቅ ይላሉ:: ኃይለኛ ነፋስ ስላጋጠመን ስነጣጥቀናቸው ቀድመን ለማለፍ በሙሉ ኃይል ቀዘፍን:: ግን እነርሱም ይበልጥ ፍጥነት ጨመሩ:: ጨዋታው ብዙ ሰዓት ወሰደ፣ እኛም ፈዝዘን ቀረን:: ሦስቱ አዲስ መጤዎች ምንም



@BOOKALEM